
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ



ማውጫ

ለአብነት ተማሪዎች የተዘጋጀ

ዓለማ ----------

↳ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርት መማር ለምን ይጠቅማል ----------

ምዕራፍ አንድ

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንነት

- ጽሕፈት እንዴት ተጀመረ ----------
- የመጻሕፍት ዓይነቶች ----------
- የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ ----------
- መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ያለው አስተዋጽዖ ----------

ምዕራፍ ሁለት

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ</u>

- የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ----------
- መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ቅዱስ ተባለ ----------
- መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ዓላማ ----------
- መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ይጠቅማል ----------
- የመጽሐፍ ቅዱስ መቼት ----------
  - ✓ መጽሐፍ ቅዱስ መቼ ተጻፈ ----------
  - ✓ መጽሐፍ ቅዱስ በማን ተጻፈ ----------
  - ✓ መጽሐፍ ቅዱስ በየት ቦታ ተጻፈ ----------
  - ✓ መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ተጻፈ ----------
  - ✓ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ቋንቋ ----------
    - ➢ የትርጉም ዓይነቶች ----------
- የመጽሐፍ ቅዱስ ዝግጅት ----------
- መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ገባ ----------

ምዕራፍ ሦስት

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና አዋልድ መጻሕፍት እና ትውፊት</u>

- የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ----------
  - ✓ የቀኖና ዓይነቶች ----------
  - ✓ ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት ----------
  - ✓ ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት ለምን አስፈለገ ----------
  - ✓ የቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅም ----------
  - ✓ የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና (ቁጥር) ----------
  - ✓ የቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት ምንጮች ----------
  - ✓ በአቆጣጠር ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችና ርትዕት መልስ ----------
- አዋልድ መጻሕፍት ----------
  - ✓ የአዋልድ መጻሕፍት ባሕርያት ----------
  - ✓ የአዋልድ መጻሕፍት ዓላማ ----------
  - ✓ አዋልድ መጻሕፍትን ስናነብ ልናስተውላቸው የሚገቡ ነጥቦች ----------
  - ✓ የአሥራውና የአዋልድ መጻሕፍት ግንኙነት (አንድነት) ----------
  - ✓ አዋልድ መጻሕፍትን ለመቀበል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ----------
  - ✓ የአዋልድ መጻሕፍት አከፋፈል ----------
- መጽሐፍ ቅዱስና ትውፊት ----------
  - ✓ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ----------
  - ✓ መጽሐፍ ቅዱስ አሁን ላለንበት ዘመን እንዴት ሊደርስ ቻለ ----------

- ✓ የትውፊት መረጃ በብሉይ ኪዳን ----------
- ✓ የትውፊት መረጃ በሐዲስ ኪዳን ----------
- ✓ የትውፊት ዓይነቶች ----------

ምዕራፍ አራት

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕል አባባልና ፈርጀ ብዙ ቃላት</u>

- ➥ የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕል ----------
  - ✓ በዕብራውያን (እስራኤላውያን) ዘንድ የስም አወጣጥ ባሕል ----------
  - ✓ ደጊሞት ቃል (ቃልን የመድገም ባሕል) ----------
  - ✓ ሥዕላዊ አገላለጥ የመጠቀም ባሕል ----------
  - ✓ የአቆጣጠር ባሕል ----------
  - ✓ አንድን ነገር አጉልቶ የማቅረብ ባሕል ----------
- ➥ የመጽሐፍ ቅዱስ አባባል ----------
  - ✓ አርቆ መናገር ----------
  - ✓ ሰውኛ ዘይቤ መጠቀም ----------
- ➥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ፈርጀ ብዙ ቃላት ----------
  - ✓ ፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ----------
  - ✓ እጮኛ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ----------

ምዕራፍ አምስት

<u>በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መልክዐ ምድሮች</u>

- ➥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ከተሞችና መንደሮች ----------
  - ✓ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ከተሞች ----------
    - ➢ የሜሶፖታሚያ ከተሞች ----------
    - ➢ የፊንቄ ከተሞች ----------
    - ➢ የግሪክ (አናቶሊያ) ከተሞች ----------
    - ➢ የፍልስጥኤም ከተሞች ----------
    - ➢ የፋርስ ከተሞች ----------
  - ✓ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መንደሮች ----------
- ➥ ደረቅ የመሬት ክፍል (የብስ የሆኑ ቦታዎች) ----------
  - ✓ ተራራዎች ----------
  - ✓ ሜዳዎች ----------
  - ✓ ዋሻዎች ----------
  - ✓ ሸለቆዎች ----------
  - ✓ በረሃዎች ----------
- ➥ ውኃማ አካላቶች ----------
  - ✓ ባሕሮች ----------
  - ✓ ምንጮች ----------
  - ✓ ወንዞች ----------
- ➥ እንስሳት በመጽሐፍ ቅዱስ ----------
- ➥ ዕፅዋት በመጽሐፍ ቅዱስ ----------

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የጦር መሣሪያዎች ----------

ምዕራፍ ስድስት

የመጽሐፍ ቅዱስ አቆጣጠርና መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ

- የሰማንያ አሐዱ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር አቆጣጠር ----------
- መናፍቃን ከማይቀበሏቸው መጻሕፍት ውስጥ ያሉ ቁም ነገሮች ----------
- ለቁጥር መለያየት መሠረታዊ ምክንያቶች ምንድናቸው ----------
- የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተወራራሽነት (ግንኙነት) ----------
- መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ ----------
- መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት (ለማንበብ) የሚረዱ መሠረታዊ መጠይቆች (መርሆች) ----
- መጽሐፍ ቅዱስ በሚጠናበት ጊዜ ጎልተው የሚታዩ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው -------
- የተለያዩ የአንድ ቋንቋ ትርጉሞች ለምን ይገኛሉ ----------
- ለችግሮቹ መፍትሔ ----------

ምዕራፍ ሰባት

የመጽሐፍ ቅዱስ ጠባይና ሥነ ጽሑፋዊ የአጻጻፍ ስልት

- የመጽሐፍ ቅዱስ ጠባይ ----------
- የመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ----------
  - ✓ መሠረታዊ ስልት ጽሑፎች (የመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ ጽሑፋዊ ስልት (አቀራረብ) -----
  - ✓ ዝርዝራዊ አገላለጽ ----------

ምዕራፍ ስምንት

ብሉይ ኪዳን

- የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጠቅላይ ይዘት ----------
  - ✓ የሕግ መጻሕፍት ----------
  - ✓ የታሪክ መጻሕፍት ----------
  - ✓ የጥበብ (የቅኔ የመዝሙር) መጻሕፍት ----------
  - ✓ የትንቢት መጻሕፍት ----------

ምዕራፍ ዘጠኝ

ሐዲስ ኪዳን

- የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጠቅላይ ይዘት ----------
  - ✓ የወንጌል መጻሕፍት----------
  - ✓ የታሪክ መጽሐፍ ----------
  - ✓ የመልእክት (የትምህርት) መጻሕፍት ----------
  - ✓ የትንቢት (ራእይ) መጽሐፍ ----------
  - ✓ የሥርዓት መጻሕፍት ----------
- ማጠቃለያ ----------

↳ ዋቢ መጻሕፍት ----------





‹‹ይህን መጽሐፍ ብላ›› ት/ሕዝ ፫÷፫ መግቢያ

ልበ አምላክ ክቡር ዳዊት ‹‹ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው ከማርና ከወለላ ይልቅ ጣፈጠኝ›› በማለት በመዝሙሩ ላይ እንደገለጸው መዝ 118÷103 የእግዚአብሔር ቃል ያለባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት የነፍሳችን ምግቦች ናቸው። ሰዎች ለመኖር (ለቁበተ ሥጋ) ምግበ ሥጋን እንደሚመገቡ ሁሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ደግሞ የሕይወት መጻሕፍት እንደመሆናቸው ለነፍሳችን እነዚህን ቅዱሳት መጻሕፍት ልንመገብ ያስፈልጋል። እንዲሁ የሰው ልጅ አሁን ባለው የኑሮ ሁኔታ ቢያን በቀን ሦስት ጊዜ ለቁበተ ሥጋ የሚሆነውን ምግበ ሥጋ ይመገባል። እነዚህን ምግበ ሥጋ በቀን ሦስት ጊዜ ስንመገባቸው ርቦን ወይንም ካልተመገብን የሚያመን ሆኖ ሳይሆን በየጊዜውና በየሰዓቱ ለቁበተ ሥጋችን የሚያስፈልግ ስለሆነ ሰዓቱን ጠብቀን እንመገባለን። እንደዚሁ ምግበ ነፍስ የተባሉት ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸውና ለቁበተ ሥጋችን በየጊዜው መመገብ አስፈላጊ ሆኖ እንደምንመገባቸው ሁሉ የነፍስ ምግቦቻችንንም (ቅዱሳት መጻሕፍትንም) በየጊዜው ልንመገባቸው ይገባል። ነብየ ልዑል ሕዝቅኤል በትንቢት መጽሐፉ ላይ ‹‹ይህንን መጽሐፍ ብላ›› ት/ሕዝ 3÷3 በማለት እንደገለጸው ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ ነፍሳችንን ልናጠግባት (ልናረካት) ያስፈልጋል። ከዚህ በተረፈ ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ልጆች እንዲመሩበት ከእግዚአብሔር የተሰጡ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደመሆናቸው ስለ ምድራዊ ሕይወታችን እንዴት መራመድ እንዳለብን የሚመክሩን የሚገስጹን መምህራችንም ጭምር ናቸው። እንደዚሁ ቅዱሳት መጻሕፍት በሕያው አምላክ የተጻፉ በመሆናቸው ዘመን የማይሽራቸው ሕያው ቃል ናቸው። ማቴ 24÷35 በእውነተኛ አምላክ የተጻፉ በመሆናቸው ቃሎቹ አማናዊ ቃል ናቸው። ዮሐ 17÷17 ቅዱሳን አባቶቻችን በመንፈስ ቅዱስ ተመርተውና ተነድተው የጻፉት መጻሕፍት በመሆናቸው ቅዱሳት አሰኝቷቸዋል። በዚህም መሠረት ቅዱሳን አባቶቻችን በቅዱሳት መጻሕፍት ተጠቅመው ወደ ዘላለማዊ የድኅነት መንገድ በመጓዝ ለቅድስና በቅተዋል ለምንግሥቱ ተዘጋጅተዋል። በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖችም የቀደሙትን የአባቶቻችንን አሰረ ፍኖት በመከተል ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ በሃይማኖት መጽናት በትምህርት መኮትኮት በምግባር መጎልመስ ይጠበቅብናል።

በመሆኑም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እነዚህን መሠረታዊ ሁኔታዎችን በመመዘገብ ከጥንት ጀምራ ጠብቃ አቆይታለች እንደዚሁ በአብነት ት/ቤቶችና በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓቱ ሳጥቆነጸል እየሰጠች (እያስተማተረች) ዛሬ ላይ አቆይታለች። ሆኖም ቅዱሳት መጻሕፍት እጅግ በጣም ፈታኝ በሆነ ፈተናዎች መሐልም አልፎም ቢሆን ዛሬ ላለንበት ዘመን ደርሷል። አባቶቻችን ‹‹ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም›› አንዲሉ አበው በደማቸው ተወራርደው የሞት ክፍያ ከፍለው ዛሬ ላይ አድርሰውልናል። ስለሆነም እኛም ይህን የሕይወት መሪ የሆነውን መጽሐፍ በማንበብ ራሳችንን ለእግዚአብሔር መንግሥት ልናዘጋጅ ያስፈልጋል።

ሆኖም አንባቢያን ይህንን ሁሉ በመገንዘብ በአጥቢያቸው የሚገኙትን የቤተ ክርስቲያንን ሊቃውንት በመጠየቅ አጋዥ መጻሕፍትን በማንበብና እርስ በእርስ በመረዳዳት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ማስፋት ይገባቸዋል። ለዚህም ደግሞ እግዚአብሔር አምላካችን ለሁላችንም ጥበብና ማስተዋሉን ያድለን። አሜን!

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርት መሠረታዊ ዓላማ

መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ ያሰጣል መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና ያላየነውን እናይበታለን ያልዳሰስነውን እንዳስስበታለን ያላወቅነውን እናውቅበታለን።ሆኖም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርት ዓላማም ጠቅለል ብሎ የሚከተሉትን ይመስላል፦

- ✓ መንፈሳዊ ሕይወትን የምንማርበትና የምንመራበት መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሆነ፣ መቼ፣ እንዴትና በማን ተጻፈ፣ እውነተኛነቱ ምን ያህል እንደሆነ፣ በውስጡም ምን እንደሚገኝበት ማሳወቅ፣
- ✓ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን ቋንቋ ቦታ የአጻጻፉን እንዲሁም የአተረጓጎሙን ስልት ማሳወቅ፣
- ✓ የመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛው ቀኖና /ቁጥር/ በማን;SŠ“ □”Èƒ; □”Å}¨c′ ወደ እኛስ እንዴት እንደደረሰ ማስረዳት፣
- ✓ በውስጡ የሚገኙትን ታሪክ፣ ሕግ፣ ትምሕርትና ትንቢት ሁሉ በትክክል ማስገንዘብ፣
- ✓ በአገኘነውም ግንዛቤ መሠረት ከቀድሞ በበለጠ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በትዕዛዙ በፍቅሩ ለመኖር እንድንበቃ ማስቻል፣
- ✓ ‹‹በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት የተዘጋጃችሁ ሁኑ›› በማለት ሊቀ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንደተናገረው ለሚጠይቁን ሁሉ እንደ ጀማሪ መልስ ለመስጠት እንችል ዘንድ ማብቃት። /1 ኛ ጴጥ 3÷15/

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርት መማር ለምን ይጠቅማል?

- ✓ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን በሚገባ የተማረና ያወቀ አንድ ክርስቲያን ለመጽሐፍ ቅዱስ ሊሰጥ የሚገባወን ክብር ይረዳል።
- ✓ መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች ምኑናት መጻሕፍት ልዩ መሆኑን ያውቃል
- ✓ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የተማረ አንድ ክርስቲያን ዛሬ በዘመናችን ተንሰራፍቶ ያለውን ቁንጽል ሐሳብ አይቶ ትክክለኛውን ትምህርት አባቶቻችን ያስተማሩንን መሠረታዊ የሆነውን አስተምህሮት በማሳወቅ ርትህቷን ትምህርት አውቆ በማሳወቅ እርሱም ትምህርቱን ጠብቆ ሌላው እንዲጠብቅ በማድረግ ክርስቲያናዊ ኃላፊነቱን ይወጣል።
- ✓ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አውቀን ባወቅነው መሠረት መጽሐፍ ቅዱስን አጥንተን የሚገኘውን በረከት እንድናገኝ ይረዳናል።
- ✓ ሊቀ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት የተዘጋጃችሁ ሁኑ›› 1 ኛ ጴጥ 3÷15 በማለት እንደሚያስጠነቅቀን መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ተምረን ለሚጠይቁን ጥያቄ ሁሉ እንደ ጀማሪ መልስ እንድንሰጥ ያስችለናል።

ምዕራፍ አንድ

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንነት

ሀ/ ጽሕፈት እንዴት ተጀመረ ?

ጽሕፈት የተጀመረው በአባታችን በሔኖ¡ ዘመን ነው። ይኸውም እግዚአብሔር መጀመሪያ በአዳም 3ኛ ትውልድ በሆነው በሴት ልጅ በሔኖስ ዘመን የፊደላትን ቅርፅ በሠማይ ሰሌዳ ላይ ቀርጾ አሳየ። በዚህን ከሔኖስ እስከ ያሬድ ድረስ የነበሩ አበው /ሰዎች/ መነጋገር ነው እንጂ ሀሳባቸውን በጽሑፍ አይገልጹም ነበር። በዚህ ጊዜ በሕሊናቸው የሚመላለሰውን ሐሳብ በጽሑፍ የሰፈረ ይሆን ዘንድ ለሌሎች ትውልድ በትውፊት መልክ ይደርስ ዘንድ በአዳም 7ኛ ትውልድ በሆነው በሔኖክ ዘመን የጽሕፈትን ምሥጢር ለሰው ልጆች ገልጾ በዚህም ሐሳባቸውን በጽሑፍ ማስፈር ጀመሩ። ለመጀመሪያ ጊዜ የተጻፈውም መጽሐፍ የሔኖክ መጽሐፍ (መጽሐፈ ሔኖክ) ነው ።

ለ/ የመጻሕፍት ዓይነቶች

በዘመናችን ላይ ብዙ መጻሕፍት አሉ። ነገር ግን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጻፈው የሔኖክ መጽሐፍ ነው። ይሁንና ምንም በዘመናችን ብዙ የእድሜ መጠን ያላቸው (የዕድሜ ባለ ጸጋ የሆኑ) መጻሕፍት ቢኖሩም በዕድሜ ባለፀጋ እና ከሌሎች መጻሕፍት በእድሜ አንጋፋው መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሆኖም አጠቃላይ በዓለማችን ላይ ያሉ መጻሕፍትን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዓይነታቸው በሦስት ከፍላ ታስተምራለች። እነሱም፦

፩. ቅዱሳት መጽሐፍት (መጽሐፈ አምላካውያን)

፪. ምሁናት (ዓለማዊያን መጽሐፍት)

፫. ርኩሳት (ክህደትን ኑፋቄን የያዙ መጽሐፍት) ሲሆኑ እነዚህንም የመጽሐፍት ዓይነቶች ከዚህ ቀጥለን አጠር አድርገን ዝርዝራቸውን እንመለከታለን።

፩. ቅዱሳት መጻሕፍት (መጽሐፈ አምላካውያን)፦ እነዚህ መጻሕፍት ቅዱስ እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን ባለሟሎቹን ቅዱሳን አባቶቻችንን እያስነሳ ለሰው ልጆች ሕይወት፣ መመሪያ ይሆን ዘንድ ያጻፋቸው መጻሕፍት ናቸው። በእነዚህ መጻሕፍት እግዚአብሔር ሐሳቡን እቅዱን ለሰው ልጆች የገለፀበት መጻሕፍት ናቸው። እነዚህም መጻሕፍት ዐሰራውና አዋልድ መጻሕፍት በመባል በሁለት ይከፈላሉ።

- ✓ ዐሥራው፦ ይህ መጻሕፍት ሰማንያ አሐዱ መጠሪያ ያለው ለሌሎች አዋልድ መጻሕፍት ስር መሰረት መሐከል የሆነ መጽሐፍ ሲሆን ብሉይ ኪዳን እና ሐዲስ ኪዳንን ያመለክታል።
- ✓ አዋልድ መጻሕፍት፦ ከቃሉ እንደምንረዳው የመጽሐፍ ልጆች ማለት ነው ልጅነታቸውም ለአስራው መጽሐፍ ነው። ሰው ከአባቱ አብራክ ከእናቱ ማኅጸን ወላጆቹን መስሎ እንደሚወለድ አዋልድ መጻሕፍትም የአስራውን መጻሕፍት ምሥጢሩን አራቀው ትርጓሜውን አቃንተው አምልተው አስፍተው አመስጥረው ተንትነው ምሥጢር ከምሥጢር አገናኝተው አብላልተው አለስልሰው የሚተረጉሙ ናቸው። በእምነትም፣ በሥርዓትም ዐሥራው መጻሕፍትን የሚመስሉ መጻሕፍ ናቸው። ለምሳሌ፦
  - ሐይማኖት አበው - ተዓምራት
  - መጽሐፈ ስንክሳር - መጽሐፈ ምስጢር
  - መጽሐፈ መነኮሳት - ገድላት
  - የአንድምታ መጽሐፍት - መጽሐፈ ቅዳሴ
  - መጽሐፈ ፍትሐ ነገሥት - የጸሎት መፅሐፍት ----- ወዘተ ናቸው።

2 ምሁናት (ዓለማዊያን) መጻሕፍት፦ እነዚህ መጽሐፍት ደግሞ ዓለማዊያን መጻሕፍት ሲሆኑ መንፈሳዊ ሕይወታችንን የማይጎዱ ነገር ግን ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ምንም የማይጠቅሙ መጻሕፍት ናቸው። ሆኖም የእነዚህ መጻሕፍት ደራሲያቸው (አሰገኚያቸው) ራሳቸው ሰዎች ሲሆን ከልቡናቸው አመንጭተው የሚጽፏቸው መጻሕፍት ናቸው።

ለምሳሌ፦ የጥናት የምርምር፣ የትምህርት፣ የታሪክ የልቦለድ--- ወዘተ መጻሕፍት ናቸው።

3. ርኩሳት (ክህደትን ኑፋቄን የያዙ መጻሕፍት)፦ እነዚህ መጻሕፍ ደግሞ በውስጣቸው ክህደት፣ ኑፋቄን እና ኃጢአትን የያዙ መጻሕፍት ሲሆኑ ለመንፈሳዊ ህይወታችን የማይጠቅሙ የሚጎዱ መጻሕፍት ሲሆኑ ከዚህ ከተቀደሰች ርትህት ከሆነች እምነት ፈንቅለው ሊያወጡን የሚችሉና ወደ ገሀነመ እሳት የሚመሩ የረከሱ ግብረ ዳቢሎስን የሚያስተምሩ መጻሕፍት ናቸው።

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*` „Ê¡e }ªIÊ

ለምሳሌ፦ የጥንቆላ መጽሐፍት፣ ደብተራ፣ ኮከብ ቆጠራ ፣ጥበብ ከጲላጦስ ....ወዘተ ናቸው።

(መ.ሐኖ 2÷@2 ፣ ሐዋ፣ !9÷ !9)

ሐ/ የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ

1. ትምህርተ ሃይማኖትን ማስተማር፦ ትምህርተ ሃይማት የምንለው ሰዎች ለሃይማኖታቸው የሚያስፈልጋቸው ሃይማኖታዊ ትምህርት ነው። እነዚህም ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተመዝግበው ይገኛሉ ምክንያቱም ቅዱሳት መጽሐፍት በቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ምስጢር ገላጭነት የተጻፉ እንደ መሆናቸው ዓላማቸው ትምህርተ ሃይማትን ማስተማር ነውና። የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳንም መጻሕፍት ተቀዳሚ ዓላማቸው ይህንኑ የእግዚአብሔርን ሕልውና አኗኗሩን (ህልዎቱን) እና መግቦት፣ ጠብቆቱን ነገረ ሃይማኖትን በማስተማር ሰዎችን በሃይማኖታቸው ጽኑዓን ማድረግ ነው።(ዮሐ 14-10፣ መዝ 101-25፣ ዮሐ 1-1)

2. የእግዚአብሔርን ቸርነቱንና ድንቅ ሥራውን ተአምራቱን መግለጥ፦ ይህ ሲባል ቅዱሳት መጽሐፍት ተቀዳሚ ዓለማቸው የእግዚአብሔርን ሥራ መግለጥ ነው። ቅዱሳት መጽሐፍት እግዚአብሔር በቀጥታ ራሱ ወይም በወዳጁ በኩል ለሕዝቡ ያደረገውን ተአምር ቸርነት ያብራራሉ ይህንን እውነታ መጽሐፍ ቅዱስ በስፋት ሲያብራራው እናገኛለን። ዓለማው የእግዚአብሔየርን ሥራ መግለጥ ከመሆኑ የተነሳ የእግዚአብሔር ሥራ ተአምር የተፈጸመላቸውንና የተፈጸመባቸው ሰዎችን ቦታዎች እምብዛም ትኩረት አይሰጧቸውም የተደረገውን የእግዚአብሔርን ሥራ ብቻ ገልጠው የሰዎችንና የቦታዎችን ስም እገሌ አንድ ሰው ከ(አብዱ) ብለው ያልፋሉ። (ማቴ 26-18 1ኛ ነገ 13-1 ማቴ 8-2 ሉቃ 11-45)። ይህን የእግዚአብሔርን ሥራ መግለጥን ተቀዳሚ ማድረግ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ዓላማ ነው። ሆኖም ለእኛ ያደረገውን ቸርነቱን ከሀሊነቱን፣ ለእኛ የሰራልንን ድንቅ ድንቅ የሆኑ ስራዎቹን መግለጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ ነው። ሠለስቱ ምዕት በጸሎተ ሃይማኖት ላይ "ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ" ብለው እንዳስቀመጡት የሚታየውንም የማይታየውንም ፍጥረታት የፈጠረው እግዚአብሔር መሆኑን መመስከር መግለጥ ማሳወቅ ነው።(መዝ 50-1፣ መዝ 75-7፣ ማቴ 26-15፣ ማቴ 8-2፣ ሉቃ 11-45፣)

3. የእምነትን ታላቅነት መግለፅ፦ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉት ቅዱሳት መጽሐፍት በእምነት ለእምበነት ስለ እምነት የተጻፉ ናቸው። ተቀብሎአቸው በንጽሕና ተጠብቆ ከጥርጥር ርቆ በእምነት በመጽሐፉ የተገለጠውን የታዘዘውን ለጠበቀ የተባለው ይፈጸምለታል። ይሁን እንጂ እኚህ ቅዱሳት መጽሐፍት የእምነትን ኃያልነት፣ ታላቅነት ይገልጻሉ። የቅዱሳን አበው ታሪክም የሚያስረዳን ይህንኑ ነው።

ለምሳሌ፦

- ሐያሉ ገናናው ንጉስ ናቡከደነፆር ሠለስቱ ደቂቅን ለጣዖት እንዲሰግዱ ሲያስገድዳቸው ለጣዖት አንሰግድም ሲሉ ናቡከደነፆርም "መኑ ያድህንክሙ እም እደዬ - ማን ከእጄ እንደሚያድናችሁ አያለው››። ሲላቸው እነርሱ ግን ጽኑዕ እምነት ስለ ነበራቸው "ሀሎነ አምላክነ ዘፈጠረ ኪያሁ ወኪያነ - አንተንም እኛንም የፈጠረ አምላክ ያድነናል›› በማለት ለጣዖቱ እንደማይሰግዱ በሙሉ እምነት ተናገሩ። ንጉሡም **49** ከንድ ወደ ላይ በሚያሕል እሳት ውስጥ እንዲጣሉ አዘዘ። በኢህ ጊዜ ከእሳት እንኳ ሲጣሉ የእሳቱን ነበልባል ሣይፈሩ " ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ስቡሕኒ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም" እያሉ አምለካቸውን እያመሰገኑ ኃይል ባላት በታላቋ እምነታቸው እግዚአብሔር ሊቀመላኩን ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ እንዳዳናቸው መጽሐፍ ቅዱስ **(ት.ዳን.ም 3÷1)** ላይ ይገልጽልናል። እነዚህ ሦስት ህጻናት ከእቶሙ እሳት መዳናቸው በታላቋ እምነታቸው ጽኑዕ ስለሆኑ ነው።
- እንዲሁ ነብየ ልዑል ዳንኤልም ከአናብስት ጉድ ÕÉ ተጥሎ ምንም አለመሆኑ የእምነቱን ታላቅነት ነው የሚያስረዳው .....ብዙ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል። ሆኖም ግን አንዲህ ባለ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ የእምነትን ታላቅነት መግለጥ ዓላማው ነው።(ዮሐ 14-12፣ መዝ 16-18፣ ዕብ 11-1)

4. በእግዚአብሔር ያመኑ የቅዱሳንን ተጋድሎ መግለጥ፦ እግዚአብሔር ድንቅ የሆነ ሥራውን ለፍጥረቱ የሚሰራው በፍጥረቱ አማካይነት ነው። ይህም በልዩልዩ መንገድ ይፈጸማል። የእግዚአብሔር ሥራ በስፋት እና በግልጥ ከሚሰራባቸው ፍጡራን መካከል ደግሞ ዐቢይ ሥፍራ የያዙት ቅዱሳን ናቸው። ቅዱሳን ለሕገ እግዚአብሔር ተገዝተው ፈቃዱን በመፈጸማቸው ንጹሕ መንፈስና ንጹሕ ልቡናን ገንዘብ አደረጉ በዚህ ንጹሕ ሰውነታቸው ከእግዚአብሔር የተቀበሉት ኃይል ብዙ ተጋድሎን ፈጽመዋል። ሆኖም ከመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ ውስጥም አንዱ ይህንን በእግዚአብሔር ያመኑ የቅዱሳንን ተጋድሎ መግለጽ ነው። ለምሳሌ፦

- ነህምያ፦ የኢየሩሳሌምን ቅጥር መስራት። እዚህ ላይ ነህምያ ብቻውን ይህን ማድረግ የሚችል ሆኖ አይደለም ነገር ግን እግዚአብሔር በነህምያ ላይ አድሮ የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንድትሰራ አደረገ፣(መጽ ነህ 1፣1)
- አስቴር፦ በጸሎት እና በጾም የእግዚአብሔርን ህዝብ መታደግ እንዲሁ ታውጆ የነበረውን የሞት አዋጅ ወደ ሕይወት መቀየር ስንመለከት አስቴር በራሷ ይህንን ሁሉ የምታደርግ ሆና ሳይሆን ነገር ግን እግዚአብሔር በአስቴር አማካይነት ህዝቦቹን ታደገ
- ሙሴ፦ ሙሴ እስራኤል ዘሥጋን ከ 430 የባርነት ዘመን በኋላ በእግዚአብሔር ታዝዞ ያወጣ ነብይ ወመስፍን ነው። ሆኖም ግን ይህን በሚያደርግበት ጊዜ ፈርዖንን ለማሳመን ያደረጋቸውን ተአምራት ስልመለከት ሙሴ በራሱ ያን የሚያደርግ ሆኖ ሳይደሆን እግዚአብሔር በሙሴ

ላይ አድደሮ ያደረገው ተአምር ነው። ---- ወዘተ ብዙ መጥቀስ ይቻላል። ሆኖም ግን ይህንን የቅዱሳኑን ተጋድሎ መግለጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማው ነው።

5. <u>ለሰውና ሕሊና የሚከብድ በእምነት የምንረዳቸውን ድርጊቶች መግለጥ፦</u> ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ ለሰው ኅሊና የሚከብዱ በእምነት ብቻ የምንረዳቸውን ድርጊቶች መግለጥ ነው። ይኸውም እምነት ኃይል አለው። በዕውቀታችን በጉልበታችን ከምንሠራውና ከምንረዳው በላይ በእምነት ይፈጸማል። ይኸውም እምነት የማናየውን ነገር የሚያስረግጥ ነገር ነው።(ዕብ 11፡1) በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልም ከተፈጥሮአዊ ሥርዓት ውጪ የሆኑ ድርጊቶች ሲፈጸሙ በምናነብበት ጊዜ ምናልባት ለሥጋዊ ለደማዊ አእምሮአችን ቢከብድም በእምነት ግም እንረዳቸዋለን ምክንያቱም ‹‹ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና››።ሆኖም እነዚህን መሠል ድርጊት በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቦታ ተጽፈው የምናገኛቸው ቢሆንም ሁሉንም መዘርዘር ባይቻልም ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመለከታለን፦

- <u>ሙሴ፣</u> የኤርትራን ባህር ከፍሎ እስራኤላዊያንን ማሻገር ኢያሱ ፀሐይን ገዝቶ ማቆም ፣ የበለዓም አህያ አንደበት አውጥታ መናገር፣ ኤልያስ በጸሎቱ ኃይል ዝናብን ገዝቶ ማቆም፣ የቅዱስ ጳውሎስ የልብሱ እራፊ ድውይ መፈወስ------- ወዘተ ይህ ሁሉ ድርጊት በሳይንስ ዓይን ሲታይ ለኅሊና ይከብዳል ነገር ግን ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ። ለሚያምን ደግሞ ሁሉ ይቻላል።(ኢያ 10-12-14፣ ሉቃ 1-37፣ ማር 9-23)

6. <u>የዘላለም ህይወት መስጠት፦</u> የዘለዓለም ሕይወት ማለት ሰዎችን ለመንግሥተ ሰማያት ማብቃት ማለት ነው። ይህ ደግሞ ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ ነው። ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ የዘላለማዊ ሕይወት ለመስጠት የጽድቁን መንገድ እየመራ (እያሳየ) ለክብር ማብቃት ዓላማው ነውና።(ዮሐ 6-41፣ ማር 16-16፣ ዮሐ 3-3-30፣ ያዕ 4) ብጹዕ <u>አባታችን አቡነ እስጢፋኖስም</u> “የመማራችን ዓላማው የሕይወት ለውጥ ለማምጣት መሆን አለበት” እንደሉት።

መ) <u>መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ያለው አስተዋፅዖ</u>

መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን አስተዋጽዖ ይሄ ነው ብሎ ዘርዝሮ መናገር የሚቻል ባይሆንም አባቶቻችን ‹‹ዓባይን በጭልፋ›› እንደሚሉት ጥቂቶቹን እንመለከታለን።ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምስጢር ገላጭነት በቅዱሳን አባቶቻችን ሲሆን። ቅደስት ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ደግሞ በእግዚአብሔር ወልድ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለዚህ ደግሞ ቅድስት ቤተ ክረስቲያን የእግዚአብሔርን ዕቅድ እና ሐሳብ የምታውቀው ድምጹ የምትሰማው በቅዱሳት መጽሐፍት ነው። ከዚህ አልፎ መጽሐፍ ቅዱስ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት ለመፈጸም የምትጠቀምበት መመሪያዋ ጭምር ነው። እንዲሁ የሕጓ መሠረትም ነው። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን አስተዋጽዖ ጠቅለል ተደርጎ ከዚህ እንደሚከተለው ተቀምጧል።

<u>የእምነት መመሪያዋ ነው</u>

የቤተ ክርስቲያን መመሪያ ተብለው የሚጠሩት ዶግማ ፣ ቀኖናና እና ትውፊት ናቸው። እነዚህ ሦስቱ የሃይማኖት መመሪያ (መሠረት) ናቸው። እነዚህም የሃይማኖት መመሪያዎች (መሠረቶች) ምንጫቸው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይኸውም

- ✓ <u>ዶግማ፦</u> ዶግማ ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙም የማይሻር የማይለወጥ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ማለት ነው። ለዚህም ሥርዓት መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ለምሳሌ፦ በዮሐ 1-1 ላይ ‹‹በመጀመሪያ ቃል ነበር ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ---›› የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን ብንመለከት መሠረታዊ የሆነ የማይለወጥ የማይሻር የዶግማ ትምህርት ነው። እንዲሁ የእመቤታችንን ዘላለማዊ ድንግልናንም ስንመለከት ዶግማ ነው። የሚሻር የሚለወጥ አይደለምና።
- ✓ <u>ቀኖና፦</u> ቀኖናም ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙ የሚለወጥ የሚታደስ በየወቅቱ የሚስተካከል ሥርዓት ማለት ነው። ለዚህም መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይኸውም ለምሳሌ፦ በ 2 ኛ ጢሞ 3-1 ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍላችን ላይ እንደተቀመጠው አንድ ኤጲስ ቆጶስነትን መሾም የሚወድ አንድ ሚስት ብቻ ያገባ ሊሆን ይገባል። በማለት ያስረዳናል። በዚህ ላይ እንደተገለጸው ኤጲስ ቆጶስ ሊሆን የሚሻ አንዲት ሚስት ብቻ ያገባ ይላል። ነገር ግን ዛሬ ያለውን ሥርዓት ስንመለከት አባቶቻችን ጳጳሳት በድንግልና ከፀኑ በኋላ የሚሰጣቸው የክህነት ደረጃ ነው። ሆኖም እነዚህ ሁለቱ ይጣረሳሉ ማለት ነው? አይደለም ምክንያቱም በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ያለው ሐሳብ ቀኖና ነውና፣ ይህም በጊዜው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ኃላፊነት ሲሰጣቸው ከሐዋርያት መካከል ሕጋውያንም ደናግላንም ነበሩ። ሥልጣነ ጵጵስናን ለሁሉም በአንብሮተ እድ ሾሞ ሰጣቸው።ምክንያቱም በጊዜው ከሐዋርያት በስተቀር ቅርብና ለኃላፊነት የተዘጋጁ ስላልነበሩ። በዚህ ጊዜ ለሕጋዊውም ለደናግላኑም ይህ ኃላፊነት እኩል ተሰጠ። ይህ ሥርዓት በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ በተሠጠበት ጊዜ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ልጁ ከላይ የጠቀስነውን መልእክት የላከለት በጊዜው ላገባም ይህ ሥልጣን ስለሚሰጥ ነው። ይሁንና ይህ ሥርዓት በዚህ መልኩ እስከ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ከቀጠለ በኋላ በዚህ ዘመን (በ 325 ዓ.ም) ይህ ሥርዓት ተቀየረ። ይኸውም በዚህ ጊዜ አርዮስን ለማውገዝ 318 ቱ ሊቃውንት (ጳጳሳት) ከሀገረ ስብከታቸው ወደ ኒቂያ ተሰብስበው ጉባኤን በዚያ አደረጉ። በጉባኤው ላይ ከውግዘት አርዮስ ሌላ ስለ ነገረ ቤተ ክርስቲያን ተነጋግረዋል በዚህ ጊዜ አቡነ ፓትናትዮስ የተባሉ ሊቅ አንድ ሐሳብ አቀረቡ ይኸውም ‹‹እኛ ባለ ትዳር ስንሆን ሁለት ነገር አንድ ላይ ማስተዳደር አንችልም ‹‹አንድ ሎሌ ለሁለት ጌቶች አይገዛም›› እንደሚሉት ወይ ለትዳራችን ወይ ለቤተ ክርስቲያን ማድላታችን አይቀርም ለዚህ ይህ የጵጵስና መዓረግ በየክትክታው ወድቀው ስለ እምነታቸው ለሚጸልዩ ለመነኮሳት ቢሰጥ መልካም ነው›› የሚል ነበር። በዚህ ጊዜ ጉባኤው በሙሉ በሐሳባቸው ተስማምተው ጵጵስና ለደናግላን ብቻ ይሰጥ ብለው ደመደሙ። ከዚህ ጊዜ አንስቶ ጵጵስና በድንግልና ላሉ ብቻ የሚሠጥ ሆኗል። ለዚህ ከላይ እንደጠቀስነው ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ልጁ

ለጢሞቴዎስ በላከው መልእክት ላይ ያለው ቃል ቀኖና ነው ማለት ነው። ነገር ግን ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌል ላይ ‹‹ቃልህ እውነት ነው›› በማለት እንደገለጠው ቃሉን ግን ልንሸር አይገባም። ‹‹ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም›› ማቴ 24-30 በማለት ጌታ የተናገረው ቃል የሚያስገነዝበንም ይህንኑ ነው።

- ✓ ትውፊት፦ ትውፊት ወደፊት በስፋት የምንመለከተው ነገር ቢሆንም አንዱ የቤተ ክርስቲያን መመሪያ ነው። ለዚህም መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ትውፊት ከቃሉ እንደምንረዳው ቅብብሎሽ ውርስ ርክክብ የሚል ትርጉም አለው። በይሁዳ ቁጥር 9 ላይ ‹‹የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያቢሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ሥጋ ሲነጋገር ጌታ ይገስጽ አለው›› ይላል። በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደተመለከትነው ዲያቢሎስና ቅዱስ ሚካኤል በሙሴ ሥጋ ላይ ያደረጉትን መከራከር አንድም የኦሪት ክፍል አይገልጽም። ታድያ ይሁዳ ከየት አምጥቶ ገለጸው ብንል በትውፊት ከቀደሙት አባቶቹ ያገኘውን በመልእክቱ ላይ አስቀምጦልናል። የዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚያስገነዝበን ነገር ቢኖር ትውፊትም መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑ ነው።

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን መመሪያ የተባሉት የዶግማ የቀኖና እና የትውፊት መሠረት (ምንጭ) ነው። ይህን ደግሞ ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ አጣቅሰን ተመልክተናል።

የሥርዓቷ ምንጭ (መሠረት) ነው

ሥርዓት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በአገልግሎቷ አንድ ልብ እና አንድ ሐሳብ እንድትሆን የሚያደርጋት ነገር ሲሆን ለዚህም ሥርዓቶቿ መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይኸውም የቤተ መቅደስ አሠራር እንዴት እንደሚሰራ ልብስ ተክህኖ (በአምልኮ ሥርዓት ጊዜ ለአገልግሎት ካህናት አባቶቻችን የሚያደርጉት ልብስ ነው) ፣ ሥርዓተ ቁርባን ፣ በበዓል ሆሳዕና ጊዜ የሚደረገው ሥርዓት ፣ በስቅለት ጊዜ የሚደረግ ሥርዓት ---- ወዘተ ሲሆኑ ከዚህ ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥርዓት እንዲህ ይላል፦ ‹‹ከሥርዓትህ የሚርቁትን አጎሰቆላካቸው።› (መዝ 118-118) በማለት ከሥርዓት መውጣት ለሥርዓት ድጋፍ አለማድረግ የሚያስከትለውን አስረዳን። በሐዲስ ኪዳንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገሰጿቸው›› (1 ተሰ 5-14) እንዲሁ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ አዘንድ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንለምናችኋለን›› (2 ተሰ 3-6) በማለት ጥብቅ የዐደራ መልእክት በማስተላለፍ ራሱ የሥርዓት መሠረትና ምንጭ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። ለዚህም በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ላሉት ሥርዓተቶች መሠረቱና ምንጩ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ያስገነዝበናል።

የሥነ ምግባር ምንጭ (መሠረት) ነው

የሰው ልጅ ሐሜትን ቅናትን ጥልን ክርክርን --- ወዘተ በመተው በሥነ ምግብር ማደግ ወይንም መታነጽ ይገባዋል። የእግዚአብሔር ልጅ ለመባል መልካ ምግባራት ወይንም የመንፈስ ፍሬዎች ፍቅር ሰላም ቸርነት የዋኅነት ትዕግስት በጎነት ደስታ ራስን መግዛት --ወዘተ ገንዘብ ማድረግ መሠረታውያን ጉዳዮች ናቸው። ይልቁንም በሃይማኖት ለሚኖር ሰው ሃይማኖቱን የሚጠብቅበት መሠረታውያን ምግባራት ያስፈልጉታል። ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ሲያስረዳን ‹‹ሃይማት ያለ ምግባር በራሱ የሞተች ናት›› (ያዕ 2-17) ይላል። ስለሆነም የሰው ልጅ ሊፈጽማቸው የሚገቡ ምግባራት በብሉይ ኪዳንም በሐዲስ ኪዳንም ተጽፈዋል።(ዘጸ 2-21 ማቴ 5-21) የሰዎች ሥነ ምግባር ጥሩ መሆን ብቻ ሳይሆን ከክፋት መራቅና ፈተናን ማለፍ የሚችል የሚሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው
እግዚአብሔርን በማወቅና እርሱን በመፍራት ላይ ሲመሰረት ነው።

የጸሎት እና የዝማሬዋ መሠረት (ምንጭ) ነው

ጸሎት እግዚአብሔር እና ሰውየሚገናኙበት ረቂቅ መንገድ ነው ‹‹ጸሎትሰ ይእቲ ተናግሮተ ሰብእ ኀበ እግዚአብሔር - ጸሎት ሰው ከልዑል እግዚአብሔር ጋር የሚነጋገርባት ነገር ናት›› (ፍት ነገ አንቀጽ 14) ተብሎ በፍትሐ ነገስት እንደተገለጸው። ዝማሬም ለአምላካችን ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ምሥጋና ነው ‹‹እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሥግን›› (መዝ 150-6)። ሆኖም ጸሎቱ እና ምሥጋናው መሠረቱ (ምንጩ) መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይኸውም በመዝ 50-1 ጀምሮ እስከ ፍጻሜው እና መዝ 135-1 ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሙሉ ጸሎት ሲሆኑ። እንዲሁ የልበአምላክ የክቡር ዳዊት የመዝሙር መጽሐፍንም ስንመለከት ሙሉ መዝሙር ነው። መጽሐፉ ራሱ የተጻፈው በመዝሙር ነውና። ለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የዝማሬም የጸሎትም ምንጭ (መሠረት) መሆኑን እንገነዘባለን።

የሥራ ምንጭ (መሠረት) ነው

ይኸውም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራን የጀመረው አምላካችን ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ነው። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ በዘፍ 1-1 ፣ መዝ 111 ፣ ዘፍ 2-15 ላይ ‹‹በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ - በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ›› በማለት ያስረዳል። እንዲሁ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ምዕመናን በላከው መልእክቱ ላይ ‹‹ሊሠራ የማይወድ አይብላ›› (2 ተሰ 3-8-10) ሲል ገልጿል። እነዚህ የሚያስረዱን በሥራችን ሁሉ ቅንነት ታታሪነት ታማኝነት ትጋት ፍቅር ትዕግስት

ጽንዐት --- ወዘተ ገንዘብ ማድረግ እንዳለብን በአጽንዖት ያስረዳናል።እንዲህ ባለ መልኩ ለሥራ ራሱ ምንጩና መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል።

<u>የሕግ መሠረት ነው</u>

ሌላው መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ያለው አስተዋጽኦ የሕጓ መሠረት ነው። ይኸውም ብዙ ነገሮች ከመመንት ጀምሮ እስከ መስረቅና መግደል ድረስ በሕግ የተከለከሉ ሆነው እስከ ዘመናችን ዘልቀዋል። (ዘጸ. 20÷12-17) ቀዳሚው ሕግም «ከገነት ዛፍ ትበላለህ ነገር ግን መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ።›› ያለው ሲሆን የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ግን‹‹ጌታ አምላክን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ኃይልህ ውደደው ታላቂቱና የመጀመሪያይቱ ትእዛዝ (ሕግ) ይህች ናት። የምትመስላት ሁለተኛይቱም ባልጀራህን እንደራስህ ውደድ የምትለው ናት። ኦሪት ነቢያት ሁሉ በእነዚህ በሁለቱ ትዕዛዝት ጸንተዋል›› የሚለው የፍቅር ሕግ ነው። (ማቴ. 22÷34) ስለሆነም መጽሐፍ ቅዱስ የሕጎች ሁሉ ፍፃሜ እና መሠረት ነው ለዚህም ለቤተ ክርስቲያን ያለው አስተዋጽኦ እጅግ ላቅ ይላል።›› ሆኖም በአንድ በኩል ማድረግ የሌለብንን በሌላ በኩል ደግሞ ልናደርገው የሚገባንን በማሰወቅ እግዚአብሔር ዓለሙን የፈጠረውና የሚያስተዳድረውም በሕግና በሥርዓት መሆኑን ያስገነዝበናል። እርሱ ሁሉንም ለማድረግ የሚችል ከኃሌ ኩሉ ቢሆንም ሥልጣንና ክኂል ስላለው ብቻ እንዲሁ ያለ ሥርዓት በዘፈቀደ አይሰራም። ፍጥረታትን እንኳ ሲፈጥር ሥነ ፍጥረቱን በጥበብ ሲያቆራኝና ሲያዛምድ ቀንና ሌሊት ወራትን ሲያፈራርቅ በሠውነታችን ያሉ አካላትንና ዑደተ ሕይወትን ሲተክልና እንዲሰሩ ሲያደርግ ... ወዘተ ሁሉንም ያደረገው በሕግና በሥርዓት ነው። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ይህን የሥነ ፍጥረት ስም ድንቅ ሥርዓት ካዘከረ በኋላ አድንቆ የማይዘልቀው ቢሆንበት ‹‹ ጥቀ ዐቢይ ግብርከ እግዚኦ ወኩሎ በጥበብከ ገበርከ›› በማለት አወድሷል፡ (መዝ.103÷24)

<u>የኪነ ጥበብ ምንጭ</u>

መጽሐፍ ቅዱ ለቤተ ክርስቲያን ካለው አስተዋጽኦ በመጨረሻ የምናነሳው የኪነ ጥበባት ምንጭ መሆኑን ነው። ይኃም የደብተራ ኦሪትን አሠራር ስንመለከት ሙሴ ከሲና ተራራ ጀምሮ ጥበብ ዲዛይን አውጥቶ ነው የወረደው። (ዘጸ. 25÷21) እግዚአብሔር ቤተ-መቅደሱን እርሱ እንዳሳየው ቅርጽና መልክ ዓይነት አድርጎ ተጠንቅቆ እንዲሠራ ደጋግሞ ያሳስበው ነበር። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጸው አጽሎስ ‹‹በመጻሕፍት ዕውቀት የበረታ ነበር።›› (የሐዋ.ሥራ. 18÷24) በጽሑፍ ሊገለጥ የማይችለውን ረቂቁን ዓለም እንኳን በግልጽ በተዋበ የሥነ ጽሑፍ አቀራረብ እንደ ሚያቀርብ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሠክራል። ‹‹እግዚአብሔር አለ፣እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ፣አትንኩትም ›› (ዘፍ. 3÷3) ለሰው ልጆች በመስማት፣በማየት፣በመዳሰስ፣በመቅመስ፣በማሽተት ማለትም በአምስቱ የስሜት ህዋሳት አስቀድሞ የሞትና የህይወትን ጉዳይ ተንትኖ አስረድቷል። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ የትምህርት ወይም የዕውቀት ሁሉ ምንጭ ነው የምንለው። ከዚህም በላይ የጥናትና ምርምር ምንጭ እንደሆነ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ሁሉን መርምሩ መልካሙን ያዙ›› በማለት አስረድቷል።(1 ተሰ 5÷21) የተዋሕዶ አርበኛ የነበረው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ‹‹ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያለማቋረጥ ያነብ ነበር። እግዚአብሔርም የሚያስረዳውን ሰው ላከለት›› በማለት በድርሰቱ ላይ ገልጿል። ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ላይ እንደ ገለጠው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲነበብ እንደነበር ያስረዳል። ይኸውም የሐዲስ ኪዳን ዘመን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ መመርመር እንደሚገባ ያስገነዝባል። (የሐዋ. ስራ. 8÷30) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ‹‹የተውኩትን በርኖሱንና መጻሕፍቱን ይዘህልኝ ና።›› በማለት ለጥናት ብዙ መጻሕፍት እንደ ነበሩት ገልጿል። (2 ጢሞ. 4÷13) በአጠቃላይ ብሉይ ኪዳንንም ሐዲስ ኪዳንንም በጥልቀት ስንመለከት የቅኔ፣የመዝሙር፣የምሳሌ፣የጥበብ፣ የምስጢር፣የታሪክ፣የሐይማኖት፣የትንቢት የትምህርት፡ የምሥጋና፡ የጸሎት፡ የሥርዓት፡ ወዘተ መጻሕፍት ሁሉ ምንጭ ነው።

ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን አስተዋጽኦ እንዲህ ከላይ በዘረዘርናቸው ነጥቦች ብቻ የሚጠቃለል ሳይሆን አጠቃላይ ለመረዳት እና እንደ መግቢያ ያህል ለማወቅ ይህን ያህል ጠቀስን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን አስተቃጽኦ ዘርዝሮ መዝለቅ አይቻልም። ሆኖም አባቶቻችን ‹‹ሁሉን በሰፌድ አትበሉ›› እንደሚሉት ጥቂቱ ይህን ይመስላል።

ምዕራፍ ሁለት
የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ

❖ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም

መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ሐረግ “መጽሐፍ” እና “ቅዱስ” ከሚሉ ሁለት ቃላት የተገኘ (የተሰናሰለ) ሐረግ ሲሆን ትርጉሙም እንደሚከተለው ነው፡-

- መጽሐፍ፡- ማለት ተጠቃሎ በአንድ ጥራዝ ስር የተሰበሰበ ጽሑፍን ሲገልጥ
- ቅዱስ፡- ማለት ደግሞ በዕብራይስጥ ቃሲሽ (ቀዳሽ) በሱርስት ካዲሽ ፡ በግእዝ በአማርኛ እና በዐረብ ደግሞ ቅዱስ የሚል ስያሜ ሲኖረው ትርጉሙም የተለየ የተመረጠ የጠራ የነጻ ንዑድ ክቡር ምሥጉን ማለት ነው።
- መጽሐፍ ቅዱስ፡- ማለት በጥቅሉ የተለየ የተመረጠ የጠራ የነጻ ንዑድ ክቡር ምስጉን መጽሐፍ ማለት ነው።

- መጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የማይለውጠው ዓለማዊውም ሆነ መንፈሳዊው ዓለም በስፋት የተዳሰሰበት ቀዋሚ የሆነ ነገር ጾታ የማይለየው ለሰው ልጆች የተሰጠ ልዩ መጽሐፍ ነው። ሰዎች በሕግ በሥርዓቱ ሕጉን ጠብቀው ሥርዓቱን አውቀው እንዲመሩ ከአምላክ የተሰጠ ሰማያዊ ስጦታ ነው። ሆኖም ይህ መጽሐፍ በፍትሐ ነገሥት መጽሐፍትን ላይ ‹‹መጽሐፈ አምላካውያን›› ተብሎ ሲጠራ በግሪክ ቋንቋ ደግሞ የሚከተለውን ትርጉም ይይዛል፡-

- መጽሐፍ ቅዱስ በግሪክ ቋንቋ ቢብሎስ ወይንም ግራፌ ተብሎ ይጠራል። ይኸውንም ስያሜ ያገኘው ቢብሎስ (Bybios) ተብሎ ከሚጠራ ከተማ ስም የተገኘ ነው። እርሱም ከኒቅያ ወደቦች መካከል ከቤይሩት 25 ማይል ይህል ርቆ የሚገኝ ሀገር ነው። ለመጽሐፍ ያገለግል ዘንድ ፓፒረስ (ደንገል) የተባለውን ተክል እንደ ወረቀት አድርገው ይገለገሉበት የነበረ ቦታ ነው። ቦታውንም መጀመሪያ ግሪኮች (Bybios) ብለው ይጠሩት ነበር።ከረጅም ዘመን ቆይታ በኋላ ግን ስያሜው ለመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የተሰጠ ስለሆነም አሁን መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ያመለክታል።
- እንዲሁ በላቲን ቋንቋም መጽሐፍ ቅዱስ ስክርፒቸር (scripture) ተብሎ ይጠራል። ይኸውም ስያሜውን ያገኘው ለሁሉም ጽሑፍ አጣቃሽ መጽሐፍ ሆኖ ስለሚያገለግል ነው።

- ቅዱሳት መጽሐፍት ወደ ድኅነት ሊያደርሱ የሚችሉ መንፈሳዊ ጥበብ ያላቸው ርትዕት መንገድ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ ስለሆነ እውነትን ለማስተማር ለመመስከር የተሳሳቱትን ለመገሰፅ ስህተትንም ለማረም ይጠቅማል። (ማቴ 21÷42 ሉቃ 24÷32)

አንድም፡- መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የልቡን አሳብ የገለጠበት የምስጢር መዝገብ ነው።

- አባቶቻችንም መጽሐፍ ቅዱስን “የእግዚአብሔር ጥበብ በሰው ቋንቋ” እያሉ ይጠሩታል ።ይኸውም ዕቅዱን ሐሳቡን ለሰዎች የገለጠበት የምስጢር መዝገብ ስለሆነ።

➢ መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ቅዱስ ተባለ?

1 አስገኚው የቅድስና ምንጭ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለሆነ፡-

አባቶቻችን፡ ‹‹ነገር ከሰሩ ውሃን ከጥሩ›› እንደሚሉት ለመጽሐፍ ቅዱስም አስገኚው የምስጥሩ ገላጭ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። በቅዱሳን ላይ አድሮ ያጻፈው እርሱ ነው ለዚህም “በመንፈስ ተሞልተው ተናገሩ” ተብሎ በተደጋጋሚ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተጠቀሰው። (ት.ኢሳ 34÷16 ፡ ዘሌ 19÷2 ፡ 1ኛ ጴጥ 1÷15)

2 ጸሐፊዎቹ ከእግዚአብሔር የተላኩ ቅዱሳን ሰዎች ስለሆኑ፡-

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*`„Ê¡e }ªIÊ

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉ መጽሐፍት ለምሳሌ የምርምር የጥናት፣ የታሪክ፣ የትምህርት፣ የልቦለድ..... ወዘተ መጽሐፍት አስገኚያቸው (ደራሲያኑ) ራሳቸው ሰዎች ናቸው። ነገር ግን የዚህ መጽሐፍ ቅዱስ አስገኚው ቅዱስ አምላካችን እግዚአብሔር ነው። ታዲያ እግዚአብሔር ነው ያስገኘው ሲባል በአንድ ጊዜ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ዮሐንስ ድረስ ያለውን ክፍል በአንድ ጊዜ ተጠርዞ ከሰማይ የወረደ ሳይሆን በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ቅዱሳን ሰዎችን እያስነሳ ለሰው ልጆች መመሪያ ሕይወት ይሆን ዘንድ ያጻፋቸው መጽሐፍት ናቸው። ለምሳሌ፦ ዘፍ **17÷14** **“**እግዚአብሔርም ሙሴን የአማሌቃውያንን ዝክር ከሰማይ በታች ጨርሼ እደመስሳለሁና ይህን ለመታሰቢያ በመጽሐፍ ጻፈው**---”** የሚል ቃል እናገኛለን ከቃሉም እንደምንረዳው ሙሴ መጽሐፉን ሲጽፍ ከራሱ አመንጭቶ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ ተመርቶ የጻፈው መሆኑን ነው። ሊቀ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም ‹‹በመጽሐፍ ያለው ትንቢት ሁሉ ግንም በገዛ ራሱ ሊተረጉመው አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ ከሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ›› (2ኛ ጴጥ 1÷20-21) በማለት የተናገረው፣ እግዚአብሔር በመረጣቸው ቅዱሳን ላይ አድሮ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንዳጻፈ ነው።

3) <u>በእድሜው</u>

መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ ከሚያደርጉት ነገር ውስጥ አንዱ እድሜው ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ በፊት የተጻፈ መጽሐፍ የለም። ለመጀመሪያ ጊዜም የተጻፈው መጽሐፍ መጽሐፈ ሔኖክ ነው። በ **186** ዓ.ዓ የተጻፈ መጽሐፍ ነው። ለዚህ ከዚህ መጽሐፍ የቀደመ መጽሐፍ ባለመኖሩና ከዓለማዊያን (ምሁናት) መጽሐፍት በእድሜ ታላቅ አንጋፋ የሆነ መጽሐፍ በመሆኑ ከሌሎች መጽሐፍ ተለይቶ ልዩ ያደርገዋል።

4) <u>ያለፈውን ነገር በእርግጠኝነት ስለማናገር</u>

መጽሐፍ ቅዱስ መጻፍ የተጀመረው በ **1086** ዓ.ዓ ነው። ነገር ግን ወደ ኋላ ዓለም ሲፈጠር የነበረውን በእርግጠኝነት ይነግረናል። ሌሎች መጽሐፍት ግን ያለፈውን ነገር ለመግለጽ ይሆናል” ወይም ሳይሆን አይቀርም” እያሉ በግምት በመላምልት ይናገራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን አስረግጦ ይነግረናል ለምሳሌ፦ ሊቀ ነብያት ቅዱስ ሙሴ በዘፍ 1÷1 ላይ ‹‹በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ **-** በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ›› ሲል ፈጥሮ ይሆናል ሳይፈጥር አይቀርም እያለ አልተናገረም እርግጠኛ ሆኖ አስረግጦ አስቀመጠልን በዘፍ **1÷@6** ላይም ‹‹ወይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርያነ ወበ አምሳሊነ›› ይላል እንጂ እግዚአብሔርም ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር ብሎ ነበር። አላለም አስረግጦ እንፍጠር አለ። ብሎ ነው ያስቀመጠልን። ለዚህ ያለፈውን ነገር እርግጠኛ ሆኖ ስለሚነግረን ከሌሎች መጽሐፍ ተለይቶ መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ ያደርገዋል።

5) <u>ወፊ ፊት የሚመጣውን በእርግጠኝነት ስለሚነግረን</u>

መጽሐፍ ቅዱስ ኃላፊያቱን እንደሚነግረን ሁሉ መጻያቱንም ይነግረናል። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ የወደፊቱን ነገር በእርግጠኝነት ስለሚነግረን ከሌሎች መጽሐፍ ልዩ ያደርገዋል። ሌሎች መጽሐፍት የወደፊቱን ሲናገሩ በግምት አልያም በመላምልት ሊሆን ይችላል በማለት ይገልጻሉ እንጂ እርግጠኛ ሆነው አይናገሩም መጽሐፍ ቅዱስ ግን በእርግጠኝነት ይነግረናል ለምሳሌ፦ ኢሳ **7÷04** **“**ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወትሰይም አማኑኤል ዘበትርጓሜሁ እግዚአብሔር ምስሌነ **-** እንሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅንም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች” ብሎ ነብዩ ሲገልጽ በእርግጠኝነት ነው እንጂ ድንግል ወንድ ልጅ ልትወልድ ትችላለች እያለ የግምት ቃል አልተጠቀመም። ልበአምላክ ቅዱስ ዳዊትም በመዝ **$9---------- 2** LÃU eK¡`e„e ÇÓU Uê›ƒ c=“Ñ` **#Ó²=›wN?`c ÑHÅ ÃSê ¨›UL¡’H> ›=Á[UU dƒ Ã’ÉÉ upÉT@G<$** ›K ”Í= Ó²=›wN?` uÓMØ K=S× Ã‹LM:: ›LKU u`ÓÖ˜’ƒ ÃS×M wKA ’¨< ÁekSÖ¨<:: ለዚህ እንዲህ ባለ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ የወደፊቱን ነገር በእርግጠኝነት በመናገሩ ልዩ ያደርገዋል።

➢ <u>መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ዓለማ</u>

1. የሚታየውንና የማይታየውን ፍጥረት የፈጠረው እግዚአብሔር እንደሆነና ዓለምን ከመፈጠሩ በፊትም ሆነ በኃላ በክብር በአንድነት በሦስትነት እንዳለ ለመግለጥ **(**ዮሐ **1÷1-4)**
2. እግዚአብሔር እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ እንሆነ ለማስረዳት እና እሱን ብቻ እንድናመልክ ለማስተማር **/**ዘዳ **0÷2-6/**
3. የእግዚአብሔር ባህርይ እና ዘላለማዊ ፈቃድ ምን እንደሆነ አውቀን እንደፈቃዱ እንድንመራ ለማድረግ **/05÷4/**
4. ሥጋን ለብሶ የተገለጠው የእግዚአብሔር Mጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር እነደሆነ አምነን በስሙም ዘላለማዊ ሕይወትን እናገኝ ዘንድ **/**ዮሐ **5÷03/**
5. እግዚአብሔር ኃጢአትን እንጂ ኃጢአተኛን እንደማይጠላ በንስሐ ወደ እርሱ እንድንመለስ እንደሚፈልግ ከተመለስን ደግሞ ከኃጢአታችን እንደሚያነጻን ለማስረዳት
6. በተዋሕዶ ዓለም መዳሉን እና የመዳኑን ድንቅ ስራ ለማሳወቅና ለማስገንዘብ።
7. ጌታችን ኢሱስ ክርስቶስ በክብር እንዳረገ በግርማ መለኮት በክበበ ትስብእት (ሥጋ) ይህን ዓለም ለማሳለፍ እንደሚመጣ አውቀን ተዘጋጅተን እንድንኖር ለማስገንዘብ።(ማቴ @4 ”“ @5):: u›ÖnLÃ SêNõpÆe ¾}éð¨< KƒUl`ƒ ’¨::< **#SêNõƒ uT>cÖ<ƒ Sê“”ƒ }eó ÃJ”M” ²”É ›ekÉV ¾}éð¨< G<K< KƒUl`ƒ }êð²M$ /aT@ 05÷4////** uTKƒ pÆe ä¨<KAe ”ÅÑKç¨<:: ”Ç=G< ¾²LKU QÃ¨ƒ ”Èƒ UÅU“Ñ˜ K=Ád¾”

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*`„Ê¡e }ªIÊ

#¾²K¯KU QÃ¨ƒ □”ÇL‹G< □¨<I ²”É ----------êôL‹ኃ KG<$ /ÄN 5÷03// c=M pÆe ÄN”e u ወ”Ñ@K< LÃ ÑM ፯ል።

➢ <u>መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ይጠቅማል?</u>

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅምን እንዲህ ነው ብሎ ዘርዝሮ መዝለቅ ይቻልም። ሆኖም ግን አባቶቻችን “ዓባይን በጭልፋ” እንደሚሉት ሁሉንም ዘርዝሮ መግለጽ ባይቻልም ከፊሉን (ከብዙ በጥቂቱን) ከዚህ ቀጥለን እንደሚከተለው እንመለከተዋለን።

1) <u>የሰው ልጅ እንዲመራበት፦</u> መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጆች ወደ ዘላለማዊ ድኅነት እንዲደርሱ የሚያደርግ ብርሃናዊ መንገድ መሪ ነው። ለዚህም ልበአምላክ ቅዱስ ዳዊት ‹‹ሕግ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው›› መዝ 118÷ 105 በማለት በመግለጽ አስረድቶታል። ከዚህ በተረፈ ሊቀ ነብያት ቅዱስ ሙሴ በዘጸ 20÷ ከ ቁጥር 3 ጀምሮ ዘርዝሮ እንዳስቀመጠልን ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ልንሻገር የምንችልበትን የጽድቅ መንገድ መሪያችን የሆነውን ፀሥርቱ ትእዛዛት (ሕገ ኦሪትን) አስቀምጦልናል። እንዲሁ ደግሞ ከላይ በምራፍ አንድ ውስጥ እንደዘረዘርነው መጽሐፍ ቅዱስ አሁን ለደረስንበት የሥላጣኔ ጊዜ መሠረት እንደሆነና ለብዙ ነገሮች ምንጭና መሠረት እንደሆነ አይተናል። ከዚህ ጋር በተያያዘም አሁን በዓለማችን ላይ የምንመለከታቸው የሥራ ዘርፎች መሠረታቸው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይኸውም፦

- ✓ <u>ምህንድስና</u> አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብ የምህንድስናን ጥበብ ይረዳን።ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው ኖህ እሱና ቤተሰቡ ከጥፋት ውሃ የሚድኑበትን መርከብ እንዴት እንደሰራ ከዘፍ 6 ËUa Ã“Ñ^M::eK u?} SpÅeU ›c^` T¨p ¾T>ðMÓ c¨< ŸSêNõ pÆe ¾›c^\” Øuw □“ u¨<eÖ< K=Á□}□†¨< ¾T>Ñu<ƒ” ’Ña‹” uT>Ñv Ã[ÇM**:: (²ç@5÷8ÝÝ: 2²?“ 3÷3 :1’Ñ6÷1-#8)**
- ✓ **<u>Q¡U“</u>:-**¾l¡U“” Øuw Kc¨< MÐ‹ ¾ÑKÖ¨< □Ó²=›wN?` ^c< ’¨<:: Ã¤¨<U ሐኪም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዱ የሥራ መስክ ነው። ሐኪም ወይም በለ መድኃኒቶች ከተለያዩ ቀጠሎች መድኃኒት በመቀመም ቁስልና የመሳሰሉ በሽታዎችን የሚፈውሱ ናቸው። ለምሳሌ፦

<u>ኖኅ</u> ከምድር እንጨቶች አጋንንት ያወጣ እንደ ነበር ደዌ ይፈውስ እንደነበር። /ኩፋ ***10+7/*** ተጽፏል። ንጉስ ሕዝቅያስ በጠና በታመመ ጊዜ ነብዩ ኢሳይያስ በበለሱ እባጭ እንደፈወሰው /ኢሳ.***38÷21/*** ላይ ተጠቅሷል። ልክ እንደዚህ ዓይነት የህክምና ሥራ ቀድሞ የነበረ ነበር። በቅዱስ ወንጌል ላይም እስራ ሁለት ዓመት ሙሉ ደም ሲፈሳት የነበረችው ሴት ገንዘቧን ከሰረች እንጂ ባለመድኃኒቶች የሚያድኗት አልነበረም። ይህ የሚያሳየን በወቅቱ በዚህ በሐኪምነት ሥራ ተሰማርተው የነበሩ እንዳሉ ነው። ወንጌላዊ ሉቃስም ‹‹ባለመድኃኒት ›› ሐኪም ተብሎ ይጠራ ነበር።/ቆላ ***4+14/*** Ÿ²=I ¾SêNõ pÆe ¡õM ¾U”[Ç¨< ¾Q¡U“” Øuw □“ SÉ□’>ƒ □”Èƒ □“ ŸU” ¯Ã’ƒ °ÎªƒƒÅT>c^ ’¨<::

- ✓ **<u>›e}ÇÅ`’ƒ</u>**:-uSêNõ pÆe ¨<eØ eK ›e}ÇÅ`’ƒ cò ƒUI`ƒ ÃÑ—M:: Ã¤¨<U u¯KU S”ÓY□ƒ SM ካ U ›e}ÇÅ` □”Ç=cõ” uS”Ó ሥƒ □“ uQ´w S”ŸM M¿’„‹ □”ÇÃcó WLU □”Ç=cõ” ØL‰“ SKÁÁƒ □”Ç=Öó ¾T>Áe}U` õƒI `ƒ° □”ÇÃ ጓደል ጽኑዕ መሠረት እና መመሪያ የሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ለዚህም ሊቀ ነብያት ቅዱስ ሙሴን አማቱ ዮቶር ‹‹**---** ከሕዝቡ ሆሉ ጎያላን ሰዎችን እግዚአብሔርን የሚፈሩትን እውነተኞችን ሰዎችን ትዕቢትንም የሚጠሉ ሰዎችን ፈልግ ከእነርሱም የሺህ አለቆችን የመቶ አለቆችን የኀምሳ አለቆችን የዐሥርም አለቆችን ሹምላቸው። በሕዝቡ ላይ ሁል ጊዜ ይፍርዱ። የከበደውን ነገር ወደ አንተ ያምጡት ቀላሉን ነገር ሁሉ እነርሱ ይፍረዱ ያቃልሉልሃልም ይረዱሃልም›› ሲል እንዳስገነዘበው ሙሴም እንዱህ አደረገ መልካም አስተዳደር ፍትህ ርትዕ እንዳይጓደል ከዚያን ዘመን ጀምሮ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት ለሥራ አመራር ጥበብ (ሳይንስ) ታላቅ መሠረት ተጣለ።(ዘጸ 18÷13-27) ሆኖም ¾K=k ’wÁƒ ¾pÆe S<c? □]¡ □”ÅU”[Ç¨<< □”Èƒ Q´u<” u`I^H@“ uƒ°Óeƒ up”’ƒ □“ uõp` □”Èƒ SU^ƒ □”ÅT>Ñv Ád¨<nM::u}KÃU Ÿ^c< ፬Mp ሕ´u<” □”Èƒ ÁekÉU □”Å’u` Áe[Ç“M:: (²é#2÷#2):: Ÿ²=I u}ÚT] ›=Ác<:Ç©ƒ: cKAV” □”Èƒ Áe}ÇÉ\ □”Å’u` }ê÷M::**(**1’Ñ 3÷07-@8)
- ✓ **<u>Ów`“</u>:-** □Ó²=›wN?` K›ÇU ¾cÖ¨<” ƒ°³´ Á’uu G<K< □`h SŠ □”Èƒ uU” □”Å}ËS[Ã[ÇM: (²õ3÷07) ይከውም እግዚአብሔር አምላክ ለአዳም አርሶ ቆፍሮ እንዲበላ ትእዛዝ ከተሰጠው በኋላ በላቡ ጥሮ ግሮ ለመብላት መሬትን እያለሰለሰ ይጠቀም ነበር። ይህ የግብርና ስራ ከብት እርባታና እርሻን አደንን የሚያጠቃልል የሥራ መስክ ነው። ገበሬ የሚለው ቃል አብዛኛውን የእርሻ ሥራን ሲያመለክት ይታያል። ከብት እርባታ ይህ የሥራ መስክ ከግብርና ጋር ይጠቃለላል። ይህ የከብት እርባታ በእስራኤል ሀገር እጅግ ጥንታዊ ከሚባሉ የግብርና ሥራዎች አንዱ ነው። የአዳም ልጅ አቤል ሥራው በግ ጠባቂ ነበር። ለዚህም ነው ለአምላኩ የበግ መስዋዕቱን ያቀረበው። አባታችን አብርሃምን፥ ሎጥንም ብንመለከት በከብት ርቢ /እርባታ/ ይተዳደሩ ነበር። /ዘፍ ***12÷5***፣ ዘፍ ***13÷5-8/*** የዐሥራ ሁለቱ ነገድ አባት ያዕቆብ ለብዙ አመታት በግ ሲጠብቅ ነበር /ዘፍ ***30÷29/*** በዚህም

ዮሴፍ አባቱን በግብጽ በጌሤም ምድር ባገኘው ጊዜ ስለ ወገኖቹ የተናገረው እስራኤላውያን በክብት እርቢነታቸው የታወቁ እንደሆኑ ያስረዳናል። /ዘፍ ***46÷31-32/*** ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ለንግስና ከመታጨቱ በፊት በግ ጠባቂ ነበር።

- <u>እርሻ</u> ይህ *ሥራ* በእስራኤል ሀገር የወይራ ዛፍ በለስ ወይን ስንዴ..... የመሳሰሉትን በማምረት ይታወቁ ነበር። ለመጀመሪያ ግብርና የተጀመረው በአባታችን አዳም እንደሆነ ቀደም ብለን አንስተናል። ሆኖም ቀጥሎም ልጁ ቃየን ምድር ያርስ ነበር። ይህም በዘፍ ***4÷2*** ላይ ተጠቅሷል ። የእግዚአብሔር ሰው ኖኅም በእርሻ ስራ ተሰማርቶ ነበር። ‹‹ኖኅም ገበሬ መሆን ጀመረ ወይንም ተከለ›› ዘፍ ***9÷20*** ተብሎ እንደተገለጸው። እንዲሁ የብዙዎች አባት አብርሃምም ገበሬ ነበር። ይተዳደር የነበረው በእርሻ ነበር።/ዘፍ ***21÷33/*** የኤልያስ ደቀመዝሙር የነበረው ኤልያዕ ኤልያስ ሳይጠራው በፊት በእርሻ *ሥራ* ተሰማርቶ ነበር። /ነገ ***19÷19/*** አክአብና ኤልዛቤል የገደሉት ምስኪኑ ኢይዝራኤላዊው ሰው ናቡቴም የወይን እርሻ ነበረው። /ነካ ***20÷1/*** ይህ የሚያሳየን ናቡቴም የሚተዳደረው በእርሻ *ሥራ* እንደነበር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ የግብርና ስራ በስፋት የተጠቀሰ እንደሆነ እንረዳለን። ከዚህ በተጨማሪ መሬትን ሁልጊዜ በየዓመቱ ከማረስ ይልቅ ሳይዘሩ ሳያርሱ የማቆየት ትምህርት ከዛሬ 3500 ዓመታት በፊት በዘመነ መሳፍንት በሊቀ ነብያት ሙሴ በኩል ከእግዚአብሔር የተሰጠ መመሪያ ነው። ‹‹ስድስት ዓመት ምድሪቱን ዝራ በሰባተኛው ዓመት ግን ተዋት አሳርፋትም›› (ዘጸ 23÷10) ምድሪቱ በሰባተኛው ዓመት ማረፏ ለቀጣዩ የምርት ዘመን በቂ ለም አፈር ለማከማቸት ይረዳል። አብሶ አሁን ባለው በዘመናዊው የስተራረስ ዘዴ የሚደገፍ ሲሆን ለአስተራረስ ዘዴያችን ምንጭ እና መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ያስገንዝበናል። ሌላው አንዳንድ ሀገሮች ማለትም ኢትዮጵያን ጨምሮ የሚጠቀሙት እኅልን ለችግር ወቅት ማስቀመጥ (በጎተራ የማስቀመጥን ዘዴ) መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ነገር ነው ይኸውም በዘፍ 41÷25-36 ድረስ ተጽፎ እንደምናገኘው ጥበበኛው ቅዱስ ዮሴፍ ለሰባቱ የድርቅ ዘመናት በሰባቱ የጥጋብ ዘመናት እንዳከማቸ እና በድርቅ ዘመን መላዋ ዓለም በድርቅ ስትመታ ግብጽን ግን ድርቅ እንዳላገኛት ያስረዳናል ይህ የሚገልጸው ለችግር ወቅት ብሎ ማስቀመጥ እንደሚገባ ነው።

✓ <u>የንግድ *ሥራ*</u> የንግድ *ሥራ* ከጥንት ጀምሮ የስራ መስክ እንደነበር ታላቁ መጽሐፍትን የሚመሰክረው ነው። *ሥ*ርወ ሃይማኖት አባታችን አብርሃም ነጋዴ እንደ ነበር /ዘፍ ***13÷3/*** ላይ ይናገራል። አባታችን አብርሃም ከክብት እርባታ ባሻገር የንግድ *ሥራ*ውን ይሰራ ነበር። ይኖር የነበረውም በከለዳውያን ምድር ዑር በምትተባል ከተማ ነበር። ዑር በንግድ ስራ የታወቀች የገነነች መሆኗን ታሪክ ያስረዳናል። ግብጽንም ስንመለከት የንግድ መነኸርያ ነበረች። ነጋዴዎች ወደዚህች ሀገር በመምጣት ንግዳቸውን ያከናውናሉ ግብጽ የባርያ ንግድ ካስፈፉት ሀገሮች አንዷ ናት። እንደውም ወልደ ያዕቆብ ዮሴፍን ለፈርዖኑ ቢጥፋራ የሸጡት ወደ ግብጽ ለንግድ ይጓዙ የነበሩት ነጋዴዎች ነበሩ ። /ዘፍ ***37÷30/*** በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የነገሰው ጠቢቡ ሰለሞን ኢየሩሳሌም የንግድ መናኸርያ ስለነበረች ግብር ይቀበል ነበር።/ ***1*** ኛነገ ***10÷14/*** ነብዩ ዮናስም ወደ ተርሴስ ለመጓዝ የተሳፈረበት መርከብ የነጋዴዎች ነበር። በዚህ የባሕር ላይ ንግድ ኖሮ ይገበያዩ እንደነበር ያስረዳል። ጌታችንም እንደሌሎቹ *ሥራ*ዎች ሁሉ ትምህርቱን በንግድ መስሎ አስተምሯል። /ማቴ ***25÷14-30/*** ነጋዴያን ለቃለ እግዚአብሔር መስፋፋት ጥልቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል ንግስተ ሳባ የሰለሞን ጥበብ የሰማችው ከነጋዴው ታምሪን ነበር። በሐዲስ ኪዳንም እነ አባታችን አባ ሰላማ አጎታቸው ነጋዴ ስለነበሩ ለንግድ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ይዟቸው እንደመጣ ይነገራል። እነዚህ በሙሉ የሚያስገንዝቡን ለንግድ *ሥራ* መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ነው።

✓ <u>አንጥረኞች እና ቀጥቃጮች</u> ፦ እነዚህ አንጥረኞች እና ቀጥቃጮች የምንላቸው ወርቅ እና ብር የሚሰሩ ናቸው። እስራኤላውያን ምድያማውያንን ወግተው ሲመልሱ የማረኩዋቸውን የወርቅ፣ የብር ፣ የነሀስ ፣የቀርቆሮ የብረት ጌጣጌጦችን እንደነበር እንዲጨፈልቁ መታዘዛቸው ከዚህ በፊት እንደዚህ አይነት *ሥራ* የሚሰሩት አንጥረኞች እና ቀጥቃጮች እንዳሉ ያስረዳል። /ዙኁ ***31÷32-23/*** የእግዚአብሔርን ታቦት ከኤልያስ ጋር ሆኖ የቀረጸው እና በወርቅ እና በዕንቁ የለበጠው ባስኤል የተባል ጥበብ ከእግዚአብሔርን ዘንድ የተሰጠው አንጥረኛ ሰው እንደ ነበር።/ዘጸ ***31 -1፥ ዘጸ 36 -1/*** ያስረዳል ንጉሱ ጠቢቡ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ሲያሰራ ቤተ መቅደሱን የሚያስጌጡ የሚያስውቡ አንጥረኞች ቀጥሮ ነበር። እንደውም ለዚህ አገልግሎት ክቡር ዳዊት ለጢሮስ ንጉስ በይሁዳ እና በኢየሩሳሌም ያሉትን ብልሃተኞች ወርቅ ብር..... የመሳሰሉትን የሚሰሩትን አንጥረኞች እንዲልክለት አዝዞ ነበር። ***/2*** ዜር ***2÷7/*** ከዚህም የምንረዳው ለአንጥረኝነት እንኳን መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ነው።

✓ <u>ግንበኝነት</u>፦ ግንበኝነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰናዖርን ግንብ ከሠሩት ሰዎች ጀምሮ ተጠቅሶ ይገኛል። /ዘፍ ***11÷1-9/*** በተጨማሪ እስራኤላውያን በዚህ በግንበኝነት *ሥራ* ይታወቁ ነበር። በግብጽ ሀገር በባርነት ሳሉ ዛሬ ዓለም የሚያደንቃቸውን ፒራሚዶች ሰርተዋል እነዚህ ፒራሚዶች ከሰባቱ የዓለም አስደናቂ ስራዎች ውስጥ እንደ አንዱ የሚቆጠሩ ናቸው። ይህ በኦሪት የተፃፈው ታሪክቸው ከዚህ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው። ጡብ በመስራት ለፈርዖን <u>ፊቶምና</u> <u>ራምሴ</u> የተባሉ ጽኑ ከተሞች እንደሰሩ ተጽፏል /ዘዳ ***1÷8-14/*** ከግንበኝነትና ከእናዒነት በተጨማሪ ሌሎች የተግባረእድ /የእጅ *ሥራ*ዎች/ መስኮች አሉ። እስራኤላውያን የተለያዩ የዓለማችን ሀገራት ላይ ተሰደው ሲኖሩ የተለያዩ የእጅ ስራዎችን ይቀስሙ ነበር። ___

1. <u>የእግዚአብሔር ትዕዛዝና ፈቃድ ለማወቅ ነው፦</u> መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠው ሕግ የሚያስረዳ በመሆኑ ይህንን ምስጢር ለብርሃን ልጆች የሚበልጥ መምህር ነውና ጥቅሙ እጅግ ላቅ ይላል።

2. <u>ስለ እግዚአብሔር መግቦትና ሕልውና ለማወቅ፡-</u> መግቦት ማለት ስልጣን አገዛዝና ጥበቃ የሚያጠቃልል ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ስልጣን፣ አገዛዝና ጥበቃ ለማወቅ ይጠቅማል።

የመጽሐፍ ቅዱስ መቼት

➢ <u>መጽሐፍ ቅዱስ መቼ ተጻፈ?</u>

መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት ጸሐፍት መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉበት ዘመን ቢለያይም መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ መጽሐፈ ሔኖክ ተጻፈ። በዚህ መጽሐፍት መጻፍ ጀመሩ በ **1086** ዓ.ዓ የሔኖክ መጽሐፍ ተጻፈ። እስራኤላዊያን በባርነት ሳሉ በፈርዖን ዘመን የኢዮብ መጽሐፍ ተጻፈ በ **3843** ቅ/ል/ክ እስራኤላውያን ከባርነት ወጡ በዚህ ጊዜ የኦሪት መጽሐፍት ተጻፈ። በ **4407** ቅ/ል/ክ ሳዖል ሞተና ዳዊት ነገሠ። በዚህ ጊዜ የዳዊት መዝሙር ተጻፈ.....እያሉ ቅዱሳት መጽሐፍት መጻፍ ጀምረዋል።

➢ <u>መጽሐፍ ቅዱስ በማን ተጻፈ?</u>

መጽሐፍ ቅዱስን ቅዱሳን አባቶቻችን በመንፈስ ተመርተው ጽፈውልናል። በእያንዳንዱ ጸሐፍት ሊቅ፣ነብይ፣ሐዋርያ ላይ አድሮ የገለጸ፣ የመራ፣ ያናገረ ያጻፈ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው።(ዮሐ **04÷ @6/ /1** ቆሮ **02÷03)** ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ሰዎች ከእግዚአብሔር እየታዘዙ የጻፉት መሆኑን እንረዳለን።መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ጊዜና ቦታ ከተለያዩ የሥራ መስክ በተጠሩ ሰዎች እንደተጻፈ ይታመናል። ሆኖም እነዚህ ቅዱሳን ሰዎች ወደዚህ ግብር ከመጠራታቸው አስቀድሞ የተለያየ ተግባር እንደነበራቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስን ከተለያዩ የኑሮ ዘይቤ እና ደረጃ የተጠሩ ከ **40** በላይ ቅዱሳን ጽፈውታል። ለምሳሌ፡-

- ✓ ከእረኝነት ሙሴ፣ ዕዝራ አሞፅ
- ✓ ከነገሥታት ዳዊት፣ ሰሎሞን
- ✓ ከካህናት ዘካርያስ፣ ኤርሚያስ፣ ሕዝቅኤል
- ✓ ከቀራጭነት ማቴዎስ
- ✓ ከሐኪም ሉቃስ
- ✓ ከአሳ አጥማጅነት፡- ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ
- ✓ ከአሳዳጅነት ቅዱስ ውሎስ .....ወዘተ ተጠርተው ጽፈዋል።

ሆኖም ግን ከእነዚህ የሥራ መስክ ተጠርተው ቅዱስ አባቶቻችን መጽሐፍን ጽፈውልናል። ግን በሐዲስ ኪዳንና በብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች መካከል መጠነኛ የአጻጻፍ ልዩነት አለ ለምሳሌ፡- ነብያት ይወርዳል ይወለዳል ይጠመቃል ይሰቀላል ይሞል ይነሳል ያርጋል እያሉ ሲጽፉ ሐዋርያት ደግሞ ወረደ ተወለደ ተጠመቀ ተሰቀለ ሞተ ተነሳ ዐረገ እያሉ ጽፈዋል።አባቶቻችን ‹‹ነብያት የዘሩትን ሐዋርያት አጨዱ›› እንዳሉ። የነብያት የተስፋ ትንቢት የተፈጸመው በሐዲስ ኪዳን ስለሆነ ነብያት ለማየት የናፈቁት ግን አረፍተ ዘመን የገታቸውን ሐዋርያት ግን አይተው የሰሙትን የዳሰሱትን ጽፈውልናል።ያዕቆብ ዘሰሩግ እና አባ ህርያቆስ በቅዳሴያቸው ላይ ‹‹ነብያት ለማየት የናፈቁት ግን ዐረፍተ ዘመን የገታቸውን እኛ ግን አየነው ዳሰስነው አልፎም ተርፎ በላነው ጠጣነው››ብለው እንደተናገሩት።

➢ <u>መጽሐፍ ቅዱስ በየት ቦታ ተጻፈ?</u>

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊያን “ ዘመኑ እንደሚለያይ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትም ቦታ የተለያየ ነው።ግን አሁን ባለው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እስያ፣አውሮፓ እና አፍሪካን ያጠቃልላል። ለምሳሌ፡-

- ➢ የኦሪት መጽሐፍት.....በሲና ምድረ በዳ
- ➢ መጽሐፈ ኢያሱ.....በኢየሩሳሌም
- ➢ ትንቢተ ዳንኤል.....በባቢሎን(ኢራቅ)
- ➢ መጽሐፈ አስቴር.....በፋርስ(ኢራን)
- ➢ መጽሐፈ ነገስት.....በኢየሩሳሌም
- ➢ የማቴዎስ ወንጌል.....በፍልስጥኤም
- ➢ መጽሐፈ መሳፍንት.....በምድረ ከነዓን
- ➢ የማርቆስ ወንጌል.....በምድረ ግብጽ
- ➢ የዮሐንስ ራዕይ.....በፍጥሞ ደሴት(ቱርክ).....ወዘተ መጽሐፍ ቅዱስ በእነዚህ ቦታዎች ተጽፈዋል።

➢ <u>መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ተጻፈ?</u>

➢ እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጣቸው ታላቁ ስጦታ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።ሆኖም ግን ይህ ቅዱስ መጽሐፍ እንዴት ተጻፈ ለሚለው፡-

1. በእግዚአብሔር ትእዛዝና ፈቃድ ተጽፏል።
2. በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሪነትና ገላጭነት ተፅፏል። (ዘጸ 17÷14 ፣ ራእ 1÷17 ፣ 2ኛ ጥ 1÷21)

3. በእግዚአብሔር መገለጥ ፡- ቅዱስ አምላካችን እግዚአብሔር ለቅዱሳን አባቶቻችን በህልም በራእይ እና ፊትለፊት እየተገለጠ ያጽፋቸው ነበር። (ዘኁ 12÷6-8) እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ አድሮባቸው ቃሉን በአፋቸው ያናግራቸው እንደነበር ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ‹‹ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ተናገረ ቃሉም በአንደበቴ ላይ ነበር›› (2 ኛ ሳሙ 23÷2) በማለት ገልጿል።
4. ከእውነተኞች ምስክሮች፣ ይኸውም ቅዱሳን አባቶቻችን በጥንቃቄና በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት በመሰብሰብ ጽፈውልናል። (ሉቃ 1÷1-4)
5. ቅዱሳን አባቶቻችን በየራሳቸው የአጻጻፍ መንገድ ቋንቋ እና ባህል ጠብቀው ጽፈውታል ለምሳሌ፡-
   - ✓ ማቴዎስ፡- ዘር ሐረግን ሲቆጥር በወንዶች የቆጠረው በዕብራውያን ልማድ ባህል ዘር የሚቆጠረው በወንዶች ስለሆነ።(ማቴ 1÷16)
   - ✓ በመጽሐፈ አስቴር ላይም ጸሐፊው የ ፋርስን ቤተ መንግስት እውቀት ያሳየናል (መጽ አስ 1 ጀምሮ)
   - ✓ በሉቃስ ወንጌል የወንጌላዊውን የሥዕል ችሎታ በሥዕላዊ አቀራረብ እናስታውሳለን።
6. አባቶቻችን ብራናንና፣ክርታስን እየወጠሩ በቀርክሀ እና በላባ ብዕርነት ከዕንፅዋትና ከእንስሳት ተዋፅዖ ቀለማትን በመሥራት ቅዱሳት መጽሐፍትን ጽፈውልናል።

➢ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ቋንቋ?

ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው ጸሐፊዎቹ የተለያዩ ቅዱሳን አባቶቻችን እነደሆኑ የተጻፈበትም ቦታና ዘመን የተለያዩ እንደሆኑ ሁሉ የተጻፈበትም ቋንቋ የተለያዩ ቋንቋዎች ናቸው። ይሁን እንጂ አብዛኛው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲጻፉ አብዛኞቹ የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ደግሞ በግሪክ ቋንቋ ተጽፈዋል። ሆኖም ግን በ 980 ቅ/ል/ክ አካባቢ ቀዳማዊ ምኒልክን አጅበው ወደ ሀገራን የገቡት ሌዋውያን ካህናተ ኦሪት የግእዝን ቋንቋ በሚገባ አጥንተው ይዘው የመጡትን እስከ ሰሎሞን ድረስ ተጽፈው ያሉትን መጽሐፍት ወደ ግእዝ ቋንቋ ተርጎመዋል። እንደዚሁ በ 284 ቅ/ል/ክ በንጉሥ በጥሊሞስ ዘመነ መንግሥት በ 70 የአይሁድ ሊቃውንት (septuagint or LXX) ከዕብራይስጥ ቋንቋ ወደ ፅርዕ (ግሪክ) ቋንቋ መጽሐፍት ብሉያት ተተርጉሟል።እንደዚሁ በሐዲስ ኪዳንም እስከ 5 ኛው መ/ክ/ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ ሲተነገም የቀጠለ ሲሆን ነገር ግን እስከ አምስተኛው መ/ክ/ዘመን ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጎመባቸው መሠረታውያን ቋንቋዎች ከዚህ የሚከተሉት ናናቸው።

መሠረታዊ መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጎመባቸው ቋንቋዎች

✓ ግዕዝ ✓ሮማይስጥ /ላቲን/ ✓ አርመንኛ ናቸው
✓ ቅብጥ ✓ ሱርስት

እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው ቋንቋዎች መጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጎመባቸው ቋንቋዎች ናቸው። ነገር ግን ከዚህ በኋላ የተነሱ የተለያዩ ቅዱሳን አባቶቻችን በየሀገራቸው ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን ተርጉመዋል። ይኸውም

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በምሥራቅ ሀገራት

- አባ ጀሮም ለ 40 ዓመታት የዕብራይስጥና የግሪክን ቋንቋ ጠንቅቆ ከተማረ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ሀገሩ ቋንቋ ወደ ላቲን ቋንቋ ተርጉሟል። ይህ የአባ ጀሮም ትርጉም ‹‹ቩልጌት›› በመባል ይታወቅ ነበር።
- በ 15/25 እ/ኤ/አ ቴንዳሌ የተባለ እንግሊዛዊ የተወሰኑ መጽሐፍትን ወደ እንግሊዘኛ ቋንቋ ተርጉሟል።
- የሮሃው ራቡላ የመንበጉ ፊሊክሲዩስ በ 5 ኛው መ/ክ/ዘመን እንደዚሁ ቶማስ ዘሄራክል በ 7 ኛው መ/ክ/ዘመን የጥንቱም የሱርስት ቋንቋ የተተረጎመውን መጽሐፍ ቅዱስ አቃንተዋል።
- በሮማንያም ቅዱስ ሜስሮኝ እና ቅዱስ ሳህክ በ 3 ኛው ና በ 4 ኝው መ/ክ/ዘመን መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አርመንያ ቋንቋ ተርጉመዋል።
- በአሁኗ ሮማንያና በጥንቷ ዳኪያ (dacis) ይኖሩ የነበሩ የጎይቲኮች ወገን የሆነው ውልፊላ በ 350 ዓ/ም በቡልጻርያ ተቀምጦ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ሀገሩ ቋንቋ መልሷል።
- ዊሊያም ኬሪ የተባለ ሚሲዮናዊ በ 1801 ዓ/ም መጽሐፍ ቅዱስን ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር በመሆን ወደ 44 የሕንድ ቋንቋዎች ተርጉመዋል።
- አዶረኒራም ጻድሰን (adoniran judson) በ 1850 ዓ/ም መጽሐፍ ቅዱስን ወደ በርማ ቋንቋ ተርጉሷል።
- የስኮትላንዱ ሚሲዮናዊ ሮበርት ሞሪሰን በ 1823 ዓ/ም መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ቻይንኛ ቋንቋ ተርጉሟል።
- ካርል ጉዝላፍ (karl gutzaf) በ 1837 ዓ/ም የዮሐንስ ወንጌልን ወደ ጃፓንኛ ቋንቋ ተርጉሟል።
- ማቶዲየስ እና ቄርሎስ የተባሉ ሁለት ግሪካውያን ወንድማማቾች መጽሐፍ ቅዱስን በ 10 ኛው ምዕት ዓመት ወደ እስላቦኒክ ቋንቋ ተርጉመዋል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በአፍሪካ ሀገራት

አፍሪካ ቀድሞ በጥፋት ውኃ ጊዜ መላዋ ዓለም በንፍር ውኃ ስትጠፋ እግዚአብሔር አምላካችን ለኖኅ አንተ እና ቤተሰብህ የምትድኑበትን መርከብ ሥራ ብሎት መርከብ አሰርቶት ስለነበር በመርከቡ ተጠልለው ከጥፋት ውኃ ድነው ነበር። በዚህ ጊዜ ኖኅ ልጆቹ ሦስት ስለነበሩ ለሦስቱ ልጆቹ ይህቺን ዓለም በዕጣ ከፍሎ በሚሰጣቸው ጊዜ ለያፌት የአውሮፓ ሀገራት ለሴም የእስያ ሀገራት ሲደርሳቸው ለካም በዕጣው የደረሰው የአፍሪካ ሀገራት ነበር። በዚህም ካም ሚስቱ አኤልታማክን ይዞ ወደ አፍሪካ ሀገራት በመምጣት አፍሪካን ቆረቆራት። ኋላም ለልጆቹ አከፋፍሎ

ልጆቹም ዛሬ በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙትን ሀገራት አቅንተው መኖር ጀመሩ። በዚህችም አህጉር የእግዚአብሔርን ቃል የያዙት ቅዱሳት መጽሐፍት በተለያዩ ሀገራት ተተርጉሟል። ሆኖም የሁሉንም ሀገራት ትርጉም ለመመልከት ባንችልም ጥቂቶቹን ግን ከዚህ እንደሚከተሉት ተጠቅሰዋል።

- በቅብጥ (ኮፕት) ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ ከ 3 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ተተርጉሟል።
- ደቪድ ሊቪንግስተን በ 1857 ዓ/ም መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ደቡብ አፍሪካ (ጽዋና) ቋንቋ ተርጉሟል።
- ሳሙኤል ክሮውዘር በ 1859 ዎቹ አካባቢ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ናይጄሪያ ቋንቋ ተርጉሟል።
- ጆን ዊልያም ቆሌንሶ በ 1857 ዓ/ም መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ሩባ ቋንቋ (ዙሉ ቋንቋ) ተርጉሟል።
- ዮሐንስ በተባሉ ጳጳስ በ 8 ኛው ምዕት ዓመት መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ዐረብኛ ቋንቋ ተተረጎመ። ኋላ እንደገና ይስሐቅ በተባለ ሰው ዳግመኛ ተተርጉሟል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በኢትዮጵያ

ቅደስት ሀገር ኢትዮጵያ ታላቁ የታሪክ ምሁር እንግሊዛዊው ባጅ ‹‹ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን ሳታውቅ የኖረችበት አንድም የታሪክ ዘመን የለም›› በማለት እንደተናገረ በሕገ ልቡና ጸንታ ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልንም በመቀበል ከእስራኤል ቀጥላ አሚነ እግዚአብሔርን ታራምድ የነበረች መሆኗን መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክርላት ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ በዚህ እግዚአብሔር በሰጣት የሃይማኖት ታሪክ ውስጥ በየጊዜው የእግዚአብሔርን ቃል የያዙ ቅዱሳት መጽሐፍት ወደ ሀገራችን በመግባት ተተርጉመዋል።(1 ኛ ነገ 10÷1-12 ፣ የሐዋ 8÷26 መዝ 67÷31----) ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል።

- በ 980 ቅ/ል/ክ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ወደ ሀገራችን የመጡት ሌዋውያን ካህናተ ኦሪት የግእዝን ቋንቋ ጠንቅቀው ካጠኑ በኋላ እስከ ሰሎሞን ድረስ የተጻፉትን ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ግእዝ ቋንቋ ተርጉመዋል።
- በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (አቡነ ፍሬምናጦስ) በ 350 ዓ/ም እንደዚሁ በ 6 ኛው መ/ክ/ዘመን በዘጠኙ ቅዱሳን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ግእዝ ቋንቋ ተተርጉሟል።
  - ✓ <u>አሳይመንት፦</u> (ዘጠኙ ቅዱሳን እነማን ናቸው? የገደሙት ገዳም የመጡበትን ቦታ ያረፉበትን ቀን ጻፉ።ሦስቱ ታላላቅ ተአምር ያደረጉት ቅዱሳን እነማን ናቸው? ያደረጉትስ ተዓምር ምንድን ነው ጽፋችሁ አምጡ፣)
- አባ አብርሃም (አባ ሮሜ) የተባሉ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ከጎንደር ተነስተው ወደ ግብጽ በመሔድ የተለያዩ ቋንቋዎችን በማጥናት በ 1832 ዓ/ም ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አማርኛ ቋንቋ ተርጉመዋል።
- በአለቃ ተወልደ መድኅን ገብሩ በ 1948 ዓ/ም መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ትግርኛ ቋንቋ ተተርጉሟል።
- በአለቃ ዘነበ ከዚያም በኋላ በአናሲሞስ ነሲቡ በ 1899 ዓ/ም መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ ተተርጉሟል።በዚህ መልኩ ከ 30 በላይ በሀገራችን ቋንቋ እንደዚሁ ደግሞ Ÿ2300 በላይ ሀዓKT‹” ቋንቋዎች ለ 3000 ዓመታት የተተረጎመ ለአብዛኛው (98 በ 100) ለዓለማችን ህዝብ የተዳረሰ መጽሐፍ ነው። ሆኖም ግን ትርጉም ስንል በአንድ ዓይነት መንገድ ብቻ የተተረጎመ አድርገን ልንወስደው አይገባም። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ዓይነት መንገድ አልተተረጎመምና። እነዚህንም የትርጉም ዓይነቶች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደሚከተለው ከፍላ ታስተምረናለች፦

➢ <u>የትርጉም ዓይነቶች</u>

መጽሐፍ ቅዱስ አሁን ባለው መልክ በአንድ ላይ ተጠርዞ ከመቅረቡ በፊት እያንዳንዱ በየራሱ ተጽፎ ይገኝ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ በተለይ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፉ በመሆናቸው ቋንቋውን የማይችሉ ሰዎች አንብበው ለመረዳት እና ለመጠቀም ይቸገሩ ነበር። ከዚህ ችግር የተነሣና እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው አምላክነቱንና መሻቱን ለዓለም ኅብረተሰብ ሁሉ የተረዳ ይሆን ዘንድ ፈቃዱ በመሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት በተለያዩ መንገዶች ተተርጉመዋል። ይኸውም፦

ከቋንቋ ወደ ቋንቋ መተርጎም

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት ምን መምሠል እንዳለበት ለማሳየት ሰውን ከድካሙ አዝ ለእግዚአብሔር መንግሥት ለማብቃት ነው። ይህንንም አስመልክቶ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለምክርና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል›› (2 ኛ ጢሞ 3÷16-17) ሲል እንደገለጸው መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ የትርጓሜያት ስልት መተርጎምም ይህንኑ የሰውን ድካም ለማገዝ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት መተርጎም የጀመሩት በተለያዩ ዘመናት ሲሆን። ይኸውም ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ጀምሮ በዚህ መልኩ ከቋንቋ ወደ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ ሲተረጎም ነበር። ይኸውም ቃለ እግዚአብሔር ለመላው ዓለም ይዳረስ ዘንድ የአምላክ ፈቃድ ስለነበር ቅዱሳኑን እያስነሳ ያስተረጎመው የትርጉም ዓይነት <u>ከቋንቋ ወደ ቋንቋ መተርጎም</u> ተብሎ ይታወቃል።ይኸውም የትርጉም ዓይነት ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ በቀጥታ የሚተረጎም ነው።

ነጠላ ትርጉም

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*` „Ê¡e }ªlÊ

ነጠላ ትርጓሜ የሚባለው ዘይቤውን ወይንም ንባቡን ወስዶ ያለ ምንም ሐተታ የሚተረጎም የትርጓሜ ስልት ነው። በዚህ የትርጓሜ ስልት መሠረት የተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት በመጀመሪያ ከተጻፉበት ቋንቋ ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል። ነጠላ ትርጉም በዚህ ዓለም ላይ አንድ ዓይነት ንባብ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክቷል። ሆኖም ነጠላ ትርጉም ሲከናወን በአንዱ ቋንቋ ሲጻፍ ያልተቃናውን እንዲሁ ምስጢሩን ሳያብራራ ስለሚተረጉም ለአንዳንድ መናፍቃን ኑፋቄንና ቁንጽል ሐሳብ እንዲዘሩ መንገድ ይከፍታል። ይኸውም በሐዲስ ኪዳን የመጀመሪያው የነጠላ ትርጓሜ ትምህርት ቤት በ 3 ኛው መ/ክ/ዘመን የተከፈተው የአንጾኪያ ት/ቤት ነው። ከዚህ የነጠላ ትርጓሜ ት/ቤት በርካታ መናፍቃን ወጥተዋል። ሆኖም በዚህ ት/ቤት መናፍቃን እንዲወጡ ያደረገው ከላይ እንደጠቀስነው ምስጢር ስለማያብራራ ነጠላውን ብቻ ሲለሚያስረዳ ነው። የሆነው ይሁንና ነጠላ ትርጉም የምንለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ሐሳብ ዘይቤውን በመውሰድ ያለምንም ሐተታ (ትንታኔ) የሚተረጉም የትርጉም ስልት ነው።

ምሳሌያዊ ትርጉም

ይህ የትርጉም ዓይነት በምሳሌያዊ አነጋገር የተነገሩትን ቃላቶች ለመተርጎም የምንጠቀምበት የትርጉም ዓይነት ሲሆን ይኸውም የበለጠ ነገሩን የሚያስረዳና ግልጽ በሆነ መንገድ ለማስረዳት በተለያዩ ነገሮች በመመሰል የምንረዳበት የትርጉም ዓይነት ነው። ጠቢቡ ሰሎሞን ስለ እመቤታችን ሲናገር ‹‹እኅቴ መሸራ የተቆለፈ ገነት የተዘጋ ምንጭ የታተመ ፈሳሽ ናት›› መኃ 4÷12 በማለት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ዘላለማዊ ድንግልና በሚገባ ያስረዳናል። እንደዚሁ ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ በትንቢት መጽሐፉ ላይ ‹‹ለመታረድ እንደሚነተት ጠቦት›› ት/ኢሳ 53÷7 በማለት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በበግ መስሎ ተናግሯል። ለዚህም ቅዱስ ዮሐንስ ‹‹እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ›› በማለት ቀድሞ በነቢዩ የተነገረውን ምሥጢር በሐዲስ ኪዳን ገልጦ ተናግሯል። ዮሐ 1÷29 አርድእቱ የወንጌል ጸሐፊ ቅዱስ ማርቆስ በወንጌሉ ላይ ስለጌታ በምሳሌ ማስተማር ሲናገር ‹‹መስማትም የሚችሉበት መጠን እነዚህን የሚመስል በብዙ ምሳሌ ቃሉን ይነግራቸው ነበር። ያለ ምሳሌ ግን አልነገራቸውም›› ማር 4÷34 በማለት እንደተናገረ እንዲሁ እስራኤላውያን በወይን ቦታ እንደተመሰሉ ኢሳ 5÷1-2 ማቴ 21 የጌታችን በዓለት መመሠል ት/ዳን 2÷34 የጻድቃን በበግ የኃጥአን በፍየል መመሰል ማቴ 27÷33-41 የጴጥሮስ በዓለት መመሰል ማቴ 16 ----- ወዘተ መጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌ የሚናገራቸውን ነገር መዘርዘር ይቻላል። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ‹‹እከሰት አፍየ በምሳሌ - አፈን በምሳሌ እከፍታለሁ›› በማለት ጌታ በምሳሌ ማስተማሩን ተናግሯል መዝ 77÷2። ሆኖም እነዚህን መሰል የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የምንተረጉምበት የትርጉም ዓይነት ምሳሌያዊ የትርጉም ዓይነት ይባላል።

ምስጢራዊ ትርጉም

ይህ ዓይነት የትርጓሜ ስልት ጥሬ ዘሩን ወይንም ንባቡን ሳይከተል አገባቡን ሳይጠብቅ ምሥጢሩን ብቻ ጠብቆ የሚተረጉም ነው። ይኸውም የመጽሐፉን ጭብጥ (መልእክት) ለመረዳት ያስችላል። ይህንንም ቃለ እግዚአብሔር በምስጢር መናገር በምስጢር መተርጎም ከእግዘዚአብሔር የሚሰጥ ሀብት ነው። ይህንንም ቅዱስ ሉቃስ ሲያስረዳ ‹‹መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው›› (ሉቃ 24÷ 45) እንዳለው። በንባብ የተሸፈነውን ምሥጢር በትርጓሜ ፈልቅቆ ማውጣት ካልተቻለ የተገለጠው ነገረ እግዚአብሔር የተሸፈነና የተከደነ ይሆናል። ለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ተሰውሮ የነበረውን የእግዚአብሔር ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን›› (1 ኛ ቆሮ 2÷7) በማለት በብሉይ ኪዳን በቅዱሳን ነብያት የተነገረው በመጻሕፍት የጻፈውን በዘመኑ ለነበሩ ሁሉ የተሸሸገ ምሥጢር ሆኖ መቆየቱንና በእነርሱ በኩል ግን መገለጡን ያስረዳል። ሆኖም ግን ይህ የትርጉም ዓይነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈ የተሰወሩትን ምሥጢር በመግለጥ የሚተረጉም የትርጉም ዓይነት ነው። ለምሳሌ፦

“አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ” ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ምስጢር አዘል የሆነ ነው። ብዙዎች በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ተሰናካክለዋል ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስን በነጠላ ብቻ ስለሚረዱት። ነገር ግን የዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምሥጢራዊ የሆነ በመሆኑ ምሥጢሩን በመፍታት ልንረዳ ይገባናል። ይኸውም ቃል ተናጋሪው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ይህንን ቃል የተናገረው በመጀመሪያ ለአቅረቦተ ሰይጣን ሲሆን እንዲሁ በልበ አምላክ በቅዱስ ዳዊት የተተነበየውን ትንቢት ፍጻሜ ለመስጠት እና ለአብነት ነው። ....ወዘተ እንደዚህ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍላት በዚህ መልኩ የሚተረጎሙበት የትርጉም ዓይነት ምሥጢራዊ ትርጉም ይባላል።

➢ <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ዝግጅት</u>

በተለያየ ቦታና ዘመን በቅዱሳን ሰዎች የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ አሁን በምናገኘው መልኩ ለማለቅ እና ዝግጅት ላይ ለመድረስ የዘመናት ሒደቶችን አሳልፋ EM:: በእነዚህን የዘመናት ሒደቶች መሐል አልፎም በሦስት ዓይነት መንገድ አሁን የምናገኘው መልኩ ዝግጅት ላይ ደርሷል። ይኸውም በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል።


✓ **<u>Tcvcw</u>** :- pÆdƒ SêNõƒ” Ácvcu¨< Ó²=›wN?` S”ðe pÆe ’¨<:: **#u Ó²=›wN?` SêNõ ðMÑ< ›”wu<U ›ô” ›µ—M“ S”ðc<U cwevE†ªM Ÿ’²=I ›”Ç=ƒ ›ƒÖóU$/ ƒ/›=d #5-÷26//** ”ÇK¨< ’w¿ ›=dÃÁe::Ç=G< ’wÃ“ ካl” °´^:- TZ^©Á” :cw¯K=n“ƒ Kƒ`Ñ<U pÆdƒ SéQõƒ” ›cveuªM::**KUdK?:-** ¾e¡”É`Á¨< ¢È¡e **u822 ¯/U** ¾w^“ pÖM S<K< wK<Ã Ÿ=Ç”“ NÇ=e Ÿ=Ç”” (¾kKT@”Ùe” SêNõ ÚUa) Ácvcu ’¨<::

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*`„Ê¡e }ªIÊ

✓ T²ÒËƒ

wK<Áƒ ¾}éñuƒ” ¾°w^ÃeØ ›“vu= □“ ¾ ቋንቋ ምልክቶችን በመስመር ለንባብና ለትርጉም ያመቻቹት ማሦራውያን ሲሆኑ፡- ይኸውም

- መጽሐፍ ቅዱስን በክፍል ከፋፍለው ያዘጋጁልን አምንዮስ እና አውሳብዮስ ናቸው።
- መጽሐፍ ቅዱስን በምዕራፍ የተከፈለው በ 12/28 ዓ/ም በእንግሊዝ ሀገር በስቴቨን ላንግቶን ነው።
- መጽሐፍ ቅዱስን በቁጥር የተከፈለው በ 15/52 ዓ/ም በፈረንሳይ ሀገር በሮበርት እስቲን (እስቲፋነስ) ነው።
- በ 16 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ሀዳግ ተዘጋጅቶ E ል፡



የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስያሜ

1 = ርዕስ

2 = ሀላፍ

3 = አምድ

4 = ሀዳግ

✓ አሰያየም

ለመጽሐፍ ቅዱስ ስያሜ የሰጡት ራሳቸው ጸሐፊያኑ ሲሆኑ አንዳንደቹ ግን በቅዱሳኑ እና በይዘታቸው ስም ሰጥተውታል።ለምሳሌ፡-

1. በጸሐፊው ስም የተጠሩ መጻሕፍት፡-
   እነዚህ መጻሕፍት መጽሐፉን በጻፈው ቅዱስ ስም የተጠሩ መጻሕፍት ሲሆኑ ምንም በጸሐፊው ስም የተጠሩ ቢሆኑም ቁጥራቸው ግን ከቅዱሳት መጽሐፍት ነው። ለምሳሌ፡-

   ✓ መጽሐፈ ኢያሱ □መጽሐፈ ሐኖክ □መጽሐፈ ሳሙኤል ----- ወዘተ

2. በይዘታቸው ስም የተሰጣቸው መጻሕፍት
   በይዘታቸው ስያሜ የተሰጣቸው መጻሕፍት የምንላቸው በውስጥ ከያዙት ሐሳብ በመነሳት ስያሜ የተሰጣቸው መጻሕፍት ሲሆኑ ምንም እንኳ በይዘታቸው ስያሜ ቢሰጣቸውም ቁጥራቸው ግን ከቅዱሳት መጻሕፍት ነው። ለምሳሌ፡-
   ✓ መጽሐፈ ኩፋሌ ✓መጽሐፈ ነገሥታት
   ✓ መጽሐፈ ኢዮብ ✓ኦሪት ዘፍጥረት.....ወዘተ
3. በጸሐፊውና በይዘታው የሚጠሩ መጻሕፍት
   እነዚህ መጻሕፍት ደግሞ መጻፉን በጻፈው ቅዱስ ስም እና መጻፉ ከያዘው ሐሳብ ስያሜ ያገኙ መጻሕፍት ሲሆኑ ምንም እንኳ በጸሐፊውም በይዘታውም ስያሜ ቢሰጣቸው ቁጥራቸው ግን ከቅዱሳት መጻሕፍት ነው። ለምሳሌ፡-
   ✓ መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን ✓ ትንቢተ ኢሳይያስ
   ✓ የማቴዎስ ወንጌል ✓ መዝሙረ ዳዊት
   ✓ ራእይ ዮሐንስ ✓ የጴጥሮስ መልዕክት ------ ወዘተ
4. በከተማ ስም የተጠሩ መጻሕፍት
   በከተማ ስም የተጠሩ መጻሕፍት የምንላቸው በቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ውስጥ የሚከኙ መጻሕፍት ሲሆኑ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በማኅበር መልእክቱን ሲልክ የተላከላቸው ሰዎች በሚገኙበት ከተማ ስም ስያሜውን አግኝቷል።ሆኖም ግን በዚህ መልኩ ስያሜን ቢያገኙም ቁጥራቸው ግን ከቅዱሳት መጻሕፍት ወገን ነው። ለምሳሌ፡-
   ✓ ወደ ሮሜ □ወደ ኤፌሶን ✓ወደ ዕብራውያን --- ወዘተ
5. በተላከላቸው ሰዎች ስም የተጠሩ መጻሕፍት
   እነዚህ መጻሕፍት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በላከላቸው በመንፈስ ልጆቹ ስም ስያሜን ያገኙ መጻሕት ሲሆኑ ምንም በተላከላቸው ስም ስያሜን ቢያገኙም ቁጥራቸው ግን ከቅዱሳት መጻሕፍት ነው ።ለምሳሌ፡-

✓ 1ኛ እና 2ኛ ጢሞቴዎስ ✓ ወደ ፊሊሞና ✓ ወደ ቲቶ

➢ <u>መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ገባ</u>?

ኢትዮጵያ አገራችን የረጅም ዕድሜ ባለፀጋ መሆኗ በሕጻን በአዋቂው ዘንድ የታመነ ነው። ሆኖም አገሪቱን የዚህ ዕድሜዋን ግማሽና ከዚያ በላይ የሚሆነውን ዘመን የክርስትና ሃይማኖትና የመንግሥት አስተዳደር እጅና ጓንት ሆነው ሲያስተዳድሯት ቆይተዋል። በጥምር አስተዳደር ሥር በምትመራበት ዘመንም ከፍተኛ የሥልጣኔ ማማ ላይ ደርሳ ነበር። ሆኖም ኢትዮጵያ ጥንትም ሆነ ዛሬ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች እናት መሆኗ እሙን ነው።እነዚህም ልጆቿ የራሳቸው የሆነ የአመጋገብ የአለባበስ የአኗኗር ባሕል አላቸው በቋንቋ እና በሃይማትም እንደዚሁ። ምንም በአኗኗርና በባሕል ቢለያዩም ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው አንድ ናቸው። እንደዚሁ ቅደስት አገር ኢትዮጵያ በሥርዓተ አምልኮዋም ከጥንት ጀምራ በአሚነ እግዚአብሔር የጸናች አገር ናት። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ‹‹ኢትዮጵያ ታበዕሕ እዳዊሐ ኀበ እግዚአብሔር›› በማለት እንደ ገለጸው ኢትዮጵያውያን እደ ሥጋቸውን ለምጽዋት እደ ልቡናቸውን ለጸሎት የሚዘረጉ መሆናቸውን አስረድቷ። እንደዚሁ የታሪክ ተመራማሪ የሆነው እንግሊዛዊው ባጅም ‹‹ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን ሳታመልክ የኖረችበት አንድም የታሪክ ዘመን የለም›› በማለት ርቱዕ ስለሆነው አምልኮቷ እና በሥስቱም ሕግጋት የጸናች ሀገር ስለመሆኗ አስረድቷል። ስለሆነም ወደዚህች ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልን በመቀበል ታሪካዊትና ጥንታዊት ሀገር ወደ ሆነችው ኢትዮጵያም የእግዚአብሔርን ቃል እና ሕግጋት የያዙ ቅዱሳት መጻሕፍት በተለያዩ ዘመናት ገብተዋል።ይኸውም፡-

<u>የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ገቡ</u>?

- ከሔኖክ መጽሐፍ ጀምሮ እስከ ሰሎሞን መጽሐፍ ድረስ ያሉት መጻሕፍት በሰለሞን ልጅ በምኒልክ ዘመን እንደገቡ ይታመናል።
- እስራኤላውያን በምርኮ በመያዛቸው በዓለማችን ከፍላት ተበታትነው ነበር። በዚህም በተለምዶ ‹‹ፈላሻ›› ብለን የምንጠራቸው አይሁዳዊያን ወደ ሀገራችን ፈልሰው ገብተው ነበር። በዚህ አማካኝነት ብዙ ቅድሳት መጽሐፍትን ወደ ሀገራቸው ይዘው ገብተዋል።
- እንደዚሁ ነገሥታት ከነገሥታት ደብዳቤ በመጻጻፍ ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ሀገራችን ገብተዋል። ለምሳሌ፡-ኢትዮጵያዊው ዜራህ (ዙሪያ) እና የይሁዳው ዘሩባቤል ተጻጽፈው ከምርኮ በኃላ ቅዱሳት መጽሐፍት እንደተለዋወጡ መጽሐፍተ ሲራክወ ሰሎሞን መግቢያው ያስረዳል
- ለንግድ እና ለመሳለም ወደ ኢየሩሳሌም በሄዱ ኢትዮጵያውያን አበው አማካኝነት ።ለምሳሌ፡- ምኒልክ ፡ጃንደረባው ባኮስ-----)

<u>የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ገቡ</u>?

- በመጀመሪያው የኢትዮጵያው ጳጳስ አባ ሰላማ (በአቡነ ፍሬ መናጦስ) ዘመን በ 330 ዓ/ም በእስክንድርያው ፓትርያርክ አአቡነ አትናቴዎስ እጅ ተሸሞ ጃንደረባው በመሰረተው ላይ ክርስትናን በማጠናከሩ በተጨማሪ ቅዱሳት መጽሐፍትን ከሱርስት ከዕብራይስጥና ከጽርዕ ቋንቋ ወደ ግእዝ ቋንቋ መልሰዋል።
- በ 490 ዓ/ም ዘጠኙ ቅዱሳን በቤዛንታይን ንጉሥ ስቃይ በበዛባቸው ጊዜ ወደ ሀገራችን ፈልሰው በመጡ ጊዜ ብሉያትንም ሐዲሳትንም እንዲሁ ሰብአ ሊቃናት የተረጎሙትን መጻሕፍት ይዘው መጥተዋል። በዚህ በሀገራችን የግእዝ ቋንቋን ጠንቅቀው ተምረው ወደ ግእዝ ተርጉመዋል።
- በ 14ኛው መ/ክ/ዘመን በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት እንደ ሃይማኖተ አበው ፍትሐ ነገሥት ያሉ መጻሕፍት ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል።

ስለሆነም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ቅዱሳት መጻሕፍትና ትርጉም አስተምራለሁ ማለት ‹‹ለቀባሪው አረዱት›› እንደሚባለው ይሆናል።ሆኖም እንዲህ አድርጋ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሥር ከሥር የተቀበለችው በመሆኗ ለሁለቱ ኪዳናት ብቸኛ ባለቤት የሆነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ ለሰማንያ አሐዱ ቅዱሳት መጽሐፍትም ብቸኛ ባለቤት ናት።

ምዕራፍ ሦስት
የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና አዋልድ መጻሕፍት እና ትውፊት

የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና

ቀኖና፡- ማለት ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙም ቀጥተኛ መንገድ ትክክለኛ መስነር መቃ ሸንበቆ መለኪያ መስፈሪያ ማለት ነው። ቀኖና የሚለው ቃል በጥንት ዘመን የታሪክ ሰዎች ጥሩ ቁመና ላለው ሰው ቀጥ ላለ ነገር ይጠቀሙበት ነበር የቡ ክርስቲያን ቀኖና ሲባልም የቤተ ክርስቲያን ሐግ ቀጥተኛ እምነት (dokterin) ለማለት ነው። የኒቂያው ውሳኔ ቀኖና ይባላል።የማይለወጥ መሠረተ ሃይማኖት ዶግማ ከተባለ መጽሐፍ ቅዱስም በቁጥር በተራው በጠቅላው ይዘቱ የተወሰነ የጠለካ የተቃናል ነውና ቀኖና ይባላል ይህም ሰያሜ ለመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ገደማ እንደሆነ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያስረዳሉ።

የቀኖና ዓይነቶች

ቀኖና የሚለው ቃል በአንድ ዓይነት መንገድ ብቻ የሚተረጎም አይደለም እንደየ ትምህርት ዓይነቱ እና እንደ አጠቃቀሙ የተለያየ ነው። ሆኖም ግን ሁሉንም ቀኖና ብለን በአንድ መጠሪያ እንጠራቸዋለን ይህም የቀኖና ዓይነቶቹ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

- ✓ ቀኖና፡- ለትምህርተ ሃይማኖት ሲሆን ከእምነት መመሪያ ውስጥ አንዱ ነው። ይኸውም በትምህርተ ሃይማት ውስጥ የሚሰጠን ትርጉም የጉባኤ (ሲኖዶስ) ውሳኔን ነው። አባቶቻችን ለቤተ ክርስቲያን ይጠቅማል ይበጃል የሚሉትን እየደነገጉ የሚወስኑት ነገር ቀኖና ተብሎ ይጠራልና።
- ✓ ቀኖና፡- ለነገረ ቅዱሳን ሲሆን ደግሞ ቅጣትን ወይንም የንስሐን ጊዜን የሚያመለክት ነው። ይኸውም ከመምህረ ንስሐችን ጋር ኑዛዜያችንን ከጨረስን በኋላ የሚሰጠን ቅጣት ቀኖና ተብሎ ይጠራል።
- ✓ ቀኖና፡- ሌላው ለመጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን ደግሞ ቀኖና ማለት ቁጥርን ያመለክትልናል። ይኸውም ከ 4 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደ ቅዱስ አትናቴዎስ ያሉ ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስን ወስነው ቀንነው ለክተው በቀኖና አስቀምጠውልናል። ይህም ተግባር ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት ተብሎ ያጠራል።

ከዚህ በመነሳት ቀኖና የሚለውን ቃል በአንድ ዓይነት መንገድ ሳይሆን እንዲህ ባለ መልኩ በትምህቶቹ ውስጥ ያለውን የትርጉም ልዩነት ተረድተን እንደየ አገባቡ (እንደየ ትምህርቱ) ያለውን ትርጉም አውቀን በዚህ መልኩ ልንረዳ ያስፈልጋል።

ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት የምንላቸው

ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖትን ለመግለጥና ለማስተማር በጉባኤ የምታነባቸው የምትተረጉማቸው ለሃይማኖት ጉዳይ መነሻና መድረሻ አድርጋ ለሚጠይቋት ሁሉ ርትዕት መልስ የምትሰጥባቸው መጽሐፍት ናቸው።

ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት ለምን አስፈለገ?

1. <u>ለመለየት</u>፡- ይኸውም እውነተኞቹን መጽሐፍት ከሐሰተኞች (ርኩሳት) ምንፍቅናን ከሚያስተምሩ መጽሐፍት ለይቶ ለማስቀመጥ
2. በቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት መነበብ የሚገባቸውን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ። ይኸውም ቅድስት ቤተ ክርዘስቲያን ሥርዓተ አምልኮዋን በምትፈጽምበት ጊዜ የሚነበቡ መጻሕፍት በቀኖና መጻሕፍት የተቀሰነ ነው። ይህም ለምሳሌ በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ የሚነበቡ መጻሕፍት በቀኖና የተወሰነ በመሆኑ ሁልግዜ የሚነበቡት መጻሕፍት ተለይተው ይታወቃሉ። ይኸውም፡-
   - ➢ ሠራዔ ዲያቆን ሆኖ የሚቀድሰው ሁል ጊዜ ከ 14 ቱ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ውስጥ አንዱን ያነባል። ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ውጪ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አያነብም።
   - ➢ ንፍቅ ዲያቆን ሆኖ የሚቀድሰው ዲያቆን ደግሞ ምንጊዜም ከጳውሎስ መልእክት ውጪ ካሉት ከተቀሩት 7 መልእክታት እና ከራእይ ዮሐንስ አንዱን ያነባል። ከእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውጪ ሌላ አያነብም።
   - ➢ ንፍቅ ካህን ሆነው የሚቀድሱት አባት ደግሞ የሚያነቡት ምንጊዜም ቢሆን የሐዋርያት ሥራን ነው ከዚህ መጽሐፍ ውጪ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አያነቡም።
   - ➢ ሠራዔ ካህን ሆነው የሚቀድሱት ካህን ደግሞ ምንጊዜም የሚያነቡት ከወንጌል ክፍል አንዱን ነው። ከወንጌል ክፍል ውጪ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አያነቡም።
   - ➢ ሠራዔ ዲያቆኑ ከመልእክት ውጪ በምስባክ ጊዜ የሚሰብከው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምን ጊዜም ቢሆን የቅዱስ ዳዊትን የመዝሙር መጽሐፍ ነው። እነዚህ በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ እንዲነበቡ የተቀነኑት ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው።

የቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅም

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*` „Ê¡e }ªIÊ

1. ለጥበቃ፡- ቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ቅዱስን ወስና፣ ሰፍራ ለክታ ባታስቀምጥ ኖሮ በየዘመኑ እንደተነሱት መናፍቃን ብዛት መጽሐፍቱም ልዩ ልዩ በሆኑ የኑፋቄ ትምህርት በተነሰነሱ ነበር። ይህ እንዳይሆንና መጽሐፍ ቅዱስን ከእንዲህ ዓይነት ደባ ለመጠበቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና የግድ ያስፈልጋል።
2. ለውርስ፡- ለሌሎች ትውልድ ለማውረስ ይህ ሲባል በየዘመኑ የተነሱት አለውያን ነገሥታት ተቀዳሚ አላማቸው ቅዱሳት መጽሐፍትን ማቃጠል ማጥፋት መበረዝ መቀነጻጸል ነበርና አባቶች በቀኖና ሰፍረው ለክተው ወስነው በዋሻ በግበበ ምድር በልጆቿ ልቡና ውስጥ በማቆየት ከትውል ወደ ትውልድ ሊተላለፍ ችሏል።
3. ለማረጋገጫ፡- በኑፋቄ ትምህርት የተሞሉ መጽሐፍት ነበሩ። አረማዊያን መጽሐፍትን ÷ማቃጠል ማጥፋት አልሆን ሲላቸው መቀነጻጸል መበረዝ ጀምረው ነበርና ይህን የኑፋቄ የክህደት ትምህርት ከአውነተኛ የእምነት የሥርዓተ አምልኮ ትምህርት በመለየት እውነተኞቹን በማውጣት ያረጋገጠች ቤተ ክርስቲያን ናት።ይኸውም በቀኖና መጻሕፍት አማካይነት ነው።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና (ቁጥር)</u>

ቅዱሳት መጻሕፍትን መሰብሰብ የተጀመረው መጽሐፉ ከተጻፈበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ሆኖም ግን ብዛታቸውንና ዓይነታቸውን ለይቶ ለማወቅ ሲባል በተለይ በሐዲስ ኪዳን ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። ይህም ሥራ የተጀመረው በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን በሐዋርያት ነው። ቅዱሳን ሐዋርያት አጠቃላይ ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን 85 ቀኖናትን ደንግገዋል። ከእነዚህም ውስጥ 85 ኛው ድንጋጌ ወይንም ቀኖና ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚናገር ነው። ከዚያም በኋላ በሎዶቅያ በተካሄደው ጉባኤ በ 393 እና 399 እንዲሁም በ 419 ዓ/ም (እ/ኤ/አ) በሰሜን አፍሪካ ትገኝ በነበረችው ቅርጣግና /ካርቴጅ/ በተካሄዱት ጉባኤዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ለይቶ ለማወቅ ጥረት ተደርጓል። ከዚህም ሌላ በ 325 ዓ/ም እ/ኤ/አ በኒቂያ በተካሄደው ጉባኤ ላይ እውነተኞቹን ቅዱሳት መጻሕፍት ለመሰብሰብ በተወሰነው መሠረት ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ በ 367 ዓ/ም በ 39 ኛው የትንሣኤ መልእክቱ ላይ ቅዱሳት መጻሕፍት ቁርና ዓይነት አስታውቋል። በተለይ በሐዋርያት ከተደነገጉት 85 ቀኖና መካከል 85 ኛው ቀኖና ይህንን ያረጋግጥልናል። ምክንያቱም 81 ቅዱሳት መጻሕፍት እንዳሉ የሚያስረዳ በፍትሐ ነገሥት በአንቀጽ ሁለት ላይ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ተወስኖ የሚገኝ ድንጋጌ ከዚያም ሲወርድ የመጣ ነው። እነዚህን ሁሉ ሰማንያ አንድ መጻሕፍት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አክብራና ጠብቃ ለአሁኑ ትውልድ አድርሳለች። እንዲሁም የላቲን (ሮም) ቤተ ክርስቲያን 73 መጻሕፍት በቀኖና ሲቀበሉ ግሪካውያን ደግሞ 76 ቅዱሳት መጻሕፍትን ይቀበላሉ። እነዚህንም ግሪካውያን መጽሐፈ ጦቢት ፡ መጽሐገፈ ጥበብን ፡ መጽሐፈ ዮዲትን ፡ ሦስቱ መጻሕፍተ መቃብያንን ፡ መጽሐፈ ባሮክን እና ሲራክን ይቀበላሉ። ይህንንም በ 1950 ዓ/ም በጻፋት መጽሐፍ ቅዱስ አካትተዋቸው ይገኛል። አንዲሁም አይሁዳውያን ከዘጠኙ ውጭ ያሉትን አፖክሪፋ (ዲዩትሮካኖኒካል) ብለዋቸዋል። ይኸውም የተሰወሩ (ጎቡዕ) ተጨማሪ ማለት ነው። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የሚያነቡት የተለየ ክርስቲያዊ ጽሑፍ ስላልነበረ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክኛ ተተርጉሞ ስላገኙት እና በጽሑፍ ውሎ የተገኘ ስለነበር ብሉይ ኪዳንን ይጠቀሙበት ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማረ እንጂ አልጻፈም ሐዋርያትም በቃል ብቻ ተማሩ ስለዚህ ሐዲስ ኪዳን ለጽሑፍ አገልግሎት ላይ የዋለው ከ 50 ዓ/ም (ከሐዋርያት ሲኖዶስ) በኋላ ነው። በዚህ ወቅት ብዙዎች በእውነተኛዋ የቤተ ክርስቲያን አስተምሮ ላይ ስህተት ሲቀላቅሉ እና በሐዋርያት ስም በመጻፍ ማጭበርበር ጀመሩ። ቤተ ክርስቲያን ይህንን ችግር ለመፍታት በጊዜው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በቀኖና ለክታ ሰፍራ መዝና ተቀበለች። ወቅቱም እጅግ አስቸጋሪ በሆነበት ዘመን ለጊዜው የመጽሐፍቱን ቁጥር 27 መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ የጠቀሰው የእስክንድርያው ትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ ሲሆን በ 367 ዓ/ም በቅርጣግና (ካርቴጅ) በተደረገው ሲኖዶስ 27 ቱን መጻሕፍት አጸደቀ።ከዚህ ከ 27 ቱ ቅዱሳት መጻሕፍት በተጨማሪ የኢትዮያያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለምግባር የሚረዱ 8 ቱን የሥርዓት መጻሕፍት በሲኖዶስ ወስና ተቀበለች መጻሕፍቱም ጌታችን መድኃኒታችን ከትንሳኤው ጀምሮ እስከ ዕርገቱ ድረስ የሠራውን የሃይማኖትና የሥርዓት ትምህርት የያዙ በሐዋርያት የተጻፉ ናቸው። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቁጥር 35 የብሉይ ኪዳን ደግሞ 46 በጠቅላላው 81 መጻሕፍት እንቀበላለን።

የቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት ምንጮች

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖናን በተመለከተ ሁለት ዋና ዋና (ዐበይት) ምንጮች ይቀርባሉ። እነዚህንም ከዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከታለን፡-

❶ <u>ፍትሐ ነገሥት፡-</u> ለፍትሐ ነገሥት አቀናባሪና ጸሐፊ ለአቡነ ዘልዘንል በምንጭነት ያገለገሉት አራት ቀኖናተ ሐዋርያት እንደሆኑ በመቅድሙ ላይ ተጠቅሰው ይገኛሉ።

❷ <u>የአበው ሲኖዶስ (ጉባኤ) መደብለ ቀኖናት፡-</u> በቀኖናቱ ምንጮች በሲኖዶስ (ጉባኤ) መድብል የመጽሐፍት ዝርዝር ቁጥር በቅድስት ቤተ ክርስቲያን መቀበላቸው የታዘዙ መጻሕፍት ቁጥራቸው 81 እንደሆነ በአንቀጽ ሁለት ላይ ይነግረናል።

<u>በአቆጣጠር ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች እና ርትዕት መልስ</u>

81 ዱን ቅዱሳት መጽሐፍት በመቀበላችን የተሳሳትን አድርጎ የሚቆጥሩ ብዙ የእምነት ድርጅቶች አሉ። እኛ ግን 81 ዱን ቅዱሳት መጻሕፍት በመቀበላችን አለመሳሳታችንን ታላቁ መጽሐፋችን ሲመሰክር እንዲህ ይላል።

 በማቴ **27÷6** ላይ በተረፈ ኤርምያስ ም **7÷3** ላይ ያለውን (ይሁዳ ጌታን በ **30** ብር መሸጡ የሸጠበትንም ብር በአይሁዶች ቤተ መዛግብት መበተኑን አይሁዶችም ያንን ብር ከእኛ ገንዘብ ጋር መቀላቀል የለብንም ብለው ለሸክላ ሰሪ እንደሰጡት) አስቀድሞ ኤርምያስ

ተናገረ ብሎ ሐዋሪያው ቅዱስ ማቴዎስ ገልጾ ጽፏል። አሁን በ 66 ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተረፈ ኤርምያስ የለም። ታዲያ ሐዋሪያው ማቴዎስ ከጌታ እግር ሥር ተቀምጦ ከዋለበት እየዋለ ካደረበት እያደረ የተማረ ምስጥር ያደላደለ ሐዋርያ ነው። እርሱም በ 81 መጽሐፍት ውስጥ ያለውን ተረፈ ኤርምያስን መጥቀሱ አለመሳሳታችንን ይገልፅልናል።

 ይሁ ቁጥር. **14** ላይ በመጽሐፈ ሔኖክ **1÷9** ላይ ያለውን ገልጾ ይሁዳ በመልዕክቱ አስቀምጦልናል። ይሁንና መጽሐፈ ሔኖክ በ 66 ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም ይህ የሔኖክ መጽሐፍ ያለው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በምንቀበለው በ 81 ዱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ነው ያለው። ሆኖም ሐዋርያት ሁሉ ከዚህ ከ 81 ዱ መጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሱ ማስተማራቸው የ 81 ዱን መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት ያስረዳና። ለዚህ 81 ዱን መጽሐፍ ቅዱስ በመቀበላችን አልተሳሳንም።

<u>አዋልድ መጻሕፍት</u>

- <u>አዋልድ መጻሕፍት</u>፦ ጥሬ ትርጉሙ የመጻሕፍት ልጆች ማለት ነው። አዋልድ መጻሕፍት የምንላቸው አሥራውን መጽሐፍ ምስጢሩን አርቅቀው ትርጓሜውን አቅንተው አስፍተው አምልተው አመስጥረው የሚተረጐሙ የሚተነትኑ መጻሕፍት ናቸው። እንዲሁ በነቢብ የተገለጠውን በገቢር በትምህርት የተሰጠውን በሰው ሕያወት የሚያሳዩ መጻሕፍት አዋልድ መጻሕፍት ይባላሉ። አዋልድ መጻሕፍት ልጅነታቸው ለአሥራው መጻሕፍት ብቻ ነው። ልጅ ከእናቱ ማኅጸን ከአባቱ አብራክ ወላጆቹን መስሎ እንደሚወለድ ሁሉ እነዚህ አዋልድ መጻሕፍትም ምስጢሩን ቢያራቅቁም ትርጓሜውን ቢያቃኑም ከአሥራው መጽሐፍ ውጪ አይደሉም። በእምነትና በሥርዓትም አስራውን የሚመስሉ መጻሕፍት ናቸው። በመሆኑም በምሥጢር በትምህርትም ከአሥራው መጻሕፍት የሚቃረን መጽሐፍ ከአዋልድ መጻሕፍት አይመደብም አይቀጠርም ምክንያቱም በሐዋርያው ቃል ‹‹ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብኩላችሁ የተረገመ ይሁን።›› (ገላ 1÷8) የአሥራው መጻሕፍት መገለጫ መብራት የሆኑትም አዋልድ መጻሕፍት ናቸው። በገመድ ያለ ኤሌክትሪክ ኃይል የሚፈካው የሚታየው በአምፖል ሲበራ እንደሆነ ሁሉም በአሥራው መጻሕፍት የሚገኝ ጥበብ ትምህርትና ምሥጢር የሚረዳው የሚገልጠው በአዋልድ መጻሕፍት ተብራርቶ ሲታይ ነው።

❖ <u>የአዋልድ መጻሕፍት ባህርያት</u>

- አሥራው /81 ዱን/ መጽሐፍ ቅዱስ መተርጎም /መተንተን/ ማብራራት።
- የአሥራው /81 ዱን/ መጽሐፍት ትርጓሜውን አቅንተው ምሥጢሩን አርቅቀው ማቅረብ።
- በትምህርት የተሰጠውን በሰው ሕይወት /በተግባር/ማሳየት።
- በእምነትም በሥርዓትም የአሥራውን መጽሐፍትን ሥርና መሠረት ይዞ መገኘት።
- የአሥራው /81 ዱን/ መጽሐፍ ምስጢሩን /ኅቡዕ የሆነውን ነገር/ መግለጥ።

❖ <u>የአዋልድ መጻሕፍት ዓላማ</u>

- የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራውን መግለጥ።
- ለሰው ኅሊና የሚከብዱ በእምነት ብቻ የምንረዳቸውን ድርጊቶች መግለጥ።
- የእምነትን ታላቅነት መግለጥ።
- በእግዚአብሔር ያመኑ የቅዱሳን አባቶቻችንን ተጋድሎ መግለጥ።
- ትምህርተ ሃይማኖትን ማስተማር።
- በሀይማኖታቸው የፀኑትን የቅዱሳን አበቶቻችንን ዋጋ መግለጥ።
- ሰውን ወደ በጎ ዘላለማዊ ድኅነት መምራት.....ወዘተ.... ናቸው።

❖ <u>አዋልድ መጻሕፍትን ስናነብ ልናስተውላቸው የሚገቡ ነጥቦች</u>

- በብሉያት በሐዲሳት የተገለጡትን መሠረታዊ የሆኑ የሃይማኖትና የሥነ ምግባራን ትምህርት ጠንቅቆ መማር
- የእግዚአብሔርን ከሃሊነት፣ ቸርነት ያለምንም ጥርጥር ማመን
- ለቅዱሳን ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ክብርና ሥልጣን መረዳት
- ከስጋዊ ፍልስፍና ጋር ቀላቅሎ ለመረዳት አለመሞከር
- መጽሐፉ በተጻፈበት ዘመን የነበሩትን ሁኔታዎች ማገናዘብ
- ከእውቀት ከኅሊና በላይ የሆኑ ነገሮችን በእምነት እንደሚሠሩ ማመን.....ዋና ዋና ተጠቃሾች ናቸው።
- ከመጻሕፍት ውስጥ ያልገቡንን ነጥቦች ሊያስረዱን ከሚችሉ ሊቃውንተተ ቤተ ክርስቲያንን ጠይቆ መረዳት
- ከማንበብ በፊት ለመረዳት እንድንእል እግዚአብሔር ምሥጢሩን እንዲገልጥልን መጸለይ።

❖ <u>የአሥራው መጽሐፍትና የአዋልድ መጻሕፍት ግንኙነት /አንድነት/</u>

- አዋልድ መጻሕፍት የአሥራው መጻሕፍት ልጆች ናቸው። ልጆች መሆናቸውንም ከመጽሐፍ ቅዱስ እያመሳከርን እንደሚከተለው እንመለከተዋለን።

አሥራው መጽሐፍ	አዋልድ መጻሕፍት
የሕግ መጽሐፍት፡- አምስትቱ ብሔረ ኦሪት፣ መ.መሳፍንት መ.ኢያሱ ------	ፍትሐ ነገሥት፣ መ.ብርሃን ሐይማኖተ አበው ------
የታሪክ መጽሐፍ፡- መ.ሳሙኤል መ.ነገሥት፣ ዜና መዋዕል....	ተአምረ ማርያም፣ መ.ስንክሣር ገድላት ።
የጥበብ መጽሐፍት፡- መዝ.ዳዊት መ.ኢዮብ፣ መ.ምሳሌ	• ውዳሴ ማርያም፣ መፅ.ሰዓታት፣ መ.አርጋኖን ፡ ድርሳናት።
የትንቢት መጽሐፍት፡- የነቢያት የትንቢት መጽሐፍት፣ ራእይ ዮሐንስ	• ፍካሬ ኢየሱስ፣ ራእይ ማርያም ፡ራእየ ሚናስ።

❖ <u>አዋልድ መጻሕፍትን ለመቀበላችን የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ</u>

➥ በይሁ.ቁ **8-10** ላይ “ቅዱስ ሚካኤልን ግን ከዲያቢሎስ ጋር በሙሴ ሥጋ በተከራከረ ጊዜ.....**..**” ይላል። በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለ ሙሴ ሥጋ ቅዱስ ሚካኤልና ዲያቢሎስ ያደረጉትን መከራከር ይገልጻል።ነገር ግን በሙሴ መጽሐፍት ውስጥ ጥሀ ታሪክ አልተጠቀሰም ታዲያ ይሁዳ ከየት አምጥቶ ጻፈው? ቢባል “ዘናሁ ለሙሴ” ከሚለው ከገድለ ሙሴ ላይ ጠቅሶ ጽፏል። ለዚህ ይሁዳ መልእክቱን ለመጻፍ አዋልድ መጻሕፍትን ተጠቅሟል።


➥ የእመቤታችን እናትና አባቷ በጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተገለጸም። ታዲያ እመቤታችን ከሰማይ እንዳልወረደች መጽሐፍ ቅዱስም ይነግረናል። (ሉቃ 1÷10) የኤልሳቤጥና የቅዱስ ገብርኤል ምስክርነት በቂ ማስረጃ ነው። ታዲያ ምድራዊ ከሆነች እናትና አባቷ ማን ይባላሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም የምናገኘው በአዋልድ መጻሕፍ ውስጥ ነው።ይኸውም በተአምረ ማርያም እና በነገረ ማርያም መጻሕፍት ውስጥ ይገኛል።

➥ በት/ሚል **3÷16** ላይ ‹‹የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን የሚያቡ እርስ በእርሳቸው ተነጋገሩ እግዚአብሔርም እንደመጣ ስማም እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ስሙን ለሚፈሩ ስሙን ለሚያስቡ የመታሰቢያ መጻሕፍት በፊቱ ተጻፈ›› በማለት መግለጹ አዋልድ መጻሕፍም በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የተጻፉ መሆናቸውንና እነርሱንም መቀበል እንዳለብን ያስረዳናል።

❖ <u>የአዋልድ መጻሕፍት አከፋፈል</u>

‹‹ወኩሉ ዘተጽህፈ ለተግሳጽ ተጽህፈ **----** የተጻፈው ሁሉ ለትምህርት ተጻፈ›› ሮሜ **05÷4**

እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ አዋልድ መጻሕፍት በውስጣቸው ከያዙት መልእክትና ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ በተለያዩ ክፍሎች ይከፈላሉ። እነሱም፡-



1. <u>የነገረ ሃ</u>[illegible]ሃይማ[illegible]ርተ ሃይማኖትንና ሥርዓተ እምነትን ጠቅሰው ያዘጋጀ E ቸው መጽሐፍት ናቸው። **(**ኤፌ **4-////5**፣ይሁ **1-3)**

<u>ለምሳሌ</u>፡-ሃይማኖተ አበው፣ፍካሬ ሐይማኖት፣መጽሐፈ ምስጢር፣መጽሐፈ ምእላድ፣ክብረ ቅዱሳን ፣መጽሐፈ ኪዳን፣አንቀጸ አሚን፣ውዳሴ መስቀል፣መጽሐፈ ብርሃን፣መጽሐፈ ቁርሎስ፣ድርሳነ ፍልሰታ፣ፊውስ መንፈሳዊ ----- ወዘተ ናቸው።

2 <u>የትርጓሜ መጻሕፍት</u>፡- እነዚህ መጻሕፍት ሊቃውንት አባቶቻችን አስፍተው አምልተው አመሥጥረው አራቀው ምሥጢር ከምሥጢር አገናኝተው ሐተታ አክለው ያዘጋጀ E ቸው መጻሕፍት ናቸው።

<u>ለምሳሌ</u>፡- ትር Õ ሜ ወንጌል፣የጳውሎስ መልእክት ትር Õ ሜና ንባብ፣ሠለስቱ ሐዲሳት ትር Õ ሜ፣መዝሙረ ዳዊት ትር Õ ሜ... ወዘተ....ናቸው።

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*` „Ê¡e }ªIÊ

3 የጸሎት መጻሕፍት፦ በቤተ ክርስቲያን በግል ለጸሎት የሚያገለግሉ መጻሕፍት ናቸው። እነዚህም በተለያዩ ቅዱሳን አበው የተደረሱ ከተለያዩ ቅዱሳን መጻሕፍት የተወረጣጠጡ ናቸው።እነዚህም መጻሕፍት ለሁለት አይነት አገልግሎት ይውላሉ፦

- የዘወትር መጽሐፍት(የእለት) ምሳሌ፦-ውዳሴ ማርያም፣ውዳሴ አምላክ፣ሰዓታ መለኮት፣የዘወትር የንግህ የሰርክ እና ኪዳን ናቸው።
- ለተለያዩ አገልግሎቶች(ለሰሞናት የምንጠቀምባቸው) ምሳሌ፦-መጽሐፈ ተክሊል፣መጽሐፈ ቀንዲል፣መጽሐፈ ጥምቀት፣ግብረ ሕማማት፣ሰአታት፣ማኅሌተ ጽጌ፣መጽሐፈ ግንዘት ----ወዘተ ናቸው።

4 **ySRxttgtrgtRsgTrgTrtTtrTftgsd** የሥርዓተ ቤተ-ክርስቲያን መጻሕፍት፦ የምሥጢራተ ቤተ-ክርስቲያን አፈጻጸም፣የቤተ-ክርስቲያን አሰራርና አስተዳደር፣የምዕመናንና የክህነት የኑሮ ሥርዐት የተደነገጉባቸው የሥርዐት መጽሐፍት ናቸው።

ምሳሌ፦-ፍትሐ ነገሥት፣መጽሐፈ መነኮሳት፣መጽሐፈ ግፃዌ፣መጽሐፈ ሥርዐተ ተክሊል፣ሕገ ብህትውና ወዘተ... ናቸው።

(ዘሌ @6-@3፣!6-@9½½½½½½፣ሕዝ @-!1½½፣1ኛተሰ 5-!4፣2ኛተሰ 3- 6-7½ qq ቆላ 2-5)

5 **y¬¶K** የታሪክ መጻሕፍት፦ የቤተ-መጽሐፍት መንፈሳዊ ጉዞ የገዳማት የአድባራት ታሪክ በዘመናቱ የገጠሙ ችግሮችን ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር በማነፃፀር፣በማዛመድ የሚመዘገቡ ናቸው።

ለምሳሌ፦-ስንክሳር፣ጤፋት(ስለ እፀ መስቀል የሚናገር መጽሐፍ ነው) የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ በኢትዮጵያ (በዓለም)፣ክብረ ነገሥት፣ታሪክ ነገሥት፣የዋልድባ ገዳም ታሪክ ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው።

6 የጥበብ መጻሕፍት፦ እነዚህ የጥበብ መጻሕፍት ለሁለት ይከፈላሉ።እነርሱም ጥበብ መንፈሳዊ እና ጥበብ ሥጋዊ ናቸው።ቅዱሳን አበው መንፈሳዊና ሥጋዊ ጥበብን የዘገቡባቸው መጽሐፍት ናቸው።

ለምሳሌ፦-ስለ ዓለማት መጽሐፈ ማስያስ፣ስለ ስነ-ፍጥረት፣መጽሐፈ አክሲማሮስ፣ስለ ዘመን አቆጣጠር መጽሐፈ አቡሻክር፣ስለ ቤተሰባዊ ኑሮ መጽሐፈ ሐዊ የሚያስተምሩ ናቸው። (2ኛጢሞ 3- !4-!5)

7 **gD§T** ገድላት፦ የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆኑ ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ስለ እግዚአብሔር አምልኮት ስለ ሕጉና ፈቃዱ መጠበቅ ብለው ከአላውያን ነህሥታት ከቢጽ ሐሳውያን ከዚህ ዓለም ገሸር ከቢያቢሎስና ከሥጋ ፈቃድ ጋር የፈጸሙት ተጋድሎ የሚናገሩ መጻሕፍት ናቸው። የቅዱሳንን ገድል መጻሕፍት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ነው። 2ኛ ቆሮ 11 ÷ 23-27 ፣ ዕብ 11÷32-40። ከዚህ በተጨማሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ‹‹የሐዋርያት ሥራ›› የተባለው መጽ ሐፍ የጎሩያን ሐዋርያትን ዜና ግብር ገድል የሚያስረዳ መጽሐፈ ገድል ነው። እንዲሁ ጌታችን ‹‹በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ እኔም በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታልሁ›› ማቴ !-#2፣ዮሐ !6-2 ባለው ቃል መሰረት ቅዱሳን በስሙ የተቀበሉትን መከራ፣የተጋደሉትን ገድል እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ቸርነት እና የተሰጣቸውን ቃል ኪዳን የሚያስረዱ ናቸው።

ለምሳሌ፦- ገድለ ጊዮርጊስ፣ገድለ አዳም፣ገድለ ተክለሃይማኖት፣ገድለ አቡነአረጋዊ፣ገድለ ገብረመንፈስቅዱስ ...ወዘተ...

8 **DR** ድርሳናት፦- ድርሳን ስለ አንድ ነገር የተጻፈ ጽሑፍ ሐተታ ማለት ነው። ድርሳንናት የቅዱሳን መላእክትን ክብርና አማላጅነት ተራዳኢነት የሰንበት ክብርና ልዕልና የሚገልጹ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተንተርሰው የጻፏቸው ድርሳናት አሉ። ለምሳሌ ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ የዕብራውያንን መልእክት የተረጎመበት መጽሐፍ ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈውርቅ ተብሎ ይጠራል።

ለምሳሌ፦- ድርሳነ ሚካኤል፣ድርሳነ ማርያም፣ድርሳነ ኤልያስ ...ወዘተ...

9 ተአምራት፦-ይህ መጽሐፍ ጌታችን‹‹በስሜ ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተላ**E** ቸዋል።በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ አዲስ **s”s** ይናገራሉ›› (ማቴ !6-!7) ባለው አምላካዊ ቃል መሠረት እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ አድሮ የገለጣቸውን ምልክቶች የሚናግሩ ናቸው።

(ሐዋ 5-!5፣ሐዋ !9-!1½/ê፣ሐዋ 3 -6 -8½፣ሐዋ !4 -8-@፣ዕብ 2-4½፣ዮሐ !4-!2)

ለምሳሌ፦-ሙሴ በግብጽ ላይ አስር መቅሰፍትን ማምጣቱ(ዘፍ 8-!2)

ጌታ ውሀውን ወደ ወይን መለወጡ (ዮሐ 2- 1-!1)

አልአዛርን ከሞት ማስነሳት (ዮሐ !1) ይጠቀሳሉ።

የተአምራት መጽሐፍት ሁለት ናቸው እነሱም ተአምረ ኢየሱስና ተአምረ ማርያም ናቸው።

- ተአምረ ኢየሱስ፦-ይህ መጽሐፍ ጌታችን ከመዋዕለ ስብከቱ ከልደት እስከ ዕርገቱ ያደረገውን ድንቅ ድንቅ ተአምራት የሚዘክር መጽሐፍ ነው።(ዮሐ @-#፣@1-@5)
- ተአምረ ማርያም፦-ይህ መጽሐፍ እመቤታችን ከጽንሰቷ እስከ ዕርገቷ እንዲሁም በአጸደ ነፍስ በመንግሥተ ሰማያት ሆና በአማላጅነቷ የደረገችውን ተአምራት የሚዘክር መጽሐፍ ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አዋልድ መጻሕፍት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ደግሞ ለምክር ይጠቅማል›› ብሎ እንደገለጠው አዋልድ መጻሕፍት አሥራው መጻሕፍትን መሠረት አድርገው የተጻፉ አሥራው መጻሕፍትን የሚተነትኑ የሚያብራሩ በመሆናቸው ልንጠቀምባቸው ለመጪው ትውልድም ልናቆያቸው ያገባል።

2ኛ ጢሞ 3÷16-17

❖ <u>መጽሐፍ ቅዱስና ትውፊት</u>

- <u>ትውፊት</u>፡- ማለት አወፈየ ካለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ቅብብሎሽ ውርስ ርክክብ ማለት ነው። ትውፊት የምንላቸው በቃል በጽሑፍ እና በተግባር የተቀበልናቸው ነገሮች ናቸው። በጽሑፍ ከተቀበልናቸው ትውፊቶች መካከል ደግሞ አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ከቀደሙት አባቶች በትውፊት የተቀበልነው ነው። በዚህ ክፍል ትምህርታችን የመጽሐፍ ቅዱስን ቅብብሎሽ እና የመጽሐፍ ቅዱስን ትውፊት ስምሪት እናያለን።

<u>በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች</u>

አባቶቻችን እንደሚያስተምሩን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ መከራ የደረሰበት ነገር የለም ይላሉ። ሆኖም እነዚህን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን በ 3 ክፍለን እንመለከታለን።

1. መጥፋት፡- በተለያዩ ዘመናት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይጠፉ አይገኙም ነበር።
   ለምሳሌ፡- ራዕይ ዮሐንስ ለዓመታት ጠፍቶ ነበር።
2. <u>ምዝበራ</u>፡- በአላዊያን ነገሥታት ትእዛዝ በተለያዩ ዘመናት መጽሐፍ ቅዱስ እንደይነበብ ታግደው ተቃጥለው ነበር። ይዘው የተገኙ ሰዎች በሰማዕትነት ይምቱ ነበር። ከፍተኛ የጥፋት ዘመቻም ተካሒዶባቸዋል። ከእነዚህም ውስጥ ለምሳሌ የሮሙ ንጉሥ ዲቅልጥያኖስ በ 302 ዓ/ም ክርስቲያኖችን ለማጥፋት ባወጣውትእዛዝ የመጨረሻ አዋጅ መጻሕፍት እንዲቃጠሉ ሲያደርግ በሀገራችንም በ 9ኛው መ/ክ/ዘ በዮዲት ጉዲት እና በ 1527-1542 ዓ/ም በግራኝ አህመድ (ኢማም አህመድ) የጥፋት እጆች በርካታ መጽሐፍትን መዝብረዋል (አጥፍተዋል)
3 <u>ቁንፀላ</u>፡- ይህ ማለት መጽሐፍትን መበረዝ ማለት ነው። በውጪ ያሉት አረማዊያንና ፈላስፎች መጽሐፍትን ማቃጠል ማጥፋት አልሆን አልሳካ ሲላቸው እውነተኛይቱን መጽሐፍት የመበረዝ የመቀንፀል ሴራቸውን አሰፉ ይሔም ቅዱሳት መጽሐፍትን ለመለየትና ለማወቅ ያስቸገረ ፈተና ነበር።

<u>መጽሐፍ ቅዱስ አሁን ላለንበት ዘመን እንዴት ሊደርስ ቻለ</u>

1. በፈቃደ እግዚአብሔር፡- ኃያሉ አምላክ ልዑለ እግዚአብሔር ከፍቅሩ የተነሳ እንደይጠፋ ሕይወት እንዲሆንልን ፈቃዱ ስነለበር ለእኛ ቃሉ ደርሶልናል።ዘጸ 17÷14 ፣ ት/ሚል 3÷16 ፣ ማቴ 5÷18 ፣ት/ኢሳ 34÷16 ማቴ 24÷35
2. በሃይማኖት በፀሁ አባቶች አማካኝነት፡- ይህን ስንል አባቶች ሰማዕትነትን በመክፈል አሁን ላለንበት ዘመን አድርሰውልናል።

ለምሳሌ፡-

- <u>ቅዱሳን በጥንቃቄ በመጻፍ በክብር በማስቀመጥ</u> ፡- ዘጸ 31÷24 ኢያ 24÷26 2ኛ ነገ 22÷8
- <u>በመገልበጥ /ብዜት/ ኮፒ እያደረጉ በማብዛት</u>፣ ማሥርያውያን ብሉያትን በብዙ ኮፒ ሲገለብጡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር። የመነሻ ቅጂዎችንም ትክክለኛነት ያጣሩ ነበር። እያንዳንዱን ፊደል ያረጋግጡ ነበር ስህተት የተገኘበትንም ያስወግዱ ነበር። የሐዲስ ኪዳን ኮዴክሶችም ያዘጋጁት አአባቶቻችን ሐዋርያት የጻፉትን የግሪክ ሰብአ ሊቃናት ትርጉም መሠረት በማድረግ ሲገልጡ ለዘመናችን ከ 10000 (አሥር ሺህ) በላይ ኮዴክሶች በተለያዩ ቋንቋዎች አዘጋጅተዋል።
- <u>ሊበላሹ በማይችሉ ሰሌዳ ላይ በመግፋ</u>፡- ለምሳሌ በሰሌዳ ፣ በክርታስ ፣ በብራና ፣ በጡብ ፣ በድንጋይ --ወዘተ ት/ኢሳ 30÷8 ት/ኤር 3÷2 2ኛ ጢሞ 4÷13 ት/ሕዝ 4÷1 ት/ሕዝ 39÷23
- <u>ሰማዕትነት በመቀበል</u>፡- ቅዱሳት መጻሕፍት ከሚጠፉ ከሚቃጠሉ እኛ እንጥፋ እንቃጠል በማለት ራሳቸውን አሳልፈው ለሞት ሰጥተው ቅዱሳት መጻሕፍትን አቆጠይተውልናል። ለምሳሌ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ የኦሮን ቄሳር ወታደሮች ሲያሳድዱት ብሕር ዳርቻ ሔዶ እግዚአብሔር ላዘጋጀው አንድ ዓሣ አጥማጅ ‹‹እነዚህ የሕይወት መንገድን ይመሩሃል›› ብሎ ካስረከበው በኋላ ሰማዕትነትን ተቀብሏል።
- <u>መጽሐፍትን በቃል በማጥናት</u>፡- አባቶቻችን ቅዱሳን ወደፊት አላውያን ነገሥታት ተነስቶ መጻሕፍትን ካጠፋብን ብለው በቃላቸው ያጠኑአቸው ነበር። ‹‹ስለዚህ የቀደመውን ትውልድ ጠይቁ››መ ኢዮ 8÷9 እናዳለ ቅዱስ ኢዮብ። ዘዳ 32÷7
- <u>በመለየት እውነተኞቹን ከሀሰተኞች</u>

<u>የትውፊት መረጃ በብሉይ ኪዳን</u>

- ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት ነበር። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ትምህርት ለአዳም አባታችን ያስተማረው ተስፋ የሰጠውም በቃል ነበር። **(ዘፍ 1÷@8)** የአዳም ልጆች የተስፋውን ቃል ሲቀበሉ ኖረው በኃላ ነው የተጻፈላቸው።
- አቤልና ቃየል መስዋዕት ማቅረብ እንደሚገባ ያወቁት የተማሩት መስዋት ያቀረቡትም ከአባታቸው ከአዳም በትውፊት ተምረው ነው። **(ዘፍ 4÷3-5)**
- ዮሴፍ ዝሙት ኃጢአት እንደሆነ ያወቀው ከቀደሙት አባቶች በትውፊት ተቀብሎ ነው እንጂ በጽሑፍ የተጻፈ ነገር አልነበረም። ዘፍ **#9÷6)**
- ሙሴ ከአዳም ጀምሮ እስከ ዮሴፍ ድረስ የነበረውን ከእርሱ በፊት የነበሩት ሲጽፍ ከእርሱ ቀድሞ ከነበሩት አባቶች በትውፊት ያገኘው ስለሆነ ነው።
- ሙሴ አፈ ኮልታፋ ነበር። እንዴት አፈ ኮልታፋ ሆነ ያወቅነው በትውፊት ነው።

<u>የትውፊት መረጃ በሐዲስ ኪዳን</u>

- ስለ እመቤታችን ልደት፣ እናት አባቷ ማን እንደሚባሉ በ 27 ቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ አይጠቅስም። ሆኖም እናቷ ሀና አባቷ ኢያቄም እንደሚባሉ ያወቅነው በትውፊት ነው።
- በመጽሐፍ የተጻፈው ክርስቶስ ከ 30 ዓመቱ በኋላ ያለው ነው። እስከ 30 ዘመኑ ድረስ ምን ሲሰራ ነበር። ይህንን ጌታ እስከ 30 ዓመቱ ድረስ ሲፈጽም የነበረውን ነገር ያወቅነው በትውፊት ነው።
- ጌታችን ያስተማረው በቃል ሲሆን ሐዋርያት ከጻፉት ያልተጻፉት እንደሚበልጥ /ዮሐ **@1÷@5/** ላይ ተጠቅሷል። ነገር ግን በመጽሐፍ ከተጻፈው ውጪ ምን እንዳስተማረ ያወቅነው በትውፊት ነው።
- ቅዱስ ጳውሎስ (በ 2 ጢሞ 3÷6) ላይ ሙሴን የተከራከሩትን አስማተኞች “እያኔስና እያንባሬስም” ብሎ ጠቅሷል።ነገር ግን በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ስማቸውን አይጠቅስም። ሆኖም እዚህ ጋር ቅዱስ ጳውሎስ በትውፊት አግኝቶ እንደጻፈው እንማራለን።
- ይሁዳ ቁ **8** ላይ ስለ ሙሴ ሥጋ ሚካኤልና ዲያቢሎስ ያደረጉትን መከራከር ጽፏል። ግን በሙሴ መጽሐፍ ላይ ይህን ታሪክ አይጠቅስም። ታድያ ይሁዳ ከየት አመጣው ቢባል በትውፊት ያገኘው መሆኑን እንረዳለን።.....ብዙ መጥቀስ ይቻላል ግን ለእኛ ይህንን ያህል ካነሳን በቂያችን ነው።

❖ <u>የትውፊት ዓይነቶች፣</u>

1) <u>ባህላዊ ወይም ተግባራዊ ትውፊት፡-</u> የምንላቸው የቀደሙ የጥንት ሰዎች ይሰሩት የነበረው ባህል ሲወርድ የመጣ ማለት ነው ። ለምሳሌ፡- ድፎ ዳቦ ገልብጦ መቁስ / የባህል ልብስ .....ወዘተ ናቸው።ኢሳ **3-!6-#2**

2) <u>ጎጂ ትውፊት፣</u> የምንለው ለምሳሌ፡- ታቦት ቆሞ መዝፈን እንጥል ማስቆረጥ ንቅሳት መነቀስ ድድ ማስቧጠጥ .... ወዘተ ናቸው።ዘዳ **@5-5/** ት/ሶፎ **1—8** /ዘሌ **!9-@7** /ዘዳ **!4-2** / ዘዳ **!2 - @/////**

3) <u>ሰይጣናዊ ትውፊት፡-</u> የምንለው ከጥንት ሰዎች ከቀደሙት ሲወርደረ ሲዋረድ የመጣ የባዕድ አምልኮ/ መተት/ ጥንቆላ /ከከብ ቆጠራ/ እንሾሽላ መሞቅ/ ኮል መካ E ል/ ቅንድብን መሸለት ..... ወዘተ ናቸው ። /ሔኖ **2 --@2** /ሔኖ **2-!9/**ሲራ**@6-9/**

4) <u>ክርስቲያናዊ ትውፊት</u>፡- ማለት ከቀደሙ አባቶቻችን የምንቀበለው የእምነት ሥርዓት .... እነዚህ ክርስቲያናዊ ትውፊት ይባላሉ ለምሳሌ ፡- ሀማማት/ ልብስ ተክህኖ /ጉልባን /በቀዳሚ ሥዑር እለት የሚታሰር ቄጠማ/ በእለተ ሆሳዕና የሚታሰረው ዘንባባ .....ወዘተ ናቸው።/ኢዮ **8-!1** /ኢሳ **!9- !5** /ዘፀ **2-3** /መኃል **4- 8 /6-9//**

ምዕራፍ አራት

የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕል አባባል እና ፈርጀ ብዙ ቃላት

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕል</u>

በዚህ ክፍላችን ውስጥ ደግሞ የዚህን የመጽሐፍ ቅዱስን ባሕሉ ምን እንደሆነ በሰፊ እንመለከታለን። እንግዲህ የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕሉን መረዳትና ማወቅ ካልቻልን የመጽሐፍ ቅዱስን መልዕክት መረዳት አይቻልም። ለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስን ባሕል ጠንቅቀን ማወቅ አለብን። የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕል ስንል አሁን በዓለማችን ላይ እጅግ በርካታ ባሕሎች ሥርዓቶች አሉ። ልክ እንደዚሁ መጽሐፍ ቅዱስም የራሱ የሆነ ባሕል አለው። ታድያ አንድ ሰው ዓለም ላይ ያለውን ባሕል ከመጽሐፍ ቅዱስ ባሕል ጋር ቀላቅሎ መረዳት መመኮር የለበትም ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ ባሕልና የአነጋገር ዘይቤ ስለተጻፈ። ለምሳሌ፦ እረኝነትን በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በበርካታ ቦታዎች ተጽፎ እናገኛለን። ጌታም እራሱን በእረኛ መስሎ ‹‹እነ ውእቱ ኖላዊ ሐር›› እኔ ቸር ጠባቂ ነኝ ሲል ገልጿል። ታድያ ይህንን የእረኝነት ጠባይ አንድ ኢትዮጵያዊ መጽሐፍ ቅዱስ ሲያነብ በሀገሩ የእረኝነት ጠባይ የሚረዳ ከሆነ የመልእክቱን ዋና ሐሳብ መረዳት አይችልም ምክንያቱም መጽሐፉ የተጻፈው በእብራውያን ባሕል ስለሆነ በእብራውያን ዘንድ አንድ እረኛ በጎቹን ሲነዳ ከፊት እየመራ ይጓዛል እንዲመገቡ ከፈለገ በትሩን ከመሬት ሲተክለው በእዚያ ዙሪያ ተሰብስበው ይመገባሉ። የሀገራችን እረኛ ጠባይ ግን ለየት ይላል። እረኛው ከኋላ በጎቹ ከፊት ሆነው ይጓዛሉ። ይህ የኢትዮጵያ እረኞች ጠባይ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ የምናገኘው የእረኛ ጠባይ ግን የእብራውያን የእረኛ ጠባይ ነው። ክርስቶስም ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ ሲል እረኛው ራሱን ለበጎቹ መስዋዕት አድርጎ እንደሚጓዝ ሁሉ የዓለም ብርሃን ክርስቶስ ስለ በጎች ሲል ራሱን በቀራንዮ መስዋዕት አድርጓልና። ልክ እንደዚህ ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ባሕል ወቅቱንና የተጻፈላቸውን ሰዎች እንደዚሁ የጸሐፊውን ባሕል እያወቅን ልናነብ ይገባል። እስኪ የመጽሐፍ ቅዱስን ባሕል ዘርዝሮ ማቅረብ ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም ለአብነት ያህል ግን የተወሰኑትን ቀጥለን እንመለከታለን፦

1. <u>በዕብራዊያን (እሥራኤላውያን) ዘንድ የስም አወጣጥ ባሕል</u>

✓ <u>ለሰዎች የሚሰጥ የተዐውዶ ስም</u>

- በዕብራዊያን (እስራኤላዊያን) ዘንድ ስም አወጣጣቸው ከግብርና ጠባይን ተንተርሰው ከተፈጥሮአዊ ክስተት ስም ያወጣሉ። ለምሳሌ፦

1. አዳም፦ በአረማይክ ቋንቋ ‹‹መሬት›› ማለት ነው ይህ አፈጣጠሩን ይነግረናል።
2. ሴት፦ ትርጉሙ ‹‹ምተክ›› ማለት ነው። እናቱ ሔዋን በአቤል ምትክ (ፈንታ) ሌላ ተክቶልኛል ስትል ሴት አለችው።
3. ይስሐቅ፦ ትርጉሙ ‹‹መሳቅ›› ማለት ነው። እናቱ ሣራ በእርጅናዋ ዘመን ልጅ የመውለዳቸውን ብስራት ሰምታ ስለ ሳቀች በዚህ ይስሐቅ ተበለ ።
4. **ያዕቆብ፦** ‹‹ተረከዝ የሸ›› ማለት ነው። ሲወለድ የመንትያውን የዔሳውን ተረከዝ በእጁ ይዞ በመወለዱ የተሰጠው ስም ነው። /ዘፍ **@5÷@6/**
5. ሙሴ፦ ትርጉሙ ‹‹ከባህር የወጣ›› ማለት ነው። እኔ ከውሃ አውጥቼሐለሁ ስትል የፈርኦን ሲት ልጅ ተርሙት ስሙን ሙሴ አለችው
6. **ምናሴ፦** ‹‹ማስረሻ›› ማለት ነው። ‹‹ዮሴፍ የበኩር ልጁን ምናሴ ብሎ ጠራው እንዲህ ሲል እግዚአብሔር መከራዬን ሁሉ የአባቴንም ቤት አስረሳኝ›› ሲል (ዘፍ **$1÷)**
7. ፋሬስ፦ ትርጉሙ ‹‹ጣሽ›› ማለት ነው። የያዕቆብ ልጅ የይሁዳ ልጅ ነው። ሲወለድ ወንድሙን ዛራን ጥሶ ስለመጣ ፋሬስ ብሎ ስም አወጡለት።
8. ዘሩባቤል፦ የባቢሎን ዘር ማለት ነው እናቱ በባቢሎን መወለዱን ስትናገር ስሙን ዘሩባቤል ስትል አወጣችለት። ወዘተ -------

✓ <u>ለቦታ የሚሰጥ ስያሜ</u>

መጽሐፍ ቅዱስ በወቅቱ ከተከሰቱት ወይም ከተፈፀሙት ሁኔታዎች አንፃር ለሰዎች ይሰጥ ከነበረው በተጨማሪ ለቦታዎችም አንዳንድ ስያሜ ይሰጣቸው እንደነበር እንረዳለን። ለምሳሌ፦

1. <u>ቤቴል</u>፦ ቤቴል ማለት ‹‹የእግዚአብሔር ቤት›› ማለት ነው። ስያሜውም የተሰጠው ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ድንጋይ ተንሰርሶ በተኛ ጊዜ “ከምድር እስከ ሰማይ መሳላል ተዘርግቶ የእግዚአብሔር መላእክት ሲወጡባትና ሲወርዱባት በላይም ንጉስ በዙፋኑ ተቀምጦ አየ” በዚህ ራእይ ያዕቆብ ደንግጦ ለመሠረት ብሎ ድንጋዩን ቀብቶ ይህ የእግዚአብሔር ቤት ነው። ሲል ቤቴል ብሎ ጠርቶታል።
2. <u>ጎለጎታ</u>፦ ቃሉ የአብራይስጥ ነው። በግሪክ ቀራንዮ ይባላል። ትርጓሜው ‹‹የራስ ቅል›› ማለት ነው። የራስ ቅልም የተባለው የአባታችን የአዳም አጽም የተቀበረበት ቦታ ስለሆነ ነው
3. <u>ጌልጌላ</u>፦ ‹‹ማንከባለያ›› ማለት ነው። በምድረ በዳ የተወለዱት የእስራኤል ልጆች አልተገረዙም ነበር። እግዚአብሔር እያሱን እንዲገረዙ አዘዘው። ኢያሱም እንደታዘዘ አደረገ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ኢያሱን “የግብፅን ነውር ከእናንተ አንከባልላለሁ” አለው በዚህ መነሻ የዛን ስፍራ ስም ጌልጌላ ብሎ ጠራው።
4. <u>መሪባ</u>፦ መሪባ ማለት ‹‹ክርክር›› ማለት ነው። ሙሴ ባሕረ ኤርትራን በከፈለበት በትር የኮሬቡን አለት መትቶ ውኃ ያፈለቀበት ቦታ ነው። ቀድሞ የሰፈሩበት ቦታ ‹‹ራፊዲም›› ይባል ነበር። ይኸውንም ስያሜ ያገኘው እስራኤላውያን ሙሴን ተከራክረውት ስለነበር ክርክራቸውን ለማሰብ ሲል ቦታውን መሪባ አለው።

1.2 <u>ለሰዎች የሚሰጥ ቅፅል ስም</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ተመሳሳይ ስም ያላቸው ሰዎች አሉ። እነሱንም ለመለየት ጸሐፊያኑ የግብርና የቤተሰብ ስማቸውን ይጠቀማሉ። ይኸውም፦

<u>በግብራቸው ስም የሚጠሩ፣</u>

1. <u>መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ</u>፦ የንስሐ ጥምቀት ዮሐንስ ያጠምቅ ስለነበር በዚያውም ጌታችንን በማጥመቁ መጥምቀ መለኮት የሚለ ቅፅል ስም ተሰጠው።
2. <u>ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ</u>፦ ከሐዋርያት መካከል የዘብድዮስ ልጅ ዮሐንስ ጌታችንን አብዝቶ ይወደው ስለነበር እስከ መስቀል ድረስ ያልተለየ ሐዋርያ ስለሆነ ፍቁረ እግዚእ የሚል ቅፅል ስም ተሰጠው።
3. <u>እህተ አልዓዛር ማርያም</u>፦ ጌታ ይወደው የነበረው የአልዓዛር እህት ስለሆነች ይህ ቅፅል ስም ተሰጣት።
4. <u>ማርያም እንተ እረፍት፦ (ባለሽቶዋ ማርያም)</u>፦ ጌታችን በቢታንያ በፈሪሳዊው ስምዖን ቤት ሳለ መጥታ ለጌታ ሽቱ በማቅረቧ ይህ ቅፅል ስም ተሰቷታል።
5. <u>ቁርበት ፋቂው ስምዖን</u>፦ በኢዮጴ የሚኖር ጴጥሮስን በቤቱ ያስተናግድ የነበረ ሰው ነው “ቁርበት ፋቂው” የተባለውም በቆዳ ስራ የተሰማራ በመሆኑው።/ሐዋ **9 ÷#6/**

<u>በትውልድ ቦታቸው የሚጠሩ</u>

1. <u>መግደላዊት ማርያም</u>፦ ትውልድ ቦታዋ መግደላ ሰለሆነ በዚህ መግደላዊት እየተባለች ትጠራለች።
2. <u>ቴስብያዊ ኤልያስ</u>፦ ይኸውም ቴስብያ በምትባል ቦታ ተወልዶ በገለዓድ ያደገ በመሆኑ በትውልድ ቦታው ቴስብያዊው ኤልያስ እየተባለ ይጠራል።
3. <u>ሞዓባዊቷ ሩት</u>፦ ሩት ሞዓብ ነው የትውልድ ሀገርዋ ነገር ግን ከኑኃሚን ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የመጣች ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ ግን በትውልድ ሀገርዋ ሞዓባዊቷ ሩት በሚል ቅፅል ይጠራታል።
4. <u>ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ</u> (ለ66 ዓመታት የተኛው)፣ ሀገሩ ኢትዮጵያ በመሆኑ በሀገሩ ስም ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ በሚል ቅፅል ይጠራዋል።
5. <u>ስምዖን ቀሬናዊ</u> ፦ በሰሜን አፍሪካ የምትገኝ መደብ ናት። በዚህችም ቦታ የተወለደ ስለሆነ ቀሬናዊ በሚል ቅፅል ስም ይጠራዋል።
6. <u>የአርማትያሱ ዮሴፍ</u> ፣(ጌታችንን ከኒቆዲሞስ ጋር የገነዘው ነው)፦ ይኸውም አርማትያስ የተወለደ በመሆኑ በሀገሩ ስም የአርማትያሱ ዮሴፍ በሚል ቅፅል መጽሐፍ ቅዱስ ይጠራዋል።

<u>በቤተሰብ ስም መጠራት፣</u>

1. ኢያሱ ወልደ ነዌ፦ የነነዌ ልጅ ኢያሱ ማለት ነው።
2. የበራክዮ ልጅ ዘካርያስ፦ ነብዩ ዘካርያስን ነው። ለመለየት ሲል የአባቱን ስም ጠቅሶ ጠራው።
3. የእልፍዮስ ልጅ ያዕቀብ፦ ይህ የማቴዎስ ወንድም ነው ከ12 ቱ ሐዋርያት መካከል አንዱ ነው።ለመለየት ግን የአባቱን ስም ጠቀሰ።
4. ያዕቆብ ወለደ ዘብድዮስ፦ ።የሐዋርያው ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ ወንድም ነው።አባቱ ዘብድዮስ ስለሚባል ወልደ ዘብድዮስ ተባለ።
5. የያዕቆብ እናት ማርያም.....(ማር **02÷$)**
6. የማርቆስ እናት ማርያም ፦-------ወዘተ .....ብዙ መጥቀስ ይቻለል።ሆኖም እነዚህን ለመለየት ሲል የቤተሰብን ስም እያከለ ይጠራቸዋል። <u>አሳይመንት፦</u>-(በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን በስምዖን ፣በማርያያም ፣በኢያሱ፣በያዕቆብ፣በፊሊጶስ፣በሐና፣በአቤሜሌክ፣በይሁዳ ስም የተጠሩትን ሰዎች ጽፋችሁ አምጡ?)

2) <u>ደጊሞተ ቃል (ቃልን የመድገም ባህል)</u>

አንድ ሐሳብን በቀጥተኝነት በአንፅኦት መገለጥ ሲያስፈልግ ዕብራዊያን (እስራኤላውያን) የሚጠቀሙበት የአነጋገር ዘይቤ ስላላቸው ከዐረፍተ ነረሩ ውስጥ አንዱን ቃል መድገም ነው። ለምሳሌ “አንተ አባታችን ነህ አቤቱ አንተ አባታችን ነህ” ሲል የእግዚአብሔርን አባትነት በአንፅዖት ለመናገር በፈለጉ ጊዜ የተናገረው እንደሆነ ያስረዳናል። (ኢሳ **^3÷!6)**

- **“**እውነት እውነት እልሃለው ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግስት መውረስ አይችልም.....**.”** (ዮሐ **3÷3)** ምንም የሰው ልጅ የጠነከረ እምነት የተመሰከረለት ምግባር ቢኖረውም ካልተጠመቀ የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ እንደማይችል በአፅንኦት ለመግለፅ ሲል “እውነት እውነት” ሲል ደጋግሞ ቃሉን ተናገር። በማቴ 23÷37 ላይም ‹‹ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ ነብያትን የምትገድል ወደ እርሷ የተላኩትን የምትወግር**---››** በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ጊዜ ኢየሩሳሌም ብሎ መናገሩ የኢየሩሳሌም ልጆችን አመጽ በአፅንዖት መናገሩ ነው።

3) <u>ሥዕላዊ አገላለጥ የመጠቀም ባሕል</u>

በአይነ ሥጋ የማይታዩ በእደ ሥጋ የማይዳሰሱ ነገሮች ለኅሊና በሚረዱና ሊታዩ በሚችሉ ሥዕላዊ አገላለጦች ጎልተው የሚቀርቡበት ወቅት አለ። ለምሳሌ፦ ቅዱስ ዳዊት ‹‹እግዚአብሔር አለቴ አምባዬ መድኃኒቴ አምላኬ በእርም የምታመንበት ረዳቴ መታመኛዬና የድህነቴ ቀንድ መጠጊያዬ ነው›› (መዝ **!7÷2)** ቅዱስ ዳዊት እግዚአብሔርን አለት ብሎታል በአለት ላይ ቤቱን የሰራ ሰው ጎርፍ ቢመጣ አውሎ

ንፋስም ቢመጣ ምንም አይነት መከራ እና ፈተና ቢፍራረቅበት አይወድቅም ማለት ነው።አምባ ማለቱ ራሱን የቻለ መግለጫ አለው አምባ ማለት መሸሸጊያ ማለት ነው። እግዚአብሔር ቢሸሸጉበት /ቢታመኑበት/ አሳልፎ የማይሰጥ መጠጊያ ነው ማለቱ ነው። የድኅነቱ ቀንድ ብሎታል እንስሳት በቀንዳቸው ይዋጉበታል ጠላታቸውን ይረቱበታል ለእኔ ጠላቴን የማሸንፍበት መዋጊያ መሳሪያዬ አንተ ብቻ ነህ ሲል ነው።

4) <u>የአቆጣጠር ባሕል</u>

መጽሐፍ ቅዱስ ለመቁጠር የዘር ሐረግ ሊኖር ይችላል ወይም የጉባኤ ብዛት ለመቁጠር መጽሐፍ ቅዱስ የራሱ የሆነ አቆጣጠር መለኪያ አለው። መጽሐፍ ቅዱስ የአንድ ሰውን የዘር ሐረግ ሲቆጥር ሰውየው ከተወለደበት ቤት ከወላጆቹ ከእናቱና ከአባቱ የዘር ሐረጉን አይጀምርም በዚህ ፈንታ ትውልድ ሐረጉን ከነገዱ ከአያቶቹ ተነስቶ ወደ አባት በስተመጨረሻም ወደ ሰውዬው ይመጣል።

<u>ለምሳሌ</u>፦ ‹‹ከይሁዳ ነገድ የሆነ የከርማ ልጅ የዘንባረ ልጅ የዛራ ልጅ አካን ተለየ›› /2ኛ ነገ ፲፭-፩/ ‹‹ወደ ሕዝቅያስ ልጅ ወደ አማርያ ልጅ ወደ ጎዶልያስ ልጅ ወደ ኩሲ ልጅ ወደ ሶፎንያስ የመጣ የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው...›› ት/ሶፎ ፩-፩ ወዘተ መዘርዘር ይቻላል።

ሌላው የአቆጣጠር ባሕል በኩል የዘመኑን፣የወሩን፣ቁጥርና ስም ከመግለፅ ባሻገር በዘመኑ በነበረው ንጉስ ዓመተ ንግስናና በየወሩ ቁጥር አንባር መቁጠር ደግሞ ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ታዋቂ ባሕል ነው። <u>ለምሳሌ</u>፦ ‹‹ንጉሥም ኢዮርብዓም በነገሰ በአሰራ ስምንተኛው አመት አብያ በይሁዳ ላይ ንጉሥ ሆነ›› 2 ዜና ፲፫-፩ ሲል እንደ ገለጸው።

ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ የቆጣጠር ባሕል ደግሞ በዘር ሐረግ ውስጥ ከአህዛብ ወደ እስራኤላውያን ከመጡት ከእነ ትእማር፣ሩት፣ራኬብ በስተቀር ሌሎቹን እነ ሳራ፣ርብቃ የመሳሰሉትን አልጠቀሰም ይህ የሆነው መጽሐፉ የተጻፈው በእብራውያን ባሕል ነው። እብራውያን ሐረግ የሚቆጥሩት በወንድ ሐረግ የሆነ እንደሆነ ነው። የብሉይን ኪዳን ስንመለከት በአባቱ ከነገደ ሌዊ ከሆነ ሥልጣነ ክህነት ወይም ከነገደ ይሁዳ ከሆነ በትረ መንግሥት ስለሆነ ንግሥናን ያገኛሉ። ሴቶችን ግን ከዘር ሐረጉ አላስገባም ምክንያቱም የአይሁዳውያን ባሕል ስለሆነ...

5) <u>አንድን ነገር አጉልቶ የማቅረብ ባሕል</u>

የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ የእግዚአብሔርን ድንቅ ድንቅ የሆኑትን ስራዎች መመስከር ፈቃዱን ትእዛዙን መናገር ፈቃደ እግዚአብሔርን በተለያዩ መንገዶች ልዑል እግዚአብሔር የሰራቸውን ሥራዎች በየዘመኑ ለሚነሳው ትውልድ መግለጥ ማስረዳት ነው። ይህንኑ ለመግለጥ ለማስረዳት ለመናገር መጽሐፍ ቅዱስ ከሚጠቀምባቸው የተለያዩ ድርጊቶች አንዱ አጉልቶ ማቅረብ ነው። አጉልቶ ማቅረብ ስንል አንድን ነገር አግዝፎ አጉልቶ ከፍ አድርጎ አብዝቶ መናገር ማለት ነው።

ለምሳሌ ‹‹ያቺ ልጅ እግሯ በርሜል ያህላል›› ቢል አሁን ያቺ ልጅ እግሯ ከበርሜል እኩል ሆኖ ሳይሆን የእግሯን ግዙፍነት ለመናገር የተጠቀመበት መንገድ ነው ይህም ዘይቤ አጉልቶ የማቅረብ ዘይቤ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እንደዚሁ አጉልቶ የማቅረብ ባህል አለው። እስኪ ጥቂት እንመልከት

<u>ለምሳሌ</u>፦ ‹‹ሺህ ጊዜ ሺህ ያገለግሉት ነበር። እልፍ አእላፋትም በፊቱ ቆመው ነበር›› ዳን ፯-፲ ብሎ ነብዩ ዳንኤል በዚህ ክፍል አጉልቶ የተናገረው ቅዱሳን መላእክትን በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ስለሚያገለግሉት ፍፁም አገልግሎት የቅዱሳን መላእክትን ብዛት ገልጧል። ‹‹ሺህ ጊዜ ሺህ ያገለግሉት ነበር›› ሲል መላእክት ቆመው የሚያገለግሉት የተወሰኑ ሆኖ ሺህ ጊዜ ሺህ ብቻ ያገለግላሉ ማለት አይደለም።ነገር ግን የመላእክቱን ፍፁም አገልግሎት አጉልቶ ለማሳየት የተነገረ ቃል ነው። ‹‹እልፍ አእላፍ በፊቱ ቆመው ነበር›› ሲልም እግዚአብሔር ፊት ቆመው የሚያገለግሉት መላእክት ብዛታቸው ለክተን ሰፍረን ቆጥረን የምናቃቸው ሆነው ሳይሆን ብዛታቸውን አጉልቶ ለማቅረብ የተጠቀመበት ዘይቤ ነው እንጂ የመላእክት ብዛት አይታወቅም።

‹‹ባለጸጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢገባ ይቀላል›› ይህን አባባል የተናገረው ክብር ይግባውና መድኃኒዓለም ክርስቶስ ነው። ታድያ ይህ አባባል አጉልቶ የማቅረብ ዘይቤ ነው። ለንፋግ ባለጠጋ የእግዚአብሔርን መንግስት መውረስ ጭንቀትና ጥበት እንዳለበት አጉልቶ ለማቅረብ የተነገረ ቃል ነው።

‹‹እንስሳቶቻቸውንና ድንኳኖቻቸውን ይዘው በብዛት እንደ አንበጣ ሆነው ነበር›› አሁን በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ‹‹እንደ አንበጣ ሆነው...›› የሚለው ቃል በየጊዜው ወደ እስራኤል ምድር ይመጡ የነበሩትን የአሞራውያንንና የአሜሌቃውያንን ብዛት የሚመጡትም ለጥፋት መሆኑን አጉልቶ ለማሳየት የገባ ነው። አንበጣ የሚሔደው በመንጋ ነው ሲጓዝ ሳር ቅጠሉን ይበላል ያደርቃል ልክ እንደዚህ

አሞራውያንና አሜሌቃውያን ወደ እስራኤል በየጊዜው ሲገቡ ቁጥራቸው አይለካም ነበር። ልክ እንደ አንበጣዎቹ በመንጋ ሲሄዱ ቁጥራቸው እንደማይታወቅ። አሞራውያንና አሜሌቃውያን ሲገቡም የእስራኤላውያንን ሀብት ያወድሙ ያቃጥሉ ነበር። ታድያ የነዚህን የአሞራውያንና የአሜሌቃውያንን የጥፋት ሴራ አጉልቶ ለመናገር የተጠቀመው ቃል ነው። እንጂ ስለ እንስሳ ለመናገር ፈልጎ አይደለም። እግዚአብሔር እስከ ሰማንያ ስድስት አመቱ ድረስ ልጅ ሳይወልድ ለኖረው ለአብርሃም ‹‹ዘርህን እንደምድር አሸዋ አበዛዋለሁ›› (ዘፍ **!3÷!6)** ብሎታል። በዚህ ኃይለቃል ውስጥ ‹‹እንደምድር አሸዋ ›› የሚለው ሀረግ ግዜት ነው።በዚህ አባባል የአብርሃም ልጆችና የምድር አሸዋ ቢቆተሩ ይስተካከልሉ ለማለት ሳይሆን የምድር አሸዋ ከብዛቱ የተነሳ ለመቁጠር እንደሚዳግት ላንተም ምንም እንካ D” e"G<” dƒ¨MÉ wƒqÃU Ÿ²=I u ‹ L Ó” ÏÓ u×U w²< ¾MÏ MÏ Ã•`HM ¾Uƒ¨ል Ç†¨< M ‚› Ãu³K< TK~ ’¨<:: ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ‹‹እኔ ግን ትል ነኝ ሰውም አይደለሁም›› (**S´ @1÷6)** ሲል ተናግ bM :: ›vvK<” ”ÅU“¾¨< pÆe Ç©ƒ #ƒM ’˜$ TK~ ƒM aÙ ¾TÁSMØ ደካማ õØ[ƒ ’¨<:: ’@U ÁK ›”} ÁK ›ULŸ? ደካማ ’˜ TK~ ”Í= cw“ ¾K˜U KTKƒ ›ÃÅKU:: ”Ç=G< uT቎ 3÷1 ጀምሮ ***#“”} ¾ñ˜ƒ MÐ‹$*** የሚል ቃል እናገኛለን። ይህን የተናገረው መትምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ነው።ለፊሪሳውያን እናንተ የእፉኝት ልጆች ሲል የተናገረው ነው። እዚህ ጋር እፉኝት ለግሉት የገባች ናት። እፉኝት ስትወንድ እናተ E”U አባተ E ንም ትገላለች ። ለዚህ እናንተ እንደ እናት የሚሆኑ ነቢያትን እንደ አባት ሚሆኑ ሐዋርያትን የምትገሉ ሲላቸው ነው። እንጂ እናንተ ከእፉኝት የተወለዳችሁ ናችሁ ማለቱ አይደለም።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ አባባል</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ነገሮችን የሚገልጽበት የራሱ የሆነ አባባል አለው። ታድያ እነዚህ አባባሎች የራሳቸው የሆነ አገባብና አተረጓጎም ያላቸው። በመሆናቸው በአንድ ጎብረተሰብ ዘንድ በተለመደው የቋንቋ ሥርዐት አንፃር ብቻ ሊወሰድ አይገባቸውም አባባሎቹን በእለታዊ ሕይወታችን መግባቢያነት አንፃር ብቻ ከተረጎምናቸው ምሥጢሩን ለማለት የተፈለገውን መልእክት በቀላሉ መረዳት ስለማንችል ለውድቀት ይዳርጉናል። በመሆኑም ይህ ምድራዊ የመግባባት ሥርዓት አንጻር የተነገረው አባባል መንፈሳዊ ምሥጢሩ ምን እንደሆነ በጾም በጸሎት እየተጉ ከመምህራን መማር ተገቢ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በጥበበ በእግዚአብሔር የተጻፈ መጽሐፍ ነው። እንደውም አባቶቻችን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገሩ **<<**የእግዚአብሔር ጥበብ በሰው ቋንቋ**>>** ይላሉ። ይህም ማለት ረቂቅና ድንቅ በእኛ በፋጡራኑ ተነግሮ የማያልቅ ከ.. እስከ የማንልለትን ጥበብ በሚገባንና በቀላሉ በምንረዳው ቋንቋ የተገለጸልን የእግዚአብሔርን እቅድና ሐሳቡን የተረዳንበት መጽሐፍ መሆኑን ይገልጻሉ። ታድያ ይህ ቅዱስ መጽሐፍ ነገሮቹን የሚገልጽበት የራሱ የአባባል ሁኔታ አለው። ይህን አባባሉን ካልተረዳን ቅድም እንደገለጽነው ውድቀታችን መጥፎ ነው። የሚሆነው ግን ስናነብ ይህን አባባሉን አስፍተው አምልተው አመስጥረው ለእኛ ግልጽ እንዲሆንልን አድርገው የሚያስተምሩ የሚያስረዱ መምህራንን በመጠየቅ እውነተኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ አባባል መረዳት ይኖርብናል ማለት ነው። እንደውም ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ባሶስ ለዚህ ምሳሌ መሆን ይችላል:: ይህ ጃንደረባ በሰረገላ ላይ ሆኖ የእግዚአብሔር መንፈስ ያረፈበትን የነቢየ ልዑል የኢሳይያስን የትንቢት መጽሐፍ ሲያነብ ወንጌላዊው ፊሊጶስ የምታነበውን መጽሐፍ ታውቀዋለህ አለው። አሁን ጃንደረባው ባኮስ የኢሳይያስን የትንቢት መጽሐፍ ቢያነብም ግን የመጽሐፉን አባባል የአገላለፁን መንገድ ምሥጢሩን ግን መረዳት አልቻለም። ታሪኩ ስለ ሳበው ብቻ ያነብ ነበር ከዚህ በኋላ ነው ፊሊጶስ የመጽሐፉን ምሥጢር አመስጥሮ ለጃንደረባው ያስተማረው ከዚህ በኋላ ጃንደረባው ምሥጢሩን ሲረዳ አምኖ የተጠመቀው። ለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስን አባባሉን በመረዳት ልናነብ ይገባል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ **<< ...** ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን**>>** እንዳለው። */1* ቆሮ *2ˆ7/* ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል እንዲህ ከተነጋገርን ከዚህ ቀጥለን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስፋት ከሚታወቁት አባባሎች የተወሰኑትን ወስደን ትርጉማቸውን ጭምር እናያለን።

<u>አርቆ መናገር</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጎልተው ከሚታወቁ አባባሎች መካከል አንዱ አርቆ መናገር ነው። ይህም አንደኛ መደብን እንደ ሁለተኛ መደብ፣ሁለተኛ መደብን እንደ ሦስተኛ መደብ አድርጎ መናገርን የሚያመለክት ነው።አርቆ መናገር ትሕትናን ለመግለጥ ያገለግላል። የሚከተሉት ምሳሌዎች የዚህን እውነታ ያስረዱናል።

ሀ. <u>ራስን አርቆ መናገር</u>

ራስን አርቆ መናገር በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተለመደ አነጋገር ነው። ከባለሥልጣን ጋር ከቅዱሳን መላእክትና ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገሩ ከትሕትና የተነሳ ራስን ማራቅ የተለመደ አነጋገር ነው።

↳ ኢ.ያ.ፏ-ፗ፱፥- ‹‹ጌታዬ ለባርያው የሚነግረው ምንድን ነው;››

ኢ.ያሱ ‹‹ጌታዬ ለባርያህ የምትነግረኝ ምንድን ነው;›› ማለት ሲችል ራሱን አርቆ ‹‹ባርያው›› አለ።

↳ መዝ.ፗ፱-፱፥- ‹‹አቤቱ ንጉሥን አድነው››

ተናጋሪው ቅዱስ ዳዊት ነው። የተናገረውም እግዚአብሔር ከመከራው ሁሉ እንዲያድነው በጸለየበት ወቅት ነበር። ቅዱስ ዳዊት እንደ አግባቡ ‹‹አቤቱ እኔን ንጉሥ አድርገህ የቀባኸኝ አድነኝ›› ብሎ ከመጸለይ ይልቅ ራሱን አርቆ ‹‹ንጉሥን አድነው›› አለ።

↳ ማቴ.ፗ፯-ፗ፫፤ፗ፯—፳፭-፳፪፤፳—ፗ፰-ፗ፱፤ማቴ.፳፭-፴፭፤ሉቃ.ፗ፰-፰።

በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የምናገኛቸው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት ነው። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከላይ በተጠቀሱት ቁጥሮችና በሌሎችም ክፍሎች ይናገር የነበረው ራሱን አርቆ ነው።

- ‹‹የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል;››
- ‹‹የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጥ ዘንድ አለው››
- ‹‹የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ...››
- ‹‹የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነት ያገኝ ይሆንን;››...ወዘተ የሚከተሉት ጌታችን ራሱን አርቆ ያስተማረባቸው ንግግሮች ናቸው።

ለ. ሌላውን አርቆ መናገር

ሁለተኛ መብን በተለይም አድማጭን አርቆ መናገር በቅዱሳት መጻሕፍት የተለመደ አባባል ነው።

- ዘፍ.፲፰-፴ ‹‹ጌታዬ አይቆጣ›› ተናጋሪው አብርሃም ነው። እያነጋገረው ያለው ደግሞ እግዚአብሔር ነው። አብርሃም የተገለጠለትና እያነጋገረው ያለውን እግዚአብሔርን ‹‹ጌታዬ አትቆጣ›› በማለት ፈንታ በትሕትና ቀርቦ ‹‹ጌታዬ አይቆጣ›› ብሎታ። ይህ ንግግሩ አድማጩን በሦስተኛ መደብ አንባር አርቆታል።
- በቀዳማዊ ሳሙኤል በ፳፬-፳ ላይ ‹‹የእስራኤል ንጉሥ ማንን ለማሳደድ መጥቷል;›› ተብሎ የተጻፈውም ‹‹ማንን ለማሳደድ መጥቷል;›› ተብሎ ማቅረቡን እንመለከታለን። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ አርቆ መናገርን አባባል ገንዘብ አድርጎ የተጻፈ መሆኑን ያመለክተናል።

➢ ሰውኛ ዘይቤ መጠቀም

ሰውኛ ማለት፡- ሰው ላልሆነ ነገር ለግዑዝ፣ለማይናገር፣በድን ለሆነ ነገር የሰውን ጠባይ መስጠት ነው። እነዚህ ግዑዛን በድን የሆኑትን ነገር ልክ ሰውን በሚያናግሩት ዓይነት ማነጋገር፣መጥራት ማለት ነው ይህ ዓይነት ዘይቤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም አለ። በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ በሰው አንቀፅ ለምድር ፣ለሰማይ...ወዘተ የሰውን ፀባይ ሰጥቶ በሰውኛ ዘይቤ ተጽፎ እናገኛለን። እስኪ ጥቂቱን እንመልከት ለምሳሌ፡- ‹‹ሰማያት ሆይ አድምጡ እኔም እናገራለሁ ምድርም የአፌን ቃላት ትስማ›› ዘዳ ፴፪-፩ ብሎ ሰማያት ሆይ አድምጡ እያለ እንደ ሰው ምድርም የአፌን ቃል ትስማ እያለ እንደ ሰው ተናግሯል። ይህ ታድያ ሰማይና ምድርን በሰውኛ ዘይቤ የተጻፈ ነው እንጂ ሰማይና ምድር የሚናገሩ ወይም ሰዎች ሆነው አይደለም።

- ‹‹ኢየሩሳሌም ሆይ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ ባላስብሽም ምላሴ ከጕሮሮዬ ይጣበቅ›› መዝ ፻፴፯-፭ እዚህ ጋርም ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ሀገሩን ኢየሩሳሌምን እንደማይተው ተናገረ እንጂ ኢየሩሳሌም ሰው ሆና የተነገረላት አይደለችም። ኢየሩሳሌም ሆይ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ ሲልም ሰውኛ መሆኑን እንረዳለን።
- ‹‹አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ ምድር ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሺም›› ማቴ ፪-፮ ከቀረቡት ምሳሌዎች እንደምንረዳው የተጠሩት በሙሉ ግዑዛን በድን የሆኑ የመሬት አካላትና ሰማያት ናቸው። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ አባባል መሠረት በሰውኛ አቀራረብ ‹‹አንቺ ኢየሩሳሌም...›› ተብለዋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ፈርጀ ብዙ ቃላት

ፈርጀ ብዙ ቃላት፡- ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ እንደየ አገባባቸው የሚያስተላልፉት መልእክት የሚለያዩ ቃላቶች ናቸው። ታድያ ይህንን መሰል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ቦታ አለ። ለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ እንደየአገባባቸው የሚለያዩትን ፈርጀ ብዙ ቃላትን ለይተን በማወቅ መሆን አለበት። አለበዚያ ብዙ ዘርፍ ያለው ቃል በሁሉም አገባቡ በአንድ አይነት መንገድ መልእክቱን እየተረዳነው ከሄድን ለእኛ የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛውን መልዕክት ለመረዳት ያስቸግረናል ለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ እነዚህን ፈርጀ ብዙቃላትን ለይተን በማወቅ መሆን አለበት እስኪ ጥቂቶቹን ለምሳሌ እንመልከት

1- ፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

እንግዲህ እንደሚታወቀው በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ <<ፊት>> የሚለው ቃል ከሌሎች ቃል ጋር ተጣምሮ ተጽፎ እናገኘዋለን ታድያ ይህ ፊት የሚለው ቃል እንደየአገባቡ ፍቺው ይለያያል መጽሐፍ ቅዱስ ፊት የሚለውን ለተለያየ ነገር ይጠቀምበታል በዛው ልክም ስንተረጉመውም የተለያየ ትርጉም ይይዛል እስኪ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደ ምሳሌ እንመልከት።

ሀ/ በእግዚአብሔር ፊት ቆመ ዘፍ /ዘፍ 18፡22/

አሁን እዚህ ጋር የምናስተውለው እግዚአብሔር አካላዊ መንፈስ ነው። ይሁን እንጂ እንደ አንድ ግዙፍ ፍጥረት ተወስኖ የሚለካ የሚገደብ ጀርባው በዚህ ፊቱ በዚያ ነው የሚባል አይደለም። እግዚአብሔር <<ምሉዕ በኩሌሄ>> በሁሉ የሞላ አምላክ ነው። አባ

ሕርያቆስ በቅዳሴው <<ላይና ታች ግራና ቀኝ ያለው አይደለም:: በሁሉ የመላ ነው አንጂ>> እንዳለው። ታድያ በእግዚአብሔር ፊት ቆመ የሚሉትን ቃላቶች ምንን ያመለክታሉ? ከላይ የጠቀስናቸውን ጥቅሶች ተራ በተራ እንያቸው ::

መዝ **105፡23** <<እንዳያጠፋቸው ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠ ሙሴ በመቅሰፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ የተናገረ...>> ብሏል ልበ አምላክ ክቡር ዳዊት እዚህ ጋር እስራኤላውያን ከባርነት በሙሴ አማካኝነት እግዚአብሔር አውጥቷቸው የኤርትራን ባሕር ከፍሎ አሻግሯቸው በምድረ በዳ ከሰማይ መና እየመገበ ከዓለት ላይ ውሃ አፍልቆ እያጠጣቸው ከተዝዙ በኋላ እስራኤላውያን ይህን ሁሉ ውለታ የዋለላቸውን አምላክ ረስተው ለጣዖት ይሰግዱ ነበር። በዚህ ጊዜ ነው እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው እንደሆነ ለሙሴ ነገረው በእውኑ የሕዝቡን ጥፋት ማየትም መስማትም የማይወድ ሙሴ ጸለየ እግዚአብሔርን ተማፀነ <<ሕዝብህን ከምታጠፋ እኔን ከሕይወት መጽሐፍ አጥፋኝ>> እያለ ለመነ <<በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ራራ>> ዘጸ **32፡1-35** ይህን ነው ዳዊት <<...በፊቱ ባይቆም ኖሮ...>> ያለው በፊቱ ያለው የሙሴን ምልጃ ስለሕዝቡ በእግዚአብሔር ፊት መማለድ ለመግለጽ የተጠቀመበት ቃል ነው:: እንደዚሁ በሉቃ 1፡19 <<እነ ውእቱ ገብርኤል ወእቀውም ቅድመ እግዚአብሔር>> ብሎ ቅዱስ ገብርኤል ለካህኑ ዘካርያስ ነግሮታል ታድያ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ሲል ሎሌ በጌታው ፊት እንደሚቆመው አይደለም። ይህን ሲል ግን የእግዚአብሔር ባለሟል መሆኑን ሲገልጽለት ነው:: ዘካርያስ ይህን ብስራት ሲሰማ ተጠራጥሮ ስለነበር። የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን ባለሟልነቱን ለመግለጽ የተናገረው መሆኑን እንረዳለን።

ዘፍ **18፡52** <<አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር>> ይላል:: ይህም የአብርሃምን ስለሰዶምና ጎመራ መማለድ ለመግለጽ የተናገረው ቃል መሆኑንም እንገነዘባለን።

ለ/ <<ፊቴን አሰውርባቸዋለሁ>> ዘዳ **32፡20**

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ደግም የምንረዳው። እስራኤል የነበራቸው አንድ ጠባይ ነበረ። እሱም በመከራቸው በስቃያቸው ጊዜ እግዚአብሔርን ሲያስታውሱ በደስታና የሚፈልጉትን ሲያገኙ እግዚአብሔርን ይረሱና ጣዖት ያመልኩ ነበር። በዚህ ውስጥም ከኃጢአታቸው የተነሣ እግዚአብሔር ልመናቸውን አለመቀበሉን ቸርነትና ረድኤቱን ከላያቸው ላይ ማራቁን ለመግለጽ የተጠቀመበት ቃል ነው ነብየ ልዑል ኢሳይያስ በትንቢት መጽሐፉ ላይ <<እጃችሁን ወደ እኔ ብትዘረጉ ዓይኔን ከእናንተ እሰውራለሁ ልመናንም ብታደርጉ አልሰማም እጆቻችሁ በደም ተመልተዋልና>> ኢሳ **1፡15** ብሎ ነቢዩ እንደተናገረው::

ሐ/ <<ፊቴን አታይም>> ዘጸ **33፡19-23**

ሊቀ ነብያቱ ሙሴ እግዚአብሔርን ከ **570** በላይ አነጋግሯል እንደ ሙሴ እግዚአብሔርን ያናገረ የለም:: ግን ከእለታት በአንደኛው ቀን ሙሴ እግዚአብሔርን <<ፊትህን አሳየኝ አለው>> እግዚአብሔርም ፊቴን ማየት አይቻልህም ጀርባዬን ታያለህ ፊቴን ግን አታይም አለው። ሙሴ የእግዚአብሔርን ፊት ለማየት የወደደው እንደሰው ፊት በቀላሉ የሚታይ መስሎት ነው:: ይህንን የሙሴን አለማወቅ የሚያውቅ እግዚአብሔር <<ፊቴን አታይም>> አለው ፊቴን ማለቱ መለኮቱን ይገልጽልናል ፊቴን ማየት አይቻልህም ሲል መለኮትን ማየት እንደማይቻል ሲነግረው ነው። ግን ጀርባዬን ታያለህ አለው ይህም በኋላ ዓለምን ለማዳን የሠውን ሥጋ ለብሼ ተገልጬ ታየኛለህ ሲል ነው። በዚህ ውስጥ ‹‹ፊት›› የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን መለኮት ነው።

መ/ <<የእግዚአብሔር ፊት ክፉን በሚያደርጉ ላይ ነው>> መዝ **33፡16**

በዚህ ክፍል ደግሞ ፊት የሚለው ቁጣን ፍርድን መዓትን ይገልጽልናል። የእግዚአብሔር ፊት ወደ ሁሉም አቅጣጫ ምሉዕ በኩሉ እንደ ሆነ ይታወቃል። ግን ነቢዩ በዚህ ክፍል <<ገጹ ለእግዚአብሔር ይገብሩ እኩየ>> በማለት ዘምሯል። አሁን በዚህ የነቢዩ አባባል ውስጥ ፊት እያለ የእግዚአብሔርን ፍርዱን ቁጣውን እየነገረን ነው።ለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ እንደዚህ እንደአገባባቸው የተለያዩ ትርጉም የሚሠጡ ፈርጀ ብዙ ቃላት ስላሉ በማስተዋል በመጠየቅ በመረዳት ልናነብ ይገባል።

2-እጮኛ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ እጮኛ የሚለው ቃል በተለያዩ ቦታዎች ላይ እናገኝዋለን። ግን እንደየ አገባቡ የጸሐፊው ወይም የተጻፈላቸው ሰዎች የአረዳድ ዘይቤ መሰረት የተለያዩ ትርጉሞች ሲኖሩት እናስተውላለን እስኪ ለምሳሌ ያህል ጥቂቱን እንመልከት።

ሀ/ እጮኛ ጠባቂ ረዳት ተንከባካቢን ያመለክታል

አሁን በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ሉቃስና ማቴዎስ ዮሴፍ የእመቤታችን እጮኛ ብለው ጠቅሰዋል። ሉቃ 1÷27 ማቴ 124 ታድያ ግን እጮኛ የሚለው የእመቤታችን ጠባቂ ረዳት መሆኑን ለመግለጽ የገባ ቃል ነው። ምክንያቱም እመቤታችን ረቅቂና ድንቅ በሆነ ጥበቡ በድንግልና ጸንሳለችና። በብሉይ ኪዳን በሙሴ መጽሐፍ ላይ ያለ ወንድ የጸነሰች ሴት እንድትገደል የሚያዝ ሕግ ነበርና በድንጋይ ወግሮ እንዳይገድሏት ለመጠበቅ ጌታን ከወለደች በኋላ ወደ ግብጽ በተሰደደች ጊዜ በስደት ወራቷ እየተላላከ ያግዛት እንደነበር ለመግለጽ የገባ ቃል ነው። ዘዳ 22÷21

ለ/ <u>እጮኛ ሌላው የተመረጠ የተለየን ያመለክታል</u>

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ደግሞ እጮኛ የሚለው መመረጥን መለየትን ያመለክተናል ይህም ደግሞ ልዑለ ባህርይ ቅዱስ እግዚአብሔር በዘመን ብሎይ እስራኤል ዘሥጋን ከሌሎች ሕብረተሠቦች /ወገኖች/ ለይቶ የመረጣቸው መሆኑን ነብዩ ሆሴዕ እንዲህ እያለ ይገልጻዋል ‹‹ለዘለአለም የእኔ እንድትሆኚ በመተማመን አጭሻለሁ በፍርድ በምህረትና በርኅራሔ አጭሻለሁ ለእኔ እንድትሆኚ በመተማመን አጭሻለሁ›› ት/ሆሴዕ **2፡20** መዓቶተ ቤተክርስቲያን ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለቆርቶስ ምዕመናን እንዲህ ሲልም ልኳል ‹‹ንፅሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁ›› **2** ቆሮ **11 ፡2**። ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጸው አጭቻችኋለሁ በማለት ምዕመናን ሕዝበ ክርስቲያን ለሰማያዊ ሙሽራ ለመድኃኒ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በሃይማኖት በምግባር የተለዩ የተመረጡ መሆናቸውን ለመግለጽ ሐዋርያው የተጠቀመው ቃል መሆኑን እንረዳለን።

ሐ/ <u>በእግዚአብሔር ፈቃድ ለጋብቻ የተፈቃቀዱትን እጮች ይላቸዋል</u>

እዚህ ላይም ለትዳር የተፈቃቀዱትን መጽሐፉ እጮኛ ይላቸዋል። ግን እጮኛ ስንል አንድ ወንድ ሊያገባት የፈለጋትን ሲት ቤተሰብ ሔዶ ጠይቆ እንዲያገባት ከተፈቀደለት ሰዓት ጀምሮ እስከ ሚያገባት ድረስ እጮኛዎች ይባባላሉ። ግን በዚህ ዘመናቸው በፈቃደ ሥጋ ግን አይተዋወቁም ለምን በሥርዐተ ተክሊል በቅዱስ ቁርባን አንድ ስላልሆኑ ያዕቆብ ወደ አጎቱ ቤት ላባ ጋር ከሔደ በኃላ ራሔል እንዲያገባ ተፈቅዶለት ግን ሰባት ዓመት እንዲያገለግል ተብሏል። ከሰባት ዓመት በኃላ አገባ ከተፈቀደለት እስኪያገባ ድረስ ያለው ጊዜ የእጮኝነት ዘመን እንደሆነው መጽሐፍ ይናገራል ‹‹ያዕቆብም ስለ ራሔል ሰባት ዓመት ተገዛ እርስዋም ይወዳት ስለነበር በእርሱ ዘንድ እንደጥቂት ቀን ሆነለት›› ዘፍ **29፡20** ተብሎ እንደ ተጻፈው። በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ እጮኛ የሚለው ቃል እንደየ አገባቡ ትርጉሙም ይለያያል ስለዚህ ስናገባ እያስተዋልን ፈርጀ ብዙ ቃላትን እንደየአገባባቸው ያላቸውን ትርጉም እየተረዳን መሆን አለበት።

ምዕራፍ አምስት
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መልክዐ ምድሮች

በዚህ ክፍል ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ መልክዐ ከተሞች መንደሮችን ተራሮችን ሸለቆዎችን ወንዞችን ባሕሮችን ወዘተ የመሳሰሉትን የምንመለከት ይሆናል። እነዚህ ሁሉ ግን በራሳቸው የራሳቸው የሆነ ምሳሌና ምስጢር ይዘዋል በመጽሐፍ ቅዱስ ባሕል ላይ እንደተመለከትነው ዕብራውያን ለቦታ የሚሰጡት ስያሜ ላይ ለቦታዎች ስያሜ ሲሰጡ ታሪካዊ ክስተትን ለማሰብ ለመዘከር ሲሉ ስያሜ ያወጡ እንደ ነበር ተመልክተናል። በዚሁ ክፍላችንም ልክ እንዲህ ያሉ ቦታዎችንና ከቃል ኪዳኗ ሀገር ከከነዓን ውጪ ያሉትን ሀገራቶች ሁሉ በማንሳት እንመለከታለን። በተጨማሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ባሕሮች ሸለቆዎች ዕፅዋትን እንስሳትን የመሳሰሉትንም በቅደም ተከተላቸው እንመለከታለን ማለት ነው። ሌላው መጽሐፍ ቅዱስ በቀድሞ ስማቸው የሚጠራቸው ሀገራቶችም ሌሎችንም እንደዚሁ በየትኛው ቦታ እንደምትገኝ መጽሐፍ ቅዱሱ የሚያቃት በየትኛው ሰያሜ እንደሆነ በስፋት ዳሰን እንመለከታለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን መንደሮችና ከተሞች በጥቂቱ ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን።

<u>በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ከተሞችና መንደሮች</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቂት ሕዝብ ከሚኖርባቸው መንደሮች ጀምሮ ብዙ ሺህ ሕዝብ እስከሚኖርባቸው ከተሞች ያሉት ተጠቅሰዋል። እንያንዳንዱ መንደርና ከተማ የራሱ የሆነ የአመሠራረት ታሪክ አለው። ይህንን ከዚህ ቀጥለን ከፋፍለን እስከነ የአመሰራረት ታሪካቸው ጋር እንመለከታለን።

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ከተማዎች

ከተማ ማለት ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦው የሚኖሩበት ቦታ ማለት ነው። በዓለማችን ላይ ለመጀመሪያ የተሰራችው ከተማ <u>ሄኖሕ</u> ትባላለች። ይህችም የተመሠረተችው በአዳም ልጅ በቃየን ነው። ስያሜዋን የሰጣት ግን በበኩር ልጁ በሄኖሕ ስም ነው። ከዚህ በኋላ ሰዎች የወኃ ምሽግ ባለበት ቦታ በመሰብሰብ ከተማን መቀርቀር ጀመሩ። እስራኤላውያን በከተሞቻቸው ዙሪያ ግንብን ይገነቡ ነበር። የግንቡ ስፋት **3** ሜትር ቁመቱ **10** ሜትር ያህል ነበር። ታላላቅ ከተሞች ላይ ደግሞ ሲገነቡ ስፋቱን **10** ሜትር ቁመቱ እስከ **20** ሜትር አድርገው ይገነቡ ነበር። በቅጥሩ ውስጥ የከተማው ስፋት ሁለት ሄክታር ያህል እንዲሆን ተደርጎ ይሠራል። የምሽግ በር አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሲሆን በቅጥሩ ውስጥ ዋናው ግንብ ወይም ምሽግ ላይ የመስገጃ ቦታ ይሠሩ ነበር። እንዲህ እየተደረገ በእስራኤልም ከእስራኤል ውጪ የሆኑ ከተሞች እየተቀረቀሩ መስፋፋት ጀምረዋል። ከዚህ ቀጥለን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን ከተሞች ከፍለን ጥቂቶቹን ለአብነት እንመለከታለን ማለት ነው።

1- የሜሶፖታሚያ ከተሞች

2- የፊንቄ ከተሞች

3- የግሪክ ከተሞች

4- የፍልስጥኤም ከተሞች

5-የፋርስ ከተሞች

6- የሮም ከተሞች ናቸው። በእነዚህ ሀገሮች ውስጥ የሚገኙትን ከተሞች ደግሞ በጥቂት በጥቂቱ እየከፋፈልን እንመልከት

1- የሜሶፖታሚያ ከተሞች

በዚህ ሀገር ሥር የምናገኛቸው ከተሞች ባቢሎን ነነዌ ዑር ካራን ወዘተ ናቸው ሜሶፖታሚያ በግሪክ ሜሶፖታምያ ማለት በሁለት ወንዞች መሐል የሚገኝ መሬት ማለት ነው። ይህም በኤፍራጠስና በጤግሮስ ወንዞች መካከል የሚገኝ ሀገር ስለሆነ ነው። በአሁኑ ጊዜ ምስራቅ ሶርያንና ስሜን ኢራቅን የሚካትት ሀገር ነው /ዘፍ **24-1** /ይህች አገር በብሉይ ኪዳን ቀዳማዊ የጥንት ሥፍራዎች ከሚባሉት ውስጥ አንዷ ናት። ጥንታዊ ሥልጣኔ ከተጀመረባቸው ቦታዎችም አንዱ ይህም ሥልጣኔን መሬትን በማለምለምና የውኃ ምንጭ የሚገኝበት ቦታ በመሆኗ ነው። ሆኖም ስለሜሶፖታምያ ብዙ ማለት ቢቻልም እኛ ግን እዚህ ጋር ይብቃንና ከተሞችን እንመልከት።

1.1 <u>ባቢሎን (ኢራቅ)</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባቢሎን እያለ የሚጠራት የአሁኗን ኢራቅን ነው። በእብራይስጥ ባብኤል ይሉታል። ትርጉሙም ‹‹የእግዚአብሔር በር›› ማለት ነው። ይቺህ የባቢሎን ከተማ በኤፍራጠስ ወንዝ አጠገብ የምትገኝ ናት። በአሁኗ ባግዳድ ከተማ በስተ ደቡብ የምትገኝ ከተማ ናት። የመልክዐ ምድሯ አቀማመጥ ለሥልጣኔዋ እጅግ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጎላታል ከከተማዋ አጠገብ የሚገኘው የኤፍራጠስ ወንዝ ለመጓጓዣነት ይጠቀሙበት ነበር። ወንዙ በሚፈጥረውም ደለል እርሻ በመጠቀም ትታወቅ ነበር። የባቢሎንን ከተማ የቆረቆራት <u>ናምሩድ</u> የሚባል የካም ልጅ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል /ዘፍ **10፡9-10** / ይህቺ የባቢሎን ከተማ አመቺ ስለ ነበረች ከየአቅጣጫዎቿ ያሉ ነገስታት ታላቅ ጥረት ያደርጉ ነበር። ባቢሎን ከሜሶፖታሚያ ከተሞች ትልቋ ከተማ ናት ባቢሎን በብሉይ ጣዖት በማምለኳ እግዚአብሔር ቢገስጻት እምቢተኛ ሆና የቀረች ከተማ ናት። ይህችም ከተማ ብዙ ጊዜ እስራኤላውያ የተማረኩበት ከተማ ናት። ግን በአርጤክስስ ንጉሥ በብልጣሶር ዘመን በቀኝ ግዛት ተይዛ ቀይታለች።

1.2 <u>ነነዌ</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪካቸው ከተገለጹ የሜሶፖታሚያ ከተሞች አንዷ ነነዌ ናት። ይህቺን ከተማ የቆረቆራት <u>ናምሩድ</u> ያባላል።/ዘፍ **10፡11** / ይህቺ ከተማ በጤግሮስ ምስራቃዊ ቆሬ ከባግዳድ በስተምስራቅ ርቀት ላይ የነበረች ከተማ ናት። ነነዌ እግዚአብሔርን በማሳዘናቸው ከነቢያት አንዱ ዮናስ በአሳ አንበሪ ተጉዞ የሔደባት ከተማ ናት። የሰናክሬም ሠራዊት በእግዚአብሔር መልአክ ከተቀሰፈ በኋላ ሰናክሬም ሸሽቶ የተሰደደባት ከተማ ናት። በዚህ ልጆቹ ገድለውታል /2 ነገ **19፡35** / ነቢዩ ሶፎንያስ ስለዚህች አገር ሲናገር ‹‹ነነዌን ባድማ እንደ በረሃም ደረቅ ያደርጋታል›› ብሎ ተናግሯል ሶፎ **2፡13** ነነዌ ከክ/ል/በፊት በ **4000** ዓመት ጀምራል የታወቀች ከተማ ሆናለች ነነዌ በባቢሎናውያን ከተማረኩ ከተሞች አንዷ ናት ።ይህቺ ከተማ እግዚአብሔርን አሳዝና ሳለች ነብዩ ዮናስ በተናገረው ትንቢት ከንጉስ እስከ ተራ ሰው ከሊቅ እስከ ደቂቅ ያለው ሕዝብ በንሰሐ የመጣባቸውን መቅሰፍት አስቀርተዋል። እንደውም በዮናስ ስብከት ሰናክሬም ንጉሥ ጭምር ንስሐ እንደገባ ይነገራል። ነቢዩ ዮናስ የነበረው ቅ/ል/ክ **700** ዓመት ነበር።

የፊንቄ ከተሞች

አራም /ሶርያ/ እና ፊንቄ ከእሥራኤል ጐረቤት ሀገሮች መካከል በብሉይ ኪዳን ታሪክ ቁልፍ ቦታ የያዙ ሀገሮች ናቸው። አራምና ፊንቄ የሚለው መጠሪያ እንደ ቀደምት የመከካለኛው ምሥራቅ ሀገሮች ሁሉ ከሕዝቦቻቸው መጠሪያ የተወሰደ ነው። አራማውያን ሶርያውን በሚለው የተለመደ

ስማቸው የሚታወቁትን ያህል ፊንቄያውያን ደግሞ ሲዶናውያን ይባላሉ። አሁን በዚህች አገር ውስጥ ያሉትን ከተሞች በጥቂቱ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

✓ ለምሳሌ ያክል ደማስቆ ጢሮስ ሲዶና ጌባል /ቢብሎስ/ ወዘተ ናቸው። ከዚህ በመቀጠል አንዱን ለምሳሌ እንመልከት

2.1 ደማስቆ

ይህቺ የደማስቆ ከተማ ከጥንቶቹ የመካከለኛው ምሥራቅ ከተሞች መካከል አየር ንብረታዊ ሁኔታዎቿ በተለይም የውኃ መገኛ ለመመሥረቷም ለሕልውናዋም መሠረት የሆናት ከተማ የደማስቆ ያህል የለም ለማለት ያስችላል። የጦር አዛዥ ንዕማን እንኳ የደማስቆ ወንዞች አባናና ፋርፋ ከእስራኤል ወንዞች ሁሉ አይሻሉም በማለት የኮራበት ከተማ ናት። 2ኛነገ 5-12 ደማስቆ ከሊባኖስ ተራራ በስተምሥራቅ በደቡብ ሶርያ የምትገኝ ከተማ ናት። ይህቺ ደማስቆ ለም አፈርና ውኃ በቂ ሀብትም አላት። ከሊባኖስ ተራራ ተነስቶ በደማስቆ የሚያልፈው የአባና ወንዝ እና እስከ ደማስቆ ደብባዊ ጠረፍ የሚጓዘው የፋርፋ ወንዞች የሕልውናቸው መሰረቶች ናቸው። የደማስቆ ከተማ ከእርሻ ሥራ ከከብት ርባታ ባሻገር የሲራራ ነጋዴዎች ለማረፊያ ከሚመርጧቸው ከተማ አንዷ ናት። ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቶስ ተገልጦ በብርሃን የመታበትም ከተማ ናት።

የግሪክ /የአናቶሊያ/ ከተሞች

አናቶሊያ ማለት በግሪክ ‹‹ፀሐይ የምትወጣበት ምድር›› ማለት ሲሆን ዛሬ በምዕራብ ቱርክ ትገኛለች። የታናሽ እሰያ ደሴት አካል ናት። ረዥም የባሕር በር ተራሮች ወንዞችና ሰፋፊ ጠረጴዛዎች ያሉዋት መሬት ናት። የደሴት አካሉዋ ዳርቻዎችዋ ከኤጅያን ከጥቁር ባሕርና ከሜዲትራንያን ባሕር ጋር ይዋሰናሉ በዚህች በግሪክ ሀገር ውስጥ የሚገኙትን ከተሞች ከፋፍለን እንመለከታለን።አሉም ገላትያ ኢጣልያ ተርሴስ ኤፌሶን አንጾኪያ መቄዶንያ ኪልቅያ ተሰሎንቄ ቆሮንቶስ ወዘተ የመሳሰሉ ከተማዎች ይገኙበታል። ከዚህ በመቀጠል ጥቂቶቹን ከፋፈለን እንመልከት።

3.1 አንጾኪያ

ይህች የአንጾኪያ ከተማ በሰሜን ሶርያ ከኦሮንጦስ ወንዝ ደቡባዊ ቆሬ ከሜዲትራንያ ባሕር በስተ ምሥራቅ 19 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች። አንጾኪያ ከኢየሩሳሌም ቀጥለ ለክርስትና መስፋፋት ታላቅ አስተዋጽዖ ያደረች ከተማ ናት። በዘመነ ሐዲስ በግሪክ ሮማዊ ዓለም ከሮም እና እስክንድርያ ጋር ስሟ የተጠራ ከተማ ናት።ሐዲስ ኪዳን ከተማዋን በተመለከተ በ15 ቦታዎች ላይ መረጃዎችን ይሰጠናል አንጾኪያ ክርስትና ለመጀመሪያ የተጀመረባት ከተማ ናት። አንጾኪያ የተቆረቆረችው በ300 ቅ.ል.ክ ከእስክንድር የጦር መሪዎች አንዱ በነበረው ሴቡክስ ከተማዋን ከሠራ በኋላ ለአባቱ ለአንጥያኮስ መታሰቢያ እንድትሆን አንጾኪያ ብሎ ሰየማት።

3.3 ተርሴስ

ይህች ተርሴስ ከተማ የሐዋርያው የጳውሎስ የትውልድ ቦታ ናት። ከተማዋም የተሰራችው ከሲዶና ወንዝ አጠገብ ሲሆን ወንዙም ከከተማዋ አጠገብ ወደ ሚገኘው ሐይቅ ይገባል። ይህም ተርሴስን ለጀልባ ትራንስፖርት ምቹ አድርጓታል። ይህቺ የተርሴስ ከተማ የሲራራ ነጋዴዎችና ወታደሮች የሚያቋርጡት በዚህቹ ከተማ መካከል ነው። በዚች በተርሴስ ከተማ ከ 170 ቅ.ል.ክ. ጀምሮ አይሁድ በከተማዋ መኖር ጀምረው ነበር። በተለይም ለከተማዋ የኢኮኖሚ ዕድገት ያመጣሉ ተብሎ በመታመኑ በሴሉሲዶች ዘመነ መንግሥት ብዙ አይሁዳዊያን በከተማዋ ከሚኖሩ ግሪካውያን እኩል መብት ነበራቸው። ሐዋሪያው ጳውሎስ ክርስትናን በተቀበለ ጊዜ ሊገድሉት ከተነሡት አይሁድ አምልጦ ብዙ ጊዜ የኖረው አንዳንድ ሊቃውንት 14 ዓመት ይላሉ። እና በኃላም በርናባስ መጥቶ የጠራው ከዚህ ከተማ ነው /ሐዋ 11-25-26/።

3.4 ተሰሎንቄ

ተሰሎንቄ በ 315 ቅ.ል.ክ የታላቋ እስክንድር የጦር አዛዥ የነበረው ንጉሥ ካስንድር ከተማዋን ቆረቆራት በሚስቱም ስም ተሰሎንቄ ብሎ ጠራት። ተሰሎንቄ የባሕር ሰላጤ ለመርከቦች ምቹ ሆኖ በተዘረጋው ወደቧ ወደ ቆሮንጦስ በሚወስደውና ጣልያንን ከምሥራቅ ሀገሮች በሚያገናኘው ትልቁ የንግድ ጎዳና ላይ የተመሠረተች ከተማ ናት። ይህቺ ከተማ በአግናዊዮረስ ጎዳና አጠገብ ሮምን ከምሥራቅ ቅኝ ግዛቶቿ ጋር የሚያገናኝ በመገኘቷ በህብት የበለጸገች ነበረች። ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለተኛው ጉዞው ሲጎበኛት ምንም የሮም ጦር ያልነበረባት ነፃ ከተማ ነበረች። የራሷንም ሳንቲሞች ታመርት ነበር። ብዙ ሰዎች ለንግድ የሠፈሩበት ከተማ ነበረች። ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለተኛው ጉዞም ለሦስት ሣምንታት ያህል በዚህ አስተምሯል /ሐዋ 17-2 /። ብዙ ግሪካውያንን አሳምኗል /ሐዋ 17-4/ ይህቺ ከተማ በአሁኑ ጊዜ የግሪክ ሁለተኛዋ ታላቅ ከተማ ናት። ሐዋርያው ጳውሎስም ለዚህቹ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ሁለት መልዕክታትን ጽፎላቸዋል።

3.5 ቆሮንቶስ

ቆሮንቶስ በ አክሮ ቆሮንቶስ ተራራ ግርጌ በተዳፋት ላይ ነው የተቆረቆረችው። ቆሮንቶስ ለምዕራብና ለምሥራቅ የመገናኛ ቦታ ነበረች። ይህቺ ከተማ የመልክዐ ምድር አቀማመጧ ተራራማ ስለነበር በቀላሉ በጠላት ልትጠቃ አልቻለችም። ለልሳነ ምድሩ ያላት ቅርበት ደግሞ የምዕራብ ምሥራቁን የንግድ መስመር ለመቆጣጠር አስችሏል። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ከተማዋ በገባ ጊዜ ቆሮንቶስ የአካይን ግዛት ዋና ከተማ ነበረች። በየብስና በባህር ለሚደረገው ንግድም አመቺ ከተማ ነበረች። ምንም እንኳን የምታገኘው ዓመታዊ የገቢና መጠን አነስተኛ ቢሆንም በባሕሩ

ጠረፍ በሚገኙት ሜዳማ ሥፍራዎች ባለው ለም አፈርዋ ፍራፍሬና ወይን በስፋት ታመርታለች። በሜድትራንያን በኩል ለቀረው ዓለም የምታቀርባቸው የሸክላና የነሐስ ውጤቶች ነበርዋት ።ይህቺ ከተማ ሰዎች ከ **4000** ቅ.ል.ክ አካባቢ ጀምሮ በአከባቢዋ ሰፍረዋል ደግሞም ከግሪክ ከተሞች ውስጥ በቅድሚያ የሠፈሩት የቆሮንቶስ ሰዎች ናቸው። ወደዚህች ከተማ ሐዋርያው ጳውሎስ ሁለት መልእክታት ጽፏል።

4) የፍልስጥኤም ከተሞች

በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ ወሳኝ የሆነ ቦታ የያዘ የእሥራኤላውያን መኖሪያ በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ ዋና ዋና ታሪኮቻቸው የተፈጸሙበት ቦታ ነው። የፍልስጥኤም ግዛት ክልል በየዘመናቱ ሲለዋወጥ ነው የኖረው ። ፍልስጥኤም ውስን የሆኑ ሀብቶች የሚገኙበት ቢሆኑም በሥልጣኔ የላቀ በልዩ ልዩ ፖለቲካዊ ነውጦች ስትታመስ የኖረች በየዘመናቱ የዓለምን ትኩረት የሳበ ሀገር ነው። አካባቢው በልዩ ልዩ ዘመናት ከነዓን ፍልስጥኤም እስራኤል በሚሉ ልዩ ልዩ ስሞች ሲጠራ ኖሯል ከነዓንና እሥራኤል የሚለው ስያሜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሀገሩ ሲቀጸል የምናገኘው ሲሆን ፍልስጥኤም የሚለውን ስም ለሀገሩ የሰጠው ግን ግሪካዊው ባለቅኔ የታሪክ ጸሐፊ ሄሮዶቱስ ነው። እነዚህ ስሞች ምድሩን ከያዙ ሕዝቦች ተወስደው በከነናውያን ከነዓን በእስራኤላውያን እስራኤል /2ኛ ነገ **5-2** / በፍልስጥኤማውያን ደግሞ ፍልስጥኤም ተብሎ ተሰይሟል። በፍልስጥኤም ውስጥ የሚገኙ ከተሞች <u>ኢያሪኮ</u> <u>ኢየሩሳሌም</u> <u>ሰማርያ</u> <u>ቤተልሔም</u> <u>ፊሊጶስ ቂሣርያ</u> <u>ቅፍርናሆም</u> <u>ጌርጌሴኖን</u> <u>ናዝሬት</u> **----** ወዘተ ናቸው።

4.1 <u>ኢያሪኮ</u>

ኢያሪኮ ማለት በዕብራይስጥ ጨረቃ ማለት ነው። በዓለም ላይ እጅግ ጥንታዊ ከተማ ነች። እስራኤል በኢያሱ መሪነት ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ ድል የመቷት የመጀመሪያዋ ከተማ ናት። ከተማዋ የተቆረቆረችው ከሙት ባህር በስተሰሜን በኩል በዮርዳኖስ ሸለቆ ውስጥ ነው። ኢያሪኮ ከዮርዳኖስ ማዶ ወደ ምዕራብ ፍልስጥኤም ለመሻገር የመግቢያ ከተማ ናት። ብዙዎቹ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር የሆኑ ሕዝቦች ወደ ዋናው ምድረ ፍልስጥኤም የገቡት በኢያሪኮ በኩል ዮርዳኖስን እየተሻገሩ ነው። የኢያሪኮ ከተማ የዘንባባ ዛፎች ያሉባት ከተማ ተብላ ትጠራለች። /ዘዳ **34-3/** የተቆረቆረችበትን የዮርዳኖስ ሸለቆ መጽሐፍ ቅዱስ የኢያሪኮ ሜዳ ይለዋል። /ኢያ **4-13/** የዮርዳኖስ ሸለቆ ውስጥ በሐሩር የአየር ንብረት እንዲሁም ዓመቱን ሙሉ የማያቋርጥ ምንጭ አጠገብ መቆርቆርዋ ኢያርኮን የበረሃ ገነት አድርጓታል የዐይን ኤል- ሱልጣን ምንጭ በመሰኖ አማካኝነት ለአከባቢው የእርሻ ሥራ ይውል ነበር። ምድሩ ሁሉ በዘንባባ ዛፎች የተሞላ ነው። ይህ ሁሉ ተደማምሮ ኢያሪኮን ከጥንቱ ዘመን አንሥቶ በከተማነት እንድትሠራ አብቅቷታል።

4.2 <u>ኢየሩሳሌም</u>

በዕብራይስጥ ቋንቋ ‹‹ይሩሻሌም›› ይባላል። ‹‹የሰላም ከተማ›› ማለት ነው። ኢየሩሳሌም በምድረ ፍልስጥኤም ከፍተኛ ቦታዎች ቁንጮ ላይ ትገኛለች። ኢየሩሳሌም ከሌሎች ከተሞች ይልቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልዩ ልዩ ሥፍራ የተሰጣት ከተማ ናት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ **771** ጊዜ ስሟ ተጠቅሷል። ኢየሩሳሌም የተመሰረተችው በጽዮንና በሞርያም ተራሮች ላይ ነው። /መዝ **124-2** / ሁለቱ ተራሮች ከሰሜን ወደ ደቡብ በሚያልፈው የጢሮጰዮን ሸለቆ ይለያያሉ። የከተማዋን ምዕራባዊና ደቡባዊ ደንበር የሚከልለው የ‹‹ረ›› ቅርጽ ያለው የሄኖም ሸለቆ ነው። የምሥራቁን ደንብሯን ደግሞ የቄድሮን ሸለቆ አጥሮ ይዘታል።

በኢየሩሳሌም የመጀመሪያው ሠፈር የተመሠረተው የዳዊት ከተማ ‹‹ኦፔል›› በተባለውና በደቡብ ምሥራቅ በሚገኘው ከፍታ ላይ ነው። ቆይቶ ደግሞ የመቅደስ ተራራ በተባለው ከፍታ ላይ መንደሮች ተመሠረቱ የኢየሩሳሌም የመጀመሪያ ስም ሳሌም ይባል ነበር። ይህም ‹‹ሰላም›› ማለት ነው። ከጌታችን ልደት **3500** ዓመት በፊት ጀምሮ በከተማነት ተቆርቁራ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ስሟ የተነሣው። /በዘፍ **14-8**// አብርሃምና መልከጼዴቅ በተገናኙ ጊዜ ነው። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሳሌም ከመባሏ በፊት ቤተ ሳይዳ ትባል እንደነበር ይገልጣሉ። በዚህች ከተማ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ አድጎባታል።

4.4 <u>ቤተልሔም</u>

ቤተልሔም ማለት በዕብራይስጥ ‹‹የእንጀራ ቤት›› ማለት ነው። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ግን ኤፍራታ ፍሬን የያዘች ቤተ ስብሐት የሚሉ ስሞች እንደነበሯት ይተርካሉ። ቤተልሔም ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደባት ከተማ ናት ቤተልሔም በሮብዓም ዘመን በግንብ ታጥራ ነበር።/2ዜና **11-5/** ከስምንተኛው መ/ክ/ዘ በኋላ ግን የተተወችና የተፈታች ከተማ ሆነች። በባቢሎን ምንኮ ጊዜ ከምርኮ ያመለጡ አይሁድ በቤተልሔም ነበሩ። ከዚያም በኋላ ሸሽተው ግብጽ ገብተዋል። /ኤር **41-17/** ከምርኮ በኋላ የቤተልሔም ነዋሪዎች ተመልሰዋል። /ዕዝ **2-21/** የቤተልሔም ታሪክ ገኖ የወጣው በዘመነ ሐዲስ ነው። ይህም የነቢዩ ሚክያስ ትንቢት ከተፈጸመ በኋላ ይህም ስለጌታችን በቤተልሔም ውስጥ ስለመወለዱ ተናግሮ ነበርና። /ማቴ **2-1** ሉቃ **2-4-7/** በ **614** ዓ.ም ፈረሰኞ አከባቢውን በወረሩ ጊዜ በቤተልሔም ዋሻ ላይ የተሠራው ቤ/ክ መጠነኛ ጉዳት ደርሶበት ነበር።

4.5 <u>ቅፍርናሆም</u>

በዕብራይስጥ ‹‹የናሆም መንደር›› ማለት ነው። ቅፍርናሆም በገሊላ አውራጃ ከነበሩት ዋና ዋና ከተሞች አንዷ ነበረች። ከተማዋ ብዙ ሕዝብ የሚኖርባት የንግድ ከተማ ነበረች። ዓሣ ማሥገር የከተማዋ ዋና የንግድ ሥራ ነበር። የአንገት ልብስና መረብ በከተማዋ ይመረታል። መርከቦችም ይሠራሉ በዙሪያዋ የነበረው ለም መሬት በእርሻ ምርት አንድትበለጽግ አድርጓታል። ‹‹ጌንሣሬጥ›› ተብሎ ይጠራ የነበረው አከባቢ

ለእርሻ ተስማሚ የሆነ መሬት ነበር። በሰሜን በኩል ያሉት ኮረብታዎች ለግንባታ የሚያገለግሉ ባልጩት ድንጋዮች እንድታገኝ ረድቷታል። ጌታችን በቅፍርናሆም በተደጋጋሚ ገብቶ አስተምሯል። /ማቴ **4-12**/ ማር **1-14**/ ቅፍርናሆም የጴጥሮስ የእንድርያስ የያዕቆብና የዮሐንስ መኖሪያ ነበረች። የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት የተጠሩትም ከእዚቹ ከተማ ነው። /ማቴ **4-18**/ የአይሁድን ታሪክ የጻፈው ዮሴፍ ወልደኮርዮን ቆስሎ በሮም ወታደሮች የተያዘው በቅፍርናሆም ነው። ዛሬ በፈራረሰችው ከተማ አጠገብ ካለችው የቴልሆም ከተማ በቀር ሌላው ታሪኳ ጠፍቷል ይህም የጌታ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው። /ማቴ **11-20**/

4.6 ናዝሬት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደገባት በስሜን እስራኤል በገሊላ አውራጃ ትገኝ የነበረች ከተማ ናት። ናዝሬት ማለት ‹‹ነጭ ድንጋይ›› ማለት ነው። ናዝሬት የእመቤታችንና የዮሴፍ የትውልድ ሥፍራ ናት። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም እመቤታችንን ያበሰራት በዚሁ ሥፍራ ነው። ጌታችንም በዚህም ከተማ በምኩራብ ቢያስተምርም አልተቀበሉትም ነበር። /ሉቃ **4-16**/ ፊሊጶስ ናትናኤልን በጠራው ጊዜ ናትናኤል ‹‹በውኑ ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን›› በማለት የተናገረው በብሉይ ኪዳን ዘመን ከተማዋ ተርታ እና እዚህ ግባ የማትባል ስለሆነች ነው። ናትናኤል ይህን የተናገረው በወቅቱ በሰዎች ዘንድ ዝቅ ተደርጋ የምትታይ ከተማ ስለነበረች እንደ ነበር የኢትዮጵያ ቤ/ክ ሊቃውንት ያትታሉ። ጌታችን ከስደት ከተመለሰ በኋላ የኖረባት ከተማ ናት። ናዝሬት ከታሪኳ ይልቅ በውስጧ የተፈጸመው መለኮታዊ ሥራ የከበረች ከተማ አድርጓታል።

5) የፋርስ ከተሞች

የፋርስ ሕዝቦች መሥፈር የጀመሩት ከ **5000** ዓመት ቅ.ል.ክ በፊት ጀምሮ ነው። ለፋርስ ሥርወ መንግሥት መነሻ የሆነው የዓለም መንግሥት ተመሥርቶ የነበረው የዛሬዋ ኢራን ናት። ፋርስ ከል/ክ በፊት በ **539** ዓመት ኃያሏን ከተማ ባቢሎንን አሸንፋ እጅግ ሰፊ ግዛት ይዛ ነበር። በዚህ ጊዜ የነበረው ንጉሧ አርጤክስስ ይባላል። ግዛቷም ከኢትዮጵያ እስከ ህንድ ይደርስ ነበር። የንጉሡ ቤተ መቅደስም የሱሳ ግንብ በመባል ይታወቃል። የፋርስ መንግሥት ለረጅም ዓመታት በገናናነት ቆይቷል። ኃላ ግን ከጌታችን ልደት **330** ዓመታት አስቀድሞ የተነሣው የግሪክ ንጉሥ ታላቁ እስክንድር ድል አድርጓታል።

5.1 ሱሳ

ሱሳ ማለት በውኃ አከባቢ የሚበቅል ሊሊ የተባለው አበባ ወገን የሆነ አበባ ስም ነው። ከተማዋ በተመሠረተችበት አከባቢ ይህ አበባ በብዛት ስለተገኘ ይህን ስም መያዝዋ ይነገራል ።ሱሳ የታዋቂዋ የፋርስ ንጉሥ ዳርዮስ አንደኛ ተወዳጅ ከተማ የነበረች ቦታ ናት። በደቡብ ምዕራብ ኢራን በሱሲያና ሜዳ ላይ አሁን ሸሽ እየተባለ በሚጠራው ቦታ ላይ ትገኝ የነበረች ከተማ ናት። ከተማዋ አምሥት ጉብታዎችን ያካተተች ሆና ትገኛለች። ከተማዋ የተመሠረተችው በቻኦር ኡባል ወንዝ ቆሬ ውስጥ ነው። /ት/ዳን **8-15**/ ይህቺ ከተማ ንግሥቷ አስቴር የነበረችበት ከተማ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መንደሮች

መንደር የሚባለው ብዙህ ቁጥር የሌላቸው አናሳ ሕዝቦች በአንድነት ተሰብስበው የሚኖሩበት አከባቢ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት መንደሮች ኑሮአቸው በግብርናና በንግድ ላይ የተመሠረተ አከባቢ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙዎችን መንደሮች ከተማ በማለት ቢጠቅሷቸውም በመንደርነት ስማቸው የተጠራ አነስተኛ ቦታዎች ይገኛሉ። እኛ ከዚህ ቀጥለን ለምሳሌ ያክል ጥቂቶቹን እንመልከት።

1)ቤተ ሳይዳ

ቤተ ሳይዳ ማለት ‹‹የዓሣ አጥማጅ ቤት›› ማለት ነው። በኢየሩሳሌም ከተማ በበጎች በር ከምትገኘው ቤተ ሳይዳ የተለየች ናት። እንደ ቅፍርናሆም ሁሉ በገሊላ የባህር ወደብ በስተሰሜን ጫፍ ሆና የተሰራች ናት። የዮርዳኖስ ወንዝ በምስራቅ በኩል ነው። ወደ ገሊላ ባሕር ሲገባ ቤተ ሳይዳን ከቦ ነው። ይህች ቦታ የጴጥሮስ የእንድርያስ የፊሊጶስ የትውልድ ቦታ ናት።

2)ዓይነ ከርም

ይህች ቦታ መጥመቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ የተወለደባት ቦታ ናት። እመቤታችን በካህኑ ዘካርያስና በኢክስቷ በኤልሳቤጥ ቤት ውስጥ ሦስት ወር የተቀመጠችው ዮሐንስም በእናቱ ማኅጸን ሳለ ለእመቤታችን የሰገደው በዚህች ቦታ ነው። ይህች ዓይነ ከርም ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን ምዕራብ ትገኛለች።

3)ኤማሁስ

ኤማሁስ ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን **12** ሜትር **60** ምዕራፍ ያህል ርቀት ላይ የምትገኝ መንደር ናት። በዚህች መንደር ሉቃስና ቀለዮጳ የተባሉት የጌታችንን በአይሁዶች እጅ መከራን መቀበሉን መሞቱን መቀበሩን ተስፋ ቆርጠው ትንሣኤውን ተጠራጥረው ወደ ኤማሁስ ስለዚሁ ስለጌታችን እየተነጋገሩ ሲጋዙ ጌታ ቀኑን ተገልጦ በማደሪያቸው ገብቶ ኅብስቱን ባርኮ በመስጠት ዓይነ ልቦናቸውን እንዲሁ እንዲያስተውሉና እርሱ መሆኑን እንዲያውቁ ያደርገው በኤማሁስ መንደር ነው። /ሉቃ **24-35** /

4)ቤተ ፋጌ

ከደብረ ዘይት ግርጌ ከቢታንያ አጠገብ የምትገኝ መንደር ናት። ቤተፋጌ ከነገደ ሌዊ ወገን የሆኑ ካህናት ይኖሩባት እንደ ነበር ይነገራል። ቤተ ፋጌ ማለትም ‹‹የተመሳቀለ መንገድ ያለበት›› ማለት ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀመጠባቸው አህያና ውርንጫ ታስረው የነበረው በቤተ ፋጌ ነበር። ሁለቱንም ደቀ መዛሙርቱን ልለኮ ከእስራታቸው አስፈትቶ ካስመጣቸው በኋላ ተቀምጣባቸው በኢየሩሳሌም ወዳለው ቤተ መቅደስ ገባ። /ማቴ **21-1/**

5) <u>ጌልጌላ</u>

ጌልጌላ የሚለው ትርጉም ‹‹ማንከባለል›› ማለት ነው። ከኢያሪኮ አጠገብ በስተ ምሥራቅ የምትገኝ ከተማ ናት። እስራኤል ከግብፅ ሲወጡ ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ በጌልጌላ ተቀምጠዋል። የዚህች ቦታ ስያሜ ዛሬ ከእናንተ የግብፅን ነውር አንከባልያለሁ ላላቸው መታሰቢያ ነው። በዚህች ጌልጌላ መንደር ንጉሱ ሳኦል ተሹሞ የነገሰበት ቦታ ነው። /**1** ኛሳሙ **11-14/**

6) <u>ቢታንያ</u>

ቢታንያ ማለት ‹‹የበለስ ቤት›› ማለት ነው። ከኢየሩሳሌም በምስራቅ 3 ኪሎ ሜትር ርቃ በደብርዘይት ተራራ በምስራቃዊው ቁልቁለት ላይ ያለች መንደር ናት። ዛሬ የዐረቦች መንደር ስትሆን የአልአዛር የማርያምና የማርታ ቤት በዚህቹ መንደር ነበር። በተጨማሪም በዚህች መንደር ጌታ ዓልአዛርን ከሞት አስነስቶ ሕይወትና ትንሣኤ እርሱ እንደሆነ ያስተማረበት መንደር ነው። ማርያም የከበረ የአልባስጥሮስ ሽቱ ገዝታ እግሩን የቀባችሁ በዚሁ መንደር ነው። ጌታም ሲያርግ ሐዋርያትን ሰብስቦ ይዞ የወጣበት መንደር ናት። ግን በአሁኑ ጊዜ የቢታንያ ይዞታ የዐረቦች ነው። /ዮሐ **12-7/**

7) <u>ጌቴሴማኔ</u>

ጌቴሴማኒ ማለት ‹‹የዘይት መጭመቂያ›› ማለት ነው። በደብረ ዘይት ተራራ ተዳፋት ላይ የምትገኝ የኢየሩሳሌም ከተማ ክፍል የሆነች ቦታ ናት። በዚህች ሰፍራ ጌታችን ከመያዙ አስቀድሞ ከደቀመዛሙርቱ ሦስቱን ቅዱስ ጴጥሮስ ዮሐንስ እና ያዕቆብን አስከትሎ ጸሎት አድርጎባታል /ማቴ **26-36**/ ከፍተኛ በሆነ የወይራ ዛፍ ተሸፍና ትገኛለች። ጌታችንም ወደ ጌቴሴማኒ የሄደው የመቃቢስ ደረጃዎች እየተባሉ በሚጠሩት ደረጃዎች አልፎ ነው። ደረጃዎቹም የተሠሩት የዳዊትን ከተማ ጽዮንን ከቄድሮን ሸለቆና ከጽዮን ተራራ ጋር ለማገናኘት ነው። የቄድሮን ሸለቆ ከኢየሩሳሌም በስተምስራቅ ይገኛል። አሣፍና ኢዮስያስ የተባሉ ነገሥታት በሸለቆው ውስጥ የነበሩትን ጣዖታት አጥፍተዋል።

ደረቅ የመሬት ክፍል (የብስ የሆኑ ቦታዎች)

በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ የምንመለከተው ደረቅ የመሬት ክፍላትን ነው። እነዚህ የመሬት ክፍሎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሠፊ ይገኛሉ። እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው መልክዐ ምድሮች ተራሮችን ሜዳዎችን ሸለቆዎችን በረሃዎችን ዋሻዎች የሚያጠቃልል ነው። ታድያ እነዚህ በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስፋት በበርካታ ቦታዎች እናገኛቸዋለን። ከዚህ በመቀጠል እነዚህ መልክዐ ምድሮች ከፋፍለን ለምሳሌ ያክል ጥቂቶቹን እንመለከታለን።

1)ተራራዎች

ተራራ እያልን የምንጠራው ከሜዳና ከደልዳላ ሜዳዎች ከፍ ብሎ የሚገኝ ሥነ-ተፈጥሮ ነው። ታድያ እኚዚህን የመሰለ ተራሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአብዛኛው ቦታ በብሉይ ኪዳንም በሐዲስ ኪዳንም በሁለቱም ኪዳናት ክፍል ውስጥ በአብዛኛው ተጠቅሰው ይገኛሉ። በቅድስት ሀገር ከተፈጸመባቸው ታሪክ አንጻር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተመዝግበው እናገኛለን። ስማቸው ሲነሣ የተፈጸመባቸውም ድርጊት አበሮ ይታወሳል ። እነዚህም ተራሮች የሲና ተራራን የታቦርተራራን የደብረ ዘይት ተራራን የቀርሜሎስ ተራራ አርሞንኤም ተራራ የሞሪያም ተራራ የገሪዛን ተራራ የሊባኖስ ተራራ የጌባል ተራራ ናቸው። እነዚህን ተራራ ቀጥለን እንመልከት።

1.1 <u>ቀርሜሎስ ተራራ</u>

ቀርሜሎስ ማለት ‹‹ፍሬያማ ተክል›› ማለት ነው። በዚህ በቀርሜሎስ ተራራ የወይራ ዛፎችና የወይን ተክል በብዛት የሚገኝበት ቦታ ነው። ከገሊላ ባህር በስተሰሜን **55** ኪ.ሜ ርቆ የሚገኝ ሲሆን ወሰጉም እስከ ታላቁ ባህር የሜዲትራኒያን ባህር ይደርሳል በዚህ ተራራ ላይ ሆኖ የጢሮስና ሲዶና የእስራኤልንም ክፍል በሩቅ መመልከት ይቻላል። ነብዮ ኤልያስ ጸልዮ ሰማይን የለጎመው **450** ካህናት ጣዖትትን ያሳረደው በዚሁ ተራራ ላይ ነው። /**1** ኛ ነገ **18-20** / በተጨማሪም ነብዮ ኤልሳዕ በብሕትውና ይኖር የነበረው በዚሁ ተራራ ላይ ነው። /**2** ኛ ነገ **4-25/**

1.2 <u>የሞሪያም ተራራ</u>

የሞርያም ተራራ ከኢየሩሳሌም በስተምስራቅ የሚገኝ ተራራ ነው። በዚህ ተራራ ላይ አባታችን አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ለመሰዋት መሰዊያውን ይዞ የወጣበት በይሰሐቅም ፈንታ በዕፀ ሳቤቅ የታሰረውን በግ ሰውተው የተመለሱበት ተራራ ነው። /ዘፍ **22-2/** በዚህ በሞርያም

ተራራ ላይ ዳዊት ለመስራት የተመኘውን የእግዚአብሔርን ቤት በኋላም ጠቢቡ ሰሎሞን የሰራው ቤተ መቅደስ በዚህ ተራራ ላይ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። /2 ኛ ዜና 3-1/

1.3 ደብረ ሲና

ደብረ ሲና ማለት ‹‹የሲና ተራራ›› ማለት ነው። ይህ ተራራ ኮሬብ እየተባለ ይጠራል። ይህ ተራራ ከግብፅ በስተ ምስራቅ ከእስራኤል በስተደቡብ ይገኛል። በዚህ ተራራ ላይ ሊቀ ነቢያቱ ሙሴ 40 ቀን ሱባዔ ይዞ ሕገ ኦሪትን የተቀበለበት ተራራ ነው። ሙሴ 5 ቱ ብሔረ ኦሪትንንና መጽሐፈ ኩፋሌን በዚሁ ተራራ ላይ ነው የጻፈው። በዚህ ተራራ ላይ የታየው ዕፀ ጳጦስ የክርስቶስን ነገረ ሥጋዌ እንደሚያወሳ ሊቃውንት ይናገራሉ።/ዘጸ 20/

1.4 አርሞንኤም ተራራ

ይህ የአርሞንኤም ተራራ በሶርያ በሊባኖስ በእስራኤል ደንበር ላይ እንደ ሰንሰለት ሆኖ ያለ ተራራ ነው። ይህ ተራራ የሚገኘው በስሜናዊው የእስራኤል ክፍል በገሊላ አውራጃ ሰሜናዊው ጫፍ ነው። በዚህ ተራራ ላይ አናብስትና አናምርት ይገኙበታል። የዚህ ተራራ ራስ ላይ ፀረ ግማር (በረዶ) ይገኛል። በረዶው እየሟሟ ወደ ገሊላ ባህርና ዮርዳኖስ ወንዝ ይገባል።/ መዝ 132-3 //

1.5 ደብረ ዘይት

ደብረ ዘይት ማለት ‹‹የዘይት ተራራ›› ማለት ነው። ይህ ተራራ ከኢየሩሳሌም በምስራቅ በኩል የሚገኝ ተራራ ሲሆን በተራራው ግርጌ ላይ ቤተ ፋጌና ቢታንያ መንደሮቹ ይገኛሉ። በዚህ ተራራ ራስ ላይ ሆኖ ኢየሩሳሌምና ሞዓብን መመልከት ይችላል። ይህች ተራራ በወይራ ዛፍ የተከበበች ስለሆነች ደብረዘይት የሚለውን ስያሜ አገኘች።ጌታችንም በዚህ ታራራ ላይ አንቀጸ ብጹዓንን አስተምሯል። በዚህ ተራራ ግርጌ በአይሁዶች እጅ በፈቃዱ እንደተያዘ /ዮሐ 18-3/ ይናገራል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ዓለምን ለማሳለፍ እንክርዳዱን ከስንዴ ለመለየት ለያንዳንዱ እንደየስራው ለመፍረድ ለዓድቃን ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላቸውን ርስት ለማውረስ የሚመጣው ደግሞ ምጽአቱ በዚሁ ደብረዘይት ተራራ ላይ እንደሚመጣ እንደሚገለጥ ቤተ ክርስቲያን ተስፋ ታደርጋለች።

1.6 ደብረ ታቦር

ደብረ ታቦር ከገሊላ ባሕር በስተ ደቡብ የሚገኝ ተራራ ነው። ይህ ተራራ በብሉይም በሐዲስም ብዙ ታላላቅ ሥራዎች ተሠርተውበታል። ይህ ተራራ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ‹‹ ታቦር አርሞንኤም በስመ ዚአከ ይትፌስሑ›› ብሎ ትንቢት ተናግሯል። በዚህ ተራራ ላይም ዲቦራና ባርቅ የእስራኤልን ጠላት የሆነውን ሲሣራን ድል ነስተውታል። በሐዲስ ኪዳንም የክብር ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሴን ሰውከማያውቀው መቃብር ጠርቶ ኤልያስንም ዐሳርጎ ከወሰደበት አምጥቶ የባሕርይ አምላክነቱን ብርሃነ መለኮቱን የገለጠበት ተራራ ነው።

በአጠቃላይ እነዚህ ተራሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተዘግበው እናገኛቸዋለን። ታደያ እነዚህን ተራሮች አሁን ከላይ በገለጽነው መሠረት እነዚህን የመሳሰሉ ታሪክና ምስጢር ይዘው ይገኛሉ ማለት ነው።

ሜዳዎች

ሜዳ ማለት የተስተካከለ የመሬት ክፍል ሲሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሜዳዎች ብዙም ተጠቅሰው አይገኙም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰው የምናገኛቸው ሜዳዎች ቢሆኑ በመጠናቸው እምብዛም ተብራርተው አልተጠቀሱም ይሁን እንጂ ጥቂት የሆኑ ሜዳዎች በስም ተጠቅሶ እናገኛቸዋለን ለምሳሌ አርማጌዶን ስናዖር ሳሮን እና የዱራ ሜዳዎች ይጠቀሳሉ /1 ዜና 27-29/ ዳን 3-1/

2.1/ የአርማጌዶን ሜዳ

የአርማጌዶን ሜዳ ከቀርሜሎስ ተራራዎች በስተደቡብ ከደብረ ታቦር ፊት ለፊት የሚገኝ ሜዳ ነው። ቀድሞ በቀርሜሎስ ተራራዎች ከሰሜን ወደ ደቡብ ጋዛንና ደማስቆን የሚያገናኘውን መንገድ ለመጠበቅ የተመሸገ ከተማ ነበረ። ይሁን እንጂ በዚህ ሜዳ ሰዎች አይኖሩበትም። ከዚህ ቀደም ዲቦራ ሲሣራን ድል ያደረገችው በዚሁ ሜዳ ላይ ነው። ፈርዖን ኒካውም ኢዮስያስን የገደለው በዚሁ በአርማጌዶን ሜዳ አጠገብ ነው። የአርማጌዶን ሜዳ የዓለም መጨረሻ ምልክት የሚሆን ጦርነት ይደረግበታል። አርማጌዶን ማለትም ‹‹መክነ ድምሳሴ (የመደምሰሻ ቦታ) መክነ ሰራዊ የ(መነቀያ ቦታ) ማለት ነው።በነቢዩ ዘካርያስ ‹‹በዚያን ቀን በአርማጌዶን ሜዳ እንደነበረው እንደ ሐዳድሪን ልቅሶ ታላቅ ልቅሶ በኢየሩሳሌም ይሆናል ምድሪቱም ታለቅሳለች እያንዳንዱ ወገን ለብቻው የዳዊት ቤት ወገን ለብቻው ሴቶቻቸው ለብቻቸው የናታን ቤት ወገን ለብቻው ሴቶቻቸውም ለብቻቸው የሌዊው ሴቶቻቸውም ለብቻቸው የቀሩት ወገኖች ሁሉ እያንዳንዱ ወገን ለየብቻው ሴቶቻቸውም ለብቻቸው ያለቅሳሉ›› ተብሎ በነቢዩ የተነገረው ትንቢትም በዚሁ በአርማጌዶን በሚደረገው ጦርነት እንደሚፈጸም ይታመናል /ት/ዘካ 21-1/

2.2 የሰናዖርሜዳ

ይህ የሰናዖር ሜዳ በባቢሎን ዙሪያ ያለ ሰፊ ሜዳ ሲሆን ከኖኅ ዘመን የጥፋት ውሃ በኋላ የተነሡ ሰዎች ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ በምድር ላይ ሳንበተንም ስማችንን እናስጠራው በማለት በፋሌቅ ዘመን የነበሩ ሠዎች ግንብ መገንባት የጀመሩት በዚሁ በስናዖር ሜዳ ነው።

የስናዖር ሜዳ የሰው ልጆች ቋንቋ የተለያየበት የተደበለቀበት ቦታ ስለሆነ ባቢሎን ተብሏል።ባቢሎን ማለትም ድብልቅልቅ ማለት ነው። በዚህ በሰናዖር ሜዳ ላይ እግዚአብሔር አንድ ቋንቋ የሆነው ወገን ግምብ ይሰሩ ጀመር። ስለዚህ ኑ አሁን ከእርሱ ፈጽመን እንድናጠፋ አንዱም የአንዱን ቋንቋ እንዳይሰማ ኑ ወርደን በቋንቋ እንለያቸው በአሕዛብም ሀገር ይበታተናሉ ከዚህ በኋላ ቁርጥ ፍርድ እንደሚደረግባት ቀን አንዲት ምክር ጸንታ በላያቸው አትኑር አለ። የሠሩትንም ለዋወጠባቸው አንዱ የአንዱን ነገር አልሰማም ከዚያም ቋንቋቸውን ስለለዋወጠባቸው መግባባት ስላልነበረ ግምብንና መንደርን መስራት አቆሙ። /ዘፍ **11-18/** ኩፋ **10-10/**

ዋሻዎች

ዋሻ ከደረቅ መሬት ክፍላቶች አንዱ ነው። ዋሻ በተፈጥሮም ሆነ በሰዎች ሀይል የተቦረቦረ የተፈለፈለ ቋጥኝ ነው። በሰዎች ሀይል ስንል ያን ሀይል ለሠዎች የሰጠው እግዚአብሔር ነው። አብዛኛውን ጊዜ ዋሻን የሚፈለፍሉት መናንያን ናቸው። ከዓለም ተለይተው ሲመንኑ ለጸሎት ቦታ ብለው ዋሻዎችን ይፈለፍላሉ። ሲፈለፍሉም ከአንድ ድንጋይ ላይ ጠርበው አስተካክለው ዋሻ ይሰራሉ። በነዚህና በተፈጥሮ ዋሻ ስደተኞች ይጠጉበታል አራዊት ይኖርበታል ማለት ነው። እንደዚህ አይነት ዋሻም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዘግቦ እናገኘዋለን። ይኸውም

3.3 <u>የኤልያስ ዋሻ</u>

ይህ የኤልያስ ዋሻ የሚባለው በይሁዳ በረሃ ይገኛል በዐረብኛ ‹‹ዋዲከልት›› እያሉ ይጠሩታል። ነቢዩ ኤልያስ በዘመኑ ያሉትን የናቡቴን ደም በግፍ ያፈሰሱትን ሰዎች እነ አክዐብ እነ ኤልዛቤልን የእግዚአብሔርን አምልኮ የዘነጉ ቢሆኑ ለልዑል እግዚአብሔር ቀንቶ እነ ኤልዛቤልን ከነሰራዎቶቻቸው ለመቅጣት ጸልዮ ሰማይ ዝናብ ለዘር ጠል ለመከር እንዳይሰጥ ለጉሟል። በዚህ የተነሣ አክዐብ እንዳይገድለው በረሃብ እንዳይንዳ እግዚአብሔር አምላክ ወደ ምስራቅ በዮርዳኖስ ወንዝ ትይዩ ወዳለው ወደ ኮራት ፈፋ ውስጥ እንዲሸሸግ አዘዘው ።/**1** ነገ **17-1/** በዛው በፈፋ ሸሽግ ውስጥ ሆኖ ቁራ ጠዋትና ማታ ኅብስትና ሥጋ እያመጣ ኤልያስን ይመግበው ነበር። ይህች ኤልያስ የተሸሸገበት ምሽግ የኤልያስ ሸለቆ ዋሻ ትባላለች።

3.2 <u>የሴይቅያስ ዋሻ</u>

የሴይቁያስ ዋሻ በአሁኑ ጊዜ ከደማስቆ በር በስተግራ በኩል **180** ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። ይህ ዋሻን የተሸሸገበት የኢዮሳፍጥ ሦስተኛ ልጅ በኢየሩሳሌም ከነገሠ የዳዊት ዘሮች የመጨረሻው ነው። ታድያ በይሁዳ ላይ ከነገሰ በኋላ በባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነፆር ላይ ግብር አልከፍልም ብሎ አመጸ። በዚህ ጊዜ ሴይቅያስ ከናቡከደነፆር ሸሽቶ ወደ አንድ ምሽግ ስር ተሸሸጎ ነበር። ከዛ ምሽግም ወጥቶ በናቡከደነጾር ሠራዊቶች ኢያሪኮ ላይ ተይዞ አይኖቹ እንዲወጡ ተደረገ። /**2** ነገ **25-1/** ይህቺ ሴይቅያስ ተሸሸጎባት የነበረው ምሽግ የሴይቅያስ ዋሻ እየተባለ መጠራት ጀመረ። ከዚህች ከሴይቅያስ ዋሻ ውስጥ የምትመነጭ ምንጭ አለች። ይህችን ምንጭ የአከባቢው ሰዎች የሴይቅያስ እንባ እያሉ ይጠሩታል።

ሸለቆዎች

ሸለቆ ማለት ጎድጓዳ የሆነና የሚሞቅ ሐሩር የበዛበት ቦታ ማለት ነው። ሸለቆ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሷል። ይኸውም የኢዮሳፍጥ ሸለቆ የሄኖም ሸለቆ የራፋይም ሸለቆ የባዔል ሸለቆ ናቸው።
ከዚህ በመቀጠል እነዚህን ሸለቆዎች በዝርዝር እንመለከታለን።

4.1 <u>የኢዮሣፍጥ ሸለቆ</u>

ይህ የኢዮሣፍጥ ሸለቆ በኢየሩሳሌም እና በደብረ ዘይት መካከል የሚገኝ ሲሆን የቄድሮን ወንዝ ይፈስበታል። ይህን ዋሻ ኢዩሳፍጥ ወልደ አሣፍ ጠላቶቹ በተነሱ ጊዜ እግዚአብሔር ጠላቶቹን ድል አስደርጎ ምርኮአቸውንም ወስዷል። በዚህ ጊዜ በዚህ ኢዮሳፍጥ ሸለቆ በመባል በሚጠራው ሸለቆ ውስጥ እግዚአብሔርን አመሰገነ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ የኢዮሳፍጥ ሸለቆ በመባል መጠራት ጀመረ። በአሁኑ ጊዜ ይህ ዋሻ ብዙ የእስላምና የአይሁዶች መቃብር ይገኝበታል። በዚህ ሸለቆ ውስጥ እግዚአብሔር በሕዝብ ላይም በአሕዛብም ላይ እንደሚፈርድ ነቢየ ልዑል ኢዩኤል ትንቢት ተናግሮበታል /ኢዩ **3-2/** በተጨማሪ በዚሁ ሸለቆ ውስጥ በኢየሩሳሌም ነግሠው የነበሩ ነገሥታት ሥጋቸው በዚህ ሸለቆ ተቀብሯል።

4.2 <u>የሄኖም ሸለቆ</u>

ይህ የሄኖም ሸለቆ ስያሜውን ሄኖም ከተባለ ሰው እንዳገኘ ይነገራል። ይሁን እንጂ በዚህ ሸለቆ ከኢዩስያስ በፊት ነግሠው የነበሩ ነግሥታት ጣዖት ያመልኩበት የነበረ የአምልኮ ቦታ ነበር። በዚሁ ሸለቆ ውስጥ ወንድና ሴት ልጆቻቸው ሳይቀር ይሰው ነበር። /ኤር **19-1/** ከዚህ በኋላ ነው ኢዮሳያስ ሲነግስ የአባቱ የዳዊትን ሥርዐተ እምነት ተከትሎ በዚህ ሸለቆ ውስጥ የነበረውን ጣዖታትን አፍርሶ መሠዊያዎችን አጥፍቷል። /ነገ **23-10/** ይህ የሄኖም ሸለቆ ከቄድሮስ ወንዝ በታች ከጥንታዊው የኢየሩሳሌም ከተማ በምዕራብና በደቡብ በኩል ይገኛል።

በአጠቃላይ እንደዚህ ዓይነት ታሪክ አዘል /ታሪክ ያለቸው/ ሸለቆዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዘግበው ይገኛሉ ማለት ነው።

<u>በረሃዎች</u>

በረሃ ማለት ምድረ በዳ ሰውና ልምላሜ የሌለበት ሐሩርና ሙቀት የበዛበት ማለት ነው። ከከተማ ራቅ ብሎ የሚገኝ የመሬት ክፍል ነው። ብዙ አባቶች በበረሀ ለተጋድሎ ብለው መንነው ይሔዳሉ ይህን መሰል በረሃ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ። እነዚህም ቃደስ የሲና ምድረ በዳ የጺን በረሃ የመሳሰሉ ናቸው። ከዚህ በመቀጠል እኚህን በረሃዎች በዝርዝር እንመልከት።

5.1/ የሲና ምድረ በዳ

ይህች የሲና በረሃ ከግብፅ በስተ ምስራቅ ከእስራኤል በስተደቡብ ትገኛለች። እስራኤላውያን ከግብፅ ምድር በሊቀ ነቢያቱ በሙሴ አማካኝነት የኤርትራን ባሕር አልፈው ብዙ የተንከራተቱበት በረሀ ነው። በዚሁ ቦታ እግዚአብሔር አምላክ ዛሬ የምንመራበትን ሕገ ኦሪት /አሥርቱ ትዕዛዛት/ ለሙሴ ተሰጥቶታል። ሙሴ የኦሪት መጽሐፍትን የተጻፈውም እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሳሉ በዚሁ በሲና ምድረ በዳ ነው። /ዘደ **/9÷1-/**

5.2/ የቃዴስ በረሃ /በርኔ/

ቃዴስ ማለት ቅዱስ ማለት ነው። ከከነዓን በስተደቡብ የሚገኝ በረሃ ነው በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ይህ የቃዴስ በረሃ በርኔ ተብሎ ተጠቅሷል። /ዙኑ 32÷8/ በዚሁ በቃዴስ በረሃ እስራኤል ዘሥጋ አርፈዋል። በዚህ በረሃ ሳሉ እግዚአብሔር ወደ ከነዓን ሊያገባቸው መሆኑን ተጠራጥረው በዚህ በረሃ ከ 40 ዓመት በላይ እንዲኖሩ ተደርጓል። /ዘዳ 1÷46 / በዚህ በረሃ ሣሉ በማጉረምረማቸው ምክንያት እባብ ነድፎ ገደላቸው በኋላ ግን ሙሴ የነሐስ እባብ ሰርቶ ቢተክለው ያን እባብ እያዩ መዳን ችለዋል የተተከለው የነሐስ እባብ አይናደፍም ነበር።

ውኃማ አካላቶች

በመጽሐፍት ቅዱስ ውስጥ ደረቅ የመሬት ክፍል ከተሞች እንደተመለከትን ሁሉ የውኃማ አካሎችም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ተጠቅሰው እናገኛቸዋለን። እነሱም ምንጮች ባሕሮች ወንዞች የመሳሰሉት ናቸው። ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዳቸውን ዘርዝረን እንመለከታለን

1/ ባሕሮች

ባሕር ማት በአንድ ቦታ በብዛት የተከማቸና ብዙ ወንዞች የሚፈሱበት የውኃ አካል ማለት ነው። በዓለማችን ላይ ብዙ ባሕሮች ቢገኙም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዘግበው የምናገኛቸው ግን ጥቂቶቹን ነው። እነሱም ታላቁ /የሜዲትራኒያ/ ባሕር የገሊላ ባሕር የሙት ባሕር የኤርትራ ባሕር የመሳሰሉ ናቸው። በሀገረ እስራኤል አሉ ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ግን ሁለት ናቸው። እነሱም የሙት ባሕር እና የገሊላ /የጥብርያዶስ/ ባሕር ናቸው። ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዳቸውን ዘርዝረን እንመልከት ።

1.1/ ባሕረ ኤርትራ

ከሲና ልሳነ ምድር እስከ ባብኤል መንደር የሚደርስ ርዝመት ያለው እስያንና አፍሪካን የሚያለያይ ባህር ነው። የባሕሩ ርዝመት **2175** ኪ.ሜ ሲሆን ስፋቱ ደግሞ **370** ኪ.ሜ ነው። ወደዚህ ወደ ባሕረ ኤርትራ የሚገባ ምንም ዓይነት ምንጭ የለም። ይህን ባሕር አስቀድሞ እስራኤል ዘሥጋ በሊቀ ነብያቱ ሙሴ አማካኝነት ተሸግረው ምድረ ርስት ገብተዋል ። እግዚአብሔር ሙሴን አዞት ባሕሩን በበትሩ በመታው ጊዜ ባሕሩ እንደግድግዳ በግራና በቀኝ ቆመ። በዚህ መሐል እስራኤል ዘሥጋ አልፈዋል ግን በኃላ ያልተፈቀደላቸው የፈርዖን ሰራዊቶች ወደ ተከፈለው ባሕር ሲገቡ ሰጥመው ቀርተዋል። /ዘደ **14÷15-31/**

1.2/ ሙት ባሕር

ይህ የሙት ባሕር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ መጠሪያዎችን ይዟል እነሱም አንደኛው ባሕረ ሎጥ ይባላል።ይኸውም የተባለበትም ምክንያት ሰዶምና ጎሞራ ተቃጥላ ከመጥፋቷ በፊት ቦታው የብስ ነበር የሰዶምና የጎሞራ ሰዎች ኃጢአታቸው ሲበዛ እግዚአብሔር ለሎጥ መላእክትን ልኮ አድኖት ሰዶምና ጎሞራ ሁለቱም ከተሞች በእሳት ጠፍተዋል ። በዚህ ነው ባሕረ ሎጥ እየተባለ የሚጠራው ቦታውም በውኃ ተሞላ የዮርዳኖስ ወንዝም ሄዶ በዚሁ ባሕር ነው የሚገባው። ሌሎችም ወንዞች ወደዚህ ባሕር ይገባሉ። የዮርዳኖስ ወንዝ በቀን ለዚህ ባህር **6** ሚሊዮን ቶን ውኃ ይገብራል። ሁለተኛው “የሙት ባህር” ይባላል። ይህም በውስጡ አንዳች ሕይወት ያላቸው ነገሮች ስለማይገኙበት በዙሪያ በድኝና ቅጥራን የተከበበ ስለሆነ ሕይወት ያለው ነገር ፈጽሞ አይገኙበትም ለዚህ ሙት ባሕር እየተባለ ይጠራል ።ሦስተኛው የጨው ባሕር እየተባለ ይጠራል። ምክንያቱ ከባሕሩ 1 ሊትር ውኃ ውስጥ 1 ኪሎ ጨው ይወጣበታልና የጨው ባሕር እየተባለ ይጠራል። ባሕሩ **88** ኪ.ሜ ርዝመት አለው። ከባሕር ወለል በታች **467** ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል ። ባሕሩ ከኢየሩሳሌም በስተምስራቅ ከኢያሪኮ በስተደቡብ የሚገኝ ነው።

1.3/ የገሊላ /ጥብርያዶስ/ ባሕር

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*` „Ê¡e }ªIÊ

ይህ ባሕር የተለያዩ መጠሪያዎች አሉት።ይኸውም ገሊላ ጥብርያዶስ ጌንሳሬጥ በመባል ይታወቃል።ግን የጥንቱ ስሙ የገሊላ ባሕር ይባል ነበር። /ዙኑ **34÷11/** ይህ ባሕር አጠገብ ጥብርያዶስና ጌንሳሬጥ የሚባሉ ሁለት ከተሞች አሉ ባሕሩ ሁለቱን ስያሜ ያገኘው ከከተሞቹ ነው። ሄሮድስ አንቲጳስ የገሊላ ባሕር ምዕራባዊ ዳርቻ ከተማ ከመሰረተ በኃላ የቄሣር ጢባርዮስ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ስሙን ጥብርያዶስ አለው። በዚህም ስያሜውን አግኝቷል። ይህ ባሕር ርዝመቱ **4.5** ኪ.ሜ ሲሆን ወርዱ **8** ኪ.ሜ ነው። የባሕሩ ጥልቀት በአማካኝ **208.5** ሜትር እስከ **213** ሜትር ከባሕር ጠለል በታች ነው። በዚህ ባሕር ላይ ጌታችን ብዙ ተአምራትን አድርጓል።

የቤት ሥራ

1/ ጌታችን በገሊላ /ጥብርያዶስ / ባሕር ላይ ያደርገውን ተአምራት ምን ምን ናቸው። ዘርዝራችሁ ጻፉ ።

2/ ምንጮች

ምንጮች የምንላቸው እንደ ባሕር ያልሰፉ ትናንሽ የሆኑትን ለመጠጥነት የምንጠቀምባቸውን ምንጮች እያልን እንጠራቸዋለን። እንደዚህ ዓይነት ምንጮች ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዘግበው እናገኛቸዋለን እነሱም የያዕቆብ ምንጭ የአጋር ምንጭ የቤተልሔም ምንጭ ናቸው ። እነዚህን ዘርዝረን እንመልከት።

2.1/ የያዕቆብ ምንጭ

ይህ የያዕቆብ ምንጭ ሲካር በምትባል የሰማርያ ከተማ ውስጥ ትገኛለች ሲካርም ከሴኬም በአንድ ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ናት። ይህ የያዕቆብ ምንጭ በያዕቆብ ወልደ ይስሐቅ ስም የተሰራችው ያዕቆብ ከአጎቱ ከላባ አገር ከሶርያ ወደ ከነዓን ምድር ወዳለች ወደ ሴኬም ከተማ መጥቶ የነበረው የእርሻ ማሳ ከኤምር ልጆች በመቶ በጎች ገዝቶ በዚያም ያዕቆብ የራሱን ምንጭ ሰርቶ እሱም ቤተሰቡም ከዛች ምንጭ እየጠጡ ኖረውበታል። /ዘፍ **33÷18-20/** በዚህ የያዕቆብ ምንጭ እየተባለ መጠራት ጀመረ። ከዚህ ምንጭ አጠገብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት መጠጥ /ውኃ/ መሆኑን አስተምሮበታል።

የቤት ሥራ

1/ በዚህ ምንጭ ጌታችን ራሱን በሕይወት ውኃ መስሎ አስተምሯል እንዴት እንዳስተማረ ዘርዝራችሁ ጻፉ።

2.3/ የቤተልሔም ምንጭ

ይህ የቤተልሔም ምንጭ ከሰሊሆም መጠመቂያ በስተምስራቅ በዳዊት ከተማ ከበሩ አጠገብ ትገኛለች። ዳዊት ከፍልስጥኤማውያን ጋር በተዋጋ ጊዜ በራፋይም ምሽግ ተሸሽጎ ሳለ ከቤተልሔም ምንጭ ውኃ ማን ያጠጣኛል ሲል ወታደሮቹ ጠየቀ ሦስቱ ወታደሮቹም ኢዮአብ አሳኤልና አቢሳ ከፍልስጤማውያን ጋር ተዋግተው ዳዊት ሊጠጣ የፈለገውን አመጡለት በዚህ ጊዜ ዳዊት ያንን የቤተልሔም ምንጭ ውኃ ከጠጣሁ ደም ይሆንብኛል ይህ ለኔ ለማምጣት ተዋግተዋልና ብሎ የወደደውን ውኃ አፈሰሰ።/ዜና **11÷15-19/** በውዳሴ ማርያም ሐሙስ ላይ እንደተጠቀሰ ‹‹ዳዊት ዘነግሥ ለእስራኤል አመይትነሥኡ ላዕሌሁ ዕልዋን ፈተው ይስተይ ማየ እም ዓዘቅታ ቤተልሔም ፍጡነ ተንሥኡ መላሕቅተ ሐራሁ ወተቃተሉ በውስተ ትዕይንት ዕልዋን ወአምጽኡ ሎቱ ውእቱ ማየ ዘፈተወ ይስተይ ወሶበ ርእየ ውእቱ ጻድቅ ከመ አጥብኡ ወመጠወ ነፍሶ ለቀትል በእንቲአሁ ከዐወ ውእተ ማየ ወኢሰትየ እምኔሁ ወእምዝ ተኾለቆ፦ ለእስራኤል የነገሰ ዳዊት ጠላቶቹ በተነሱበት ጊዜ ከቤተልሔም ምንጭ ውኃ ይጠጣ ዘንድ ወደደ የጭፍቹንም አለቆችም ፈጥነው ተነሱና በጠላቶቹ ከተማ ተዋግተው ሊጠጣ የወደደውን አመጡለት ጻድቅ ዳዊት ግን ጨክነው ሰውነታቸውን ስለ እርሱ ለጦርነት ለሞት አሳልፈው እንደሰጡ ባየ ጊዜ ያን ውኃ አፈሰሰ ከእሱም አልጠጣም ከዚህ በኋላ ለዘለአለም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት›› ብሎ ቅዱስ ኤፍም ሶርያዊ በውዳሴ ማርያም ላይ እንደተናገረ።

3/ ወንዞች

በእስራኤል ሀገር ካሉ ወንዞች በርካታ ወንዞች አይታወቁም። ሆኖም ከታቦር ተፈራ የሚመነጨው ሲሆን ከገሪዛን ተራራ የሚመነጭ ቃና ከኬብሮን ኮረብታ የሚመነጭ ሶሪክ ከአርሞንኤም ተራራ የሚመነጭ ዮርዳኖስ ከኢየሩሳሌም ተነስቶ ወደ ዮርዳኖስ የሚፈስ ቄድሮስ ከሀገራችን ከኢትዮጵያ መንጭቶ የሚጓዘው ግዮን የመሳሰሉ ወንዞች ይገኛሉ። እኛ ግን ጥቂቱን ወስደን ለምሳሌ ያህል እንመልከት ።

3.1/ የዮርዳኖስ ወንዝ

የዮርዳኖስ ወንዝ ከላይ ከገሊላ ምድር ከአርሞንኤም ተራራ ይመነጫል ከሰሜን ወደ ደቡብ የሁልጎን ሐይቅ አቋርጦ ይወጣና ወደ ገሊላ ባሕር ገብቶ እንደገና የገሊላን ባሕር ለሁለት ክፍሉ ወደ ሙት ባህር ይጓዛል ። እዚያግን ገብቶ ይቀራል ወንዙ **320** ኪ.ሜትር ርቀት አለው እስከ **3** ሜትር ጥልቀት እና እስከ **30** ሜትር ስፋት የሚደርስበት ወቅት ይኖራል። በዚህ ወንዝ ጌታችን ተጠምቆ የእዳ ደብዳቤያችንን ደምስሶ ጥምቀታችንን ቀድሶልናል። እነ ኢዮብ ንዕማን በዚህ ወንዝ በብሉይ ተጠምቀዋል። እስራኤል ዘሥጋ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ይህን ወንዝ ተሻግረው ከነዓን ገብተዋል። ኤልያስ ይህን ወንዝ ተሸግሮ ዐርጓል።አብርሃምም ይህንን ወንዝ ተሸግሮ ከመልከ ጼዴቅ ጋር ደርሷል።

<u>የቤት ስራ</u>

1/ ኤልያስ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሸግሮ እንዴት ሊያርግ እንደቻለ አብራርታችሁ ጻፉ**?**

2/ ንዕማን በዚህ ወንዝ እንዴት ሊጠመቅ ቻለ በመጠመቁስ ምን አገኘ**?**

3.2/ <u>የግዮን /ዓባይ/ ወንዝ</u>

የግዮን ወንዝ በኢትዮጵያ የሚመነጭ ወንዝ ነው። የዮርዳኖስ ወንዝ የገሊላ ባሕርን ለሁለት ሰንጥቆ እንደሚጓዝ የግዮን ወንዝም የጣና ሐይቅን ለሁለት ከፍሎ ወደ ሜድትራኒያን ይገባል። የግዮን /ዓባይ/ ወንዝ አጠገብ አስቀድሞ የካህኑ መልክ ጻዴቅ ወዳጅ የገበረው ኢትኤል የተሰጠውን ዕንቁ ይዞ ይኖር ነበር። ይህ ወንዝ ከኢትዮጵያ ተነስቶ ሱዳንን አጠጥቶ የግብጽ በረሀ ላይ በሰፊው ሰፎ የግብጽን ሀገር ያለመልማል ለግብጽ ሀገር እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዎ ያደረገ ወንዝ ነው። ይህ የግዮን /ዓባይ/ ወንዝ ከመነሻው እስከ መጨረሻው ያለው ርዝመት **6470** ኪ.ሜ ያህል ነው። የሙሴ ቤተሰቦች ፈርዖን ሕጻናትን ሲገል ልጃቸው እንዳይሞት ሙሴን ከዚህ ወንዝ ለቀው በኋላ የፈርኦኑ ልጅ ተርሙት ከዚህ ወንዝ እንዳነሳቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። /ዘጸ **2÷1-10/** በተጨማሪም ፈርዖን ሕዝበ እስስራኤልን አለቅም ብሎ ከወረደው መቅሰፍት አንዱ በግብጽ ሀገር ላይ ያለው ብቻ የግዮን /ዓባይ/ ወንዝ ደም ሆነ /ዘደ **6 ÷20-21/**

<u>እንስሳት በመጽሐፍ ቅዱስ</u>

እንስሳት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ ቦታ ላይ ተጠቅሰው ይገኛሉ። እነዚህም ከትናንሽ ፍጥረታት እስከ ታላላቅ ግዙፋን ፍጥረታት ድረስ በተለያ ሁኔታና ምሳሌ ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል የተወሰኑትን እንስሳት እንደየባሕሪያቸው የመሳሰሉት ይገኙበታል። በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰው ከሚገኙ እንስሳት ውስጥ <u>ለምሳሌ፦ ርግብ</u>፣<u>በግ</u>፣<u>ፍየል</u>፣<u>ዋኖስ</u>፣<u>ዋልያ</u>, <u>ንሥር</u> ፣<u>ላም</u>፣ <u>አህያ</u> <u>ሰጎን</u>፣ <u>አንበሳ</u> ፣<u>ገብረ ጉንዳን</u>፣ <u>የሜዳ አህያ</u> ፣<u>አርያ</u>፣ <u>ውሻ</u>፣ <u>እንሽላሊት</u>፣ <u>አንበጣ</u>፣ <u>እባብ</u>፣<u>ቀበሮ</u>፣<u>ቁራ</u>፣<u>ተኩላ</u>፣<u>እፉኝት</u> ፣<u>ዓሳ</u>፣ የመሳሰሉ ናቸው። ከዚህ በመቀጠል ለምሳሌ ያህል ጥቂቶቹን በዝርዝር እንመለከታለን።

1/ <u>ርግብ</u>

ርግብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ የምትነሳ ከአዕዋፍ ወገን የሆነች እንስሳ ናት። ርግብ መጥዳት ወራት ሲፈፀም ለመስዋዕት ትቀርብ ነበር። /ዘሌ፡**12÷6-8**፡ ሉቃ **2÷22-24/** ርግብ ሁላችንም እንደምናውቃት መልኳ ነጭ ነው። አንዳንዴ ሌላ አይነት መልክ ይኖራታል። ርግብ አብዛኛውን በየዋህነቷ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሳለች ጌታችን እኳን ሐዋርያትን ሲልካቸው “እንደ እባብ ልባም እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ” /ሜቴ **10÷16/** ብሎ እንደተናገረው እንደውም ርግብ በየዋህነቷ የተነሣ በጥፋት ውሃ ጊዜ በእባብ አፍ ውስጥ እንቁላል ጥላለች ነገር ግን በፍፁም የዋህነቷ በእግዚአብሔር ቸርነት ተጠብቃ በእባብ አፍ ውስጥ ጫጩቶቿን ፈልፍላ ወጥታለች እናም ርግብ በዚህ የዋህነቷ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፡ በመንፈስ ቅዱስ በእመቤታችን ትመሰላለች ርግብ በጥፋት ውኃ ጊዜ ኖኅ ውኃው እንደ ቀነሰ እንድታይ ሲልካት መልክቷን ፈፅማ የወይራ ዝንጣፊ ይዛ በመምጣት የውኃውን መጉደል የምሥራች ለኖህ ይዛ መጥታለች። /ዘፍ.**8÷11/** እና ርግብ በተለያዩ ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስሟተመዘግቦ ትገኛለች።

2/ <u>በግ</u>

በግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት እንስሳት መካከል አንዱ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየዋህነታቸው ለተጠቀሱት የየዋሐን ምሳሌ መሆኑ ተጠቅሷል በግ አራት እግር ያለው ቆዳው በጸጉር የተሸፈነ ሥጋቸው ለምግብነት ከሚውሉ የቤት እንስሳት መካከል አንዱ ነው። ከምግብነት ባሻገርም ለእግዚብሔር መሥዋዕት ይቀርቡ ከነበሩት እንስሳት የመጀመሪያው ነው።/ዘፍ **4፥8/** በግ ከጠባዩ የተነሳ በቅዱሳን አባቶቻችን ይመሰላል። በተጨማሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግ በጌታችን መድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተመስሏል ።

የቤት ሥራ

1/ በግ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንደሚመስል አብራርታችሁ ግለፁ።

3) ፍየል

ፍየል በቆላ አካባቢ የምትኖር ቆዳዋ ስስ የሆነ በጸጉር የተሸፈነ ለማዳ የቤት እንስሳ ስትሆን ሥጋዋ ለምግብነት ቆዳዋ ደግሞ ለተለያዩ አገልግሎት ይውላል። በተለይም ቆዳው ለብራና በጣም ተፈላጊ ነው። ለልብስነት ያገለግላል /ዕብ **11÷37/** ፍየል በብሉይ ኪዳን ለመስዋዕትነት ከሚቀርቡ እንስሳት አንዷ ናት **(**ዘፍ **15÷19)** ፍየል አብዛኛውን ከጠባይዋ የተነሳ በኃጥአን ትመሰላለች ፍየል ቀንድ ያላት የቤት እስሳ ናት።

አሳይመንት፡- ጻድቃን በበግ ኃጥአን በፍየል ለምን እንደሚመሰሉ በዝርዝር አብራርታችሁ ጻፉ?

4) አህያ

አህያ የቤት እንስሳ ስትሆን ቁጥሯ ከማይበሉ እንስሳ ወገን ናት። እንደውም የጋማ ከብቶች ከሚባሉ ወገን ናት። እንደ ፈረስ በቅሎ የጭነት አገልግሎት በመስጠት ከፍተኛ ደረጃ ይዛለች። /በዘፍ **4÷26/** ‹‹እነርሱንም እህሉን በአህዮቻችሁ ላይ ጫኑ›› ተብሎ እንደተገለፀው ከጥንት ጀምራ በጭነት ስራ ትሰማራ እንደነበር ያሳየናል። በተጨማሪ ሰዎች ለመጓጓዣነት ከሚጠቀሙባቸው እንስሳትም አንዷ አህያ ናት “ወደ እግዚአብሔር ሰው በፍጥነት ደርሼ እመለስ ዘንድ አንድ ሎሌና አንድ አህያ ላክልኝ” ሲል /**2** ነገ **4÷22/** 1 ነገ **13÷11-25/** ላይ እንደተገለፀው አህያን ሰዎች ከጥንት ጀምረው ይጓዝባት ነበር። /ዙኑ **22÷21-35/** ላይ እንደተገለፀውም በለዓም የተባለ ሀብተመርገም የተሰጠው ሰው ከሞአቡ ንጉሥ ከባላቅ ጋር በተስማማው መሠረት እስራኤላውያንን ለመርገም በአህያ ላይ ተቀምጦ ጉዞ ጀመረ። በዚህ የእግዚአብሔር መልአክ በፊቱ ቆሞ ነበር። አህያዋም መልዕኩን አይታ ቆመች ቢቀጠቅጣት አልሔድም አለች። በዚህ ጊዜ አህያዋ አፍ አውጥታ “ሦስት ጊዜ የመታኸኝ ምን አድርጌህ ነው “ አለችው። በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በብሉይ ኪዳን በበላዓም ጊዜ አህያ እንደተናገረች ይገልጽልናል። በተጨማሪ ለሆሳዕና ጊዜ ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም የገባው በአህያዋ ላይ ተቀምጦ እንደገባ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። አህያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ምሳሌ ተመስላ ተገልጣለች።

የቤት ሥራ

1/ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ አህያ የምዕመናን ምሳሌ የሰላም የእስራኤልና የአሕዛብ የኦሪትና የወንጌል ምሳሌ ሆና ተገልጻለች ይህን ምሳሌነቷን አብራርታችሁ ግለጹ።

5/ ዓሣ

ዓሣ በባሕር ውስጥ የሚኖር የባሕር እንስሳ ነው። ዓሣ የሚተነፍሰው በጊል /በስንጥብ/ ሲሆን ከባህር ውስጥ ከወጣ ከጥቂት ሴኮንድ በኋላ ይሞታል ።ዓሣ በሰዎች ዘንድ ተወዳጅ የሆነ ምግብ ነው ። ዓሣ በመጽሐፍ ቅዱስ በምዕመናን ይመሰላል ጌታ ጴጥሮስ ዮሐንስ ያዕቆብ ዓሣ ሲያጠምዱ አግኝታችሁ “በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ” አላቸው። በዚህ ውስጥ ዓሣ የተባሉት ምዕመናን ወንጌሉ መረቡ ነው። ባሕሩ የዓለም ምሳሌ ነው። ወደ ዓለም ተልከው በወንጌል አስተምረው ምዕመናንን እንደሚያሳምኑ ሲናገር ነው። /ማቴ **4÷19/** በተጨማሪ ጌታ ሁለት ዓሣና 5 እንጀራ አበርክቶ **5000** ህዝብ መግቧል የነዚህም ምሳሌነታቸው ሁለት ዓሣ የፍቅር እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ ሲሆን የ 5 ቱ እንጀራ ደግሞ የአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ምሳሌ ነው። ዓሣ ከባሕር ሲወጣ መሞቱ ምዕመናንም ከሕገ እግዚአብሔር ሲወጡ በሥጋም በነፍስም ይሞታሉና።

6/ ንሥር

ንሥር ታላላቅ ከሚባሉ የወፍ ዝርያዎች አንዱ ነው። ንሥር እጅግ ፈጣን አይኑም በርቀት ላይ ያለ ነገርን መመልከት የሚችል የወፍ ዝርያ ነው ። ንሥር በሰማይ እየበረረ ከባሕር ውስጥ ዓሣ ሲያይ ፈጥኖ ጠልቆ ከሰማይ ወደ ባሕሩ ይወርዳል። ይህ የሚያሣየን የንሥር ዓይን ሩቅ ያለውን ነገር መመልከት እንደሚችል ነው። ንሥር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንዳንድ ክፍሎች ውስጥ ተዘግቦ ይገኛል። ተረፈ ኤር **10÷12** ላይ እንዳለው የባሮክን ደብዳቤ ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን በምርኮ ወደ ነበረው ነቢዩ ኤርምያስ ያደረሰው ንሥር ነው። ንሥር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም በፈጣንነቱ ሲመሰል “ከንሥር ይልቅ ፈጣኖች ነበሩ” /**2** ሳሙ **1÷23/** ተብሎ ተጠቅሷል። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያደረገውን ቸርነቱን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል። “ከግብፃውያን ያደረኩትን በንሥርም ክንፍ እንደተሸከምኳችሁ ወደ እኔም እንደመጣችሁ

አይታችኋል” ዘዳ **19÷4** ላይ እንደተገለፀው። ንሥር በሰማይ ሲበር የሚያስተጓጉለው እንቅፋት የሚሆነው ነገር የለም። እኔም እናንተን ከግብፃውያን ከባርነት ግዛት ሳወጣችሁ የቀትር ሐሩር እንዳያቃጥላችሁ በደመና ጋርጄ የሌሊት ግርማ እንዳያስደነግጣችሁ ብርሃንን አብርቼ በባሕረ ኤርትራ እንዳትሰጥሙ ባሕሩን ከፍዬ በቸርነት ያወጣኋችሁ እኔ ነኝ ሲል ነው። ልክ እንደዚህ በምሳሌም ንሥር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል ። ንሥር የወንጌላዊው የቅዱስ ዮሐንስ ምሳሌ ነው። /ኢዮ **39÷27-29**፣/ኢሳ **40÷31** ራዕ **4÷7**፣ ተ ኤር **11÷8** /

የቤት ሥራ

1/ ንሥር እንዴት በወንጌላዊው ዮሐንስ ትመሰላለች አብራርታችሁ ጻፉ ?

17/ እፉኝት

እፉኝት ዝርያዋ ከእባብ ነው። ነገር ግን እፉኝት ለየት የሚያደርጋት ጠባይ አለ ይህም ሀይለኛና ተናዳፊ እባብ ናት። እፉኝት አፈማህፀኗ ጠባብ ስለሆነ በተራክቦ ጊዜ ዘር ሲሰጥ ወንድዬው ብልቱ ተቆርጦ ይሞታል። መውለጃዋ ሲደርስ መውጪያ ስለሌላቸው ልጆቿ ሆዷን ቀደው ይወጣሉ። እፉኝት ስትወለድ እናቷንም አባቷንም ትገድላለች። እፉኝት በዚህ ለየት ባለ ጠባይዋ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምሳሌ ተጠቅሳለች ይኸውም “እነሆ አስማት የሚከለክላቸውን እባቦችንና እፉኝቶችን እሰድባችኋለሁ እነርሱም ይነድፏኋል” /ኤር **8÷17/** ሲል እንደተገለፀ ስለ ሐሳውያን መሲህ መንገድ ጠራጊዎች መስሎባቸዋል ። ልክ እንዚሁም በማቴ **3÷7** ላይ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ለፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን “እናንተ የእፉኝት ልጆች” ብሏቸዋል። የእፉኝት ልጆች ያላቸው እፉኝት በምትወልድበት ጊዜ አባቷንም እናቷንም እንደምትገድል እናንተም እንደ አባት የሚሆኑትን ነቢያትን የገደላችሁ እንደ እናት የሚሆኑትን ሐዋርያትን የምትገድሉ ሲላቸው ነው። ልክ እንደዚህ እፉኝት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምሳሌነት ተዘግባለች ። በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደዚህ በምሳሌም በተለያዩ ነገሮች እንስሳቶች በመጽሐፉ ውስጥ ተጠቅሰዋል። ግን ከላይ የጠቀስናቸው ብቻ አይደለም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ያልተጠቀሱ በርካታ እንስሳቶች አሉ። እነዚህ ለምሳሌ ያክል የጠቀስናቸው ናቸው።

ዕፅዋት በመጽሐፍ ቅዱስ

በበረሃ ከሚገኙ ወቅታዊ ከሆኑ ቁጥቋጦዎች እስከ ትላልቅ ዛፎች ያሉ የዕፅዋት ዘር ከማታዩባቸው በረሃዎች እስከ በጥቅጥቅ ደን እስከተሸፈኑ ቦታዎች በመጽፍ ቅዱስ ውስጥ ተዘግበው ይገኛሉ። ዕፅዋት የዕለት ሠሉስ /ማክሰኞ/ ፍጥረታት ናቸው። እነዚህ ጠቅለል ብለው ዕፅዋት አዝርትና አትክልት ናቸው። እነዚህም ዕፅዋቶች ከእሳት ስለተፈጠሩ ሲፈተጉ እሳት ይወጣል። ከመሬት ስለተፈጠሩ ቆርጠን በምንጥላቸው ጊዜ ይበሰብሳሉ በውኃ ስለተፈጠሩ በምንቆርጣቸው ጊዜ ውኃ ደም ወተት ነገር ከላያቸው ላይ ይወጣል በነፋስ በመፈጠራቸው በነፋስ ያድጋሉ ። ከዚህ በተጨማሪ በዝናብ ይበቅላሉ በነፋስ ያድጋሉ በፀሐይ ይበስላሉ ከመሬት ምግባቸውን ይገኛሉ። እነዚህ ዕፅዋት አዝርዕትና አትክልት አበቃቀላቸው የተለያየ ነው። በክረምት ደርቀው በበጋ የሚለመልሙ ለምሳሌ በለስ ወይንም እንዶን የመሳሰሉ ሲሆን በክረምት ቅጠላቸውን አራግፈው በበጋ ይለመልማሉ ሌሎች ደግሞ ክረምት ለምልመው በጋ የሚደርቁ አሉ። ለምሳሌ አበቦች የመሳሰሉት በክረምት ለምልመው በበጋ ቅጠላቸው የሚረግፉ ናቸው ልክ በእንደዚህ ዓይነት ተፈጥረው የሚበቅሉ ልዩ ልዩ የዕፅዋት ዓይነቶች በመጽሐፍ ቅዱሳችን ተጠቅሰዋል ምንም እንኳ በፍጥረታቸው በአንድ ስም ዕፅዋት ተብለው ቢጠቀሱም እንደሚሰጡት አገልግሎትና እንደ አስፈላጊነቱ ስያሜ አግኝተው የሚጠሩትን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዘግበው የምናገኛቸውን ዕፅዋቶች ከዚህ ቀጥለን በተራ እንመለከታለን

1/ ወይን

ወይን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ሥፍራ ከተሰጣቸው ዕፅዋቶች ውስጥ አንዱ ነው ወይን ከጥንት ከብሉይ ዘመን ጀምሮ ሰዎች ይመገቡት የነበረ ፍሬ ነው። በሀገረ እስራኤልም ከጥንት ጀምሮ በከፍተኛ ደረጃ ይመረታል ለምሳሌ ‹‹ኖኅም ገበሬ መሆን ጀመረ ወይንም ተከለ›› ተብሎ በዘፍ **9÷20** ላይ እንደተጠቀሰውና መልከ ጼዴቅም እንጀራንና የወይን ጠጅን አመጣ ተብሎ በዘፍ **14÷18** ላይ እንደተዘገበው ከጥንት ጀምሮ ይጠመቅ የነበረ ለምግብነት ይገለገሉት የነበረ ዕፅዋት እንደሆነ እንረዳለን የወይን እርሻ ዙርያ ቅጥር ይቀጠርለት ነበር። በመከር ለመብል በደረሰ ጊዜ ጠባቂ ይቀጠርለት ነበር።ከላም ከቀበሮዎች ከሌቦች ከመንገደኞች ለመጠበቅ ቀን ከለሊት ይጠበቃል። ከእርሻውም አጠገብ የመጥመቂያ ጉድጓድ ይሰራለታል በዓመቱ ይገረዛል። የወይን ጠጁን ለማውጣት ፍሬውን በመጠመቂያው ጉድጓድ ውስጥ ይረገጣል ። ሐረጉም በመደገፊያ ይዘረጋል። /ኢስ **16÷10**÷ኢሳ **5÷1-2** መኃ **2÷15** ማር /**2÷1**/ በዚህ መሰረት ወይን ጠጅ እያወጡ ይጠጡ ነበር ። ወይን ጠጁን ለቁስል መድኃኒትነት ይጠቀሙ ነበር። /ሉቃ **10÷34**/ ወይን በብሉይ መስዋዕት ሆኖ ይቀርብ ነበር። በሐዲስ ኪዳን ደግሞ የቅዱስ ደሙ ምሳሌ ነው። ዮሐ **6÷54**

የቤት ስራ

1/ የወይንን ምሳሌነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አብራርታችሁ ጻፉ?

2/ በለስ

በለስ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነ ዕፅ ሲሆን ሲቆረጥ ወይም ቅጠሉ ሲቀነጠስ ወተት መሰል ደም ይወጣዋል። በለስ አጭርና ከቁጥቋጦ የሚመደብ ተክል ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች በለስ ሰዎች ከቤታቸው ጓሮ ይተክሉታል። በለስ ልክ እንደ ወይን በሀገር እስራኤል ለምግብነት ይውላል። በለስ በገነት ከሚበቅሉ ከሦስቱ ዕፅዋት አንዱ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስም ስለ በለስ እንዲህ ተብሏል ‹‹ስንዴ ገብስም ወይን፣ በለስም ሮማንም ወይራም ማርም ወደ ሞሉባት ምድር ሳይጎድልህ እንጀራን ወደ ምትበላበት ምድር ያገባሃል›› ሲል የበለስን ምግብነት መናገሩን ያመለክታል /ዘዳ **8÷8/** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማለዳ ወደ ከተማ ሲመለስ ተራበ በመንገድም አጠገብ በለስ አይቶ ወደ እርሷ መጣ ከቅጠልም ብቻ በቀር ምንም አላገኘባትምና እያለ የሚገልጸው ጌታችን በሥጋ በመራቡ ወደ በለሲቱ ሲሔድ ፍሬ አለማፍራቷ በዛም መራገሟን ነው። የሚያትትልን በዚህ ውስጥ በለስ ለምግብ አገልግሎት እንደሚውል እንረዳለን ። /ማቴ 21÷1 ጀምሮ/



የበለስ ዛፍና ፍሬው

3/ ስንዴ

ስንዴ በዓለማችን ላይ በበርካታ ክፍሎች /ሀገራት/ በጣም የተለመደ የምግብ እህል ነው። ገብስ በመካከለኛው ምሥራቅም እንጀራና ቂጣ የሚጋገረው ዳቦ የሚደፋው በስንዴ ነው። ስንዴ እንደዚህ ባለ አገልግሎት የታወቀ ነው። በሀገራችንም ለዳቦ ለቆሎ ለመሳሰሉት የሚውል እህል ነው። ስንዴ ገለባውና እንክርዳዱ እንደዚሁም አፈሩ ተለቅሞ ይበጠርና ታጥቦ ሲያበቃ ከቤት ጣሪያ ላይ ይሰጣል። ከደረቀም በኃላ ወደ ጎተራ ይከታተል ጎተራው ከሥር የእህል ማውጪያ ቀዳዳ አለው ። እህል የሚፈጩት በቤተ ወፍጮ ሲሆን የወፍጮው መጅ ለሁለት ሴቶች እንዲያመች ሆኖ የተሰራ እጀታ ለዚህ እኮ ነው ጌታችን ‹‹ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ አንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች›› ብሎ ማቴ **24÷4** ስለማንነቱ የተናገረው ስንዴ ከምግብነት በተጨማሪ በብሉይ ለመስዋዕት ይቀርብ ነበር። /ዘፍ **4÷1/** መልከጼዴቅ ለአብርሃም ያመጣው ኅብስተ አኮቴት ከስንዴ የተዘጋጀ ነው። /ዘፍ **14÷18-20** / አይሁዶች በዓለ ሸዊት /የእሸት በዓል/ ብለው ከፋሲካ እስከ **50** ኛው ቀን ያከብሩት የነበረው በዓል ይህንኑ ነው። ‹‹እርሱም የስንዴ መከር በኩራት ነው›› እንዲል /ዘደ ***34÷22/*** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንጀራ እየተባለ የተጠቀሰው ከስንዴ የተሰራ ነው። በሐዲስ ኪዳን የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋው ምሳሌ ነው ። ዮሐ **6÷54**

4/ ዘንባባ

ዘንባባ የሰሌን ተክል ነው። በብሉይ ኪዳን የዳስ በዓል ሲከበር እስራኤል ለዳስ መሥሪያ ከሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች አንዱ ነው። /በነህ **8÷14-15** / ላይ እንዲህ ተብሎ እንደተገለፀው “የዘይትና የበረሃ ወይራ የባርስነትም የዘንባባም የለመለመውን ዛፍ ቅርንጫፍ አምጡ” እንደተባለ በብሉይ ኪዳንም ለእግዚአብሔር ምስጋናቸውን ይገልጡበት ነበር። አብርሃም ይስሐቅ በተወለደ ጊዜ ዘንባባ ይዞ አመስግኗል። መ.ኩፋሌ **13÷21** ዮዲት የእስራኤላውያን ጠላት የናቡከደነፆር የጦር አበጋዝ የሆነውን ሆሎፎርኒስን በገደለች ጊዜ ዘንባባ ይዛ

እግዚአብሔርን አመስግናለች። መ.ዮዲት 15÷12 በሆሳዕና ዕለትም ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው የነበሩ ሰዎች የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ጌታችንን ተቀብለውታል። ራእ 7÷9 ጻድቃን በዘንባባ ይመስላሉ ጻድቃን እንደዘንባባ ያፈራሉና።ይኸውም በመዝ 91÷12 ላይ እንደተጠቀሰው።

5/ <u>የሾላ ዛፍ</u>

የሾላ ዛፍ ቅጠሉ ስፋት ያለው አንድ ዓይነት ዛፍ ነው። ፍሬውም ለሰውና ለእንስሳት ምግብ የሚሆን ነው። /1 ዘና 27÷28 ሉቃ /9÷4/ በተጨማሪ የሾላ ዛፍ ቅጠሉ ሠፊ ስለሆነ ሰዎች ከፀሐይ ሐሩር ይጠላሉበታል። የሾላ ዛፍ ትልቅ ቅጠሉም ሰፊ ቢሆንም ፍሬው ግን ትናንሽ ፍሬ ናቸው። ለዚህ እኮ ነው አንድ ሰው ከሾላ ዛፍ ሥር ከፀሐይ ተጠልሎ ሳለ ሲመለከት ዛፉ ትልቅ ነው ፍሬው ግን ትንሽ ነው። ካጠገቡ ደግሞ የዱባ ተክል አየ።ይህም ዛፏ ትንሽ ፍሬው ትልቅ ነው በዚህ ጊዜ በእግዚአብሔር ሥራ ገብቶ እግዚአብሔር ተሳስተሀል የሁለቱን ዛፎች ፍሬ አቀያይረሃል አለ። በዚህ ጊዜ እንቅልፍ አሸለበውና ተኛ በዚህ ጊዜ የሾላዋ ፍሬ ከአፍንጫዋ ላይ ወድቃ አደማችው ሲነሳ የሾላዋ ፍሬ ወድቃበት አፍንጫውን አድምታዋለች በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር አንተ ትክክል ነህ እንደ እኔ ሀሳብ ቢሆን ኖሮ ዱባው ከላዬ አርፎ በገደለኝ ነበር አለ ይባላል። ይህ ታሪክ የሚነግረን የሾላ ዛፍ ትልቅ ነው ነገር ግን ፍሬው ትንሽ መሆኗ ነው።

6/ <u>ከርቤ</u>

ከርቤ በበረሀ የሚበቅል ሲሆን *ሙጫው መራራ* እና ሽቱ ለመስራትም የሚያገለግል ተክል ነው። /ዘደ ***30÷23***።/ <<በልብሳችሁ ሁሉ ከርቤና ሽቱ ዘውድም አለ>> በማለት ከርቤ ጥሩ ሽታ እንዳለው ይነግረናል። /መዝ. ***44÷8***/ ጌታችንና *መድኃኒታችን* ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል ወርቅ ዕጣን ከርቤ ገብረውለታል /ማቴ ***2÷11***/ ወርቁን ለመንግስቱ እጣኑን ለክህነቱ ከርቤውን ስለኛ ሲል በፈቃዱ ለተቀበለው ሞቱ አምጥተውለታል ጌታችንን የገነዙት ዮሴፍ ዘአርማትያስ እና ኒቆዲሞስ ከርቤውን ከአሬት እና ሽቱ ጋር በመቀላቀል ሰውነቱን ቀብተውታል በተልባ እግር ገንዘው ነበር የቀበሩት። /ዮሐ. ***19÷39***/

በአጠቃላይ በአገልግሎታቸው በሚሰጡት ጠቀሜታ የተለያየ ስያሜ የተሰጣቸው ዕፅዋቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዘግበው የሚገኙት በዝርዝር ተመልክተናል። ነገር ግን ከላይ ያየናቸው /የዘረዘርናቸው/ ብቻ ሳይሆኑ በርካታ ያልተጠቀሱ ዕፅዋት አሉ። ሆኖም ከላይ ያየናቸው ለምሳሌ ያህል ጠቅሰናቸዋል።

<u>አሳይመንት</u> <<ወይራ እጣን ሰናፍጭ>> እነዚህን ዕፅዋቶች እንዴት እነደሚበቅሉ የሚሰጡትን አገልግሎትና ምሳሌነት ካላቸው ምሳሌነታቸው ፅፋችሁ አምጡ>>

<u>በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የጦር *መሣሪያዎች*</u>

ሰዎች እርስ በርሳቸውና አራዊትን ማደን ከጀመሩበት ሰዓት ጀምሮ የተለያዩ የጦር *መሣሪያዎች* መሰራት ተጀምረዋል። ከድንጋይ ጀምሮ እስከ አዋንት ድረስ ከተለያዩም ብረታብረቶች ከዋንት ጊዜ ጀምሮ የጦር *መሣሪያዎች* ሆነው አገልግለዋል። ለመጀመሪያ የተገደለው አቤል የሞተው በድንጋይ ተገድሎ ነው።/ዘፍ ***4÷8***/ ሶምሶን *መ*ስፍኑንም ብንመለከት በአህያ *መ*ንጋጋ እልፍ የሚሆኑ ፍልስዋኤማውያንን ገድሏል። በዚህ መልኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን የጦር *መ*ሳሪያዎች እንመልከት። /መሳ ***15÷15***/

1/ <u>ጦር</u>

ጦር ጫፎቹ ሹል ሲሆኑ ሰዎች ብረትን በማሾል ለአደን እርስ በእርሳቸው ለመዋጋት ይገላገላሉ። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ከጎልያድ ጋር ለመዋጋት ወደሜዳ ሲወጣ ጎልያድ ጦር ይዞ ነበር። /1 ሳሙ ***17-7***/ በዚህ ጦር እየወረወረ ዳዊትን ለማጥቃት ቢሞክርም ጎልያድ ዳዊትን *መ*ግደል አልቻለም። የሮማውያን ወታደር የነበረው ሌንጊኖስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ግራ ጎኑን በጦር እንደወጋው /ዮሐ ***19÷34***/ ተገልጿል።በተጨማሪም ጌታንን ለመያዝ ወደ ጌቴ ሴማኔ የመጡ ፈሪሳውያንና የካህናት አለቆች ጋር የነበሩ ጫፎሮች ጦር ይዘው እንደነበር በዮሐ ***18÷3*** ላይ ተገልጸል።

2/ <u>ጋሻ</u>

ጋሻ ከተለያዩ ነገሮች ከብረት ከቆዳም ከነሐስ ከመሳሰሉት የሚሰራ ሲሆን በጦር ጊዜ ከተለያዩ የጦር *መሣሪያዎች* ለመመከት ለመከላከል የሚጠቅም በእጅ የሚያዝ የጦር *መ*ሳሪያ ነው። <<እኩሌቶችም ጋሻና ጦር ቀስትና ጥሩርም ይዘው ነበር>> /ነህ ***4÷16***/ ላይ እንደተገለጸው ጋሻ ራሱን የቻለ አንድ የጦር *መሣሪያ መ*ሆኑን እንገነዘባለን። ሌላው ጋሻ በመጽሐፍ ቅዱስ በእምነት በረድኤተ እግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ ተጠቅሷል። /ዘፍ ***15÷1*** ኤፍ ***6÷16*** መዝ ***34÷2***

3. ወንጭፍ

ወንጭፍ ውስጡ ድንጋይ ወይም ጠጠር ነገር ገብቶበት በማሽከርከር የሚታደንበት የጦር መሣሪያ ነው። በሀገረ እስራኤል በርካታ ጦርነቶች ተካሂደዋል። በነዚህም የጦር ጊዜያት እንደ ጦር መሳሪያ ከተጠቀሙባቸው ውስጥ አንዱ ወንጭፍ ነው። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ጎልያድን የሚያህል ግዙፍ ሰው የገደለው ያሸነፈው በወንጭፍ ነበር። /ሳሙ ***17÷40-49/*** እንደዚህ ባለመልኩ ለጦር መሣሪያነት ወንጭፍንም ይጠቀሙ ነበር።

4/ ሰይፍ

ሰይፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት የጦር መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ ነው። ሰይፍ በሁለቱም በኩል የተሳለ የጦር መሣሪያ ነው። ሰይፉ ከጎራዴ የሚለየው በሁለቱም በኩል በመሳሉ ነው። ግን አንዳንድ ሰይፎች በአንድ ቦታ ብቻ የተሳሉም ይገኛሉ። የዕብራውያን ሰይፍ በመሳል ይታወቃሉ። ለዚህ ነው። ፍልስጤማውያን ዕብራውያን /እስራኤላዊያንን/ ከመፍራታቸው የተነሳ በአንድ ወቅት ማንም ዕብራዊ ጦርና ሰይፍ እንዳይሰራ አዘው ነበር። /ሳሙ ***13÷19-22/*** ጌታችንን ለመያዝ የመጡት ቄፍሮች ሰይፍ ይዘው እንደነበረ /ሉቃ ***22÷53/*** ከዛ ውስጥ ሊቀ ሐዋርያቱ ጴጥሮስ የሊቀ ካህናቱን የቀያፋን ባርያ /አገልጋይ/ የነበረውን ማልኮስን ቀኝ ጆሮውን በሰይፍ መቶት ቆርጦት ነበር። /ዮሐ ***18÷10/*** ። በተጨማሪ ሰይፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቃለ እግዚአብሔር ይመስላል።/ኤፌ ***6÷17/***

ምዕራፍ ስድስት

የመጽሐፍ ቅዱስ አቆጣጠር እና መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ

የሰማንያ አሐዱ ቅዱሳት መጽሐፍት ዝርዝር አቆጣጠር


ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ የተለያዩ አቆጣጠሮች ቢኖሩም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የምትቀበለው ግን በፍትሐ ነገሥት መጽሐፍ ተዘርዝሮ እንደተቀመጠው **81** /ሰማንያ አሐዱ/ ቅዱሳት መጻሕፍትን ትቀበላለች። ይኸውም **46** የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እና **35** የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍ በአጠቃላይ **81** /ሰማንያ አሐዱ/ ቅዱሳት መጻሕፍትን ትቀበላለች። ነገር ግን በ **198** ዐ ዓ.ም የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን ተዘርዝረው ለየብቻቸው የተቀመጡት መጻሕፍት አሉ። እነዚህም፥-

- ፀሎተ ምናሴ ፥- ይህ መጽሐፍ ከ 2 ኛዜና መዋዕል ጋር ተደምሮ የሚቆጠር መጽሐፍ ነው።
- መዝሙር ዘሠለስቱ ደቂቅ
- ተፈረ ዳንኤል — መጻሕፍት ከትንቢተ ዳንኤል ጋር
- መጽሐፈ ሶስና — ው የሚቆጠሩ መጻሕፍት ናቸው
- ተረፈ ኤርምያስ
- መጽሐፈ ባሮክ — ሕፍት ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር ተደምረው
- ሰቆቃው ኤርምያስ — ቆጠሩ መጻሕፍ ናቸው።

እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው መጻሕፍት ተዘርዝረው ራሳቸውን ችለው ቢቀመጡም ሲቆጠሩ ግን ከእናት መጻሕፍታቸው ጋር ተደምረው ይቆጠራሉ።

አሳይመንት፥- ሰማንያ አንዱን ቅዱሳት መጻሕፍት ከእናት መጻሕፍታቸው ጋር ተደምረው መቆጠር ያለባቸውን ደምራችሁ በመቁጠር ጽፋችው አምጡ?

መናፍቃን ከማይቀበሏቸው መጻሕፍት ውስጥ ያሉ ቁም ነገሮች



እነዚህን መጻሕፍት ግዴታ እንድንቀበላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ይኸውም ለምሳሌ፦

1) ሔዋንና አባብ የተግባቡበት ቋንቋ የት ገባ?

በፍጥረታት መካከል እንስሳትና የሰው ልጆች የሚግባቡበት የጋራ ቀ E ንቀ E እንዳላቸው ሔዋንና አባብ ባደረጉት ንግግር መረዳት ይቻላል። ዘፍ **3-1-5** ታድያ ይህ ቀ E ንቀ E የት ገባ? 66 ቱ መጻሕፍት ይህንን አይገልጽም የዚህን ጥያቄ ርትዕት መልስ የምናገኘው ከ 81 ዱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዱ በሆነው ከመ.ኩፋሉ 5----8-!7 ላይ ነው።

2) የአዳም ልጆች ቃየልና ሴት ሚስት ከየት አምጥተው አገቡ?

ዘፍ **4-!7** ላይ ‹‹ቃየንም ሚስቱን አወቃት ፀነሰችም ሄኖዕንም ወለደች›› ይላል። በዘፍጥረት ላይ ሲገለጽ ከቃየል አቤል እና ሴት በስተቀር ሌላ ልጆች አልተጻፈም ታድያ ሚስታቸው እነማን ናቸው። ይህ በ 66 ቱ መጻሕፍት አይገኝም የሚገኘው በ 81 ዱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። እነሱም፦ ኩፋ 5-8!7 ላይ ‹‹ሄዋን በአምስተኛው ሱባኤ አዋንን ወለደች **-----** አዳም በስድስተኛው ሱባኤ ልጁ አዙራን ወለደ››። ይላልና።

3) ዘፍ **6-1-4** እንደምናነበው የእግዚአብሔር ልጆች በማግባታቸው እግዚአብሔር መንፈሱን በሰው ላይ ለዘለአለም አይኖርም እስኪል ያቆጣው ። እነዚህ የእግዚአብሔር ልጅና የሰው ልጅ የተባሉት እነማን ናቸው። በ 66 ቱ መጽሐፍ ቅዱስ አይጠቅስም መልሱን የምናገኘው በ 81 ዱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው።እሱም፦ ሔኖክ 9-!6-@3 ላይ በደብረ ቅዱስ የሰፈሩት የሴት ዘሮች የእግዚአብሔር ልጆች የቃየል ልጆች ደግሞ የሰው ልጆች እያለ ይገልጻል።

4) ዘንባባ ይዞ ማመስገን አመጣጡ እንዴት ነው?

ጌታችን ለሆሳና በአህያዋ ላይ ተቀምጦ በመጣ ጊዜ የዘንባባ ዝንጣፊና ልብሳቸውን አንጥፈው እንደተቀበሉት በዮሐ !2-!3 ላይ ተገልጻ E ል ። ለመሆኑ እንዲሂ ዓይነት ሥርዓት ከምን የመጣ ነው።

በብሉይ ኪዳን ይህ ሥርዓት ስለ ነበር ይኸውም አንድ ንጉሥ ሲሾም ልብሳቸውን አውልቀው እያነጠፉ ይቀበሉ ነበር።

ለምሳሌ፦ ኢዩን ነብዩ ኤልሳዕ ደቀመዝሙሩ ንጉሥ መሆኑን ያወቁ ልብሳቸውን እያወለቁ እያነጠፉ ተቀበሉት።ይኸውም እስራኤላውያን ላንተ እንገዛለን ሲሉነው። ለዚህ ልብሳቸውን አውልቀው መቀበላቸው ከብሉይ የነበረ ሥርዓት ነው።

- ዘንባባውስ ከየት መጣ ? ይህ ከ 66 ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም መልሱ ያለው በ 81 ዱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። ይኸውም ለምሳሌ፦

✓ ኩፋ **!3'@1** አብርሃም በእርጅና እድሜው ልጅ በወለደ ጊዜ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረበ። ‹‹ዘርህ እንደ ሰማይ ከዋክብት.....›› ብሎ ቃል የገባለት እንደተፈጸመ ባየ ጊዜ። አብርሃም የዘንባባ ዝንጣፊ ይዞ እግዚአብሔርን ያመሰገ ።ይስሐቅም እንደዚሁ ያዕቆብን ሲወልድ ዘንባባ ይዞ እግዚአብሔርን አመስግነው ነበርና። እንዲሁም

✓ ዮዲት **!5'!2 §YM** ላይም ××Ä ዮዲት ሆሎፎርኒስን በገደለችው ጊዜ ለእግዚአብሔር ምስጋና ለማቅረብ የዘንባባ ዝንጣፊ እንደያዘች ይናገራል። (አብርሐም በጎልማሳነቱ ቢውልድ አይገርምም ሆሎፎርኒስም በወንድ ቢገደል አይገርምም ነበር) ነገር ግን ይህ የሚያሳየን የእግዚአብሔር ኃይል እንደሆነ ነው። እንደዚሁ የኢየሩሳሉም ሰዎች በእኛ ኃይል ጠላታችንን ድል መንሳት በተሳነን ጊዜ ለአዳም በገባኸው ቃል ኪዳንህ ጠላታችንን ዲያቢሎስን ድል ነሳህልን ሲሉ የዘንባባ እንጣፊ ይዘው አመሰገኑ።

5) የምናሴ ጸሎት ምን ነበረ?

2z ዜና **#3-!8** §Y ላይ የሕሰቅያስ ልጅ ምናሴ እንደጸለየ ቢገልጥም ምን ብሎ እንደ ጸለየ ግን አናገኝም ለመሆኑ ምን ብሎ ጸለየ? የምናሴ ጸሎት የሚገኘው ‹ጸሎ ምናሴ›› በተባለው መጽሐፍ ላይ ብቻ ነው።ያለ ጸሎተ ምናሴ ሁለተኛ ዜናመዋል የተማ E ላ አይደለምና ለዚህ ደግሞ 81 ዱ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል መሆኑን ያስረዳናል።

6) ስለ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ የተነገረው ትንቢት እንዴት ተፈጸመ?

N ኤር **#9-!5-!8** §Y ላይ እግዚአብሔር ለኤርምያስ በግዞት ሳለ እንዲህ ሲል ነገረው ‹‹ሂድ ለኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ በዚህ ምድር ለበጎ ሳይሆን ለጥፋት እጄን እሰዳለሁ አንተን ግን አድንሀለሁ›› በለው ብሎታል ታድያ እግዚአብሔር እንዴት አዳነው? 66 ቱመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይገልጽም የሚገኘው በ 81 ዱ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ ነው።ይኸውም ተረፈ ኤርምያስ **8÷8-9-#** v ላይ። ታሪኩ ይገኛል ይኸውም አቤሜሌክ በበለስ ዛፍ ሥር ለ 66 ዓመት ሲተኛ እነ ኤርምያስ የመከራው ተካፋይ /ቀማሾች/ ነበሩ።በዚህ በበለስ ዛፍ ሥር አቤሜሌክ ተኝቶ የቀጠፋት በለስ ስንካ E ሳትጠወልግ በዚህ እንደ ዳነ ይናገራል።

7) ቅዱስ ማቴዎስ በተረፈ ኤርምያስ ላይ ያለውን ሐሳብ መጥቀሱ

ሐዋርያው ማቴዎስ በማቴ @7—--9 ላይ ‹‹በዚያን ጊዜ በነብዩ ኤርምያስ የተባለው ዕጣ ከእስራኤል ልጆችም አንዳንዶቹ የገመቱትን ፣የተገመተውን ዋጋ ***30*** ብር ያዙ ጌታም እንዳዘዘኝ ስለ ሸክላ ሠሪ መሬት ሰጡ የሚለው ተፈፀመ›› በማለት የጠቀሰው የኤርምያስን ትንቢት በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ አናገኘውም። ታድያ ሐዋርያው ከየት አምጥቶ ጠቀሰው በ 66* መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም የሚገኘው በ 81* መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው።ይኸውም በተረፈ ኤርምያስ 7-3 ላይ ተጠቅሶ ይገኛል።

8) ሐዋርያው ይሁዳ በሔኖክ መጽሐፍ ላይ ያለውን ሐሳብ መጥቀሱ

ይሁዳ በመልእክቱ ቁ !4 እና !5 ላይ ስለ ጌታ ምፅዓት የተናገረውን ‹‹ለወላጆቹ ይፍርድ ዘንድ እነሆ ከብዙ መላእክት ጋር ይመጣል። ህገ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎችና ሀጥአን በሱ ፈፅመው ስላደረጉት ነገር ስጋዊ ደማዊን ሁሉ ይወቅሳል›› አስቀድሞ የአዳም ሰባተኛ ትውልድ የሆነው ሔኖክ በመጽሐፉ ላይ ተናግሮ ነበር። ይህንንም በሔኖክ መጽሐፍ ላይ ያለውን ቃል ሐዋርያው ይሁዳ የአዳም 7ኛ ትውልድ የሆነው ሔኖክ ብሎ በመናገር ጠቅሶ መጻፉን ይነግረናል። ነገር ግን የሔኖክን መጽሐፍ በ 66* መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኝውም የምናገኘው በ 81* መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። ይኸውምበ ሔኖ 1-9 ላይ ተጽፎ ይገኛል።

ለቁጥሩ መለያየት መሰረታዊ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

ሀ) የአይሁድ ምክንያቶች

- ✓ አይሁዶች በ **90** ዓ.ም በጃሚ ጉባኤ ላይ ሊቃውንተ አይሁድ ከ 46 ቱ የብሉይ መጻሕፍት 39 ኙን ብቻ ለመቀበል ወስነዋል። የተቀሩትን 7 መጻሕፍት ግን ላለመቀበል መሰኑ ምክንያቱም፦
  - ➢ ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ የሚናገሩ በመሆናቸው።
    ምሳሌ፦-(ዕዝ **4-1**፣ሲራክ **@4-!)**
  - ➢ በግሪክ ቋንቋ ተጽፈው መገኘታቸውና አይሁዶች ግሪኮችን በመናቅ
  - ➢ መጽሐፈ ሔኖክና መጽሐፈ ኩፋሌን በወቅቱ አለመገኘታቸው።

ለ) የፕሮቴስታንቶች ምክንያት

- ✓ ከካቶሊኮች ጋር በነበራቸው ጥላቻና
- ✓ የሊቃውንተ አይሁድን ውሳኔ በመቀበላቸው

የብሉይ ኪዳን እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተወራራሽነት (ግንኙነት)

- ➢ የሁለቱ ኪዳናት አንድነት
  - ✓ ሁለቱም ዘመን የማይሽራቸው በመሆናቸው
  - ✓ ሁለቱም በእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነት በመጻፋቸው
  - ✓ ሁለቱም ፈጣሪ ፍጥረታት እግዚአብሔር እንደሆነና እርሱም በአንድነት በሦስትነት እንደተገለጠ በመግለጻቸው።
  - ✓ ሁለቱም ሰውን ወደ ቅድስና በመምራታቸው

- ✓ ሁለቱም ተመሳሳይ ሁኔታዎችን በመግለጻቸው

ለምሳሌ፦ ዘፍ !2- 1-4«‹‹...ከሀገርህ ከዘመዶችህ...››

ሐዋ 7- 1-8‹‹...ከሀገሮችህና ከዘመዶችህ ወጥተህ...››

ዘዳ 6-5፣ዘሌ !9-!8‹‹...ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ...››

ማቴ @2- #7-#9 ‹‹...ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ...›› ----ወዘተ


መሠረታዊ የመጽሐፈ ቅዱስ አጠናን ዘዴ

መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ይነበባል (ይጠናል)?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ለሚያመልኩ በሃይማኖት መንገድ ለሚጓዙ ሰዎች የሕይወት መመሪያ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር በመረጣቸው አባቶች አማካይነት የተጻፈ ቅዱስ መጽሐፍ ነው። ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሌሎች (ምኑናት) መጻሐፍት በተገኘው አጋጣ ሚ ቦታና ጊዜ ሚነበብ አይደለም (2ኛ ጴጥ 1÷20) ነገር ግን አንባቢው አንብቦት ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ ልዩ የሆነ ውሳጣዊና ልቡናዊ ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል።(2ኛ ጢሞ 3÷16) ይህምም የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት በእግዚአብሔር አመላካችን ቅዱስ ፈቃድ እና በመንፈስቅዱስ ምሥጢር ገለጭነት በቅዱሳን አባቶቻችን የተጻፈ መጽሐፍ ስለሆነ ራሱን የቻለ የአነባብ ይዘት አለው። ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ (ለማጥናት) አንባቢው (አጥኚው) ምን ማድረግ እንዳለበት ከዚህ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን።

ሀ. ቅድመ ዝግጅት ያስፈልጋል

ቅድመ ዝግጅት የሚባለው አንባቢው (አጥኚው) ለማንብ (ለማጥናት) ከመቅረቡ በፊት ቀድሞ ሊያመቻቻቸው ሊያዘጋጃቸውና ሊያሟላቸው የሚገባውን ነገር ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። ይህንንም ቅድመ ዝግጅት ለሁለት ከፍለን እንመለከታቸዋለን።ይኸውም፦



እነዚህን በሠንጠረዥ ውስጥ የጠቀስናቸውን መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበብ (ከማጥናታችን) በፊት ልናሟላቸው ልናዘጋጃቸውና ልናመቻቻቸው የሚገቡንን ነገሮች ከዚህ ቀጥለን በዝርዝር አብራርተናቸው እንመለከታቸዋለን።

አፍአዊ (ውጪያዊ) ዝግጅት

አፍአዊ (ውጪያዊ) ዝግጅት የሚባለው አንባቢው (አጥኚው) ለማንብ (ለማጥናት) ከመቅረቡ በፊት ከልቡናው አእምሮው ውጪ ሊያመቻቻቸው ሊያዘጋጃቸውና ሊያሟላቸው ሊያሰናዳቸው የሚገባውን ነገር ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። ይኸውም፦

- <u>የመጽሐፍ ቅዱስ መኖር</u>፦ ሰው ሁሉ የሚያነበው (ማጥናት የሚችለው) የሚነበብ (የሚጠና) መጽሐፍ ሲኖረው ብቻ ነው። በመሆኑም እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ማወቅና መፈጸም እንዲሁም ነገረ ሃይማኖትን ነገረ ቅዱሳንን ለመረዳት የሚፈልግ ሰው አስቀድሞ መጽሐፍ ቅዱስን ማግኘት (መግዛት) አለበት። ያለበለዚያ መጽሐፍ ቅዱሱ ሳይኖር መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት መሰናዳት ስለማይቻል። ለዚህ ከምንም በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ሊኖረን ይገባል።
- <u>ለጥናቱ የሚረዱ ሌሎች ሰነዶች (መጻሕፍት) መኖር</u>፦ መጽሐፍ ቅዱስ እንደባሕር ጥልቅ የሆነ ምሥጢር ያለበት መጽሐፍ ነው። ይህን መጽሐፍ በምናነብ (በምናጠናበት) ጊዜ ሊያግዙን ሊረዱን የተሰወረብንን ምሥጢር የሚገልጡልን የረቀቀውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አብራርተው አመሥጥረው ተንትነው የሚያስረዱን። ከእኛ የራቀውን የወንጌል ምሥጢር የሚያቀርቡልን መጻሕፍት (ሰነዶች) በአጠገባችን ሊኖሩ ይገባል። 2ኛ ጢሞ 4÷13
- <u>የሚነበበውን (የሚጠናውን) ክፍል መምረጥ</u>፦ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ሰው ለንባብ ከመቅረቡ በፊት የሚያነበበትን ቦታና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መምረጥ ይኖርበታል። ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ቃል የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ስለሆነ። በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ (የሚያጠና) ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ገልጦ ከማንበቡ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር የሚያደርገውን ንግግር ሊቋርጡ የሚችሉ ነገሮች በአካባቢው እንዳይከሰቱ ቦታና ጊዜ እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስም ክፍል በመምረጥ ማጥናት (ማንበብ) ይጠበቅበታል።ማቴ 6÷6 መዝ 1÷2-3 ማሳ 27÷7
- <u>ማስታወሻ (note) መያዝ</u>፦ የቀደሙት አባቶቻችን ‹‹በቃል ያለ ይረሳል በጽሑፍ ያለ ይወረሳል›› እንደሚሉት መጽሐፍ ቅዱስን በቃል ብቻ ማንበብ ለጊዜው በአንባቢው ጎሊና ውስጥ ከሚፈጥረው ስሜት በስተቀር ሊረሳ ይችላል። ይህ እንዳይፈጠር አንባቢው ያነበበውን እንዳይረሳ ከሚያነበው ውስጥ የሚገነዘበውን (የተረዳውን) የሚጽፍበት የማስታወሻ ደብተር **(note book)** ማዘጋጀት ይኖርበታል። 2ኛ ጴጥ 3÷15

<u>ውሳጣዊ (ውስጣዊ) ዝግጅት</u>

ውሳጣዊ (ውስጣዊ) ዝግጅት የሚባለውም አንድ ሰው ከላይ የዘረዘርናቸውን አፍአዊ (ውጪያዊ) ዝግጅቱን ካጠናቀቀ በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማንበብ ከመቀበጡ በፊት ልቡናው አእምሮው ሊያደርገው የሚገባውን ዝግጅት ነው። ይኸውም፦

- <u>የማንበብ ፍላጎት (ጉጉት) መኖር</u>፦ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ሰው አስቀድሞ የማንበብ ፍላጎት (ጉጉት) በውስጥ ሊኖረው ይገባል። ይህ ደግሞ የቅዱሳት መጻሕፍትን ጥቅም ከመረዳት የሚመጣ ነው። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ማለት ነው። ለሰው ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ከመነጋገር በላይ ክብር የለውም።ለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ሰው መጀመሪያ በውስጡ የመረጋጋት መንፈስ ሊኖረው ይገባል።
- <u>ውሳጣዊ መረጋጋት ሊኖረው ይገባል</u>፦ ውሳጣዊ መረጋጋት የመጽሐፍ ቅዱስን ምሥጢር ለመረዳት ከሚያስችሉ ነገሮች መካከል አንዱ ነው። የተረጋጋ ልቡና ያለው ነገረ እግዚአብሔርን ለማስተዋል ሰማያዊ ምሥጢርን ለመረዳት አይቸገርም። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት የተነሳ ሰው ቀድሞ የተረጋጋ ልቡና ሊኖረው ይገባል።ያለበለዚያ ተቻኩሎ ተጣድፎ በሐሳብ ተወጥሮ መጥቶ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ መሞከር ራስን አደጋ ውስጥ መጣል ነው የሚሆነው።ስለዚህ መጀመሪያ ራሱን ማረጋጋትና ውሳጣዊ መረጋጋትን መፍጠር ይሻላል።(ምሳ 1÷33 ፣ ምሳ 18÷15)
- <u>ጸሎት</u>፦ ‹‹ጸሎትሰ ይእቲ ተናግሮተ ሰብእ ኀበ እግዚአብሔር›› እንዲል ፍትሐ ነገሥት ጸሎት ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙበት ረቂቅ መንገድ ነው።(ፍት ነገ አንቀጽ 14) ሆኖም መጽሐፍ ቅዱን የሚያነብ ሰው እግዚአብሔር የተሰወረውን የወንጌል ምሥጢር እንዲገልጥለት እና ለስህተት እንዳይዳረግ (እንዲያድነው) መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበቡ (ከማጥናቱ) በፊት አጥብቆ መጸለይ ይኖርበታል።(ኤፌ 6÷19-20 ፣ ቆላ 4÷3-4 ፣ ማቴ 22÷29)

- ድካምን ማራቅ፦ ከሥራ ብዛት ይሁን ከጤና መታወክ የተነሳ የአእምሮም ሆነ የሥጋ ድካም የሚፈጠርበት ወቅት አለ። በዚህ ጊዜ መጻሕፍትን ከማንበብ ይልቅ ለሰውነታችን ዕረፍትን ልንሰጥ ይገባል። ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍትንም ለማንበብ ዝግጅት ስናደርግ ሥጋዊ ድካምንም ልንቀርፍ ያስፈልጋል። ምክንያቱም በሥጋዊ ድካም መጻሕፍትን ማንበብ ማለት ትርፍ የሌለው ኪሳራ ማለት ስለሆነ። ከድካማችን ብዛት የተነሳ ያነበብነውን አንዱንም ቃል ስለማንይዝ ስለማንረዳ። በመሆኑም መጻሕፍትን ለማንበብ በምንነሳበት ጊዜ ራሳችንን ለሥጋዊ ድካም ልናርቅ ይገባል። ማቴ 26÷43
- ከተለያዩ ሥጋዊ ሐሳብ አእምሮን ነጻ ማድረግ፦ ብዙ ከማሰብና ብዙ ከመጨነቅ የተነሳ አእምሮአችን በሐሳብ ሊወጠር (ሊጨነቅ) ይችላል። በዚህም ወቅት ከላይ እንደገለጽነው ለአእምሮአችን ዕረፍትን መስጠት እንጂ የባሰ ማጨናነቅ አይገባም። በመሆኑም መጻሕፍትን ለማንበብ ንጹሕ አእምሮ ስለሚያስፈልግ ለአእምሮአችንን ዕረፍት ሰጥተን አእምሮአችን ሲረጋጋ መጻሕፍትን ልናነብ ያስፈልጋል። ‹‹የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል›› እንዲል።

- ከሥጋዊ ፍልስፍና (ዕውቀት) ጋር ቀላቅሎ ለመረዳት አለመሞከር፦ የዓለም ዕውቀት በቤተ ክርስቲያን ቦታም የለውም በመሆኑም ሥጋዊ ዕውቀታችንን በዓለም ትተን መጻሕፍት ጋር ስንመጣ ራሳችንን ዝቅ አድርገን በእምነት ልናነብ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናነብ ከአእምሮ በላይ የሆኑ ነገሮች ነገር ግን በእምነት ብቻ የምንረዳቸውን ነገሮች በስፋት ስለሚኖሩ።

ለ. ፈሪሃ እግዚአብሔርን ገንዘብ ማድረግ

መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ማለት ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነበው ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት እያነጋገረው ባለው በእግዚአብሔር ፊት መፍራት ይጠበቅበታል።ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፈ ምሳሌው ላይ ‹‹የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው። ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው›› በማለት እንዳስረዳው። መጻሕፍትን ስናነብ (ስናጠና) ፈሪሃ እግዚአብሔርን ገንዘብ ማድረግ የማዕዘን ድንጋይ ነው።

ሐ. ከመረዳት ጋር ማንበብ

መጽሐፍ ቅዱስ የሚነበበው ነገረ እግዚአብሔርን ፈቃደ እግዚአብሔርን ለማወቅና ነፍስን መንፈሳዊውን መና ቃለ እግዚአብሔርን መግቦ ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖራት የሚገባውን አንድነት ለማጠናከር ነው። ይህንን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የግድ የመጽሐፉን ምሥጢር መረዳት ያስፈልጋል ። በመሆኑም ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመረዳት ጋር የሚያነብ ሰው ራሱን ከመጥቀም ባሻጋር ሌሎችንም መጥቀም ይችላል። (ት/ዳን 12÷3) ያለበለዚያ ግን ጌታችን በማቴ 22÷29 ላይ ‹‹መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ›› እንዳለው ለውድቀት መጋለጣችን አይቀሬ ነው። ይኸውም ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን በቤተ መቅደስ በዘመናቸው የነበሩትን መጻሕፍት ዘወትር ያነቡ ይመረምሩ ነበር። ነገር ግን የሚያነቡት በነጠላ ስለነበር ምሥጢሩን ለመረዳት ግን አልቻሉም። ምሥጢሩን ቢያውቁት ኖሮማ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹አውቀውስ ቢሆን ኖሮ የክብርን ጌታ አሳልፈው ባለሰቀሉት ነበር›› ብሎ ባልተናገረ ነበር። እንደዚሁ በኋላም ዘመን አርዮስ የተባለ መናፍቅ ሊስትና ምንፍቅናን ሊያስተምር የቻለው መጻሕፍትን ከመረዳት ጋር ስለማያነብ ነበር። ስለሆነም መጻሕፍትን ከመረጋት ጋር ማንበብ የግድ ያስፈልጋል።

መ. መምህራንን በመጠየቅ

መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ (የሚያጠና) አንድ ሰው የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳይዝ ከጉባኤ ቤት ውለው ምሥጢር ካደላደሉ መምህራን ዘንድ ቀርቦ እየጠየቀ መማር ይኖርበታል። በዚህም የነቢዩን መጽሐፈ ትንቢት ያነብ የነበረው ኢትዮጵያዎው ጃንደረባ ባኮስ ‹‹በእውኑ የምታነበውን መጻሐፍ ታውቀዋለህ›› ብሎ ከእግዚአብሔር የታዘዘው ዲያቆኑ ፊሊጶስ ‹‹የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል››ብሎ መመለሱ የሚያስረዳን ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናነብ የሚመሩን የሚያስረዱን መምህራንን መጠየቅ እንደሚገባ ነው። ሐዋ 8÷#-#1

መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ (ለማጥናት) የሚረዱ መሠረታዊ መጠይቆች (መርሆች)

መጽሐፍ ቅዱስን በምናጠናበት ጊዜ የተጻፈውንና የሚነበበውን ድርጊት በምልዓት ለመረዳት ለመተርጎም የሚከተሉትን መጠይቆችን በመጠየቅ ምላሽ ማግኘት ያስፈልጋል።

ማን?

ይህ በድርጊቱ መግለጫ ውጥ ባለቤቱን ወይንም ምንነቱን ለመረዳት በመጠየቅ የምንጠቀምበት ቃል ነው። በዚህ ውስጥ ተናጋሪው ማነው? ሰሚዎቹስ እነማን ናቸው?መጻሐፉስ ለነማን ተጻፈ?የመጽሐፉ ጸሐፊ ማነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ይነሳሉ። ለዚህ መልስ ሊሆን የሚችሉትን ባለቤት ገላጭ የሆኑ በተገቢው ሁኔታ ማጥናት ማንን የሚወክል መሆኑን ለመረዳት እንድንችል ያግዘናል።በመሆኑም ሁል ጊዜ በ መጽሐፍ ቅዱስ የምናገኛቸውን ቃላት ያለ ትርጉም የማይመጡ ስለሆኑ እንዲህ የመሰለውን ሁሉ ትኩረት መስጠት ይጠቅማል።ዮሐ 3÷1 ዮሐ 2÷6 ማር 5÷25 2ኛ ነገ 9÷1 ዮሐ 13÷23 ዘፍ 6÷71ኛ ነገ 17÷9

ምን?

ይህም ደግሞ ከገጸ ንባቡ ሳንወጣ ለመመልከት የምንጠቀምበት ቃና ሐሳብን የማግኘት ሌላው የአጠናን ስልት ወይንም ዘዴ ‹‹ምን›› የሚለው ነው። በዚህ ውስጥም፦

- ✓ ስለ ምን ይናገራል?
- ✓ የድርጊቶቹ ቅድመ ተከተል ምንድን ናቸው?
- ✓ የተጠቀሱት ሰዎች ጸባይ ምን ይመስላል?
- ✓ ጸሐፊው (ተናጋሪው) ቀደም ሲል ስለነዚህ ሰዎች ምን ብሏል?
- ✓ በተጠቀሱት ሰዎች ላይ ምን ደረሰ?------ወዘተ የሚሉትን ጉዳዮች እንመለከትበታለን (እናጠናበታለን) ለምሳሌ ዮሐ 2÷1-11 ላይ እንደተጠቀሰው በቃና ዘገሊላ ምን በሠርግ ቤት ምን ተደረገ?የሚለውን በጥልቀት መመልከት በቂ ማስረጃ ነው።

መቼ?

ይህም ደግሞ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ጊዜና ሁኔታ ለማወቅ የሚረዳን መጠይቅ (መርሕ) ሲሆን ይኸውም፦

ድርጊቱ የተፈጸመው መቼ ነው? ብለን ስንጠይቅ ጠዋት ማታ በኋላ በፊት ---ወዘተ የሚሉትን ምንባቦች በአንክሮ መመልከት ለዚህ ጥያቄ መልስ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ይልቅ የተለያዩ ዘመናት ያመለክትልናል። በዘመነ አበው (ሕገ ልቡና) በእስራኤላውያን ከምርኮ በፊት በኋላ በሐዲስ ኪዳን ----- የተነገረብን ዘመን የመልእክቱን ትርጉም በማመልከት ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል።የሐዋ ሥራ 3÷1። በመሆኑም ሁል ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸውን ቃላት ያለ ትርጉም የማይመጡ ስለሆኑ እንዲህ የመሰለውን ሁሉ ትኩረት መስጠት ይጠቅማል። ስለሆነም 3 መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና (ስናነብ) ድርጊቱ የተፈጸመበትን ጊዜ በማጤን ልናነብ ያስፈልጋል።

የት?

ይኸውም መጠይቅ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቦታ ለማወቅ የሚረዳን ነው። ይኸውም፦

- ✓ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ጊዜና ሁኔታ ማወቅ
- ✓ ሰዎቹ ከየት መጡ? ወዴት ነው የሚሔዱት?
- ✓ ጸሐፊው ይህን ሲጽፍ የት ነበር?
- ✓ የተጻፈላቸውስ የት ነበሩ? ---ወዘተ የሚሉትን ሲሆን ይህንንም ቦታውን በትክክል ማወቅና መረዳት ለንባባችን እና ለአስተምሯችን እጅግ ጠቃሚ ሐሳቦችን እንድናገኝ ይረዳናል። ለምሳሌ ጌታ የት ነው የተወለደው? የት ነው ያደገው? የት ነው የተጠመቀው? ያስተማረባቸው ቦታዎች የት የት ናቸው? የተሰቀለው የት ነው? የተቀበረው የት ነው? ያረገው የት ነው? ------ ወዘተ የሚሉትን መጠየቅ ዋና ዋና ምሥጢራትን እንድናገኝና እንድናውቅ ይረዳናል። ሉቃ 24

ለምን ?

ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ ሁኔታው ወይንም ድርጊቱ የተፈጸመበትን ዋና ምክንያት የሚያስረዳ መጠይቅ ነው። ለምሳሌ ጌታ ለምን በግርግም ተወለደ? ለምን ከስደት መልስ ናዝሬት ገባ? ለምን በዮርዳኖስ ተጠመቀ? ለምን በውኃ ተጠመቀ? ለምን በሰርግ ቤት ተገኘ? ለምን ውኃውን ወደ ወይን ለወጠው? ------ ወዘተ የሚለውን ማጥናት ለንባባችን የማዕዘን ድንጋይ ስለሆነ ይህንን መጠይቅ በመጠየቅ ልናነብ ይገባል። መዝ 143÷7 ዘፍ 2÷16-17 ሉቃ 2÷13-14

እንዴት ?

ይህም በንባባችን ውስጥ ድርጊቱ እንዴት ተከናወነ ውጤቱ ሐሳቡ ስሜቱ ምን እንደነበረ የሚያመለክትና የመጨረሻ መፍትሔውን ለማግኘት የሚረዳን መጠይቅ ነው። ለምሳሌ ጌታ እንዴት ውኃውን ወደ ወይን ለወጠው? የበርተሎሜዎስን ዓይን እንዴት ፈወሰው? መጻጉን እንዴት አዳነው? --- ወዘተ የሚለውን መጠየቅ መጠየቅ ለንባባችን የማዕዘን ድንጋይ ስለሆነ ይህንን መጠይቅ በመጠየቅ ልናነብ ይገባል። ዮሐ 2 1-11 ዮሐ 9 ዮሐ 5

መጽሐፍ ቅዱስ በሚጠናበት ጊዜ ጎልተው የሚታዩ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው።

ቅዱሳት መጻሕፍት በሚጠኑበት ጊዜ የሚከተሉትን መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዮች ባለማስተዋል (ባለመመልከት) ልብ ሳንል መጻሕፍትን ለመተርጎም ለማመስጠር ለማብራራትና ለመረዳት ችግሮች ይከሰታሉ።ይኸውም ቅዱሳት መጻሕፍትን በምናጠናበት ጊዜ ይልቁንም የተጻፈውን ክፍል ወይንም ድርጊቱን ለመረዳት የተለያዩ ነገሮችን ማጤን (ማስተዋል) ትርጉማቸውን በሚገባ መገንዘብ ሲኖርብን ይህን ዓይነት የማንበቢያ (የማመስጠሪያ) ዘዴውን ዘንግተነው በራሳችን የማንበቢያ መንገድ እየተጓዝን ነው። ይህ ደግሞ ለትልቅ ስህተት መጋለጡ (መዳረጉ) አይቀሬ ነው። ሆኖም ጠቅለል አድርገን ቅዱሳት መጻሕፍት በሚጠኑበት ጊዜ ጎልተው የሚታዩትን ችግሮች እንደሚከተለው እንመለከተዋለን፦

የመጽሐፍ ቅዱስን ባሕል አለማወቅ

መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ ባሕል የተጻፈ እንደመሆኑ መጠን የመጽሐፍ ቅዱስን ባሕል ማወቅና በመጽሐፉ ባሕል ማንበብ ሲኖርብን በራሳችን ባሕል መጽሐፉን በመተርጎም ብዙዎቻችን ለውደቀት ተዳርገናል ። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ የነበሩት ሰዎች የአለባበስ ባሕል የአስተሳሰባቸው ሁኔታ የኑሮ ዘይቤ ----- ወዘተ ባሕላቸው ከእኛ ባሕል ጋር ስለሚለያይ። ለምሳሌ፦

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*` „Ê¡e }ªIÊ

ስምን አለመግለጥ ይኸውም በዮሐ 13÷23 ‹‹ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር›› እንዲሁ ማቴ 5÷1 ላይ ‹‹ሕዝቡን አይቶ ወደ ተራራ ወጣ›› የሚሉት ናቸው። ------ወዘተ ሲሆኑ እነዚህን ባሕሎች ያለማወቅና ያለመጠበቅ ችግሮች ጎልተው ይታያሉ።

የመጽሐፍ ቅዱስብ አባባል አለመረዳት

ይኸውም በዘፍ 3÷9 ላይ ‹‹አዳም ወዴት ነህ›› እንዲሁ በዮሐ 2 ላይ ‹‹ከአንቺ ጋር ማን አለኝ›› ----ወዘተ የሚሉት ሲሆኑ እነዚህን አባባሎች ባለማወቅና ባለመገንዘብ ብዙዎች እየሳቱና ትክክለኛ የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ሳይረዱ ለውድቀት የተዳረጉ ብዙዎች ናቸው። በመሆኑም የመጽሐፍ ቅዱስን አባባል አለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስ በሚጠናበት ጊዜ ጎልቶ እየታየ ያለ ችግር ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጓሜ ጠንቅቆ አለማወቅ

ይኸውም ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስለ ትርጉም ሦስት ዓይነት እንዳለ ታስተምረናለች። ይኸውም ነጠላ ፣ ምሳሌያዊ እና ምሥጢራዊ ትርጉሞች ናቸው። እነዚህን የትርጉም ዓይነቶች ጠንቅቆ ካለማወቅ ብዙዎች ለውድቀት የተጋለጡ አሉ። በመሆኑም እነዚህን የትርጉም ዓይነቶች ጠብቆ ያለመረዳር ችግርም ሌላው መጽሐፍ ቅዱስ በሚጠናበት ጊዜ ጎልቶ እየታየ ያለ ነው።

የተለያዩ የአንድ ቋንቋ ትርጉሞች ለምን ይገኛሉ

መጽሐፍ ቅዱስ አሁን ባለንበት ዘመን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ሰዎች በመተርጎሙ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የተለያዩ ዓይነት ትርጉም ያላቸው መጻሕፍት አሉ። እነዚህም የተለያዩ የአንድ ቋንቋ ትርጉሞች ሊከሰቱ የቻሉት ፦

- ✓ ከተለያዩ ምንጮች በመተርጎማቸው
- ✓ በተለያዩ አካላት በመተርጎማቸው
- ✓ ሃይማኖት እና ሃይማኖታዊ እውቀት በሌላቸው ሰዎች በመተርጎማቸው

ለምሳሌ፡ በእጃችን የሚገኙ ትርጉሞች

- የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
- የሊቃውንት ጉባኤ
- ለተለያዩ ዓላማዎች መተርጎም

- ✓ መደበኛ ትርጉም ያለ መኖር

የትርጉም መዛባት የሚያስከትለው ችግር

- አንባብያንን ያደናግራል፡- ይኸውም ለምሳሌ፡-
  - ✓ ‹‹ዋኖስ›› የሚለው በአማርኛ ‹‹ዋልያ›› ተብሏል። ሉቃ 2÷24
  - ✓ ‹‹---- በአባቶችሽ ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ›› የሚለውን ‹‹በአባቶች ፈንታ ልጆች ተወለዱልህ›› ተብሏል። መዝ 44÷16
- አንባብያን እውነተኛነቱን እንዲጠራጠሩ ያደርጋል፡- ይኸውም ለምሳሌ፡-
  - ✓ ከክርስትናው ውጪ የሆኑት (ሐራጥቃዎች) ‹‹የእግዚአብሔር ቃል የቱ ነው›› እያሉ እንደሚሳለቁት ማለት ነው።
- መሠረታዊ የሃይማኖት ልዩነት ያስከትላል። ይኸውም ለምሳሌ፡-
  - ✓ ሮሜ 8÷34 ላይ ‹‹ወይትዋቀስ በእንቲአነ = ስለ እኛ ይፈርዳል›› የሚለውን ስለኛ ይማልዳል ተብሎ ተተርጉሟል።

ለችግሮቹ መፍትሔ

- ❖ መደበኛ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ማዘጋጀት
  - ✓ ይኸውም ከግእዝ፣ ከዕብራይስጥ፣ ከግሪክ ጥንታዊ መጻሕፍት ጋር በማገናዘብ (በማመሳከር)
- ❖ ማዕከላዊ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የምርምር ማዕከላት ማቋቋም።
  - ✓ ጥንታዊ ቅጂዎች የሚቀመጡበት
  - ✓ ነጠላና አንድምታ ትርጉሞች የሚጠኑበት
- ❖ በጠጊኤው ትምህርት መስጠት
- ❖ ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ጋር ያላትን ግንኙነት መመርመር።

ምዕራፍ ሰባት

የመጽሐፍ ቅዱስ ጠባይና ሥነ ጽሑፋዊ የአጻጻፍ ስልት

የመጽሐፍ ቅዱስ ጠባይ

የመጽሐፍ ቅዱስን ጠባይ ያልተረዳ (ያላወቀ) ሰው በቀላሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛውን ምስጢር ለመረዳት ያስቸግረዋል። ያለ ስህተትና ያለ ጭንቀት ለማንበብና ለመረዳት የቋንቋውን ጠባይ በሚገባ ተንትኖ ሁኔታውን ማጤን (ማስተዋል) ተገቢ ነው። ስለሆነም በአጠቃላይ መልኩ ጥቂቶችን የመጽሐፍ ቅዱስ የቋንቋ ጠባይዓት እንደሚከተለው እንመለከታለን።

<u>ሕዝባዊ ነው</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ሁሉን ባቀፈ እና ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ ሲሆን እንዲሁ ትውልድን ሁሉ የሚታደግ እውነተኛ ዳኛ ነው። የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ቀድሞም የነበሩትን አሁን ያሉትን ወደፊትም የሚኖሩትን ሕዝቦች ያጠቃልላል። ስለሆነም ማንኛውም የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ ለራሱ ምግብ የሚሆነውን ሃይማኖቱን ለማጽናትም ሆነ ምግባሩን ለማስፋት ሕዝባዊ ሆኖ የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስ በአግባቡ የመረዳትና በአክብሮት የመቀበል መንፈሳዊ ኃላፊነት አለበት። ይህ ክፍል እኔን አይመለከትም እገሌን ነው ሊባል የሚቻልበት ሁኔታ የለም። የመጽሐፍ ቅዱስ የተግሳጽ ክፍል ፣ የመልእክት ክፍል ፣ የመዝሙር ወይም የቅኔ ክፍል ፣ የትንቢት ወይም የራዕይ ክፍል ወዘተ ለሠው ልጅ ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ነው። ‹‹ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም›› እንዲል። /ዮሐ 4÷4/

<u>ክስተታዊ ነው</u>

መጽሐፍ ቅዱስን በማስተዋል ከተመለከትነው ቋንቋው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚገልጠው ነገር ጋር ይዛመዳል። ይኸውም ነገሮችን ከተመልካቹ መረዳትና ግንዛቤ አኳያ መመልከትና መመርመር ተገቢ ይሆናል ማለት ነው። ለምሳሌ ‹‹ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል... ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለው ዋጋው አይጠፋበትም›› በማለት የገለጸውን በአጽንዖት መረዳት ካልተቻለ አንዲት ጽዋ ውኃ በመጠንም በዓይነትም ልናቃልላት ወይም ቦታ ላንሰጠው እንችል ይሆናል። --- ምንድነው? ለምንስ እንዴት ጽዋ ብቻ አለ ማለት ይገባናል። እዚህ ላይ በሚገባ ማስተዋል ያለብን እግዚአብሔር የሚገልጥበትን ክስተታዊ ሁኔታ ነው። /ማቴ 10÷42/

<u>ኢሳይንሳዊና ኢንድፊ ሐሳባዊ ነው</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የአንድን ነገር እውነተኛ ባሕሪ በንድፈ ሐሳብ አያስቀምጥልንም። መልእክቱን ለማስተላለፍ ከንድፈ ሐሳብ በላይ የመለኮታዊ ባሕርይ መገለጥን ይከተላል። ሳይንሳዊ የፍልስፍና ትምህርትን ከዋናው ምሥጢር የበለጠ ሠፊ ቦታ ሰጥቶ አያስተምርም። ለምሳሌ ‹‹ሰማይና ምድርን ፈጠረ››/ዘፍ. 1÷1/ ‹‹ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ።›› /ዘፍ. 1÷3/ ‹‹በመጀመሪያ ቃል ነበር ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ቃልም እግዚአብሔር ነበር። ሁሉ በእርሱ ሆነ።›› /ዮሐ. 1÷1-3/ ‹‹ቃል ሥጋ ሆነ›› /ዮሐ. 1÷14/ የሚሉትንና ሌሎችንም ብንመለከት በሰው አቅምና ፍላጎት ሳይንሳዊ የፍልስፍና እይታ አንጻር ብቻ ሊታይና ሊመረመር አይችልም። ስለሆነም መጽሐፍ ቅዱስ በአጻጻፍ ስልቱና ጠባዩ ኢሳይናሳዊና ኢንድፊ ሐሳባዊ ነው። _

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ</u>

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጸሐፊያኑ እደሚለያዩ ሁሉ የአጻጻፋቸው (የአገላለጻቸው) ስልት ዘይቤም የተለያየ ሆኖ እናየዋለን።ሆኖም እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ የአገላለጽ ስልት ጠንቅቀን ልናውቅ (ልንረዳ) ያስፈልጋል። ያለበለዚያ አሁንም ለውድቀት መጋለጣችን አይቀሬ ነው። ታድያ እነዚህን የአጻጻፍ ስልቶች መሰረታዊ ስልት ጽሑፎች እና ዝርዝር የአገላለጽ ስልቶች ብለን በዚህ ትምህርታችን ከፍለን እንመለከታቸዋለን።

<u>መሠረታዊ ስልት ጽሑፎች (የመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ ጽሑፋዊ ስልት (አቀራረብ)</u>

የመጽሐፍ ቅዱስን ሥነ ጽሑፋዊ አጻጻፍ ስልት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። ይኸውም፡-

1) ትረካዊ አጻጻፍ
2) ሥነ ግጥማዊ አጻጻፍ
3) ትምህርታዊ አጻጻፍ
4) ራእያዊና ሕልማዊነትን የያዘ አጻጻፍ በማለት ይታወቃሉ።

ትረካዊ የአጻጻፍ ስልት

ትረካዊ የአጻጻፍ ስልት የምንላቸው ክስተትና ሁኔታዎችን የቀደሙትን ታሪኮች በትረካ መልክ የሚዘግቡ አጻጻፋቸውም በታሪክ መልክ ሆኖ በታሪካዊ አቀራረብ የተጻፉትን መጽሐፍት ያካትታል። ሆኖም የመጽሐፍ ቅዱስ ብዙው ክፍል ትረካዊ የአጻጻፍ ስልት እንዳለው ሊታውንተ ቤተ-ክርስቲያን ያስረዳሉ። ትረካዊ የአጻጻፍ ስልት ታሪኮችን በዘገባ መልኩ ያቀርባል። በብሉይ ኪዳንም ሆነ የሐዲስ ኪዳን ትረካዊ የአጻጻፍ ስልት በስፋት ቀርቧል። ከእነዚህም መካከል ለምሳሌ መጽሐፈ ሩት ፣ መጽሐፈ ሳሙኤል ፣ የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል ፣ የሐዋርያት ሥራ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው።

ሥነ ግጥማዊ የአጻጻፍ ስልት

ይህ የአጻጻፍ ዓይነት በግጥም፣በቅኔና በምሳሌያዊ መንገድ የተጻፈ ጽሑፍ ሲሆን ኪነ-ጥበባዊ አቀራረብ አለው። ሆኖም ይህ የአጻጻፍ ስልት ደግሞ ብዙውን ጊዜ ተአዳሚው ወይም የመልእክቱ ተቀባይ በሚገባውና የሚረዳው ሁኔታ አንጻር ሥነ ጥበባዊ በሆነ መልኩ የሚቀርብ የጽሑፍ ስልት ይዘት ነው። በዚህ ዓይነት ሥነ ግጥማዊ የአጻጻፍ ስልት ወይም ጥበብ ከተጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል መጽሐፈ ኢዮብ ፣ መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን ፣ መዝሙረ ዳዊት ፣ መጽሐፈ ጥበብ ፣ መጽሐፍ ተግሳጽ ፣ መጽሐፈ ሲራክ ፣ መጽሐፈ ምሳሌ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው። ብዙውን ጊዜ እነዚህ መጻሕፍት ነገርን በጥበብ ፣ በምሳሌ ፣ በምክር ፣ በመዝሙር ፣ በቅኔ ፣ በአጠቃላይ በሥነ ግጥም መልክ የሚያቀርቡበት ሁኔታ ይስተዋላል።

ትምህርታዊ የአጻጻፍ ስልት

ይኸውም የአጻጻፍ ስልት የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረተ ትምህርት በቀጥታ የሚገለጽ የሚያብራራ የሚያስተምር በትምህርታዊ አጻጻፍ የተጻፈ ነው። ይህም ዓይነቱ የአጻጻፍ ስልት ደግሞ መሠረታዊ የሆኑ ትምህርተ ሃይማኖት ፣ ሥርዓተ እምነት ትውፊት እንዲሁም ትንቢታዊ መልእክቶች ማለትም የቤተ-ክርስቲያን ዶክትሪንና ቀኖና በዚህ የአጻጻፍ ስልት ይቀርባል። ለምሳሌ ኢሳይያስ ፣ ትንቢተ ዘካርያስ ፣ የጴጥሮስ መልእክታት ፣ የዮሐንስ መልእክታት ፣ የጳውሎስ መልእክታት ወዘተ በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው።

ራእያዊና ሕልማዊ የአጻጻፍ ስልት

ይህ ማለት ቅዱስ እግዚአብሔር በተለያየ ዘመን የተለያዩ ቅዱሳን አባቶችን እያስነሳ ይህን መጽሐፍ ሲያጽፋቸው በገሃድ በመገለጽ እየታየ በተዘዋዋሪው ደግሞ በራእይ በሕልም እየታየ አጽፏቸዋል።በዚህ ክፍል የምናገኘው ወደፊት የሚፈጸመውን እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ ገልጾ የጻፏት ሲሆን ምሥጢራዊ መግቢያዎች /እንቆቅልሾች/ በብዛት ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፡- በትንቢተ ዳንኤል የተገለጸው ነብር አንበሳ፣ በራእይ ዮሐንስ ላይ የተገለጸው የዘንዶውና የአውሬው አካላዊ አገላለጽ.... እነዚህ ምሥጢራዊ ናቸው። በነዚህ አጻጻፍ የተጻፉት ራእያዊ እንላቸዋለን። በመሆኑም እግዚአብሔር ፈቅዶና ወዶ መጽሐፍ ቅዱስን ካጻፋባቸው የጻጻፍ ስልቶች ጠለቅና ጠንከር ያለው ይህ ራእያዊና ሕልማዊ የተሰኘው የአጻጻፍ ስልት ነው። ይኸውም መልእክቱ በራእይም ሆነ በህልም በመግለጥ ልዑል እግዚአብሔር የፈቀደውን መልዕክት ለጻድቁም ሆነ ሊኃጥኡ የሚገልጥበት መንገድ ወይም የአጻጻፍ ስልት ነው። ለምሳሌ ትንቢተ ሕዝቅኤል ፣ ትንቢተ ዳንኤል ፣ ትንቢተ ኢዩኤል ፣ ራእይ ዮሐንስ ፣ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። መጻሕፍት ስናነባቸው በቀላሉ የሚረዱ የማይሆኑትም ምክንያት ለዚህ ነው። ስለሆነም እነዚህን ዓይነት መጻሕፍት ስናጠና የመጽሐፍ ቅዱስን የአጻጻፍ ስልት ለማንበብና ለመተርጎም ምሥጢሩን በሚገባ ለመረዳትና ለማጤን ብሎም መንፈሳዊ ምርምር ለማድረግ እጅግ ማስተዋል ይኖርብናል።

ዝርዝራዊ አገላለጽ

ቀደም ሲል መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ዘመናትና ቦታዎች በነበሩ ከ 40 ባላነሱ ቅዱሳን አባቶቻችን መጻፉ ተገልጿል እነዚህ ጸሐፊዎች ከእግዚአብሔር የመጣላቸውን ቃል የጻፉት በተለያየ አገላለጽ ሲሆን።በቅዱሳት መጻሕፍት ያለውም የእግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ ሰውን ወደ ዘላለማዊ ሕይወት መጥራት ሲሆን ይህ ግን በተለያዩ መጻሕፍት የተጻፈበት የተለያየ አቀራረብና አገላለጽ አለው። በመጽሐፍ ቅዱስ አንድን ጉዳይ አስመልክቶ በተለያዩ ጸሐፊዎች የቀረቡት ትምህርቶች ስንመለከት የጎላ የአገላለጽ ልዩነቶች ሊስተዋሉ ይችላሉ። ከዚህ የተነሳም አንዳንድ በሥጋ ሐሳብ የተነሣሱ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚገኙ የአገላለጽ ልዩነቶችን (ገጸ ንባባትን) ብቻ በመመልከት መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ እንደሚጣላ አድርገው ይገምታሉ። በመሠረቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ያለው ሐሳብ አንድ ነው። በተለያዩ መንገዶች የተገለጡ ሐሳቦች ዞረው ዞረው አንድ ዓላማ የሚያመለክቱና የሚመሩ ናቸው። ይህን ስንል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ፍጹም አንድነትን እንደምናስተውል ሁሉ በተለያዩ ጸሐፊያን አቀራረብ የተለያዩ የአጻጻፍ ያአገላለጽ ልዩቶች ሲኖሩት። ፈጽሞ የሐሳብ ልዩነቶች ግን አይኖረውም ይህንንም ለመገንዘብ ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌዎች እንመለከታለን፡-

- ማቴ. !7፥1 ″.... ከስድስት ቀንም በኃላ ኢየሱስ ጴጥሮስን ያቅብን ፣ ዮሐንስ.... ″
- ሉቃ. 9፥@8 ″.... ከዚህም ቃል በኋላ ስምንት ቀን ያህል ቆይቶ....″

በዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን ነገር እዚህ ላይ የአገላለጽ ልዩነት ነው እንጂ የሐሳብ ልዩነት አለመኖሩን ነው። ይኸውም ጌታችን ሐዋርያትን ወደ ደብረ ታቦር የወሰዳቸው በ 8 ኛው ቀን ነው እዚህ ጋር ሉቃስ ወንጌሉን ሲጽፍ አስረግጦ ነው የሚናገረው ማቴዎስ ግን

ከስድስት ቀን በኋላ አለ እንጂ በስድስተኛው ቀን አላለም። ስምንት ከስድስት በኋላ ነውና የሚመጣው በኋላ ሲል ስድስትተኛዋ ቀን አልፎ ማለቱ ነውና።

- ማር. !5÷!5 “.... በሦስት ሰዓት ተሰቀለ”
- ሉቃ. 3÷$4 “..... በስድስት ሰዓት ተሰቀለ”

በዚህም ላይ ልናስተውለው የሚገባን ነገር የሐዋርያቱ የአገላለጽ ልዩነት ነው እንጂ የሐሳብ ልዩነት በሁለቱም በኩል አለመኖሩን ነው። ማርቆስ ሲጽፍ የተወሰነበትን ሰዓት ነው።ይኸውም ጲላጦስ የፈረደበትን ሲሆን ሉቃስ ደግሞ ልክ እንደተሰቀለ ባየ ጊዜ ጻፈ። ጌታ የተሰቀለው 6 ሰዓት ነውና። ------ ወዘተ ብዙ ማንሳት እንችላለን ግን ለእኛ እነዚህ በቂ ናቸው። በአጠቃላይ ስናነብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደነዚህ ዓይነት የገላለጽ ልዩነቶች እንደሚኖር ልናስተው ይገባል።

ምዕራፍ ስምንት

ብሉይ ኪዳን

<u>የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጠቅላይ ይዘት</u>

➧ ብሉይ ኪዳን፡- ማለት የሁለት ቃል ጥምር ሲሆን ብሉይና ኪዳን የሚል ቃል አለው። ይኸውም፦

- ✓ ብሉይ፡- ማለት የቆየ፣ የጥንት ያረጀ፣ የድሮ ማለት ሲሆን።
- ✓ ኪዳን፡- ማለት ደግሞ ውል፣ ስምምነት፣ መሐላ ማለት ነው።

➧ <u>ብሉይ ኪዳን</u>፦ ማለት ተጠቃሎ የቆየ የጥንት ያረጀ የድሮ ውል ስምምነት መሀላ ማለት ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለው (5500 ዓ.ዓ) ሲሆን። በዚህ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለው የአንድ አምላክ አማኞች የሆኑት የዕብራውያን (እስራኤላውያን) ታሪክ ይተረካል። በዘመኑ ውስጥ የነበሩት አበው ተስፈኞች ዘመነ ሐዲስን የሚጠባበቁ ነበሩ። ሆኖም በዘመነ ብሉይ እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ነው። ለምሳሌ፦

1. ኪዳነ አዳም ፦ <<ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሐለው>> በዘፍ 9÷1
2. ኪዳነ ኖህ፡- እግዚአብሔር ዳግመኛ ምድርን በንፍር ውሃ እንደማያጠፋ በቀስተ ደመና የገባለት ቃል ኪዳን ነው።/ዘፍ. 9፥1-7/
3. ኪዳነ አብርሃም፡- እግዚአብሔር አብርሃምን ዘርህን እንደሰማይ ከዋክብት እንደምድር አሸዋ አበዛዋለሁ ያለው ነው።/ዘፍ. !7፥1-2፣ ሮሜ. 4፥!1/
4. ኪዳነ ሙሴ፡- ይህ ሙሴ እግዚአብሔር ፊትህን አሳየኝ ባለው ጊዜ የገባለት ቃል ኪዳን ነው።/ዘጸ **#3**፥5-6/
5. ኪዳነ ዳዊት፡- ይህ እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠው ቃል ኪዳን /2 ኛ ሳሙ.@3፥5/ ------ ወዘተ

በዚህ ምክንያት ከክርስቶስ ልደት በፊት የተጻፉት መጻሕፍት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተብለዋል።

ሆኖም ብሉይ ኪዳን ከሐዲስ ኪዳን ተነጥሎ አይታይም። ምክንያቱም ብሉይ ኪዳን የሐዲስ ኪዳን ትንቢት ሲሆን ሐዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ነው ሐዲስ ኪዳን ራሱ የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ ነው። ብሉይ ኪዳን የሐዲስ ኪዳን ጥላ ነው። ሐዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን አካል ነው፤ ብሉይ ኪዳን የሐዲስ ኪዳን ትንቢት ነው ሐዲስ ኪዳን ደግሞ የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ነው። በብሉይ ኪዳን የተሰወረው በሐዲስ ኪዳን ተገልጧል ስለዚህ ብሉይ ኪዳንም ሐዲስ ኪዳንም የማይነጣጠሉ ኪዳናት ናቸው። ሆኖም ብሉይ ኪዳን ስንል በኋላ በክርስቶስ ደም ለተመሰረተው ሐዲስ ኪዳን ጥላ እንደመሆኑ። ከሐዲስ ኪዳን ቀድመው የነበሩት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት በውስጣቸው የተሰፋና የትንቢት ቃል የያዙ ሲሆኑ የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ግን የዚህ የብሉይ ኪዳን የተሰፋ ቃል የትንቢቱ መፈጸሚያ ነው። ለዚህ ነው አበው ሊቃውንት " ነብያት የዘሩትን ሐዋርያት አጨዱ" የሚሉት።ስለሆነም ሐዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን ውስጥ አለ። ሆኖም ግን ነቢያት የተነበዩት አምላክ ወልደ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመኑንና ጊዜውን ቆርጦ በተገለጸ ጊዜ ስውር የነበረው ሐዲስ ኪዳን ተገልጸል። በዚህ ምክንያት ብሉይ ኪዳን የሐዲስ ኪዳን ፍጻሜ እንዳገኘ እንረዳለን። ብሉይም ሲባል ሕጉ ሁሉ ወይንም ቃል ኪዳኑ ሁሉ ያረጀ የፈጀ ነው ማለት አይደለም። ግን ዘመኑ አርጅቷል ብዙ ጊዜም አሳልፏል ስለዚህ በዚያን ጊዜ የነበረ መሆኑን ለማስረዳት ሲባል ብሉይ ኪዳን እንለዋለን።

❖ 70(ሰባው) ሊቃናት የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍ ከፍለው ባስቀመጡት መሠረት እኛም በአራት (4) ከፍለን እንማራለን፡-

1. የሕግ መጻሕፍት
2. የታሪክ መጻሕፍት
3. የጥበብ (የቅኔ ፡ የመዝሙር) መጻሕፍት
4. የትንቢት መጻሕፍት ናቸው።

ቀጥለን እያንዳንዳቸውን ጠቅላይ ይዘታቸውን በዝርዝር እንመለከታለን

ክፍል ፩

<u>የሕግ መጻሕፍት</u>

የሕግ መጻሕፍት የሚባሉት አምስት ሲሆን እነሱም የሚከተሉት ናቸው

1. ኦሪት ዘፍጥረት
2. ኦሪት ዘጸአት
3. ኦሪት ዘሌዋውያን
4. ኦሪት ዘኁልቁ

5. ኦሪት ዘዳግም ናቸው።

ስያሜያቸው

እነዚህ አምስቱ መጻሕፍት በግእዝና በአማርኛ ኦሪት ሲባሉ በዕብራይስጥ ደግሞ ቶራ በግሪክ (ጽርዕ) ኖምስ ይባላሉ። ትርጉሙም ሕግ ማለት ነው። ከዚህ ሌላ አምስቱ ብሔረ ኦሪት ይባላሉ። ኦሪት ማለትም ቃሉ የሱርስት ሲሆን ብርሃን ማለት ነው። ይኸውም ክፍል አንቀጸ ኦሪት ማለት ነው።

ጸሐፊው

የአምስቱ የኦሪት መጻሕፍት ጸሐፊ ወይም አዘጋጅ ሊቀ ነቢያቱ ሙሴ ነው። ሙሴ እናቱ ዮካብድ አባቱ አንበረም ይባላሉ። ያደገው በግብጽ ቤተ መንግሥት ነው። ኋለ ግን ወደ ምድያም (ኢትዮጵያ) በመሄድ ሲፓራን አግብቶ በዚያ ሲኖር እግዚአብሔር በኮሮብ ተራራ ላይ አናግሮት ሕዝበ እሥራኤልን ከ 430 የባርነት ሕይወት አውጥቶ ወደ ምድረ ርስት የመራ የመጀመሪያው የእሥራኤል መስፍን ነው። ሆኖም ግን መጻሕፍቱን የጻፈው ከእግዚአብሔር በቀጥታ እየሰማና እየታዘዘ ነው። ከሙሴ በፊት በዘፍጥረት የተመዘገበው ታሪክም ቢሆን ሙሴ በመንፈሰ እግዚአብሔር ተመልቶ ተገልጾለት የጻፈው ነው።

ይዘታቸው

ስያሜያቸው እንደሚያመለክተው የአምስቱ መጻሕፍት ዋና ይዘት ሕግ ነው። በአጠቃላይ ስንመለከት ሦስት(3) ዓይነት ሕግጋትን ይዘዋል። እነሱም፡-

√ የሞራል ሕግጋት

√ የክህነት ሕግጋት

√ የአስተዳደር ሕግጋት ናቸው።

ከዚህ ሌላ መጽሐፍቱ ታሪክን፣ ትንቢትንና ትምህርትን የያዙ መጻሕፍት ናቸው። ኦሪት ዘፍጥረት ሙሉ በሙሉ ታሪክ ሲሆን ሌሎቹ ግን ዋና ክፍላቸው ሕግ ሆኖ ታሪክም ይገኝባቸዋል። ስለ እስራኤላውያን በባርነት ስላሳለፉት እና በሙሴ አማካይነት መውጣት ይዘ እስከ ሙሴ ሞት ድረስ ይተርካል።

ክፍል 2

የታሪክ መጻሕፍት

የታሪክ መጻሕት የሚባሉት አስራ ሰባት(17) ሲሆኑ እነዚህ መጻሕፍት በአብዛኛው የእስራኤል ነገስታት እና ሕዝብ ታሪክ የሚናገር ክፍል ነው።እነዚህን መጻሕፍት በቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው።

1. መጽሐፈ ኢያሱ
2. መጽሐፈ መሳፍንት
*3.*መጽ ሐፈ ሩት
*4.1*ኛ እና *2*ኛ ሳሙኤል
*5.1*ኛ እና *2*ኛ ነገስት
*6.1*ኛ ዜና መዋል
*7.2*ኛ ዜና መዋል መጽሐፈ ምናሴ
*8.*መጽሐፈ ዕዝራና መጽሐፈ ነህምያ
*9.*መጽ ሐፈ ዕዝራሱቱኤልና መ.ዕዝራከልዕ
*10.*መጽሐፈ ጦቢት
*11.*መጽሐፈ ዮዲት
*12.*መጽሐፈ አስቴር
*13.1*ኛ መጽሐፈ መቃቢያ
*14.2*ኛ እና *3*ኛ መቃቢያ
*15.*መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደኮርዮን
*16.*መጽሐፈ ኩፋሌ
*17.*መጽሐፈ ሔኖክ

ስያሜያቸውና ጠቅላላ አስተዋጽኦአቸው

እነዚህ መጻሕፍት በአይሁድ ዘንድ ከነብያት መጻሕፍት መካከል ቢመደቡም ከጽሑፋቸው ይዘት አንጻር ሲታይ ሰባው ሊቃውንት እንዳደረጉት በቤተ ክርስቲያን የታሪክ መጽሐፍት መባላቸው ተገቢ ነው።እስራኤላውያን በሙሴና በኢያሱ ርስት ሀገራቸውን ምድረ ከነዓንን ከወረሱ ጀምሮ እስከ እስራኤላውያን በባቢሎን ምርኮ እስከ ተያዙበት ከዚያም በኋላ የተፈጸሙትን ሌሎች ታሪኮች ይተርካሉ።እነርሱም፦

- ✓ 12 ቱ ነገደ እስራኤል በኢያሱ አማካይነት ርስት መከፋፈላቸውን
- ✓ ከኢያሱ ሞት በኋላ ያለ መሪ በእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ መተዳደራቸውን
- ✓ እግዚአብሔርን ሲያሳዝኑ (ሲያስቀይሙ) ጠላት ይነሳባቸው እንደ ነበር
- ✓ ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው ሲጮሁ መሳፍንቶችን እንዳስነሳላቸው።

- ✓ ከሳኦል ጀምሮ እስከ ሰሎሞን ድረስ ለ 120 ዓመታት በአንድ መንግሥት ስር እንደነበሩ
- ✓ በሮብዓም ጊዜ በኃጢአታቸው ምክንያት መንግሥቱ ለሁለት እንደተከፈለ
- ✓ ዐስሩ ነገድ በሰሜን ሁለቱ ነገድ በደቡብ እያንዳንዳቸው ዐስራ ዘጠኝ ነገስታትን እንዳነገሱ
- ✓ በበደላቸው ምክንያት አስሩ ነገድ በአሦር ንጉስ ሁለቱ ነገድ በባቢሎን እንደተማረኩ
- ✓ ከሰባ ዘመን የባቢሎን ምርኮ በኋላ ወደ ሀገራቸው እንደተመለሱ
- ✓ ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ ፈርሶ የነበረው ቤት መቅደስና የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደሰሩ ---ወዘተ ይተርካሉ።

ከዚህ የታሪክ ክፍል ውስጥ በሴቶች ስም የተሰየሙት መጻሕፍት ሦስት ሲሆን እነርሱም መጽሐፈ ሩት፣መጽሐፈ ዮዲትና መጽሐፈ አስቴር ናቸው።እነዚህም የተለየ ይዘት አላቸ ፤ሩት ሙዓባዊት ብትሆንም የእስራኤላዊያንን እምነት ተቀብላ የዳዊት ቅድመአያት ለመሆን መብቃቷ ተመዝግቧል።አይሁዳዊቷ አስቴር በፋርስ ሀገር በአሕዛብ መካከል ንግሥት በነበረችበት ጊዜ ወገኖቿን በጾም ከሐማ የጥፋት ተንኮል እንዲያመልጡ አድርጋለች።ዮዲት እስራኤላዊ ስትሆን የናቡከደነፆር የጦር አዛዥ (አበጋዝ) የነበረው ሆሎፎርኒስ እስራኤልን ለማጥፋት በመጣ ጊዜ በተኛበት ገድላ ሕዝበ እስራኤልን ማዳኗን የሚተርክ ነው።

<u>የታሪክ መጻሕፍት ዓላማና ይዘት</u>

የታሪክ መጻሕፍት በእስራኤል ታሪክ ውስጥ የነቢያትን ታሪክና አገልግሎት ይናገራሉ።እግዚአብሔር ለንገሥታቱ ሆነ ለሕዝቡ መልእክቱን የሚያስተላልፈው በነቢያቱ በኩል ነበር።ለሚታዘዙ ምህረትን ለማይታዘዙ ደግሞ ፍርድን ያደርግ እንደነበር የታሪክ መጻሕፍት ይገልጻሉ።መጻሕፍቱ የያዙት ታሪክ ዓለማዊ ሳይሆን ፍፁም መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ነው።በተለይ ዘግየት ብሎ በዕዝራ የተጻፈው የዜና መዋዕል መጽሐፍ በመጽሐፈ ሳሙኤልና በመጽሐፈ ነገሥት ውስጥ ያልተመዘገቡትን ጨምሮ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ሆኔታውችን ከሌሎች ይልቅ አጎልቶ ያሳያል።እነዚህን ሁሉ ከምርኮ በፊት ያለውን ታሪክ ሲጽፍ መጽሐፈ ዕዝራና መጽሐፈ ነህምያ ደግሞ ከምርኮ በኋላ በሚጠት□በመመለስ□ጊዜ የነበው ታሪክ ይጽፋሉ።አብዛኞቹ የታሪክ መጻሕፍት የእስራኤልን ሃይማኖታዊ ታሪክ መዝገበው ቢታይም ከእስራኤል ውጪ በአሕዛብ ሀገር የተፈጸመውን ታሪክም ይገልጹልናል።

<u>ጸሐፊዎቻቸው</u>

የታሪክ መጻሕፍትን የጻፉት <u>ነብያት ባለ ራእዮችና</u> እንዲሁም <u>በዘመኑ የነበሩት ጸሐፍት</u> ናቸው።እነዚ ሁሉ ቅዱሳን ሰዎች ስለ ሆኑ ያዩትን ከእግዚአብሔር የተገለጠላቸውን እውነተኛ ታሪክ ጽፈዋል። ከጸሐፊዎቹ አንዳንዶቹ የሚጽፏቸውን ታሪኮች ሌሎች መጻሕፍት ይጠቅሳሉ።ይህ ሁኔታ በተለይም በነገሥትና በዜና መዋዕል ጸሐፊዎች በጉልሕ ይታያል።ታሪክ መስታዋት ስለሆነ ጸሐፊውቹ ባሰፈሩልን ታሪክ ዛሬ ያለነው የእኛን ሕይወት እንድናይበት መልእክት አስተላልፈውልናል።

<u>አሳይመንት፡-(</u>በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ የተጠቀሱትን መሳፍንቶች ዘርዝራችሁ ጽፋችሁ አምጡ***?)***

ክፍል 3

<u>የጥበብ /የቅኔ ፡የመዝሙር/ መጻሕፍት</u>

የጥበብ መጻሕፍት የሚባሉት 8 ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው። አጻጻፋቸው በግጥም በመዝሙር፣ በምሳሌና በቅኔ ስለሆነ በመዝሙር ክፍል ተመድበዋል።

መዝሙር፡- ማለት ዘመረ፣ አመሰገነ ካለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ማመስገን ማዜም ሰብሐት ማለት ነው። መጻሕፍቱም የሚከተሉት ናቸው።

1) መጽሐፈ ኢዮብ
2) መዝሙረ ዳዊት
3) መጽሐፈ ምሳሌ
4) መጽሐፈ መክብብ
5) መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን
6) መጽሐፈ ጥበብ
7) መጽሐፈ ተግሳጽ
8) መጽሐፈ ሲራክ

<u>ስያሜያቸው</u>

<u>ጥበብ</u> ማለት የማስተዋል፣ ማንኛውም ነገር ለማግኘት የመመርመር ችሎታ ማለት ነው።/ዘጸ. #1፥1-6/ የሥራ ችሎታ ያላቸው ጥበበኞች ይባላሉ። ጥበብ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ምንም እንኳ ሰዎች የዚህ ዓለም ጥበብ ቢኖራቸውም በእግዚአብሔር ፊት የተናቀ ነው።(1 ቆሮ. 1፥@4) የጥበብ መጻሕፍት የሚገለጹት ግን ከእግዚአብሔር የሆነውን ጥበብ ነው። ስያሜያቸው የሚያመለክተው ይህንኑ ነውና በቤተ አይሁድ እነዚህ መጽሐፍት ጽሑፋት/ ከቱቢም/ ከሚባሉት መጽሐፍት ውስጥ የሚመደቡ ናቸው። ቤተ ክርስትያን እነዚህ መጻሕፍት በሌሎች ሁለት ስያሜዎች ይጠራሉ።

1. <u>የቅኔ መጻሕፍት፡-</u> እነዚህ መጻሕፍት አብዛኞዎቹ በሰምና በወርቅ በምሳሌም የተነገሩ በመሆናቸው የእብራይስጡን የቅኔ መንገድ የተከተለ ነው። ቅኔው በሌሎች ቋንቋዎች ሲተረጐሙ ፍሬ ሐሳቡን ካልሆነ በቀር ቅኔውን እንዳለ ለመረዳት አዳጋች ነው።

2. መዝሙራት፡- በሉቃ. @4፥$4 እና በሌሎችም ጥቅሶችም እንደተገለጠው ብዙ ጊዜ መዝሙራት ሲባል ያሚያመለክተው እነዚህን መጻሕፍት ነው። ምክንያቱም ከመጽሐፍቱ አንዳንዶቹ በመዝሙር መልክ የቀረቡ በመሆናቸው ነው። ለምሳሌ፡- መዝሙረ ዳዊትንና መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞንን መመልከት ይቻላል።

አቀራረባቸው

የጥበብ መጻሕፍት አብዛኞቹ የቀረቡት በግጥም መልክ ነው። ልክ እንደ ቅኔው በዕብራይስጥ ቋንቋ ካልሆን በቀር በሌሎች ቋንቋዎች ተተርጉሞ ግጥምነቱ ጠፍቷል ከጥበብ መጽሐፍት አንዳንዶቹ በስድ ንባብ የቀረቡ አሉ። ለምሳሌ፡- መጽሐፈ መክብብ ሙሉ የቀረበው በስድ ንባብ ነው። መጸሐፈ ኢዮብ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ምዕራፍ በስድ ንባብ ቀርቧል።

እነዚህ መጻሕፍት በተለይም ለልጆችና ለወጣቶች ለጠቢባንም ሊገባ በሚችል መልክ የቀረቡ መጻሕፍት ናቸው። ምሳሌያዊ አቀራረባቸው መልእክቱ እንዳይረሳ/እንዲስተዋል/ ያደርጋል።ብዙን ጊዜ በሁለተኛ መደብ አነጋገር የቀረቡ መጻሕፍት ናቸው። ባለቤቱም/ ተናጋሪው/ ራሱን በአንደኛ መደብ አነጋገር ያቀርባል። በአንዳብዶቹ መጻሕፍት ውስጥ የሁለት ሰዎች የሐሳብ ልውውጥ ይታይባቸዋል። ለምሳሌ፡- መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ይህ ዓይነት አቀራረብ አለው።

ይዘታቸው

የጥበብ መጻሕፍት ዋና ይዘት በፈሪሃ እግዚአብሔር የሚገኘውን ጥበብ መግለጥ ነው። ብዙዎች የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔር መፍራት ነው። ይላሉ /ኢዮ. @8፥@8፣ መዝ.)!፥!፣ ምሳ.1፥7/ ጥበብ በተለይም ለአስተዳዳሪዎች ለነገሥታት ለመኳንንት ሕዝብን እንዲመሩበት በእጅጉ ያስፈልጋቸዋል። ከእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ መጽሐፈ ምሳሌ፣ መጽሐፈ መክብብን ና መኃልየ መኃልይ የጻፈው ንጉሥ ሰሎሞን ነው።መንግሥቱን እንደተረከበ ሰሎሞን ከእግዚአብሔር ሀብትና ብልጥግና ሳይሆን ጥበብና ማስተዋልን ነበር የጠየቀው። (1ነገ. 3፥9-!3)። ከዚህም የተነሳ ከ#) በላይ የሚሆን ምሳሌዎች በጥበብ ተናግሯል። አባቱ ዳዊትም በጥበብ የተሞላ ሰው ስለ ነበር (1ሳሙ. !4፥@9-#4) መዝሙረ ዳዊትን በጥበብ ጽፋ E ል።

ጸሐፊዎቻቸው

የጥበብ መጻሕፍት የጻፏቸው ሰዎች ጥበብን በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞሉ ናቸው። የኢዮብ መጽሐፍ ኤሊሁ እንደ ጻፈው ሲናገር መዝሙራትን በተመለከተ ግን አብዛኛው ንጉሥ ዳዊትና ሌሎች የእግዚአብሔር ሰዎች አዘጋጅተዋል። መጽሐፈ ምሳሌም እንዲሁ ከሰሎሞን ሌላ የሌሎች የእግዚአብሔር ሰዎች ዝግጅት እንዳለበት ከመጽሐፉ ርእሶች መረዳት ይቻላል።(መዝ .*፣1፣)$5፣)$6፣ ምሳ. @5፥1፣ #፥1....) ተመልክቱ። መኃልየ መኃልይንና መጽሐፈ መክብብን ሰሎሞን እንደዘጋጃቸው በርዕሶቻቸው ተገልጿል።

ክፍል 4

የትንቢት መጻሕፍት

የትንቢት መጻሕፍት የምንላቸው !6 ሲሆኑ ከኢሳይያስ እስከ ሚልኪያስ ያሉት መጻሕፍት ናቸው።
ነብይ፡- ማለት አፈ አምላክ/የአምላክ አፍ/ መምህር ማለት ነው። በአጠቃላይ የትንቢት መጻሕፍት የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

1) ትንቢተ ኢሳይያስ
2) ትንቢተ ኤርሚያስ
3) ትንቢተ ሕዝቅኤል
4) ትንቢተ ዳንኤል
5) ትንቢተ ሆሴዕ
6) ትንቢተ አሞፅ
7) ትንቢተ ናሆም
8) ትንቢተ ሶፎንያስ
9) ትንቢተ ሚክያስ
10) ትንቢተ ዕንባቆም
11) ትንቢተ ሐጌ
12) ትንቢተ ዘካርያስ
13) ትንቢተ ዮናስ
14) ትንቢተ ኢዩኤል
15) ትንቢተ አብድዩ
16) ትንቢተ ሚልክያስ

ስያሜአቸው

እነዚህ መጻሕፍት የትንቢት መጻሕፍት ተብለው ተሰይመዋል። ምክንያቱም የሁሉም ጸሐፊዎች ነብያት ናቸው። አንዳንዶቹ ግን በደቀ መዝሙሮቻቸው አጽፈዋል፤ መጻሕፍቱም በጸሐፊዎቻቸው ምክንያት ነቢያት ይባላሉ።(ማቴ. 5፥!7) ነቢያት ትንቢት የሚናገሩና ከእግዚአብሔር የመጣላቸውን ቃል ተቀብለው ስለሆነ የጻፉትም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በማለት ነው።(አሞ 1፥1) እግዚአብሔር በእዉነት ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም(አሞ. 3፥7)። እነዚህ የነቢያት መጽሐፍት ከእግዚአብሔር ለነቢያት የተገለጠው ቃል ይዘው ስለ ሚገኙና ወደ ፊት የሚሆነውን ስለሚናገሩ የትንቢት መጻሕፍት ተብለዋል።

አከፋፈላቸው

የነቢያቱን ዓይነት በተመለከተ

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*` „Ê¡e }ªlÊ

- <u>ዐበይት ነቢያት</u>፡- እነዚህ በመጽሐፋቸው ብዛት ዐበይት ተብለዋል። እነሱም ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ዳንኤል ናቸው።
- <u>ደቂቅ ነቢያት</u>፡- እነዚህ በመጽሐፋቸው ምዕራፍ ማነስ ደቂቃን ተብለዋል። እነሱም የተቀሩት አስራ ሁለቱነቢያት ናቸው።
- <u>ቀደምት</u>፡- እነዚህ ከአዳም ጀምሮ የነበሩ ደጋግ አባቶች ናቸው። የመጀመሪያው ነቢይ አዳም ነው። እነሱም ኖህ፣ አብርሃም ፣ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ፣ሙሴ ቀደምት ነቢያት ናቸው።
- <u>ድኃርት</u>፡- የምንላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትንቢታቸውን የምናገኝው 16 ቱ ነቢያት ናቸው።
- <u>የቃል</u>፡- እነዚህ የተናገሩትን በቃል ያላሰፈሩ ነቢያት ናቸው። ለምሳሌ፡- ጋድ፣ ናታን፣ ኤልያስ፣ ኤልሳዕ.... ናቸው።
- <u>የጽሑፍ ነቢያት</u>፡- የተናገሩትን በጽሑፍ ያሰፈሩት ናቸው።እነሱም ከነቢዩ ኢሳይያስ እስከ ሚልክያስ ድረስ ያሉት ናቸው።
- <u>ሴት ነቢያት</u>፡- የሙሴ እኅት ማርያም ዘጸ 15÷2 ነቢይት ዲቦራ መሳ 4÷14 በኢዮስያስ ዘመን የነበረችው ሕልዳና 2ኛ ነሰ 22÷15 ነቢይት ሐና ሉቃ 2÷36 የቅዱ ፊልጶስ 4 ቱ ደናግላን የሐዋ 21÷9
- <u>የሐሰት ነቢያት</u>፡- እግዚአብሔር ሳይልካቸው ተልከናል ሳይጠራቸው ተጠርተናል የሚሉ ናቸው።እነዚህም ሐሰተኛነታቸው የሚታወቀው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።
  - ✓ የተናገሩት ሳይፈጸም ሲቀር ዘዳ 18÷20
  - ✓ ባዕድ አምልኮት ሲከተሉ ዘዳ 13÷1-4
  - ✓ አካሄዳቸው ክፉ ሲሆን ኤር 23÷16
  - ✓ ኃጢአት ሲበዛ ንስሐ ሳይሆን ሰላምን ሲሰብኩ ኤር 14

<u>ቦታን በተመለከተ ደግሞ በ 3 ይከፈላሉ</u>

1) <u>የይሁዳ ነብያት</u>፡- ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሚክያስ፣ አሞጽ፣ ሶፎኒያስ፣ሐጌ፣ ሚልክያስ ናቸው።
2) <u>የሰማርያ ነብያት</u>፡- ሆሴዕ፣ አሞጽ፣ዮናስ ናቸው።
3) <u>የባቢሎን ነቢያት</u>፡- ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል..... ናቸው።

<u>እነዚህ ነብያት ዘመንን በተመለከተ እንደገና በ 3 ይከፈላል</u>

1) <u>ከባቢሎን ምርኮ በፊት</u>፡- ኢሳይያስ፣ ሆሴዕ፣ አሞጽ፣ ሚክያስ፣ ኢዩኤል፣ አብድዩ
2) <u>በባቢሎን ምርኮ ጊዜ</u>፡- ኤርምያስ፣ ዕንባቆም፣ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል።
3) <u>ከባቢሎን ምርኮ በኋላ፡-</u> ሐጌ፣ ዘካርያስ፣ሚልክያስ፣ ናቸው።

<u>ይዘታቸው</u>


የነቢያት መጻሕፍ ይዘት በአጠቃላይ ሲታዩ ሁለት የተያያዙ ነገሮች ያካተተ ነው። ይኸውም


1) የእግዚአብሔር ውሳኔ ስለሆኑ ድርጊቶቹ ስለመንግሥታትና ስለሰዎች ስለነቢያት ይገልጣሉ።
2) ወደፊት ስለሚሆነው ድርጊቶች ይናገራሉ

መጻሕፍቱ ትንቢቱ ብቻ ሳይሆን ነቢያት ትንቢቱን ብቻ ሳይሆን ነቢያት ትንቢቱን እንዴት ይገለጡ እንደነበር መዝግበዋል ነቢያት ትንቢታቸውን በምሳሌና፣ በድርጊት ይገለጡ ነበር። ነብያት የጻፏቸው እነዚህ መጻሕፍት ዋና ይዘታቸው ትንቢት ቢሆንም ከነቢያት ብዙዎቹ በዘመነ ነገሥታት የነበሩ ስለሆነ አልፎ አልፎ በመጽሐፈ ነገሥትና በዜና መዋዕል የተተረኩ ታሪኮች በስፋት ይዘዋል። በምሳሌያዊ አነጋገር የተነገሩ ትንቢቶችንም አካተዋል።

<u>መልእክታቸው</u>

የትንቢት መጻሕፍት ስለ እስራኤል ዘሥጋ የሚናገሩ ቢሆንም ፍጻሜያቸውና ዋና መልእክታቸው በዚህ ዘመን ላለነው ለእኛና ወደ ፊት ለሚመጣው ትውልድ የሚሆን ነው። በብዙዎች እንደሚታመነው ያለንበት ዘመን ነቢያት የመጨረሻው ዘመን በማለት የሚገለጡት ዘመን ነው። ስለዚህ መልክታቸውን ጠንቅቀን መረዳት አለብን ይሁን እንጂ የትንቢት ቃል ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም (2 ጴጥ. 1፥@)። በእግዚአብሔር መንፈስ መተርጎም አለበት። ትንቢቱ በተግባር በተፈጸመ ጊዜ ደግሞ የተፈጸመውን ማስታዋል ያስፈልጋል(ማቴ. @4፥!5) አለማስተዋል እንደ አይሁድ ከስሕተት ላይ ይጥላል(ማቴ.@2፥@9) ከእግዚአብሔር የተነገረው ቃልና ትንቢት ባለ ማስተዋል በኃጢአትና በበደል ለሚኖሩ ሰዎች የትንቢት መጽሐፍት ብርቱ ማስጠንቂቂያዎች ይዘዋል። ለሚያስተውሉ ሰዎች ደግሞ ታላላቅና ብሩህ የሆኑ የተስፋ ትንቢቶችን ይዘዋል።







የብሉይ ኪዳን አባቶች በከፊሉ

ምዕራፍ ዘጠኝ
ሐዲስ ኪዳን

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጠቅላይ ይዘት

ኪዳን፡- ማለት በሁለት ወገኖች መካከል የሚመሠረት በመሐላ የሚፀና ከተመሰረተ በኋላ በሁሉቱ ወኖች መካከል እንደ ሕግ ሆኖ የሚሠራ ስምምነት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኪዳን ሲባል ከእግዚአብሔር ለሠው የተሠጠ እና ሠዎች በእምነት የተቀበሉት ውል ነው። ከእግዚአብሔር ለሰዎች የተሠጠ የድህነት ኪዳን ነው። ይኸውም በወልደ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንደሚያገኝ የሚያረጋግጥ ኪዳን ነው። የዚህ የኪዳን ቃላትም፡-

- " ያመነ የተጠመቀ ይድናል" ማር !6÷!6
- ‹‹በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው›› 1 ዮሐ 3÷ #6
- ‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው›› ዮሐ 6÷ $7
- ‹‹ሰው በልቡ አምኖ በአፋ መስክሮ ይድናል›› ሮሜ !÷!3
- ‹‹ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው›› ዮሐ 6÷ %4 እነዚህ ጥቂቶቹ ናቸው።

ሐዲስ ኪዳን ሲባል ፊተኛ ኪዳን እንዳለ ያመለክታል ይህም ፊተኛ ኪዳን ብሉይ ኪዳን ነው። ብሉይ ኪዳን ብሉይ ያሠኘው የሐዲስ ኪዳን መምጣት ነው። ሐዲስ ማለት ፊተኛውን አስረጅቷል እንዲል ዕብ 8÷ !3 ሐዲስ ኪዳን ሐዲስ የተባለው በብሉይ ኪዳን ያሳለፋቸው ማለትም ምሳሌነታቸውን በመፈጸማቸው የተካቸው አንዳንድ ሥርዓቶች ስላሉ ነው። ምሳሌ፡- ግዝረት ፣መስዋዕተ ኦሪት --ቆላ 2፡!1 ፣ ዕብ 9÷9

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*`„Ê¡e }ªIÊ

የሐዲስ ኪዳን ተስፋው የዘላለም ሕይወት ሲሆን ምልክቱም ቅዱስ ቁርባን ነው። ዮሐ 6÷ %4

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በ 5 ይከፈላሉ፦

እነሱም፦

1. የወንጌል ክፍል 4
2. የታሪክ ክፍል.....1
3. የመልእክት ክፍል.....21
4. የትንቢት (ራእይ) ክፍል..1
5. የሥርዓት ክፍል.....8

ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዳቸው በቅደም ተከተል እንመለከታለን።

ክፍል አንድ

የወንጌል ክፍል

ስያሜያቸው

ወንጌል የሚለው ቃል የጌታ ትምህርት ስያሜ ሲሆን ትምህርቱን ወንጌል ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ የጠራው ራሱ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል በማለት። ማቴ @4፡!4

ከዚህ የጌታ ቃል በመነሣት ሐዋርያት ስለ ክርስቶስ የጻፉትንና ያስተማሩትን ሁሉ ወንጌል ብለውታል። ወንጌል የሚለው ቃል ኢቫንጌልዮን የሚለውን የግሪክ ቃል የተካ ሲሆን ትርጉሙም ስብከት ብስራት ወይም የምስራች ማለት ነው። ወንጌል የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ከዳዊት ዘር በሥጋ ተገልጦ ዓለምን ስለማዳኑ የሚናገር ታላቅ የምስራች ነው። በነቢያት አፍ አስቀድሞ ተናግሯል።ኢሳ ^1፡1-2 በሐዲስ ኪዳን ግን ይህን የምስራች በመጀመሪያ የተናገሩት ቅዱሳን መላእክት ናቸው። ሉቃ 2፡!-!1 ከዚህ በኋላ በተስፋ ሲጠበቅ የነበረዉ ወንጌል በጌታችንና በተከታዮቹ በሚገባ ተነግሯል ተሰብኳል። ዛሬም የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ እየተሰበከ ነው።

የወንጌላት ጸሐፊዎች

የዚህ የወንጌል ክፍል ጸሐፊዎች 4 ቱ ወንጌላውያን ማቴዎስ ፣ማርቆስ ፣ሉቃስና ዮሐንስ ናቸው። አራት የሆኑትም የቤ/ክ ሥርዓት በሰማይም በምድርም አንድ ስለሆነ በሰማይ የእግዚአብሔርን ዙፋን የማሸከሙ 4 ቱ ኪሩቤል አሉ። የእነዚህ ምሣሌ ነው። ሌላው በአራቱ አፍላጋት ኤፍራጠስ፣ጤግሮስ፣ኤፌሶን ፣ግዮን ሌላው በአራቱ ወቅታት ፀደይ፣መፀው፣ክረመት፣ሐጋይ/በጋ እንዲሁም በያዕቆብ በ 4 ቱ ሚስቶቹ ራሔል፣ ልያ፣ባላ፣ ዘለፋ በነዚህ ይመሰላሉ ጌታም ወንጌሉን እንዲጽፉ ወንጌላውያንን ሲመርጥ ሁለቱን ከአርድዕት ሁለቱን ከሐዋርያት ያደረገው ስለ ወንጌል ክብር ነው። ሙሉ ከአርድት ቢያደርግ ኖረ ደገኛይቱ ወንጌል በሐዋርያት ቀርታለች ባሉ ነበር። ጨርሶ ከሐዋርያት ያላደረገው ስለ አርድዕት ክብር ሲል ለምን ከዛ በኋላ አርድዕቶች ወጥተው ሲያስተምሩአቸው ስለማይቀበሏቸው ስለ ሁለቱም ክብር ሲል ሁለቱን ከሐዋርያት ሁለቱን ከአርድዕት እንዲጽፉ አድርጓል።

ይዘታቸው

አራቱም ወንጌላት የሚከተሉትን ታሪኮች ሁሉ መዝግበው ወይም ይዘው ይገኛሉ።

1. ስለ ክርስቶስ ጥምቀት
2. ስለ 5 ቪህ ሰዎች መመገቡን
3. ስለ ጌታ መያዝ
4. ስለ ጌታ ስቅለት
5. ስለጌታ ትንሣኤ

አሳይመንት፦ (አራቱ ወንጌላውያን ለምን በአራቱ ነፋሳት ይመሰላሉ?)

ክፍል ሁለት

የታሪክ መጽሐፍ

ስያሜው

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የታሪክ መጽሐፍ በመባል የሚታወቀው የሐዋርያት ሥራ ብቻ ነው። መጽሐፉ የሚገኘው ከወንጌላት ቀጥሎ ነው። ልክ እንደ ማቴዎስ ወንጌል @8 ምዕራፎች ያሉት ታላቅ መጽሐፍ ሲሆን። የታሪክ መጽሐፍ ሊባል የቻለው ወንጌላት ከቆሙበት በመቀጠል የቤተ

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*` „Ê¡e }ªlÊ

ክርስቲያንንና የሐዋርያትን ታሪክ ስለ መዘገበ ነው። በግዕዙ ይህ መጽሐፍ ግብረ ሐዋርያት ተብሎ ይጠራል። ይኸውም የሐዋርያት ሥራ ማለት ነው። አንዳንድ የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት በመጽሐፉ ውስጥ በብዛት የተገለጸውን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በመመልከት ይህን መጽሐፍ ግብረ መንፈስ ቅዱስ /የመንፈስ ቅዱስ ሥራ / ብለው ይጠሩታል። ፍትሐ ነገሥት ደግሞ መጽሐፈ አብረክሲስ ብሎ ይጠራዋል።

<u>ጸሐፊው</u>

የግብረ ሐዋርያት ጸሐፊ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ሲሆን የጻፈውም ወንጌሉን በመጀመሪያ ለጻፈለት ቴዎፍሎስ ለተባለው ባለ ሥልጣን ነው። ሉቃ 1÷1 ፣ ሐዋ 1÷1 ሉቃስ መጀመሪያ ባለመድኃኒት /ሐኪም/ በኋላም የቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙር ነበር። ቈላ 4፡!4 ሰዓሊም እንደነበረ ምስለ ፍቁር ወልዳን እንደሳለም ይነገራል። ወንጌሉን የጻፈው መጀመሪያ ጌታን በዐይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት ባስተላለፉት መሠረት ሲሆን ግብረ ሐዋርያትን የጻፈው ግን በብዛት ራሱ ካየው ከሰማው ነው።



ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ የእመቤታችንን ሥነ ሥዕል እንደሳለ

<u>ይዘቱ</u>

የታሪክ ክፍል በመባል የሚታወቀው የሐዋርያት ሥራ ቅዱስ ሉቃስ ወንጌሉን ካቀመበት ከጌታ ዕርገት ጀምሮ ቅዱስ ጳውሎስ ሮሜ እስከ ገባበት ድረስ ያለውን ታሪክ ይዟል። ይኸውም በአጠቃላይ ሲታይ የ@8 ዓመታት ታሪክ ሆኖ ከ#4-^2 ዓ.ም ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ነው። የመጽሐፉ ይዘት በአስተዋጽኦ ሲዘረዘር እንደሚከተለው ይታያል።


- ✔ ጌታ እንዳረገ
- ✔ ከጌታ ዕርገት በኋላ 12 ዐ ቤተሰብ በአንድነት እንደነበሩ
- ✔ በይሁዳ ምትክ ማትያስ እንደገባ
- ✔ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት እንደወረደ
- ✔ እኩያን አይሁድ እስጢፋኖስን እንደገደሉት
- ✔ በኢየሩሳሌም የሐዋርያት ጉባኤ /ሲኖዶስ/ እንደተካሄደ
- ✔ የቅዱስ ጳውሎስ መጠራትና ሐዋርያዊ ጉዞዎቹ ናቸው።

ክፍል ሶስት

<u>የመልዕክት ክፍል</u>

¾SêNõ pÆe Ø“ƒ ²*` „Ê¡e }ªlÊ

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ መልዕክታት @1 ሲሆኑ እነሱም የሚከተሉት ናቸው። !4t ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈው መልዕክት ሲሆን 2 የጴጥሮስ ፣ 3 የዮሐንስ ፣1 የያዕቆብ ፣ 1 የይደሁዳ መልዕክታት ሲሆኑ እነሱም፦



<u>ስያሜያቸው</u>

እነዚህ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መልዕክታት የተባሉት ሐዋርያት በተለያዩ ቦታዎች ወንጌልን በመስበክ ብዙዎቹን ካሳመኑ በኋላ ለተመሳሳይ ሥራ ወደ ሌላ ቦታ እየተዘዋወሩ ያስተማርዋቸውን ሰዎች ለማጽናት ከስሕተትም ለመጠበቅ ሲሉ በደብዳቤ መልዕክት እየጻፉ ይልኩላቸው የነበሩ ጽሑፎች ስለሆኑ ነው። ጽሑፎቹም መልዕክታት/ደብዳቤ/ እንደሆኑ ተገልጿል። ሮሜ **6÷@1** ሃያ አንዱ መልዕክታት የትምህርት መጻሕፍት በመባል ይታወቃሉ። ሌሎቹ መልዕክታት ታሪክንና ትንቢትን የሚገልጹ ሲሆኑ እነዚህ ግን ሃይማኖት ነክ ምክርንና ተግሳጽን በትምህርት መልክ ስለያዙ የትምህርት መጻሕፍት ሊባሉ ችለዋል።

<u>አከፋፈላቸው</u>

<u>የተጻፈላቸውን ሰዎች በተመለከተ ለሦስት /3/ ይከፈላሉ።</u>

1. <u>የግል መልዕክት</u> ፦ 1 ኛና 2 ኛ ጢሞቴዎስ ፣ቲቶ ፣ፊልሞና፣2 እና 3 ዮሐንስ ሲሆኑ
2. <u>የማኅበር መልዕክታት</u>፦ ሮሜ 1 ኛ እና 2 ኛ ቆሮንቶስ ፣ገላትያ፣ ኤፌሶን፣ ፊሊጵስዮስ ፣ ቆላስያስ፣ 1 እና 2 ተሰሎንቄ ፣ዕብራውያን ሲሆኑ
3. <u>ዓለም አቀፍ /አጠቃላይ/መልዕክታት</u> 1 ኛና 2 ኛ ጴጥሮስ ፣ያዕቆብ ፣1 ኛ ዮሐንስ ፣ይሁዳ ናቸው።

<u>ይዘታቸው</u>

ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን ወይም ሰዎችን መንብኘት ባልቻሉ ጊዜ መልዕክታት በመጻፍ የተለያዩ ትምህርቶችን ያስተላልፉላቸዋል። በመልዕክታቸውም ስህተትን ይቃወሙ ፣አካሄድን ያርሙ ፣ሰዎችን ያፅናኑ ነበር። ስለዚህ የመልዕክታቱ ዋና ይዘት ላመኑ ሰዎች ክርስቲያናዊ ትምህርትን መስጠት ነው። የመልዕክታቱ ይዘት በአስተዋፅኦ ዝርዝር ሲታይ የሚከተለው ይሆናል።

- ✔ ሰው ሁሉ በክርስቶስ በማመን እንዲድን ይገልጣል
- ✔ ስለ እምነትና ስለ መልካም ሥራ ሰፊ ትምህርት ይሰጣሉ
- ✔ በወንጌል አስተማሪዎች ምክንያት መከፋፈል /መለያየት/ እንደማይገባ ያስተምራሉ
- ✔ ወንጌል በመስበክ የስሕተት ትምህርት የሚያስተምሩትን ያወግዛሉ
- ✔ የሥጋ ሥራዎችን በተለይም ዝሙት፣ጣዖት ማምለክን ይቃወማሉ

- ✓ በሃይማኖታቸው ምክንያት ስለ ክርስቶስ ስም መከራና ስደት የደረሰባቸዉን ያጽናናሉ።
- ✓ በብሉይ ኪዳን ጥላ የሆኑት ነገሮች በሐዲስ ኪዳን እካላቸው ክርስቶስ እንደሆነ ያሳያሉ።
- ✓ ስለ ትንሣኤ ሙታንና ስለ ዳግም ምጽዓት ያስተምራሉ።

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ነገሮች ሃያ አንዱ መልዕክታት ይዘዋል። ከ!4 ቱ የጳውሎስ መልዕክት ውስጥ 1 ኛ እና 2 ኛ ጢሞቴዎስ ፣ቲቶ የኖላዊነት /የመምህር ፣የጠባቂነት/ መልዕክታት ናቸው። የዕብራውያን መልዕክት ደግሞ ከሌሎማች ለየት በማለት የብሉይ ኪዳንን መፈፀምና በተለይም ይባሱን ለኃጢአተኞች እራሱን መስዋዕት አድርጎ ያቀረበውን የኢየሱስ ክርስቶስን ሊቀ ካህናትነት ይገልጻል።

ክፍል አራት

የትንቢት (የራእይ) መጽሐፍ

ስያሜው

በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የትንቢት መጽሐፍ የሚባለው የዮሐንስ ራእይ ብቻ ነው። ከሐዲስ ኪዳን ውስጥ ጌታችንና ሐዋርያት የተነበዩአቸው ብዙ የትንቢት ቃላት ቢኖሩም እንኳ መጽሐፉ በሙሉ የትንቢት ቃል የሆነው ይህ መጽሐፍ ብቻ ነው። የትንቢት ቃል ስመሆኑም ከራሱ መጽሐፍ ውስጥ ተገልጧል። ራዕ @2፡!8 የትንቢቱን ቃል የተናገረው ዮሐንስ በደሴተ ፍጥሞ ሆኖ ሠማይ እስከ ጽርሐ አርያም ምድር እስከ በርባኖስ /እንጦሮንጦስ/ ድረስ ተከፍቶ ምሥጢራት ተመልክቶ በተመለከተው ራእይ መሠረት ስለጻፈ የዮሐንስ ራእይ ተብሏል። በግሪክ ቋንቋ ይህ መጽሐፍ አቡቀለምሲስ /ኢፓካሉኘሲስ/ በመባል ይጠራል። ይኸውም የምስጢር ባለቤት /ባለ ራእይ/ ማለት ነው። ሰማይ ተከፍቶ ለዮሐንስ ድንቅ ምሥጢር በራእይ እንደታየው መዝግቦ ስለሚገኝ የተሰጠው ስያሜ ነው።

ይዘቱ

የዮሐንስ ራእይን ይዘት እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል።

1. ለ 7 ቱ አብያተ ክርስቲያናት ያስተላለፈው መልእክት
2. ሰባት ፍፁም ቁጥር ስለሆነ ስለ ሰባቱ ነገሮች በብዛት ይናገራል
3. ቤ/ክ ከዘንዶው ከዲያቢሎስ ጋርና ከአውሬው ከሐሳዊ መሲህ ጋር ያላትን ሰልፍና በመጨረሻ የምታገኘውን ድል ይናገራል
4. ስለ ወደፊቱ የጌታ ምጽዓትና ስለ መጪው የፍርድ ቀን ይናገራል
5. ስለ አዲሲቱ ሰማይና ስለ አዲሲቱ ምድር ይናገራል

ከዚህ ሌላ የዮሐንስ ራእይ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስን አምነው በቅድስና በመኖራቸው ምክንያት መከራ ሲደርስባቸው ተስፋቸው ሙሉ እንዲሆን የሚያበረታታና በደረሰባቸው ስደተና መከራ ውስጥ በእምነታቸው እንዲፀኑ የሚያደፋፍር መጽሐፍ ነው።

አቀራረቡ

የትንቢት መጽሐፍ ከሥነ ጽሑፍ አንጻር ሦስት ዓይነት አቀራረብ አለው።

1. በማሳሰቢያ ክፍል ፡- የቀረበ አለው። የመጽሐፍ መግቢያና መደምደሚያ በዚህ ዓይነት የቀረቡ ናቸው።
2. በደብደቤ መልክ፡- የቀረቡ የመልእክት ክፍል አለው። በምዕራፍ 2 እና 3 ላይ የሚገኙት ለሰባቱ አብያተ ክርሰቲያናት የተላለፉት መልእክታት በቤ/ክ መልአክ /አለቃ/ ስም የቀረቡ ደብዳቤዎች ናቸው።
3. በራእይ የቀረበው፡- አንድ የተወሰነ ክፍል ሲሆን ይህም የመጽሐፉ አብዛኛው ክፍል ነው። ራእይ በብሉይ ኪዳን በነበሩ የመቅደስ ሥርዓቶችና ንዋያተ ቅድሳት ምሳሌነት ለዮሐንስ የታየ ነው።



ባለ ራእዩ ወንጌላዊ ቅዱስ ዮሐንስ (ነባቤ መለኮት)

ክፍል አምስት

<u>የሥርዓት መጻሕፍት /መጻሕፍተ ሥርዓት/</u>

<u>ዝርዝራቸው</u>

እንደ ቤተክርቲያናችን አቆጣጠር 8 የሥርዓት መጻሕፍት አሉ። እነሱም፦

- ✔ ትእዛዛተ ሲኖዶስ
- ✔ ግጽው ሲኖዶስ
- ✔ አብጥሊስ
- ✔ ሥርዓተ ጽዮን ሲኖዶስ
- ✔ መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ
- ✔ መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ
- ✔ መጽሐፈ ቀሌሜንጦስ
- ✔ መጽሐፈ ዲድስቅልያ ናቸው።

<u>ጸሐፊዎቻቸው</u>

የሐዲስ ኪዳን የሥርዓት መጻሕፍትን ከጸሐፊዎቻቸው አንጻር በ 3 መድበን እንመለከታቸዋለን።

1. <u>አራቱ መጻሕፍተ ሲኖዶስና መጽሐፈ ዲድስቅልያ</u>፦ሐዋርያት እየተሰባሰቡ ያዘጋጇቸውን መጻሕፍት እንደ ሆኑ ይነገራል።
2. <u>ሁለቱ መጻሕፍተ ኪዳን</u>፦ ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ከዕርገቱ በፊት የተናገራቸው ናቸው። ጸሐፊያቸው ግን ማን እንደሆነ አልተገለጠም
3. <u>መጽሐፈ ቀሌምንጦስ</u>፦ የጻፈው ከስያሜው እንደምንረዳው ከሰባው አርድዕት ጋር የሚቆጠረው የጴጥሮስ ደቀ መዝሙር የነበረው ቀሌመንጦስ ነው። ይህ ሰው በሮም በኤጴስ ቆጶስነት ተሾሞ የነበረው በፊሊ. **4፡3** ላይ የተገለጠው እሱ ነው።

<u>ይዘታቸው</u>

የእነዚህ የሐዲስ ኪዳን የሥርዓት መጻሕፍት ዋና ይዘት የቤ/ክ ሥርዓት ነው። ከመጻሕፍቱ አንዳንዶቹ ግን የተለየ ይዘት አላቸው ለምሳሌ፦ መጽሐፈ ዲድስቅልያ ይዘቱ ትምህርታዊ ነው። ዲድስቅልያ ማለት ራሱ ትምህርት ማለት ነው። ይህም ከመጽሐፈ ሲራክ ፣ከሰሎሞንና ከመዝሙረ ዳዊት ጋር ለልጆች ትምህርት ሆኖ እንዲሰጥ ያዝዛል። ይሁን እንጂ በሌላው ዓለም ዲዳኪ/ዲድስቅልያ/ ሙሉ በሙሉ ትምህርት አዘል ሲሆን በኢትዮጵያ ያለው ዲድስቅልያ ግን በሥርዓት መልክ የቀረበ ትምህርት ነው።

<u>መጽሐፈ ቄሌምንጦስ</u> ከሥርዓተ ቤ/ክ ሌላ ስለ ወደፊቱ የተነገረ ትንቢትና ራእይ ይዟል። ቀሌምንጦስ በሰው ስም የተሰየሙ ብዙ ጽሑፎች ቢኖሩም ይህ መጽሐፍ 7 ክፍል አለው። ጌታ ለጴጥሮስ ለቀሌምንጦስ ያስተላለፈውን ቃል የያዘ ጽሑፍ እንደሆነ ይነገራል።

መጻሕፍተ ኪዳንንም ስንመለከት አንደኛው መጽሐፍ የቤ/ክ ሥርዓት ሲሆን ሁለተኛው መጽሐፈ ኪዳን ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት የሚገልጽ ጽሑፍን ይዟል።

መጻሕፍቱ የተጻፉበት ቋንቋ

ከመጻሕፍቱ አንዳንዶቹ በአሁኑ ጊዜ በሌለ ቋንቋ ተጽፈው የሚገኙ ቢሆንም በኢትዮጵያ ቤ/ክ ግን እስከ አሁን ድረስ መጻሕፍቱ ተጽፈው የሚገኙት በግዕዝ ቋንቋ ብቻ ነው። ለዚያውም የእጅ ጽሑፍ ነው። እንጂ የማሕተም ጽሑፍ አይደለም የሚገኙትም በአንዳንድ አብያተ መጻሕፍትና በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እቃ ቤቶች ውስጥ ነው። ሁሉም ሰው መጻሕፍቱን አንብቦ መረዳት እንዲችል በአማርኛ ቋንቋ ቢተረጎም መልካም ይሆናል።

ማጠቃለያ

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በሕያው አምላክ በልዑል እግዚአብሔር ምሥጢር ገላጭነት ነው። ስለሆነም መጽሐፉ ሕያው ነው። እኛንም ስናነብ ሕያዋን ያደርገናል ቅዱስ ነውና ቅዱሳን ያደርገናል። ክቡር ነውና ስናነበው ይባርከናል። በመሆኑም ይህን መጽሐፍ ስናነብ ከላይ የጠቀሰናቸውን ትምህርቶች ባሕሎች የአነጋገር ዘይቤዎች በትክክል በመረዳት የአገላለጽ ስልቱንም በመገንዘብ ልናነብ ያስፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስ ተጠጥቶ የማያልቅ ባሕር ተነግሮ የማያልቅ ረቂቅ ምሥጢር ነው። ስለሆነም ይህን ምሥጢራ ጥልቅ ሰፊ የሆነው መጽሐፍ አባቶች በትርጓሜ ያመሰጥሩታልና። እኛም ስናነብ ምሥጢሩ ሲረቅብን ይህን ትርጓሜ መጽሐፍ በመጠቀም ትክክለኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት በመረዳት ልናነብ (ልናጠና) ይገባል።

አነሳስቶ ያስጀመረን አስጀምሮ ያስፈጸመን ልዑል እግዚአብሔር ስሙ የተመሠገነ ይሁን። አሜን!

ዋቢ መጻሕፍት

1. ---------- ።1980 ዓ/ም። መጽሐፍ ቅዱስ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ።
2. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)።1972 ዓ.ም። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አዲስ አበባ ኢትዮጵያ።
3. ዳንኤል ክብረት (ዲያቆን)። 2002.ዓ.ም። የመጽሐፍ ቅዱስ ከተሞች አዲስ አበባ ኢትዮጵያ።
4. አባይነህ ካሴ (ዲ/ን)።1992 ዓ.ም። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት 1 ኛ መጽሐፍ አዲስ አበባ።
5. ቸርነት አበበ (መምህር)።2003 ዓ.ም። መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ አዲስ አበባ።
6. ሐረገወይን አገዘ (ሊቀጠበብት) እና ስንታየሁ አባተ (ቀሲስ)።1996 ዓ.ም። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቁ 2 አዲስ አበባ።
7. ስንታየሁ አባተ (ቀሲስ) እና ብርሃኑ አድማሱ (ዲያቆን)።1996 ዓ.ም።ሥነ-ፍጥረት አዲስ አበባ።
8. ብዙነህ አድማሱ (መምህር)።2005 ዓ.ም። ይህንን ይወቁ አዲስ አበባ።
9. አባይነህ ካሴ (ዲያቆን)።1997 ዓ.ም። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት 2 ኛ መጽሐፍ አዲስ አበባ።
10. ሜርልሲ ቴኒ እንግሊዛዊ፡- ትርጉም። የአዲስ ኪዳን ቅኝት
11. በቀለ ወንድም አገኘሁ።1981 ዓ.ም። የጌታች የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ አዲስ አበባ።
12. ቸሬ አበበ (መምህር) እና ቴዎድሮስ በየነ (ዲያቆን)።1997 ዓ/ም። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቁ 1 አዲስ አበባ
13. ዘላለም መንግስቱ(ሊቀ ጠበብት)።2001 ዓ.ም። ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ አዲስ አበባ።
14. ያረጋል አበጋዝ (ዲያቆን) እና ስንታየሁ አባተ (ቀሲስ)። 1995 ዓ/ም። አዋልድ መጻሕፍት አዲስ አበባ
15. ---------- ። 1986 ዓ.ም።የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አዲስ አበባ።

16. ሣህሉ አድማሱ (መምህር)። 2000 ዓ/ም። እግዚአብሔር ለሕዝቡ በቅዱሳት መጽሐፍት ይናገራል አዲስ አበባ።

17. እርቅይሁን በላይነህ። 2007 ዓ/ም። አምስቱ የመከራ ዘመናት አዲስ አበባ።

18. እርቅይሁን በላይነህ። 2006 ዓ/ም። የኢትዮጵያ ታሪክ ከኢማም አህመድ እስከ ዐጤ ቴዎድሮስ አዲስ አበባ።

19. ብርሃኑ ጎበና (መምህር)።1986 ዓ/ም። ፍኖተ ጽድቅ አዲስ አበባ።

20. ታሪኩ አበራ (መምህር) 2002 ዓ/ም። ኢየሱስ ማን ነው? አዲስ አበባ።

21. አብርሃም አድማሴ (መምህር)። 1995 ዓ/ም። አንቀጸ ሕይወት (የሕይወት በር) አዲስ አበባ።

22. ማኅበረ ቅዱሳን። ለተተኪ ሰባክያን የተዘጋጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማንዋል።

23. አቡነ ሺኖዳ (ፓትርያርክ ዘግብጽ)። ጉዞ ወደ እግዚአብሔር።

24. ብርሃኑ ጎበና (መምህር)።1985 ዓ/ም። አምደ ሃይማኖት አዲስ አበባ።

25. ሰሎሞን ኃ/ማርያም (መምህር)። ትርጉም። 2003 ዓ/ም። የሐዲስ ኪዳን ሰነዶች አማናዊ ናቸውን አዲስ አበባ።

26. ቸሬ አበበ (መምህር)።2003 ዓ/ም። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሞጁል ። ለቅድስ ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የተዘጋጀ።

27. አምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት።ታህሳስ 1994 ዓ.ም። ኤፍራታ መጽሔት ልዩ እትም ።

28. ማኅበረ ቅዱሳን።ጥር-የካቲት 19/94 ዓ.ም። ሐመር መጽሔት ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ ።

29. ቦ/መ/ብ/ቅ/ እግዚአብሔር አብ ቤ/ክ ሰ/ት/ቤት። 2005 ዓ/ም። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሞጁል።

30. ---------- ። የግል ማስታወሻ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!
ወለወላዲቱ ድንግል!
ወለመስቀሉ ክቡር!